
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፬ኛ ዓመት ቁጥር ፩ መስከረም / ጥቅምት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

## «ሽብር ሃይማኖት የለውም»




ሺሕ ዓ.ም.

## በሣልሳይ (፫ይ) ሺሕ ዓመት ዋዜማ...

© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## የጠበል ቦታ ክፍያ አስገዳጅ ባይኾን

ይህን ትዝብቴን ስጽፍላችሁ በእጅጉ እያዘንኩ ነው:: በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በቅድስት ክርስቶስ ሠምራ እና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ጠበል ተጠምቄ እና በከፍተኛ ሁኔታ ከሚያሠቃየኝ ሕመሜ ተፈውሼ በሥራዬ ላይ እገኛለሁ:: በተመሳሳይ መልኩ በርካታ ምእመናን በጠበሉ እየተጠመቁ ለመፈወስ በተስፋ ይጠባበቃሉ:: ይህ በኾነበት ሁኔታ በሥፍራው አገልግሎት ከሚሰጡት ወገኖች ምእመናኑ ሊጠየቁ የማይገባቸው ጥያቄ ይቀርባል:: *«ስእለታችሁን በወረቀት አስፍራችሁ ስጡን»* የሚለው የአጥማቂው ጥያቄ አንዱ ነው:: ተጠማቂዎችም: - *«ስእለት በስውር እንጂ በግልጽ አይነገርም»* በማለት በጥያቄው አዝነዋል:: በተጨማሪም አቅም ያለው ተጠማቂ በየሰባት ቀኑ ሦስት ብር ሲከፍል ሌላውም ለስንቁ የቋጠረውን እንኳ እየከፈለ ይጠመቃል:: ምንም የሌለው ነዳዩ ግን የሚከፍለው አጥቶ በሕመሙ እየተሠቃየ በበር ላይ ቆሞ ይማፀናል:: ይህም የማይፈቀድለት ኾኖ በገዳሙ የጥበቃ ኃይል ከአካባቢው እንዲርቅ ይደረጋል:: ከበሽታው ሊገላገል የመጣው ደኻው ምእመን በሕመሙ እንደ ተሠቃየ ወደ ቤቱ ሲመለስ መመልከቴ በእጅጉ ተሰምቶኛል:: እግዚአብሔር በጠበሉ አማካይነት በጸጋው የሚሰጠውንና ምእመኑም በእምነት የሚቀበለውን ፈውስ እንዳያገኝ የጠበል ላይ ክፍያን አስገዳጅ ማድረግ አግባብ አይመስለኝም:: በመኾኑም የሚመለከታቸው የበላይ ሐላፊዎች የማስተካከያ ርምጃ ቢወስዱ መልካም ነው እላለሁ::

በሌላ በኩል በየጠበሉ ሥፍራ: - «እምቤታችን ላከችኝ፤ ተልኬ ነው...» እየተባለ የምእመናንን ኅሊና የሚያውክ ተግባር እየተፈጸመ መኾኑ ግር እያሰኘን ነው:: በዚህም መንፈስ አሁን በቤተ ክርስቲያን ላይ እየመጣ ያለውን ፈተና ልናስተውለው ይገባል:: ችግሩን ወዳ የኾኑባቸው የጠበል መጠመቂያዎች በሄድኩና እኅትና ወንድሞቼን በተመለከትኩ ቁጥር አለቅሳለሁ፤ በበኩሌም ስለ ጉዳዩ ለማስረዳት ጥረት አደርጋለሁ:: ለማንኛውም ሁላችንም በጉዳዩ ላይ ግንዛቤው እንዲኖረን ትምህርት ቢሰጥ፣ አስተዳደራዊ መፍትሔም ቢበጅለት መልካም ነው::

*ወ/ሮ ሐረግ ጀንበሬ - አሶሳ*
*እመቤት ኃይለ ሚካኤል - አ.አ*

## ሐዋርያዊ አገልግሎት ከተማና ገጠር የማይለይበት ነው

በጋሞ ጎፋ ዞን አይዳ ወረዳ ከአምስት በላይ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: የየአጥቢያቸው ምእመናን ግን አገልግሎት ለማግኘት አልቻሉም:: በጎፋና አካባቢዋ ዲያቆንና ቄስ ያልኾነ አያገለግልም:: በተለያየ ደረጃ የሠለጠኑ ሰባክያንም የገጠሩን ክፍል አይጎበኙትም:: ለምሳሌ ያህል:- በአይዳ ወረዳ ሽፈቴ ቀበሌ ካሉት የምእመናን ብዛት አንጻር አንድ ካህን ተመድበው የነበረ ቢኾንም በአስመሳዮች ተደብድበው፣ የሚያገለግሉባትም ቤተ ክርስቲያን ታሽጋለች:: በሥፍራው የኖሩ የዕድሜ ባለ ጸጎችና የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችም ከዙሪያዋ አልተለዩም:: መቀናጀቱና መተባበሩ ባለመኖሩ ግን አገልግሎቱ ተስተጓጉሏል:: ሐዋርያዊ አገልግሎት ከተማና ገጠር የማይለይበት ነውና ቢያንስ የክብረ በዓላትን አጋጣሚዎች በመጠቀም የወረዳው ምእመን አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲመቻችለት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ:: በአጠቃላይ ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ሥፍራ ሳይገድበንና ሳንታክት በአንድነት ተባብረን መቆም ይገባናል::

*መ/ር መሰለ ማሞ*
*ጎፋ ሳውላ*

## «ለራሴ ምቾት ከሰጠኝ ለተመልካቹ ግድ የለኝም»

አለባበሳችን በአካባቢያችን የአየር ሁኔታና የሥራ ጠባይ፣ በሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ግንኙነታችን እንዲሁም ኅብረተሰቡ ዋጋ በሰጣቸው መሠረተ ሐሳቦች መልክና ሥርዐት የያዘ እንዲኾን ግልጽ ነው:: ምእመናን ሥነ ምግባርን የተከተለ አለባበስ እንዲኖራቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ:: /ዲድ.1፥55፤ 3፥16-17 ተግሣጽ ዘቅዱስ ዮሐ.አፈ.፥ገጽ 323፣ 326/:: ይሁንና ዘመናችን ልዩ ልዩ የዓለማችን ባህሎች በመገናኛ ዘዴዎች የተቀራረቡበት በመኾኑ ሁሉም የየራሱን በጎ ማንነት ብቻ ጠብቆ ለመጓዝ ያዳገተው መስሎ ይታያል:: ዘመኑ የሚያመጣቸው የተለያዩ የልብስ ፋሽኖች /ሞዶች/: - «ለራሴ ምቾት ከሰጠኝ ለተመልካቹ ግድ የለኝም» የሚባልላቸው ናቸው:: አንዳንዶቹም ዕርቃንን ከመሸፈን ባልተናነሰ ኩኔታ አስነዋሪ መልክን የሚያላብሱ ናቸው:: በርካታ የቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች ከአለባበስ አኳያ በየዋህነትም ኾነ ባለማወቅ ስሕተት ሲሠሩ ወይም የሚለብሱትን ለመምረጥ ሲቸገሩ እናያለን:: መገንዘብ ያለብን ግን የዘመናችን የልብስ ዲዛየኖች መነሻ የሚያደርጉት የለባሹን አካላዊ ቁመና በማጋነን የሰውን አትኩሮት እንዲስብ በማድረግ ላይ መኾኑን ነው:: ልብሱ ለእኛ የሚሰጠው ምቾት በሁለተኛነት የሚታይ ጉዳይ ነው:: ስለዚህም የዲዛየኑ ትኩረት በለባሹ ላይ ሳይሆን በተመልካቹ ላይ ነው:: ጥብቅ አድርጎ በመያዝ አካላዊ ቅርጽን እንዲያሳይና እንዲያጋልጥ ማድረግ /Tightening/፣ ወደ ተወሰኑ የአካል ክፍሎች የተጠጉ ቅዶችን በማበጀት፣ ደረትን በመክፈት፣ ከጀርባ በመተልተል /Approaching/፣ በተለያየ ጊዜ ተጋልጠው የሚታዩ የአካል ክፍሎችን በመቀያየር ዲዛየን ማውጣት /Shifting/ የሚባሉት ጥቂቶቹ ናቸው:: ... ታድያ ብዙዎች በተለይ እኅቶቻችን የአለባበስ ውድድር ውስጥ የገቡ እስኪመስል በአለባበሳቸው ለሌሎች መሰናክል እየኾኑ ያሉት ሥራው «ሰይጣናዊ ጥበብ» ያለበት መኾኑን ከመዘንጋት /ልብ ካለማለት/ አልያም በግዴታ ቢስነት /ራስ ወዳድነት/ ሊኾን ይችላል::

አስተሳሰቡ በአደባባይ ብቻ ሳይኾን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያናችንም ጎልቶ መታየቱ እየተለመደ መጥቷል:: ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን የሚከተል ማንኛውም ወጣት /ወንድም ኾነ ሴት/ ግን የሌላውን ኅሊና የሚሰርቅ ልብስ መልበስ አይገባውም/ትም/:: የለበስነው ነጠላ እንኳ በተለየ መንገድ ቆሽሾ በመታየቱ በአጠገባችን ያሉ ሰዎች ኅሊና ሊታወክ ይችላል:: በአንጻሩ በነጠላችን ላይ አለመጠን የተርከፈከፈ ሽቶ የባልንጀራችንን ትኩረት ሊያዛባ ይችላል:: በእኒህና በመሳሰሉት ከአለባበስ ጋር በተያያዙ ጥቃቅን የሚመስሉ ጉዳዮች እንኳ የፈቃደ ሥጋ አቀጣጣዮችና የሰይጣናዊ ተልእኮ አስፈጻሚዎች እንዳንኾን ሁላችንም አበክረን ልናስብበት ይገባል:: *«አለባበስህ በጥንቃቄ ይሁን::»* እንዳለ /ሃይ.አበው ዘሠለስቱ ምእት 21፥12/::

*ዮናስ ተስፋዬ*
*መቐለ*


| የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com

«መስቀል የሰላማችንና የዕርቃችን ምልክት ነው። የሰላማችን ምልክት የሆነውን ቅዱስ መስቀል በምናከብርበት በዚህ ዕለት ስለ ዓለማችንና ስለ አገራችን ሰላም ልናስብ ይገባናል። . . . አስቀድሞ ራስን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ በዚህ በአስጨናቂው ዓለም ውስጥ ሰላምንና ዕርቅን ለማምጣት ተቀዳሚ ተግባር ነው። ... በሰው ልጆች መካከል ሰላምና ዕርቅ እንዲሰፍን፣ መቻቻል፣ መከባበር፣ እርስ በርስ መተማመን እንዲኖር፣ ስስትና ራስ ወዳድነት፣ ጥርጥርና አለመተማመን መጥፋት ይኖርባቸዋል። . . . ሰዎች ሁሉ የጎሳ፣ የዘርና የቀለም፣ የዕድሜና የጾታ ልዩነት ሳያሳዩ እርስ በርሳቸው ተከባብረው በሰላም የመኖርን ምስጢር መረዳት አለባቸው። ሰላም ከሰፈነና ጥርጣሬ ተወግዶ በመተማመን መሥራት ከዳበረ ዛሬ ተስፋ የቆረጡት ተስፋቸው ይታደሳል። በቂ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና ሥራ የሌላቸው ሕይወታቸው ይለወጣል፤ የታመሙት ይፈወሳሉ፤ በሌሎች የሚበዘበዙት የድካማቸውን ተገቢ ዋጋ ይቀበላሉ። ሰብአዊ መብት፣ ነጻነትና እኩልነት ይከበራል። ... ዛሬ የምንገኘው በሁለተኛው ሺሕ ዘመን ፍጻሜ፣ በሦስተኛው ሺሕ መግቢያ ዋዜማ ላይ ነው። ... ባለፉት ሁለት ሺሕ ዓመታት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ክፉና ደግ ታሪክ ተመዝግቧል። እጅግ ታላቅና ድንቅ የሆነ የሥልጣኔ ዕድገትም ታይቷል፤ በቀጣዩም ሦስተኛ ሺሕ ዘመን ካለፈው የተሻለ ፦ድኾችና ሀብታሞች አገሮችን የሚያካትት ዕድገትና ታሪክ እንደ ሚታይ የሁላችን ጸሎት፣ ምኞትና ተስፋ ነው።»

(ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት)
/መስከረም 16 ቀን 1999 ዓ.ም./

በቅርቡ በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በደረሰው የጎርፍ አደጋ
በሞት በተለዩ ወገኖቻችን የተሰማንን ልባዊ ሐዘን
እንገልጻለን።
እግዚአብሔር አምላክ በሞቱት ዕረፍተ ነፍስን፣ ለቤተሰቦቻቸውም
መጽናናትን እንዲሰጥልን እንጸልያለን።
በአደጋው ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን መልሶ
በማቋቋሙ ረገድ ዜጎች ሁሉ የሚያደርጉትን ትብብር አጠናክረው
እንዲቀጥሉ የዝግጅት ክፍላችን ጥሪውን ያቀርባል።


ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
ም/ ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን
ሪፖርተር - ዲያቆን ደረጀ ጅማ

ኮምፒዩተር ዲዛይነር - ወይንሸት ወጉ
የኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ጸዳለ ሁንዴሳ
- ገነት ግርማ

E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org
ስልክ 011-1-242753
መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፬ኛ ዓመት ቁጥር ፬
መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.


# ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
• በሣልሳይ ሺሕ ዓመት ዋዜማ ........................ ፪
ደብዳቤዎች ........................ ፫
የኢትዮጵያ ሚሊኒየም /ሣልሳይ ሺሕ ዓመት
ሐሳበ ዘመን በሚሊኒየም ዋዜማ........................ ፭
የሚሊኒየም ትርጉም -ምእት፣ሺሕ ወይስ
እልፍ?........................ ፭
ወቅታዊ ጉዳዮች
• ሽብር ሃይማኖት የለውም........................ ፲
• እምነት እና እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች........ ፲፬
ትምህርተ ሃይማኖት
• ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ........................ ፲፰
• ተሠግዎተ ቃል ........................ ፳.
ኪነ ጥበብ
• .የ«ስምዖን ጫማ ሰፊው» ፊልም ሲቃኝ........................ ፳፫
• «የዳ ቪንቺ ኮድ» ብዙ ሐሰቶች በመጽሐፍ
ቅዱሳዊ እውነቶች ሲመዘን........................ ፳፭
ሐመረ ሕይወት
• ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት ቤተ ክርስቲያን
ያላት ሀብትና የሚጠበቅባት ድርሻ........................ ፳፱
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
• ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት
ውስጥ........................ ፴
ሥነ ኪን
• ፍጥረትን ተመልከት........................ ፴፭
አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
• «ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በምርጫ እንዲጠና
ዕድል ይሰጠው።» ........................ ፴፯
• ዘንድ አንቀጽ ወይም ትእዛዝ አንቀጽ........................ ፴፱


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# የማኅበሩ መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።*

# በሚልሳይ ሺሕ ዓመት ዋዜማ

በጎርጎሮሳውያኑ ዘመን አቆጣጠር 2000 ዓመት ሲከበር አንድ የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህን፡- *«ዛሬ 2000 ዓመት ገባን ብለን እየተደሰትን ነው፤ እኛ ግን በ11ኛው መ/ክ/ዘ ላይ ነው የምንገኘው»* በማለት መናገራቸውን ቢ.ቢ.ሲ ዘግቦ ነበር። ካህኑ እንዲህ ለማለት ያስገደዳቸው በዘር እና በእምነት ልዩነት ላይ ተመሥርቶ በአገራቸው የተፈጠረው ክፋትና ጥላቻ ይህንንም ተከትሎ የተከሠተው ዘግናኝ ሰብአዊ እልቂትና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ነው። የዘመን ቁጥር መለወጥ ብቻውን ልብን አይለውጠውም፤ አመለካከትን አይለውጠውም፤ ሥርዐተ ማኅበርን አይለውጠውም።

የኢትዮጵያን ሁለት ሺሕ ዓመተ ምሕረት በዓለም አቀፍ፣በአህጉር እና በብሔራዊ ደረጃ ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ነው፤ በእውነትም ይህ ከነምሳ ትውልዶች መሐል የታደሉት ብቻ የሚያከብሩት በየሺ ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚፈጸም አጋጣሚ በመሆኑ መከበርም መታሰብም ይገባዋል። አገራችን ኢትዮጵያ ልዩ የሚያደርጓት ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ከምትገልጽባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱ በመሆኑ ሊከበር ይገባዋል። አከባበሩ ግን ከቁጥር የዘለለ የአመለካከት፣ የመንፈስ፣ የልቡና እና የተነሣሽነት ለውጥ ሊኖ ረው ይገባዋል።

በሚልሳይ ሺሕ ዓመት /በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም/ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት መልክ ያለው ጉዞ ይጠብቃታል። የመጀመሪያው፡- ያላትን ሀብት፣መንፈሳዊ ዕሴትና ጥበብ ስብስባ፣ለይታና ቀምራ ለዓለም ይበልጥ እየገለጸች፥ እያስተዋወቀች የራሷን ሀብት የሕዝብ ሁሉ ሀብት ማድረግ (GLOBALIZING THE LOCAL) ነው። ይህ ነገር በአንድ በኩል ያላወቋት እንዲያውቋት፣ያልተቀበሏት እን ዲቀበሏት፣ያልተረዷት እንዲረዷት ከማድረጉም በላይ በሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ዘመን ተነጥሎ ከመቅረት ይታደጋታል። በሌላ በኩል ደግሞ በዓለም አቀፋዊ ተልእኮዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም የዓለም ወገኖች እንዲሆኑ፣ መሠረቷ በኢትዮጵያ፥ ቅርንጫፏ ግን በዓለም ሁሉ የመላ ያደርጋታል።

ሁለተኛ ደግሞ እምነቷን፣ሥርዐቷን፣ትውፊቷን፣ብሔራዊ አሠራሯን ዓለም አቀፋዊ አድርጎ መጓዝ ነው። ዘመናዊ የሒሳብ አሠራሮች፣የአስተዳደር ዘይቤዎች፣ የማስተማርያና የመገናኛ አውታሮች፣የአደረጃጀትና የአወቃቀር መንገዶች ከወዲኹ በተቋማዊ መንገድ ተጠንተው ለቤተ ክርስቲያኒቱ በሚስማማ መልኩ ተቀርጸው (LOCALIZING THE GLOBAL) ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። እኛ ራሳችን የሚ ስማማንን መርጠን፣የማይስማማንን አርመን ካላስገባን ነገ ዓለም አቀፋዊውን ተጽዕኖ ሳንወድ በመጡበት ሁኔታ ለመቀበል እንገደዳለን።

በአጭርና በቀላል ምሳሌ፡- ከግሪክና ከሩስያ የምናስመጣቸው ንዋያተ ቅድሳት የአገራችንን ገበያ ሞልተውታል። «ቅዱሳን» ሥዕሎች ከሕንድና ከቻይና ነው የሚገቡት። ምንጣፎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ምርቶች ናቸው። እነዚ ህን ፈትሾና መርምሮ እንድንገለገልባቸው የፈቀደ ማን እንደ ሆነ፣ ሥርዐት መጠበቃቸውን ያረጋገጠ የትኛው አካል እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም። ይህ ሁኔታ ከቀጠለ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ ያቆየችውን ኦርቶዶክሳዊ ማንነቷን ማጣቷ አይቀሬ ይሆናል።

በመሆኑም ቢያንስ እንደ መንፈሳዊነታችን አንድ እርምጃ ከጊዜው መቅደም ይኖርብናል፤ ከዘልማዳዊ አስተሳሰብ ወጥተን አርቀን ማሰብ በሚገባን ሁነኛ ወቅት ላይ እንገኛለን። ከዚህ በኋላ ተጋድሏችን በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እየመጠቀና እየረቀቀ፣ ከእኛ ጋር ያለው ልዩነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ነገር ግን ወደ አንድ መንደርነት እየሄደ ነው ከሚባለው ዓለም ጋር እና በሚባለው ዓለም ውስጥ ነው፤ ካልዋጥን እንዋጣለን፤ ካላሸነፍን እንሸነፋለን፤ ካልቀደምን እንቀደ ማለን ፤ ካልወጣን ይገቡብናል፤ የእኛን እየሰጠን የሌለንን ለበጎ መቀበል ካልቻልን የሌሎችን ሁሉ እንዳለ መቀበላችን ወይም ለመቀበል መገደዳችን አይቀሬ ነው።

ሺሕ ዓመቱ ሊለወጥ በዋዜማው ላይ በምንገኝበት ወቅት በእነዚህ ነገሮች ላይ በጋራ ተቀራርቦ ለመወያየት የሚያበቃንን የመንፈስ ልዕልና ገንዘብ ልናደርግ ይገባል። ✥

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ለሞቱት ዕረፍትን ላሉት መጽናናትን

በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች የተከሠቱት ተከታታይ የጎርፍ አደጋዎች በወገኖቻችን ላይ ባደረሱት ጉዳት በእጅጉ አዝነናል:: በአደጋው ከ647 ያላነሱ ወገኖቻችን ሕይወት ማለፉ ተገልጧል፣ ቤተሰቦች ተለያይተዋል፣ ለዓመታት ያካበቱትን ጥሪት አጥተዋል:: በሕይወት የተ ረፉትም መጽናናትንና መልሶ መቋቋሚያን በእጅጉ በሚሹበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ:: ቸሩ አምላካችን የምሕረት ዐይኑን መልሶ በሞት ለተለዩን ዕረፍተ ነፍስን፣ በሕይወት ላሉትም መጽናናትን እንዲሰጥልን እንጸልያለን:: እኛም በአደጋው የተፈናቀሉትን ወገኖች መልሶ በማቋቋም ረገድ በየአጥቢያችን የበኩላችንን ድርሻ በመወጣት አገር ዓቀፉን ጥረት መደገፍ ይኖርብናል::

*ደጀኔ አለኸኝ - አርባ ምንጭ*
*ጸጋዬ ዘውዴ - ወልድያ*

## ከየመን ምእመናን የምንማረው

ነዋሪነቴ በየመን ሲኾን የመጣኹትም በስደት ነው:: በየመን የሚኖሩት ኦርቶዶክሳውያን ካህናትና ምእመናን ሁኔታ «ክርስቲያንና ሚስማር ሲመቱት ይጠብቃል» የሚለውን አባባል በጉልሕ ያሳያል:: በየመን ሰነዓ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አለ:: እንደ አገሩ የመንግሥት ሥራት ዐርብ ከሥራ የምናርፍበት ቀን በመኾኑ በዕለቱ ቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በምእመናን ተጣብቦ ሲታይ በባዕድ አገር መኖራችንን እንረሳዋለን:: ጸሎተ ቅዳሴው ፣ መዝሙሩ፣ የጸሎቱ መርሐ ግብር፣ ተምሮ ማስተማሩ ሁሉ በትጋት ይከናወናል:: እንቅስቃሴያችን ግን በነጻነት ሳይኾን በመሸማቀቅ፣ በመደበቅም ጭምር ነው:: ምእመኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄድበት ወቅት ይሰደባል፤ ድንጋይ ይወረወርበታል፤ ሌሎችም በደሎች ይፈጸሙበታል:: ካህናቱና ምእመኑ ግን የገጠማቸውን ችግር ተቋቁመው ቤተ ክርስቲያኑን አሁን ካለበት የኪራይ ቤት አውጥተው የራሳቸውን ቤተ መቅደስ የሚያንጹበትን ሁኔታ እያመቻቹ ነው:: እስከዚህ ድረስ ጽናቱን ያደለን አምላክ በቀሪውም እንዲያበረታን በጸሎታችሁ አስቡን:: በእውነቱ የአገር ቤቱ ምእመን በየመን ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ብርታት የሚማረው ብዙ ነገር እንዳለ አምናለሁ:: እኔም በጋዜጠኛነት ሞያዬ እዚህ ያለውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በሐመር መጽሔት በኩል ለሕዝቡ በማስተዋወቅ ላበረክት የምችለው አገልግሎት አለ ብዬ አምናለሁ:: የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል ዕድሉን እንደ ማይነፍገኝ ተስፋ አደርጋለሁ::

*ግሩም ተክለ ሃይማኖት*
*የመን - ሰነዓ*

## የማያቋርጥ ሂደታዊ ተግባር

*በሐመር መጽሔት 14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትም «የአበው የጽሑፍ ዘመን ይደገም» በሚል ርእስ የተላለፈውን የማኅበሩን መልእክት በጥሞና ተመልክቼዋለሁ:: ወቅታዊና ተገቢ መልእክት ነው:: የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን የወቅቱ ስልት፦ ከአዋልድ መጻሕፍት ስሕተት የሚመስሉ ነገር ግን በትርጉም የሚቃኑ ንባቦችን ከአገባባቸው ውጭ /Out of context/ እየወሰዱ ለኑፋቄአቸው ድጋፍ የሚኾኑ አስመስሎ ማቅረብ ነው:: ግኖስቲኮች እንዳደረጉት ሁሉ ተጠብቀው የቆዩ ጽሑፎቻችንን መበረዝም ሌላው የጥፋት ሙከራቸው ነው:: የሚያዳግምና በቂ ነው ባይባልም በዘመናችን ለሚጠነሰሱት ለቤተ ክርስቲያናችን የውስጥና የውጭ ጠላቶች ሤራ ከዝምታ የሚሻል መልስ ተሰጥቷል:: የበለጠውና የማያቋርጠው ሂደታዊ ተግባር ደግሞ ከርቱዐነ አበው ሊቃውንትና መምህራን ይጠበቃል:: የማኅበረ ቅዱሳን ሚና ለዚህ የማያቋርጥ ሂደታዊ ተግባር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይመስለኛል፣ ኑፋቄንና መናፍቃንን መከላከል እንጂ ጨርሶ ማጥፋት አይቻልምና:: እኛ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንም መናፍቃኑ እንደ ሚነግዱበት በጽሑፎች ላይ ሊከሠት የሚችለው የመላሽ፣ የጣፊ፣ የገልባጭ ስሕተት እንዲሁም ጠባይዐዊ የኾነው የሰዎች የምግባር ጉድለት በቤተ ክርስቲያናችን ተገኝቷል ብለን በሃይማኖታችን ጥርጥር ሊገባን አያስፈልግም:: ይልቁንም የስሕተት መጻሕፍት እንዲታረሙ፣ በምግባር የደከሙ በንስሐ ሕይወት እንዲጠነክሩ በተባበረ ድምፅ እያሳሰብን ከመቼውም በላቀ መልኩ በሃይማኖታችን ጸንተንና ጎልምሰን መገኘት ይኖርብናል::*

*ዲ/ን ኪዳነ ወልደ ኀይለ ጊዮርጊስ*
*ደብረ ገሊላ ቅዱስ ዐማኑኤል ካቴድራል*
*አ.አ*

## መንፈሳዊ ተቋማት ለልማት

የ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ግንቦት /ሰኔ/ ሐምሌ 1998 ዓ.ም እትም ወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ *«ለአገር ዕድገት እና ልማት የቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ አጋርነት»* በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ በራሱ መልካም ኾኖ አግኝቼዋለሁ:: ከ75 ሚልዮን ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከ45 ሚልዮን የማያንስ ምእመን ያላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንግሥታዊ በኾኑና ባልኾኑ ድርጅቶች፣ በሲቪክ እና ሞያ ማኅበራት አማካይነት በዚህች አገር የሚከናወኑ የልማት ተግባራት በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ይመለከቷታል:: የልጆቿን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት የተቃና ለማድረግ ስትራቴጂያዊ ማለትም ዋነኛ አጋር መሆን እንደ ምትችልና እንደ ሚገባት የቀረበው ሞያዊ ትንተና በመርሕ ደረጃ ያመለክታል:: ባለንበት ዘመን በሌላው ዓለምም ቢኾን የእምነት ተቋማት ለሕዝብ ዕድገትና ልማት ያላቸው ሚና እየጎላ የመጣበት ሁኔታ ነው ያለው:: ስለኾነም ጥንታዊትና ኵላዊት ቤተ ክርስቲያናችን በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት የሚያወጣቸውን የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማስፈጸም ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበትንና የሚጠቀምበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባታል::

*ይመስላል አለባቸው*
*ወልድያ*
*አብርሃ ትኩሶ*
*ናዝሬት*

## መዘግየቷ አሣቅቆናል

የሐመር መጽሔት የነፍሳችን ስንቅ ናት:: ምግበ ሥጋ በየተወሰነ ሰዓት እንደ ሚያስፈልገን ሁሉ የነፍሳችን ስንቅ የኾነችውን ሐመር መጽሔትንም በመደበኛ ጊዜዋ በጉጉት እንጠብቃታለን:: ከዚህ አኳያ የ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ግንቦት /ሰኔ/ ሐምሌ 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ሁለት ወራትን አሳልፋ ከሦስት ወር በኋላ በመውጣቷ ቢያስደስተንም በተለያዩ ስጋቶች መሣቀቃችን ግን አልቀረም:: በዝግጅትና በኅትመት ሥራ ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደ ሚችሉ ቢታወቅም ያን ያህል መዘግየቷ ግን አግባብ አልነበረምና ለወደፊቱ ቢታሰብበት መልካም ነው:: እትሙም የሦስት ወር የኾነበት ምክንያት መግለጫ ሊሰጥበት ይገባል::

*ሰሎሞን ገሳ- ጎፋ ሳውላ*
*ጸጋዬ ዘውዴ - ወልድያ*
*ብርሃን መስፍን - አ.አ*

**ከአዘጋጁ፡-** የተወደዳችሁ አንባብያን፥ በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትማችን መደበኛ ጊዜያችንን ጠብቀን ባለማውጣታችን ከፍ ያለ ይቅርታ እንጠይቃለን:: መዘግየቱ የተፈጠረው በሌሎች ወቅታዊ ሥራዎች መደራረብ ምክንያት ነው:: በዚህና በቀጣይ እትሞቻችን መጽሔቷን እንደ ተለመደው ወቅቷን ጠብቀን በየሁለት ወሩ የምናደርስ መኾኑን በአክብሮት እንገልጻለን::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ከተጨባጭ ሁኔታዎች አንጻር ተራርቆብኛል

በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ሐመር መጽሔት እትም ወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ፡- *«ለአገር ዕድገት እና ልማት የቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ አጋርነት»* በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ በአጠቃላይ እይታ ጥሩ ኾኖ አግኝቼዋለሁ:: የእውነተኛና ዘላቂ ልማት ዕንሰ ሐሳብን በተሻለ ሁኔታ ለመገንዘብ በሚረዳ መልኩ የተዘጋጀ ነው:: ይኸውም ልማት በምጣኔ ሀብታዊ ይዘቶች ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን መንፈሳዊና ሰብአዊ ገጽታዎችም ሊኖሩት እንደ ሚገባ ማሳየቱን ወድጄዋለሁ:: እንደ እነ ጄምስ ሚጅሊይ ባሉ የርእስ ጉዳዩ ጠበብት፥ ብዙ ሰዎች ስለ ልማት ያላቸው ግንዛቤ የተዛባና ሙሉ ያልኾነ ነው፤ በእርሳቸው አገላለጽ «Distorted development» ይሉታል:: በመኾኑም ልማት በኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች የሚገኘውን ውጤት ብቻ መሠረት ካደረገ ከዚህ አገላለጽ የወጣ አይኾንም:: በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ በዋናነት በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ ሊሰመርበት ይገባ የነበረው ልማት የሰውን ክብርና ልዕልና ማእከል ያደረገ /Man centered/፣ ሰውን መነሻም፣ መገሥገሻም መድረሻም /means and end/ ያደረገ መኾን እንዳለበት ነው:: ሰው የልማቱ አንቀሳቃሽና የልማቱ ተጠቃሚ መኾን ይገባዋልና:: በሌላ በኩል የቤተ ክርስቲያንን ዋነኛ የልማት አጋርነት ከመርሕና ከንድፈ ሐሳብ አኳያ ለማስረገጥ የተደረገው ጥረት መልካም እንደ ኾነ አያለሁ፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ለአገር ልማት ስትራቴጂያዊ አጋርነት ዝግጁ መኾኗን በተጨባጭ የሚገልጹልኝን ፍንጮች ለማሰብ ስሞክር ከእውነታው የራቀ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፤ የጽሑፉ ርእስና መንደርደሪያ የሚያመለክተውን ያህል ቀሪው የጽሑፉ ይዘት የሚያሳምነኝ አልኾነም:: ለወደፊቱ መሰል ሞያዊ ጽሑፎች መቅረባቸው የሚበረታታ ነው:: ይሁንና መርሖዎችና ንድፈ ሐሳቦች መሬት ላይ ባሉት ሁኔታዎች /*መጠናዊና ዓይነታዊ መረጃዎች*/ ተደግፈው መተንተንና ትንተናዎቹ ለሚያመለክቷቸው ችግሮችም የመፍትሔ ሐሳቦች መጠቆም ይኖርባቸዋል እላለሁ::

ዲ/ን ዜና ብርሃኑ
አ.አ.ዩ

## ብርታትንና ጥንካሬን ይሰጣል

በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ *«ቅድስና እና ትዳር»* በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ በእጅጉ አስደስቶኛል:: ዝግጅቱ በርካታ ወጣቶች በቅድመ ጋብቻ ሕይወታቸው ከሚፈተኑበት ፍትወተ ሥጋ ራሳቸውን ጠብቀው ለተቀደሰ ትዳር እንዲበቁ ብርታትንና ጥንካሬን ይሰጣቸዋል:: ስለዚህም በተለያዩ የኑሯችን ፈርጆች ተመሳሳይ ጽሑፎችን እያቀረባችሁ አስተምሩን፤ አሳውቁን:: ለጸሐፊውም እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛለት::

ሲሳይ ታረቀኝ
ይርጋለም

## «ዬምሳ» የሚለው በ«የም» ይስተካከል

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት ጥር/የካቲት 1998 ዓ.ም እትም፡- «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመናን ሥርጭት በብሔር /በመቶኛ/-1994 እ.ኤ.አ» በሚል ርእስ ከቀረበው መረጃ ውስጥ «ዬምሳ» የሚለው ስመ ብሔር አጠራር በስሕተት የተቀመጠ ነው:: «ዬምሳ» ማለት በየምኛ ቋንቋ «የምኛ» ማለት ነው:: የብሔረሰቡ መጠሪያ «የም» ሲኾን ቋንቋውም የምኛ ነው:: በሌላ በኩል መረጃው የተገኘበት የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ቢሮ ሰነድ የታተመበት 1994 እ.ኤ.አ እንጂ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አለመኾኑ መመልከት ይኖርበታል::

*ታምሩ መኰንን*
*ሚዛን ተፈሪ*
*አንተነህ ዓምዴ*
*አ.አ*

## በቂ አይደለም - ተጠናክሮ ይቀጥል!!

በሐመር መጽሔት 14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ *«የዳቪንቺ ኮድ በመንፈሳዊ ዐይን ሲገመገም»* በሚል ርእስ ፍሬምናጦስ ከተባሉ ጸሐፊ የቀረበው የተቃውሞ ጽሑፍ አስደስቶኛል:: ይሁንና በቂ አይደለም፤ ገና ብዙ ሊጻፍበት ይገባል:: ደራሲው እና የድርሰቱ ተርጓሚዎች የክርስትናን ሃይማኖት ለማጥፋት የሚያሤሩ ወይም የሤራው ተባባሪዎች ኾነው የሚሠሩ ይመስለኛል:: በርግጥ በክፉ ድርጊታቸው ክርስትናችን ቢጠናከር እንጂ አይዳከምም፤ ይህም ሊኾን የሚችለው አሁን በጊዜያዊ ስሜት /በወረት/ የዳን ብራውንን ልብ ወለድ መጽሐፍና ፊልም «እያጣጣሙ» ያሉ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ክፋቱን ምሬቱ እንዲሰማቸው የሚያስደርግ ሥራ ሲሠራ ነው:: ያን ያህል ክሕደት ያለበትን መጽሐፍ፡- *«የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ምርጥ ሥራ»* ብለው የሚያሞካሹትና የሚያቀነቅኑለት፥ ደጋግመው የሚያነቡትና በስሜት የሚያወሩለት የሚያሳዝኑን ወገኖቻችንን ባሉበት ሁኔታ በሐመር መጽሔት በኩል የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንደ ሚቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ::

ተስፋዬ አንቶሼ - ደቡብ ኦሞ /ጂንካ/
በላይ ዘገየ እና ግርማ
ጌታቸው - ከሚሴ
ቡሩክ አበበ - ጅማ

## ይመለሱልን!!

በሀገረ ስብከታችን በምእመናን ዘንድ ተደማጭነትና በቂ የስብከተ ወንጌል ችሎታ ያላቸው መምህራን ቢኖሩም ወደ ተለያዩ የቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዕድል አግኝተው ይኼዳሉ:: ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁም ወደ ተለያዩ ቦታዎች ተመድበው መኼዳቸው ይነገረናል እንጂ ተመልሰው መጥተው በሀገረ ስብከታቸው ሲያገለግሉ አናይም:: ጉዳዩን አስመልክቶ ከምእመናን ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም አጥጋቢ ምላሽ የሚሰጥ አይገኝም:: ለምን ይሆን ተመልሰው ሀገረ ስብከታቸውን እንዲያገለግሉ የማይደረገው? ከሚመለከተው አካል ምላሹን በጉጉት እጠባበቃለሁ::

*ዲ/ን እንግዳ ወርቅ ጥላሁን*
*ወላይታ ቦንቤ*

*ከዚህ በመቀጠል ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: እናመሰግናለን:: መልእክቶቻችሁንና የጥቆማ ሐሳቦቻችሁን ወደፊት እንዳስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን:: ሐመርን ያንብቡ፤ ለሐመር ይጻፉ::*

*ዲ/ን ብዙአየሁ በላይ /ጅቡቲ/፤ መ/ር ሽመልስ ሞገስ /ባሌ - ጋሠራ ወረዳ/፣ አብነት ጌትነት /ቀብሪ ደኅር/፣ ካሣሁን ብርሃኔ /ዓዲ ሃገራይ/፣ በለጠ ፎሌ /ቡታጅራ/፤ ሕይወት ጎፉይ /አቡዳቢ/፤ አዜብ አብዱላሂ፣ ሰሎሞን ገረመ /ድሬዳዋ/፤ ነጻነት ቢሰጥ /ወግዲ ግንኙነት ጣቢያ/፤ ሚራኬ ሙላቱ /የተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች- ሻርጃ..የ ቅድስት ማርያም/፤ ጌትነት ጉዳይ /ደጀን- የትኖራ/፤ ዲ/ን ዮርዳኖስ ተከሥተ /ዘሀገረ ግራርያ/፤ ይኩኖ አምላክ ይልማ /ደብረ ብርሃን/፤ ሰሎሞን ጌታቸው /ደብረ ማርቆስ ዋሻው ቅዱስ ሚካኤል ሰንበት ት/ቤት/፤ ንጉሤ መብራቱ /ጋምቤላ/፤ የኋላ እሸት ኃይሉ /ነጌሌ ቦረና/፤ አክሊሉ ግርማ /ቀንጥቻ/፤ አበበ ተስፋ /አርሲ ሮቤ/፤ ዐሥር አለቃ ግርማቸው ወርቁ /ብር ሸለቆ/፤ ወልደ ጻድቅ ወልደ ገብርኤል /ወልድያ/፤ ሙሉጌታ ሥዩም /ባቲ/፤ ዲ/ን ሀብተ ማርያም መንግሥቴ /አዊ ዞን - ግምጃ ቤት/፤ ኃይሉ መግራ /ሶማሌ ክልል/፤ ተስፋዬ አድማሱ፣ ክንፈ ገብርኤል፣ ወለተ ሥላሴ ወልደ ትንሣኤ፣ ሰይፈ ገብርኤል፣ ሥነ ኤልሳዕ፣ አልዓዛር ኪዳኔ፣ ቢ.ኤም /አ.አ/::*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐሳበ ዘመን በሚሊኒየም ዋዜማ

/ጌታቸው በቀለ/

የያዝነው 1999 ዓ.ም - አዲስ ዓመት ነው፤ የኻያኛው ምእት ዓመትና የካልኣይ ሺሕ ዓመት መጠናቀቂያ ነው፤ የኻያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ የሣልሳይ ሺሕ ዓመት /አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም/ ዋዜማ ነው:: በአንድ ወቅት የአንድ በጎ ፈቃደኛ ቡድን አባል በመሆን ከኡጋንዳ ወደ ኢትዮጵያ መጥታ የነበረች ጄሲካ አቤናክዩ ባዴብዬ የተባለች ኡጋን ዳዊት «Ethiopian at a glance» በሚል ርእስ ባቀረበችው ጽሑፍ የሚከተ ለውን አስፍራ ነበር:: «ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየኹባቸው ጊዜያት እጅግ ካስገረሙኝ ነገሮች አንዱ እ.አ.አ 2004 ላይ ሆነን ኢትዮጵያ ውስጥ ግን 1996 ዓ.ም መሆኑ ነው:: የተቀረው ዓለም በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ሲገኝ ኢትዮጵያውያኑ ወደ አዲስ ሚሊኒየም ለመድረስ ገና አራት ዓመታት ከፊታቸው ይጠብቋቸዋል:: ይህ እንቆቅልሽ ቢመስለንም ሐቅ ነው:: ሌላው ዓለም በዚህች ፕላኔት /መሬት/ ላይ ስንገኝ ኢትዮጵያውያን ግን በራሳቸው ዓለም ያሉ ናቸው::»

ርግጥ ነው፥ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተለየ በመሆኑ ለሌላው ይቅርና ለእኛ ለኢትዮጵያውያኑ እንኳ ግር ማሰኘቱ አይቀሬ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያዩ ወገኖች በርካታ ጥያቄዎች ይነሣሉ:: ዘመን አቆጣጠራችን ከምዕራባውያን ለምን ተለየ? 12ቱ ወራት እንዴት እኩል ቀናት ያዙ? 13ኛዋ ወር ጳጉሜን ከየት መጣች? የዘመን መለወጫችን ለምን መስከረም ወር ሆነ? እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ለመመለስ ባሕረ ሐሳብን ማወቅ የግድ ይላል:: ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ካበረከተቻቸው ቅርሶች አንዱ ባሕረ ሐሳብ ነው::

«ሣልሳይ ሺሕ ዓመት» ወይም «የኢትዮጵያ ሚሊኒየም» ብለን በሰየምነው አዲስ ዓምዳችን ባሳለፍናቸው 50 ትውልዶች /1000 ዓመታት/ ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ብሎም ለዓለም ያበረከተችውን አስተዋፅኦ፣ ያለፈችባቸውን ውጣ ውረዶች መለስ ብለን እንዳስሳለን:: በቀጣይም የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች፣ ዕድሎችና ጸጋዎች ወደ በጎ ለመለወጥና ለመጠቀም ምን ዝግጅት ማድረግ እንደ ሚገባ ለማ መልከት እንሞክራለን:: ይህ እትማችን የመስከረም /ጥቅምት 1999 ዓ.ም በመኾኑና የዓምዱ መጀመር ዋነኛ መግፍኤም ልዩ በኾነው የዘመን አቆጣጠራችን ሳቢያ በተሰፋ የምንጠብቀው አዲሱ የኢትዮጵያ ሣልሳይ ሺሕ ዓመት ነውና በቤተ ክርስቲያናችን የቀጥር ትምህርት /ባሕረ ሐሳብ/ እንዲሁም ተጓዳኝ ርእስ ጉዳዮች ላይ በሚያተኩረው ዝግጅታችን አሐዱ ለማለት ወደድን:: አንባብያንም ከዓምዱ ዓላማ ጋር የሚሄዱ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በመላክ እንድትሳተፉ እንጋብዛለን:: የዘመናት ባለቤት ልዑል እግዚ አብሔር ዘመኑን የአንድነት፣ የፍቅርና የሰላም ያድርግልን:: መልካም ንባብ::

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትም ህርት ዘመንን ለመቁጠር የሚያገለግለው ቀመር-ባሕረ ሐሳብ፣ በዐረብኛ አቡ ሻኸር፣ በአማርኛ የዘመን አቆጣጠር እንዲሁም መርሐ ዕውር ይባላል:: በአ ንዳንድ ሊቃውንት ዘንድም ሐሳበ ብር ሃን፣ መጽሐፈ ሐሳብ በሚል ስም ይታወቃል::

## ሐሳበ ዘመን

ሐሳብ ማለት ቁጥር ማለት ነው:: ዘመን ደግሞ በቁሙ ሆኖ ዘመ ናትን፣ ዓመታትን፣ ወራትን፣ ሳምንታ ትንና ቀናትን እስከ ሰዓታት፣ ደቂቃና ቅጽበት /ሰከንድ/ ጊዜያት ሳይቀር የሚሰፍር ነው:: እነዚህ ሁሉ በሐሳብ ተመርምረው፣ ተመዝነው፣ ተሰፍረው፣ ታውቀው፣ ተቆጥረው ሲያበቁ ምድብና ቀመር ተሰጥቶአቸው የሚገኙበትን ውሳኔና ድንጋጌ እያሰማ የሚጠራበት ስለሆነ ሐሳበ ዘመን ተባለ::

### ባሕረ ሐሳብ

ባሕረ ሐሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው:: አንድም ሐ ሳበ ባሕር ይለዋል:: ባሕር ማለቱ የት ምህርቱን ስፋትና ጥልቀት የሚያመ ለክት ነው:: የዘመን አቆጣጠርን ፊሊጥ ስለሚናገር ዘመንን በቁጥር እየሰፈረ ከዚህ ይህን ያህል አለፈ፤ ለዚህ ይህን

/ወደ ገጽ ፮ ዞሯል/

# የሚሊኒየም ትርጉም- ምእት፣ሺሕ ወይስ እልፍ?

/ፍቅርተ ማርያም/

<ሚሊኒየም> /Millennium/ የሚለው ቃል ከላቲኑ <ሚሊ> /Mille/ የወጣ ሲሆን በትርጉሙም ሺሕ ማለት ነው:: አንድ ሚሊኒየም አንድ ሺሕ ዓመት ነው:: ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዙኀን መገናኛ <ሚሊኒየም> የሚለው ቃል የተለየ ትርጉም ሲሰጠው አንብበን፣ ሰምተን ታዝበናል:: /መስከረም አራት ቀን 1999 ዓ.ም ምሽት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት በተላለፈው የጥያቄና መልስ ፕሮግራም <ሚሊኒየም> ለሚለው ቃል እንደ ትክክኛ መልስ የተሰጠው «እልፍ» ማለት እንደ ኾነ ተደርጎ ነው:: «The Millennium Development Goals» /MDGs/ የሚለውን ሐረግ «የምእተ ዓመቱ የልማቱ ግቦች»፣«የክፍለ ዘመኑ የልማት ግቦች» በአንዳንዶቹም ዘንድ «የእልፍ ዓመቱ የልማት ግቦች» ብሎ መተርጎሙ የተለመደ ኾኗል:: በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት የሐመር መጽሔት እትም የወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ ጽሑፍ «የምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች» የሚለውን ትርጉም ተጠቅሟል::/ እንግዲህ <ሚሊኒየም> የሚለውን ቃል ለመተርጎም በቀጥታ እያገለገሉ ያሉት ምእት እና እልፍ የሚሉት የግእዙ ቁጥሮች ናቸው:: ነገር ግን የግእዙ ምእት፥ መቶ ማለት ሲሆን እልፍ ደግሞ በሐዲስ የግእዝ ልማድ ዐሥር ሺሕ ማለት ነው:: በርግጥ በጥንታዊው ግእዝ እንደ ዕብራውያኑ፣ ዐረቦቹና ሱርስቶቹ ሁሉ ዐሥሩ መቶ፥ እልፍ ይባል እንደ ነበር እናስታውሳለን:: ይህንንም አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እንደ ሚከተለው ይገልጹታል፤

«ፊደላችንና የፊደል ቁጥራችን በሀ ለ ሐ አካሄድ ተፋልሶ ከላይ እስከ ታች መሳሳቱን ከጥቂት ሰዎች በቀር ኹሉ ሳያውቀው ይኖር ነበር:: የፊደሉም ቁጥር በዚያው በስሕተቱ ከሀ እስከ ፐ ፰፻/800/ ብቻ ነበር፤ ዛሬ ግን ባዑጊዳ አካሄድ ፫ ፊደላት ኊ ቈ ኧ ተጨምረውለት እልፍ/፻፻/ መልቷል፤ እስከ እልፍም በፊደል መቁጠር የጥንት ልማድ ነው እንጂ ያኹን ልብ ወለድ አይደለም:: በሴም ቋንቋ ኹሉ እንደዚህ ነው፡ በፊደል እስከ እልፍ ይቈጥራል:: ኊ፦ ስለ ቀለበቱ የ፱፻ አኀዝ መኾኑ ኀርም ኀ የሐ ተወራጅ ነውና በተራ ቁጥር ዘጠነኛነት ስላለው ነው:: ቈ፦ ስለ ቀለበቱ የ፲፻ አኀዝ መባሉ ወይም የሺሕ አኀዝ መኾኑ፤ ቆፍ ፻ ነውና የርሱን የእባቱን አሥር ተከትሎ ነው፤ ኧ ደግሞ እልፍ መባሉ /የ፲ ሺሕ አኀዝ መኾኑ/ በራሱ ላይ ስለ ተቀዳጀት ስላንዲቱ ቅንጣት ነቁጣ ነው፤ የእልፍ አ ጠባይ በዕብራይስጥም እንደዚህ ነው፤ ብቻውን አሌፍ ይባል የነበረው በራሱ ላይ ነቁጣ ሲሆንበት አንድ እልፍ ይባላል:: ዕብራውያን ግን እልፍ የሚሉት እንዳረቦች ዐሥሩን መቶ ነው፤ የግእዝም እልፍ ጥንታዊው እንደዚህ ነበር ፤ ይኸውም በአኀዙ አካሄድ ይታወቃል፤፻ /ምእት/ ብሎ ፻፻ /እልፍ/ በማለቱ:: ዐሥሩን መቶ ወይም አንዱን ሺሕ አምኣት ብሎ ዐሥሩን ሺሕ አንድ እልፍ ማለት ከጽርዕ እና ከቅብጥ የመጣ የሐዲስ ግእዝ ልማድ ነው::» /ሊ.ወ.ክ፣ 1926 ዓ.ም/::...

« ሺሕ ማለት ዐሥር መቶ ወይም መቶ ጊዜ ዐሥር ማለት ነው:: ከስላማ በፊት/330 ዓ.ም / በነበረው ባሮጌው ግእዝ መቶ ብሎ እልፍ ነው እንጂ ሺሕ የለም፤ አለመኖሩም በአኀዙ አካሄድ/ተራ/ ይታወቃል፤ ፻ ብሎ ፻፻ በማለት:: በትግሬም ቢኾን እልፍና ሺሕ አንድ ወገን ናቸው፤ እልፍ የሚባለው ያው ሺሑ ነው:: ሺሑን አምኣት ወይም ፲፻ ማለትና ዐሥሩን ሺሕ ፻፻ ማለት ከጽርእና ከቅብጥ የመጣ ነው:: ጥንታዊው ፊደል የአበገደ ተራ ሲ ፋለስ አኀዙም ተፋልሷል:: ከአሁን በፊት ለሺሕ፡ ለአምኣት እንደ ሌላው ቁጥር አኀዝ ምልክት አልነበረውም፤ ዛሬ ግን በአበገደ ሥርዐት ቀ ምእት እንዲባል፤ ቈ ደግሞ ስለ ቀለበቱ አምኣት ይባላል፤ ሺሕ ማለት ነው::» /ሊ.ወ.ክ፡ 1948 ዓ.ም::/

በመኾኑም በአኀዝና በቃላት አጠቃቀም ረገድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር በአበገደ የፊደል ተራ ቁጥር አካሄድ የግእዙንና የዐረብኛውን አኀዝ በንጽጽር አቅርበናል::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| አ _ | ፩ | አሐዱ /ዱ/ | 1 አንድ/ዱ/ |
| በ _ | ፪ | ክልኤት/ቱ/ | 2 ሁለት/ቱ/ |
| ገ _ | ፫ | ሠለስት/ቱ/ | 3 ሦስት/ቱ/ |
| ደ _ | ፬ | አርባዕት/ቱ/ | 4 አራት/ቱ/ |
| ሀ _ | ፭ | ኀምስት/ቱ/ | 5 ዐምስት/ቱ/ |
| ወ _ | ፮ | ስድስት/ቱ/ | 6 ስድስት/ቱ/ |
| ዘ _ | ፯ | ሰብዐት/ቱ/ | 7 ሰባት/ቱ/ |
| ሐ _ | ፰ | ሰመንት/ቱ/ | 8 ስምንት/ቱ/ |
| ጠ _ | ፱ | ተስዐት/ቱ/ | 9 ዘጠኝ /ኙ/ |
| የ _ | ፲ | ዐሥርት/ቱ/ | 10 ዐሥር/ሩ/ |
| ከ _ | ፳ | ዕሥራ/ሁ/ | 20 ኻያ ፤ ኹለት ዐሥር |
| ለ _ | ፴ | ሠላሳ /ሁ/ | 30 ሠላሳ ፤ ሦስት ዐሥር |
| መ _ | ፵ | አርብዓ | 40 አርባ፤ አራት ዐሥር |
| ነ _ | ፶ | ኀምሳ | 50 ዐምሳ፤ አምስት ዐሥር |
| ሠ _ | ፷ | ስድሳ | 60 ስልሳ፤ ስድስት ዐሥር |
| ዐ _ | ፸ | ሰብዓ | 70 ሰባት፤ ሰባት ዐሥር |
| ፈ _ | ፹ | ሰማንያ | 80 ሰማኒያ፤ስምንት ዐሥር |
| ጸ _ | ፺ | ተስዓ | 90 ዘጠና፤ ዘጠኝ ዐሥር |
| ቀ _ | ፻ | ምእት ፤100 | ፤ መቶ፡ ዐሥር ጊዜ ዐሥር |
| ረ _ | ፪፻ | ክልኤ/ቱ/ ምእት፤200፤ሁለት መቶ፤ኻያ ጊዜ ዐሥር | |
| ሰ _ | ፫፻ | ሠለስቱ ምእት፤300፤ ሦስት መቶ፤ ሠላሳ ጊዜ ዐሥር | |
| ተ _ | ፬፻ | አርባዕቱ ምእት፤400፤አራት መቶ፤ አርባ ጊዜ ዐሥር | |
| ኀ _ | ፭፻ | ኀምስቱ ምእት፤ 500፤አምስት መቶ፤ዐምሳ ጊዜ ዐሥር | |
| ዐ _ | ፮፻ | ስድስቱ ምእት፤ 600፤ ስድስት መቶ፤ስልሳ ጊዜ ዐሥር | |
| ጸ _ | ፯፻ | ሰብዐቱ ምእት፤ 700፤ ሰባት መቶ፤ ሰባ ጊዜ ዐሥር | |
| ፐ _ | ፰፻ | ሰመንቱ ምእት፤800፤ ስምንት መቶ፤ ሰማኒያ ጊዜ ዐሥር | |
| ኈ _ | ፱፻ | ተስዐቱ ምእት፤ 900፤ ዘጠኝ መቶ፤ ዘጠና ጊዜ ዐሥር | |
| ቈ _ | ፲፻ | ዐሥርቱ ምእት፤1000፤ዐሥር መቶ ፤መቶ ጊዜ ዐሥር፤፩ ሺሕ | |
| አ _፻፻ | | እልፍ፤ ምእት በበ፻፤መቶ ጊዜ መቶ፤ ዐሥር ሺሕ | |
| የአ _፲፻፻ | | አእላፍ፤ ዐሥር እልፍ ወይም መቶ ሺሕ | |
| ተአ _፻፻፻ | | አእላፋት፤ መቶ እልፍ፣ ሺሕ ጊዜ ሺሕ፤፩ ሚሊዮን | |
| ቈአ _፲፻፻፻ | | ትእልፊት፤ ሺሕ እልፍ፤ እልፍ ጊዜ ሺሕ፤፲ ሚሊዮን | |
| አአ _፻፻፻፻ | | ትእልፊታት፤ ሺሕ እልፍ ጊዜ እልፍ፤ ሺሕ ሚሊዮን | |
| አአአ _፻፻፻፻፻ | | ምእልፊታት፤ እልፍ /፻፻/ ሚሊዮን፤ እልፍ እልፍ ጊዜ እልፍ፤ እልፉን እልፍ | |

ከእልፍ በላይ ያሉ ቁጥሮች በውሳኔም ያለ ውሳኔም ይነገራሉ፤ ውሳኔው አስቀድሞ እንደ ተገለጸው በአኀዝ ደረጃ የተገለጸው ነው፤ ያለ ውሳኔ ሲነገር፦ ሺሐት/ዐሥር ሺሕ፡ አንድ እልፍ/፤ ሺሐታት /መቶ ሺሕ፣ዐሥር እልፍ/፤ እልፍ አእላፊ፤አእላፊ አእላፋት፤ ወትእልፊት አእላፋት ምእልፊት ይባላል። ትርጉሙም፦ ብዛቱ እንደ አሸዋና እንደ ኮከብ ያለ፤ ሰፍረው ቆጥረው ሊያውቁት የማይቻል፤ ከፈጣሪ በቀር ሰፋሪ ቈጣሪ ልክና መጠን የሌለው፣ ስፍር ቁጥር መጠን የሌለው፣ የብዙ ብዙ ማለት ነው። አባይን በጭልፋ እንዲሉ። ዘፍጥ.13፥16፤15፥15።

ከላይ በቀረበው ገለጻ መሠረት መጪውን ሦስተኛ ሺሕ ዓመት /2000 ዓ.ም/ «አዲሱ ምእተ ዓመት፤ አዲሱ እልፍ ዓመት»እያሉ ከመጥራት ይልቅ *«አዲሱ ሺሕ ዓመት፤ ሣልሳይ ሺሕ ዓመት /፫ ፲፻/፤ 2000 ዓ.ም፣ ዘዕሥራ ወአሐዱ ምእት ክፍለ ዘመን /ኻያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን/፣ ዘ፳፩ ምእት ክፍለ ዘመን»* ማለት ይሻል ይሆናል።

<u>ምንጭ</u>፦አለቃ ኪዳነ ወልድ ፊደል ሌማውያት፤ 1926 ዓ.ም፤ ገጽ 21-23
-አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ</u>፣ ገጽ፣36-37፤ 224፤861።

<u>፲፻</u> ዐሥርቱ ምእት = ዐሥር መቶ /Ten hundreds/
ሺሕ = ሺ /Thousand = millennium
ቀዳማይ ሺሕ = የመጀመሪያው ሺ ዓመት = First millennium /0-999 A.D/ /0-999 ዓ.ም/
ካልአይ ሺሕ = የኹለተኛው ሺ ዓመት = Second millennium /1000-1999 A.D/ /1000- 1999 ዓ.ም/
ሣልሳይ ሺሕ = የሦስተኛው ሺ ዓመት = Third millennium /2000-2999 A.D/ /2000-2999 ዓ.ም/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

/ከገጽ ፳ የዞረ/

ያህል ቀረ፤ እያለ ያልተሟላውን የተረፈውን የሚነግር ነው። ስለምን ዘመንን ባሕር አለው ቢሉ፦ ባሕር ከምንጩ ከነቅዑ ወጥቶ ቢፈስ አያልቅም፤ ዘመንም ምጽአተ ክርስቶስ እስኪያገድው ድረስ ሰውን እያሳለፈ ሲመላለስ ይኖራል። አንድም ከባሕር ሁከት እንዳይታጣ፤ ከዘመንም ሁከተ ሥጋ ሁከተ ነፍስ አይታጣምና። አንድም ከባሕር ማዕበል ሞገድ እንዲነሣሣ ከዘመንም ማዕበለ ኃጢአት ማዕበለ ክሕደት ይነሣልና፤ መልሕቅ ጥለው ዓላማ ተክለው የባሕር ሁከቱን ማዕበለ ሞገዱን ጸጥ እንዲያደርጉት የዘመንንም ሁከተ ሥጋ ሁከተ ነፍስ÷ ማዕበለ ኃጢአት ማዕበለ ክሕደት ጾመው ጸልየው ምሕላ ይዘው ጸጥ ያደርጉታልና። መዝ. 103 /104/÷25÷27። /አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ</u>፣ ገጽ 261/።

## አቡ ሻኸር

የሐሳበ ዘመንን ትምህርት ካዘጋጁና ካስፋፉ ሊቃውንት ዮሐንስ አቡሻኽር አንዱ ነው። በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ እጅግ ይወደዳል። የሐሳበ ዘመን አቀራረቡ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ዝነኛና የተወደደ በመሆኑ መጽሐፉን በስሙ አቡ ሻከር ብለውታል። ድርሰትን በደራሲው ስም መጥራት የተለመደ ነው። ይህንም በመጽሐፈ አቡ ሻኸር መግቢያ ላይ እንዲህ ሰፍሮ ይገኛል።

*«ዝንቱ መጽሐፍ ቡሩክ ዘደረሶ እግዚእ ትሩፈ ምግባር ማእምረ መጻሕፍት አቡ ሻኸር ወልደ አቡእልከረም ጴጥሮስ መነኮስ ዕብንልመሐደብ ዘበትርጓሜሁ ወልደ ግሡጽ ወእመ አኮ ወልደ ምሁር ዘእሙር በረሺ ዘተሰይመ ዲያቆነ በቤተ ክርስቲያን ዘመዓልቃ እንዘ ይነግር በእንተ ሐሳበ ዓለም እም ፍጥረተ አዳም፤*

*ይህን የተመሰገነውን መጽሐፍ የደረሰ ምግባሩ የቀና መጻሕፍትን የሚያውቅ መነኮስ የአቡእልከረም ጴጥሮስ ልጅ ሊቁ አቡ ሻኸር ነው። ዕብንልመሐደብም ይሉታል። የታረመ ምሁር ልጅ ማለት ነው። በረሺ የታወቀ በመዐልቃ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሆኖ የተሾመ ሲሆን በመጽሐፉም አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ ስለ ሐሳበ ዓለም ይናገራል።» /አቡ ሻኸር፣ ገጽ 7/።*

## የቁጥር ትምህርት

የሰውን ልጅ ማለትም አዳምን በሚመለከት ታሪክ የሚቀምረውን *የዘመን አቆጣጠር ሲያመለክት፦ «የዘመን አቆጣጠር ፈሊጥ፤ የቁጥር ትምህርት»* ብሎ ይጠራዋል። የቁጥር ትምህርት ራሱን የቻለ ቀዋሚ የባለሞያ መደብ ተሰጥቶት እንደ ሚገኝ የታወቀ ነው።





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## ዘመነ ዓለም

የዘመን አቆጣጠር ዘመነ ዓለም ተብሎ የሚጠራበት ጊዜም አለ። ይኸውም የሰው ልጅ ማለትም ዓለመ አዳምን በሚመለከት ታሪክ የሚቀምረውን የዘመን አቆጣጠር ሲያይ የተሰጠው ስያሜ ነው። /ዕዝራ ሱቱኤል 13÷10-13/።

## መርሐ ዕውር

የዘመን አቆጣጠር መርሐ ዕውር መባሉ «የዐይነ ስውር መሪ፣ ዐይነ ስውርን የሚመራ» ለማለት ነው። ዐይነ ስውር እሾኽ እንዳይወጋው፣ እንቅፋት እንዳይመታው፣ ባሕር ጠልቆ ገደል ወድቆ እንዳይሳዳ መሪው ጠብቆና መርቶ ከቤት እንዲያደርሰው፣ የዘመን ቁጥርም አላዋቂውን ሰው ሶከ ኃጢአት /የኃጢአት እሾኽ/ እንዳይወጋው፣ እቅፍተ ሥጋ እቅፍተ ነፍስ /የሥጋ÷ የነፍስ እንቅፋት/ እንዳያገኘው፣ በባሕረ ኃጢአት ሠጥሞ በክሕደት ወድቆ እንዳይሞት ጠብቆና መርቶ እንደ ነቢያት /ዳንኤልና ዕዝራ/ አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ወደ ማወቅ ያደርሰዋልና። ሰው ሆኖ ዕድሜውን የሚያሰላ በማንኛው ዘመን ላይ እንዳለ ለማወቅ የማይችን የለምና ዘመንን ዐዋቂውም አላዋቂውም ስለሚጠቀምበት በተለይ ለአላዋቂው ለመንገር ለማስተማር ሲባል ይህን «*መርሐ ዕውር*» የተሰኘውን ስያሜ አግኝቷል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም:- *«መርሐ ዕውር ውእቱ መጽሐፈ ድሜጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእለ እስክንድርያ፤ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ የድሜጥሮስ መጽሐፍ መርሐ ዕውር ነው።»* ብለዋል።

## የዘመን አቆጣጠር ቅድመ ልደተ ክርስቶስ

እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን ሁሉ:- «ብላ ጠጣ፣ ግዛ ንዳ» ብሎ በገነት አኖረው። አዳምም ሰባት ዓመት ትእዛዙን ጠብቆ በሕጉ ጸንቶ ከቆየ በኋላ ምክረ ከይሲን ሰምቶ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ወጣ። አዳም ንስሐ ቢገባ ቃል ኪዳን ሰጠው፤ «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንነለሁ.... » ብሎ ተስፋውን ነገረው። አዳምም ለልጆቹ ይህን ተስፋ ነገራቸው። ልጆቹም እኩሌቱ በጨረቃ እኩሌቱ በከዋክብት እንዲሁም በፀሐይ ዘመናትን ሲቆጥሩ ኖረዋል። የዘመን ቁጥር የተጀመረው በዚህ ምክንያት ነው። ነቢያትም ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔ ሲቆጥሩ ኖረዋል።

የሰው ልጆች የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ዘንግተው በእጃቸው የሠሯቸውን ጣዖታት ያመልኩ ነበር። ተስፋውን ከሚጠባበቁት በስተቀር የቀጠሮውን ቀን፣ ከ5500 ዘመን ጀምሮ ያለውን ቁጥር የሚያስብ፣ ወደታች የሚቆጥር፣ የነቢያትን ሱባዔ የሚመረምር ሕዝብ ጠፋ። ጨረቃን የሚያመልከው በጨረቃ ሲቆጥር፣ በዋክብት የሚያመልከው ከዋክብትን ሲቆጥር÷ ለዘመን መቍጠሪያ የተሰጡት መጋብያን ዕለታት ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን አማልክት አደረጋ ቸው። ፈላስፎችና የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ደግሞ ለዚህ ድርጊት ዋነኞች ነበሩ። እነዚህም «መሰግላን ወይም መጥ ዓውያን ጠንቋዮች /ኮከብ ቆጣሪዎች/፣ ፋሴካውያን፣ ሠራዕያነ ሕግ» እየተባሉ የሚጠሩናቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ዘመናትን ይቆጥሩ ነበሩ።

## ጥንታውያን የዘመን አቆጣጠሮች

ጥንታውያን የዘመን አቆጣጠሮችን ስንመለከት ቀደም ብሎ እንደ ተጠቀሰው ቀን መቍጠርና ማስላት የተጀመረው አዳም ከገነት ከወጣና ተስፋውን ከሰማ ጊዜ ጀምሮ ነው። እነዚህ ጥንታውያን አቆጣጠሮች የሚባሉት:

- የአይሁድ ሐሳበ ዘመን፣ የግብጻውያን፣ የዮልዮስ ቄሣር እና የሩቅ ምሥራቁ /ሕንዱ/ ሐሳበ ዘመን ናቸው። እኒህን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን።

### 1. የአይሁድ የዘመን ስሌት

ይህ አቆጣጠር የፀሐይንና ጨረቃን ዑደት የተከተለ ሲሆን ሁለቱንም ለማጣጣም ይሞክራል። በክርስትናም የዘመን አቆጣጠር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ዓመቱን በአራት የአየር ጠባይ ወቅቶች ከፍሎ በጨረቃ አንዳንዴ 30 አንዳንዴ 29 ቀን የሆኑ 12 ወሮች አሉት። ይህ አቆጣጠር የ30 ቀናት ዑደት ካሉት ከባለ12ቱ ወር የፀሐይ ወር በ11 ቀኖች ያንሳል።

### 2. የግብጻውያን የዘመን ስሌት

ታላቁ እስክንድር ከግሪክ እስከ ፋርስ ሲገዛ አሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ የሥነ ፈለክ /Astronomy/ እና ኮከብ ቆጠራ /Astrology/ ማእከል ነበረች። ይህ ሁኔታ ግብጻውያንን ቀደም ብሎ በጨረቃ በኋላ ደግሞ በፀሐይ እንዲቆጥሩ አድርጓቸዋል። 30 ቀናት ያላቸው 12 ወራት ለአንድ ዓመት መቍጠሪያ ይጠቀማሉ። ትርፉን አምስት ቀን ጨምረው በአጠቃላይ 365 ቀናትን አንድ ዓመት ይላሉ። 239 ቅ.ል.ክ በበጥሊሞስ ውሳኔ አንድ አራተኛ ቀን ጨምረው $365^{1}/4$ ቀንን አንድ ዓመት ማለት ጀመሩ። ይህን አቆጣጠር እስከ ጁሊየስ ቄሣር ዘመን ድረስ ይጠቀሙበት ነበር። አሁን ግን የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ዓመቱን ትሰፍርበታለች።

### 3. የዮልዮስ ቄሣር የዘመን ስሌት

ታሪክ እንደ ሚያስረዳው የጁሊየስ ቄሣር ዘመን አቆጣጠር በመጀመሪያ አንድ ዓመት 304 ቀናትን በያዙ 10 ወሮች ተወሰነ። ከዚያ ሮምን ከመሠረተው ከንጉሥ ሮሙለስ ቀጥሎ የነገሠው ሁለት ወራትን በመጨመር የዓመቱን ቀኖች ወደ 355 ከፍ እንዲል አደረገ።

ጁልዮስ ቄሣር በሮም ሲነግሥ /46 ዓመት ቅ.ል.ክ/ ከሶሲጀንስ /Sosigenes/ ጋር በመሆን 365 ቀናት ያሉትን የአሌክሳንድርያ ዘመን አቆጣጠር አብነት በማድረግ የጳጒሜን አምስት ቀን እየበተነ 30 ቀን የሆነውን የካቲትን 28 አድርጐ መስከረም፣ ኅዳር፣ ሚያዝያ፣ ሰኔ-30 ቀናት እንዲኖራቸው ሌሎቹ ጥቅምት፣ ታኅሣሥ ፣ ጥር፣ መጋቢት፣ ግንቦት፣ሐምሌና ነሐሴ-31 ቀናት ሆኖ የካቲት በአራት ዓመት አንድ ጊዜ /Leap year/ 29 እየሆነ በሌሎቹ ደግሞ 28 ቀናት ይዞ እንዲኖር አደረገ። በዚህም ሮማውያኑ 12ቱን ወር በ365 ቀን ወይም በ366 ቀን ሲያጠናቅቁ አንድ ዓመት ይላሉ። እኛና ግብጻውያን ግን በ12ቱ ወር ላይ አንድ ባለ አምስት ወይም ስድስት ቀን ያለው ትንሽ ወር በመጨመር በእኩል ቀን ብዛት ነገር ግን በሚለያዩ ወሮች አንድ ዓመት እንላለን። ይህ ሐሳበ ዘመን በተደረገበት ለውጥና ማሻሻያ የምዕራቡን ዓለም ሲያገለግል ቆይቷል። አሁን ያለውም የጎርጎሮሳውያን ሐሳበ ዘመን /Gregorian Calender/ ተብሎ ተሰይሟል።

ከዚህ በላይ ያየናቸውን አቆጣጠሮች የቀናቱን፣ የዓመታቱን የወራቱን ስያሜያቸውን ስናያቸው ከአምልኮተ እግዚአብሔር የራቁ ሆነው እናገኛቸዋለን።

### 4. የክርስቲያኖች ዘመን አቆጣጠር

ክርስትና በመጀመሪያ የነበረበት ዘመን በሁሉም አንጻር ሲታይ እጅግ በጣም አስቸጋሪና መከራ የመላበት ነበር። በአረማውያን በኩል ምዋርት፣ ጥንቆላ፣ ጣዖት አምልኮ፣ ክርክር፣...የመሳሰሉት የተባባሰበት ወቅት ነበር። አይሁድም ጌታን ከሰቀሉ በኋላ ራሳቸውን ከተጠያቂነት ነጻ ለማውጣት ለጌታ የተነገረውን ትንቢት ማዘበራረቅ፣ የተቆጠረውን ሱባዔና የዘመን ልክ ማዛባት የተያያዙበት ወቅት ነበር፡ ይህንንም ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴ መጻሕፍትን መቆንጸል፣ ቁጥራቸውን መቀነስ ነበር።

የዕብራውያን ሐሳበ ዘመን ከሁሉም ይልቅ በክርስትና ዘመን አቆጣጠር መሠረት በመሆኑ በመጠኑም እንመለከተዋለን። ዓመቶቹ የሚቆጠሩት በፀሐይ ነው። ዕድሜ ደግሞ በዓመት ነው የሚሰፈረው። «አዳም ይህን ያህል ዓመት ኖረ» ከሚለው አባባል ይህን ማወቅ ይቻላል። የአዳምን ዕድሜ መነሻ በማድረግ ከአዳም እስከ ክርስቶስ ያለው ዘመን ሲቆጠር 5500 ዓመት ነው።

<u>ዝርዝሩም</u>:-

ዘመነ አበው - 3842

ዘመነ መሳፍንት - 589

ዘመነ ነገሥት - 543

ዘመነ ካህናት - <u>526</u>

ድምር =<u>5500</u> ዓመት ነው።

/ማኅበረ ቅዱሳን÷ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላንት ዛሬና ነገ፤</u> 1994 ዓ.ም/።

## ሐሳበ ዘመን ዘኢትዮጵያ

ክርስቶስ ካረገ ከ180 ዓመት በኋላ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ድሜጥሮስ ተሾመ። ክርስቲያኖች ከሐዋርያት ዘመን ጀምረው እስከ ቅዱስ ድሜጥሮስ ዘመን ድረስ የጌታችንን ጾም /ሁዳዴን/ በየዓመቱ ሁል ጊዜ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከጥምቀት ማግሥት /ከጥር 12 ቀን/ ጀምረው እስከ የካቲት 21 ቀን ድረስ አርባ ቀን ከጾሙ በኋላ ጥቂት ቀኖች ቆይተው የሕማማትን ሳምንትና የትጠንሣኤውን በዓል ሲያከብሩ አየ:: የቀድሞዎች ሰዎች እንደዚህ ያደርጉ የነበረው የአጽዋማቱን፣ የበዓላቱን መንሥኤ /ጥንት/ ሲፈልጉ ማለትም የቀኖቹን ቁጥርና ሁለተኛም የጾሞቹን መግቢያና በዓላቱ የሚውሉበትን ዕለት ፈልገው በደረሱበት ቀን ለማዋል ነበር:: አስልተው /ለበዓል መዋያም ሆነ ለጾም መግቢያ/ የሚያገኙት ዕለት÷ እሑድ ወይም በማናቸውም አዘቦት ቀን ቢሆን በዚያ ዕለት ያከብሩታል እንጂ እኛ ዛሬ እንደ ምናደርገው ለውጠው /ከሳምንቱ ዕለታት/ የተወሰኑ ቀኖች አይሰጧቸውም ነበር:: /ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ባሕረ ሐሳብ-የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን፣ ገጽ 110/::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሐሳበ ዘመን መምህራን እንደ ሚያስተምሩት:- አጽዋማት፣ በዓላት ጥንታቸውን እንዲጠብቁ ይመኝ የነበረው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ድሜጥሮስ በዓላትና አጽዋማት በጥንቱ መገኛቸው የሚውሉበትን ጊዜ ለማስተካከል ይህን የሚወስን የቁጥር ሕግ ለማግኘት ተመኝቶ ሱባዔ ገባ::

ነነዌ፣ በኣተ ጾም /የዐቢይ ጾም መግቢያ/፣ ጾመ ሐዋርያት-ከሰኞ፣ ደብረ ዘይት፣ ሆሳዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ - ከእሑድ፣ ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት - ከረቡዕ፣ ዕርገት- ከኀሙስ፣ ስቅለት ከዓርብ፣ ባይወጡ እያለ ይመኝ ነበር:: ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ መጥቶ: - «ድሜጥሮስ ሆይ÷ ይህ ሁሉ በሐሳብ አይፈጸምም፤ በተግባር ቢያደርጉት ስለሆነ ሱባዔ ግባ» ብሎታል:: ድሜጥሮስም ሱባዔ ገብቶ በአንድ የጸሎት ጊዜው ሰባት ጊዜ አቡነ ዘበሰማያት እየደገመ ከቀኑ ሰባት /7/ ከሌሊቱ ኻያ ሦስት /23/ ሱባዔ ያዘ::

ስለምን የቀኑን ሱባዔ አሳነሰው ቢሉ ቀን በማስተማር፣ የተጣሉትን በማስታረቅ ስለሚውል ሌሊት ግን ከዚህ ሁሉ ነጻ ነውና የሌሊቱን ሱባዔ አበዛው:: ከቀኑ ሰባት ሱባዔ በሰባት አባዝቶ 49 ሲሆንለት 49 አቡነ ዘበሰማያት ይደግማል:: በ30 ገድፎ /አካፍሎ/ ትርፉን 19ኙን ጥንተ መጥቅዕ ብሎታል:: ከሌሊቱም 23 ሱባዔ ደግሞ በሰባት አባዝቶ 161 ሲሆንለት 161 አቡነ ዘበሰማያት ይደግም ነበር:: በ30 ገድፎ ቀሪውን 11ዱን ጥንተ አበቅቴ ብሎታል:: መጥቅዕ ለቀን÷ አበቅቴ ለሌሊት ማውጫ ያገለግላሉ::

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ድሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት «ኢይዓርግ ኢይወርድ» ተገልጾለት ለአጽዋማቱ÷ ከሰኞ እንዳይወጡ፤ መግቢያ ሥርዐት ሠራላቸው:: ለበዓላቱ ደግሞ ደብረ ዘይት፣ ሆሳዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ /በዓለ ኀምሳ/ ከእሑድ፤ ስቅለት ከዓርብ፤ ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት ከረቡዕ፤ ዕርገት ከዕለተ ኀሙስ እንዳ ይወጣ አደረገ:: የሕማማትን ሳምንትና የትንሣኤን በዓልም ከጾመ አርባ አያይዘው አከታትለው እንዲያከብሩ ሥርዐት ሠራ:: በተጨማሪም በዓመቱ ውስጥ ከወሰኑላቸው ጊዜ ወደ ታች እንዳይወርዱ ወደ ላይም እንዳይወጡ የቀመር ሕግ አወጣ::

እነዚህን በሰባት አዕዋዳት ዐውዶ በሶርያ፣ በአንጾኪያ፣ በሮም ላሉት ለሦስቱ ሊቃነ ጳጳሳት÷ አራተኛ በኢየሩሳሌም ላለው ኤጲስ ቆጶስ ጽፎ ሰደደላቸው:: እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ሆነው ቢያገኙት ደስ ብሎአቸው ተቀብለው ባሕረ ሐሳቡን አስተምረውታል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም÷ ተቀብላ በሥራ ላይ አውላዋለች:: ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ሐሳብን ካህኑም ክርስቲያኑም ሊማረው እንደ ሚገባ ታስተምራለች:: ሐሳበ ዘመንን የተማረ ሰው ከአገሩ ተሰዶ ቢሄድ እንኳን ጾም አይገድፍም፣ በዓል አይሽርም፤ ምክንያቱም አጽዋማት የሚገቡበትን በዓላት የሚውሉበትን ተምሯልና:: ባሕረ ሐሳብን ያልተማረ ካህን፤ ካህን መባል አይገባውም በማለት ያስተምራሉ:: ቤተ ክርስቲያንም በአዲስ ዘመን መባቻ ምእመናን በተገኙበት በዓላት የሚውሉበትን አጽዋማት የሚያዙበትን ኢይዓርግ /ከዚህ አይወጣም/ ኢይወርድ /ከዚህ አይወርድም/ እያለች በባሕረ ሐሳብ እያሰላች አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ለምእመናን ታውጃለች:: ምእመናንም ይህን በመያዝ በዓላትን ያከብራሉ፤ አጽዋማትን ይጾማሉ::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የመሸጋገሪያው ዕለት ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል:: ርእሰ ዓውደ ዓመት በግእዝ ሲሆን በአማርኛ *«የዘመን መለወጫ፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ዕንቁጣጣሽ»* እየተባለ ይጠራል:: ይህ በዓል ለዓመት መጀመሪያ እንደ መሆኑ መጠን ለአውራኅም ጥንታቸው ነውና በዓመቱ ወሮች በመጀመሪያ ቀን ይከበራል::

ርእሰ ዓውደ ዓመት መስከረም 1 ቀን ለምን ይከበራል? በኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ በመስከረም ወር የሆነበትን ምክንያት ሊቃውንቱ ሲያትቱ ብርሃናት /ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት/ የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜን ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው:: ያን ጊዜ ሌሊቱም ከቀኑ ጋር ይተካከላል:: ዓመቱንም ጠንቅቀው ቢቆጥሩት 364 ይሆናል:: «ለዘመን መታወቂያ ይሆን ዘንድ ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ::» ይላልና:: ኄኖ. 21÷49:: በሌላ በኩልም በዘመነ ኖኅ ዓለምን ንፍር ውኃ አጥለቅልቋት ከቆየ በኋላ ዳግመኛ ከነበረው ውኃ የተገለጠችበት ወር ነው:: ኩፋ.7÷1:: «በመጀ መሪያም ወር ምድር ታየች፤ የንፍር ውኃም ከምድር ደረቀ::» የሚለውን መሠረት አድርገው የአቡ ሻኸር ሊቃ ውንት የዘመን መለወጫን ታሪካዊ አመጣጥ ያስቀምጣሉ::

ኢትዮጵያ ጥንታውያን በሆኑና በታወቁ የአሕዛብ መንግሥታት ዘመን እንኳ ሳይቀር የራስዋን ብሔራዊ ድርሻ በሐሳበ ዘመን ለትውልድ ማስተላለፍዋ ይታወቃል:: የኢትዮጵያ የዓመተ ዓለም አቆጣጠር መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ ከሱባዔያት ተስማምቶ የልደተ ክርስቶስን ተስፋዊ ቀጠሮ አስገንዝቦአል:: በአበቅቴና በመጥቅዕ ዐዕቅና ፍሬ እየሆኑ የተገኙት ቀዋምያን የሐሳብ አውታሮች እግባቸው ሲደርሱ የሚታዩት መንሥኤያቸውን /መነሻቸውን/ መስከረም አንድ ቀን አድርገው ነው::

የዓመተ ዓለም ተረፈ ዘመን ያስገኘው አበቅቴ መስከረም አንድ ቀንን ተደግፎ ይገኛል:: ለአበቅቴ ቅርንጫፍ የሆኑ የስድስት ወር ሕጸጽና ሠርቀ ሌሊት፣ የጨረቃ ብርሃን ሙላትና ጉድለት የሚለካበት የጨረቃ አቆጣጠር መነሻዎች መስከረም አንድ ቀን ነው:: መጥቅዕ:- አጽዋማትና በዓላት በጥንተ ተረክቦአቸው /ቀድሞ በዋሉበት ቀን/ እንዲውሉ የሚሆንበት ነው:: መጥቅዕ ለሚወድቅበት ቀን መነሻው የመስከረም መባቻ /መስከረም አንድ ቀን/ መሆኑ ይታወቃል::

የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖናዊ ሥርዐት ጥናት ያደረጉ አበው ርእሰ ዐውደ ዓመት መስከረም አንድ ቀን መሆኑን አስመልክተው በክታባቸው እንዳሰፈሩት:- «አራቱ ወንጌላውያን ዘመኑን እየተካፈሉ÷ በዮሐንስ ተፀንሶ በዘመነ ማቴዎስ ተወልዷል፤ በዘመነ ማርቆስ ተጠምቋል፤ በዘመነ ሉቃስ ተሰቅሎ ዓለምን ከፍዳና ከመርገም ነጻ አውጥቷል» እያሉ ታሪካዊ ሐረጋቸውን ተከትለው ያለ እንቅፋት እንደ ሚጓዙ ያስረዳሉ::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት ለምን «ቅዱስ ዮሐንስ» ተባለ?

ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን ሲጽፍ: - «የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ወንጌል መጀመሪያ:: እነሆ÷ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፤ <የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ> እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በኢሳይያስ እንደ ተነገረ፤ የነቢዩ ዘካርያስ ልጅ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በዘመነ ብሉይ መጨረሻና በዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ ላይ ተነሥቶ:- «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት እየመሰከረ በምድረ በዳ የንስሐን ጥምቀት እያጠመቀ ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ::» ብሎ ለዘመነ ወንጌል የመጀመሪያ ምዕራፍ እንዳደረገው ይታያል:: ማር.1÷14:: ኢሳ.40÷3-4::

የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል በር ወይም መነሻ ሆኖ መገኘቱን በመረዳት የቤተ ክርስቲያን አበው የበዓላትን ድንጋጌ በወሰኑበት ጊዜ፤ የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰቢያ በዓል የኢትዮጵያ ርእሰ ዐውደ ዓመት በሚሆን መስከረም አንድ ቀን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንዲከበር በየዓመቱ የዘመኑ መጀመሪያ በእርሱ ስም እንዲጠራ አደረጉ:: /ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ገጽ 1-3/::

ይህንንም በዓል አባቶቻችን በርእሰ ዐውደ ዓመት ማክበር እንደ ሚገባ አስበው ያደረጉት ነው እንጂ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በሰማዕትነት ያረፈበት ቀን ሆኖ አይደለም:: ስለዚህ የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ወይም ርእሰ ዐውደ ዓመት «ቅዱስ ዮሐንስ» ይባላል::

*ስንክሳሩ የዓመቱን መጀመሪያ /መስከረምን/ ሲያትት እንዲህ ይላል፡- «ዝንቱ ወርኅ መስከረም ቡሩክ፤ ወውእቱ ርእሰ ዓመታት ዘግብጽ ወዘኢትዮጵያ:: መዓልቱ ወሌሊቱ ለዝንቱ ወርኅ ዕሩይ ፲ወ፪ ሰዓቱ:: ወእምዝ የሐፅፅ እምአሚሩ ለወርኅ መስከረም:: ትርጉሙም፡- ይህ የመስከረም ወር የተባረከ ነው፤ እርሱም የግብጽና የኢትዮጵያ ዓመቶች መጀመሪያ ነው:: የዚህ ወር ቀኑና ሌሊቱ እኩል 12 ሰዓት ነው:: ከዚህ በኋላ ከመስከረም 1 ቀን ጀምሮ ቀኑ እየጐደለ ይሄዳል::»*

*ርእስ ዓውደ ዓመት ዕንቍጣጣሽ የተባለበትም ምክንያት፡- <ዕንቁ - ዕፅ - አወጣሽ> ብሎ የአበባውን መፈንዳት ወይም <ዕንቁ - ዕጣ - ወጣሽ> ብሎ መልካሚቱ ምድር ኢትዮጵያ በዕጣ ለካም መድረሷን የሚያመለክት ነው:: /አለቃ አያሌው ታምሩ፥ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፥1953 ዓ.ም፥233-235/::*

## 1500 ዓ.ም = ስምንተኛው ሺሕ = ዐፄ ናዖድ

ጥንቱ ሲታሰብ የስምንተኛው ሺሕ ፍጻሜ አባታችን አዳም በየሺሕ ዓመቱ ዕፀ ሕይወትን እየበላ፥ሰውነቱ ከብልየት እየታደሰ በዔደን ገነት ቆይቶ ርስት መንግሥት ሰማያትን የሚወርስበት ነበር ይላሉ:: ከስሕተት በኋላ ግን በትንሣኤ ዘጉባኤ ነፍሳት ሁሉ ለኀሣር ወይም ለክብር የሚነሡበት፣ ዋጋ መንግሥተ ሰማያትን ወይም ፍዳ ገሃነመ እሳትን የሚቀበሉበት፣ ሰማይና ምድር በወልደ ዕጓለመሕያው ክርስቶስ ቃል እንደ ብራና ተጠቅልለው የሚያልፉበት ይሆናል::

በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ለ2000 ዓ.ም መሸጋገሪያ በኾነው 1999 ዓ.ም ላይ እንገኛለን:: በዓመተ ዓለም ስንቆጥረው ደግሞ 7499/1999+5500=7499/ ላይ እንገኛለን:: በድምሩ ስምንተኛውን ሺሕ አጋምሰነዋል ማለት ነው:: ሊቃውንቱ ስምንተኛው ሺሕ የዘመን ፍጻሜ እንደ ሚሆን በዚህም የተለያዩ ምልክቶች የሚታዩ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው ያስተምራሉ:: ማቴ.24:: የስምንተኛውን ሺሕ አቆጣጠር፡- ስንመለከት ከ1500 ዓ.ም ጀምሮ ስምንተኛው ሺሕ ገባ ብለን እንቆጥራለን፤ ዓመተ ፍዳን /5500/ እና ዓመተ ምሕረትን /1500/ ደምረን የምናገኘው ድምር 8000 ዓመተ ዓለም ይሆናል:: በዚህም መሠረት ስምንተኛው ሺሕ ላይ መሆናችን ይታወቃል:: ታላቁ ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዐፄ ናዖድ /1485 - 1499 ዓ.ም/ በስምንተኛው ሺሕ ዋዜማ ላይ የነበሩ ንጉሥ ናቸው::

ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዐፄ ናዖድ የስምንተኛው ሺሕ ነገር ተገልጾላቸው፡- «ከጊዜው አታድርሰኝ፤ ከእህል ከውኃው አታቅምሰኝ» እያሉ እግዚአብሔርን ይለምኑ፥ እመቤታችንን ይማፀኑ ነበር:: ወላዲተ አምላክም የዐፄ ናዖድን ጸሎትና ልመና ሰምታ ስምንተኛው ሺሕ በመስከረም ሊገባ 28 ቀናት ሲቀሩት ዐሥራ አራት ዓመት አስተዳድረው ነሐሴ 7 ቀን 1499 ዓ.ም ዐርፈዋል::/<u>መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው</u> /መዝ 11፥1/ ተመልከት/::

## የዘመን አቆጣጠራችን ከምዕራብ ክርስቲያኖች ለምን ተለየ?

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ «ባሕረ ሐሳብ» በሚለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከምዕራባውያን የተለየበትን ምክንያት ሲያትቱ፡- «ዋናው ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እርሱን መነሻ ማድረግ ነው:: ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገውት ነበር፡ ታላቁ እስክንድር የገነነበትም የዘመን መቍጠሪያ ሆኖ ነበር:: የእኛ ካህናትም «ዘመነ እስክንድር» በሚል ስም ይጠቀሙበት እንደ ነበር የብራና መጻሕፍቶቻችን ይመሰክራሉ:: ሶርያውያን፣ የዘመን አቆጣጠርን /ማለት በፀሐይ ቆጥሮ ለዓመቱ 365/6 ዕለት መስጠትን/ ከሮማውያን በተዋሱ ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ ጥቅምት /ኦክቶበር/ 1 ቀን ላይ አድርገውት ነበር:: በኋላ የሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓመተ እግዚእ ወደ መስከረም /ሴፕቴምበር/ 1 ቀን ለወጡት:: ግብጾችና እኛ ርእሰ ዐውደ ዓመታችንን መስከረም 1 ቀን ያደረግነው ይኸንን በመከተል ነው:: የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብጾች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ይገዛ የነበረው ቄሳር ዮልዮስ ስለነበረ የዮልዮስ ባሕረ ሐሳብ /Julian Calendar/ ይባላል::

ዮልዮስ ቀሣር በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዐት መሠረት ዓመቱን 365 ዕለት ከ6 ሰዓት አድርጎ ለአራቱ ወሮች 30፣30 ዕለት ለአንዱ ወር 28/29 ዕለት ለቀሩት ሰባት ወሮች 31፣ 31 ዕለት መድቦላቸው 12 ቦታ ከፈለው:: 12 ወሮች መሆናቸው ነው:: እኛ በዓመቱ ቀኖች ተስማምተን ቀኖቹን በወር ስንከፍል ተለያይተናል:: ዋናው ነገር ዓመቱ ውስጥ ባሉ ት ዕለቶች መስማማታችን ነው::» ይላሉ::

ዓሥራት ገብረ ማርያም ደግሞ፡- «የዘመን አቆጣጠር» በሚለው መጽሐፋቸው እንደ ገለጹት ዲዮናስዮስ የተባለው የሮማ መነኩሴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተወለደበት ዘመን በስሌት ለመድረስ የተከተለው መንገድ የታሪክ ክሥተትን ነበር:: ይኸውም የሮማ ከተማ የተመሠረተችበትን ዘመን ተንሥቶ በመቁጠሩ ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ዘመን ለመወሰን የታሪክ ክሥተትን አልተከተለችም:: እርስዋ የተከተለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዘመንን ነው:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይህን አባባል ሲያረጋግጡ እንዲህ ብለዋል፡- «ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን እንዲህ አስተካክላ 5500 ብላ ስትቆጥር ዘመነ ሐዲሷ ልዩ ሆኖ ከማንም ቁጥር አይገጥምም፤ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከምሥራቆቹም ከምዕራቦቹም ወትሮ በሰባት ዓመት ታጐድላለች:: ምክንያቱም ባለታሪኮችንትታ ወንጌል ተርጓሚዎችን ስለ ተከተለች ይመስላል::» ብለዋል:: በዚህም መሠረት የኢትዮጵያና የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ሊኖረው የቻለው ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ መሠረት መነሻዋ የ5500 ዘመን ፍጻሜ ሲሆን አውሮፓውያን ግን መነሻ ያደረጉት የታሪክ ክሥተትን በመሆኑ ነው:: /ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ <u>የዘመን አቆጣጠር</u>፤ ከገጽ 58-59/::

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

*«ሚልሳይ ሺሕ ዓመት» ወይም «የኢትዮጵያ ሚሊኒየም» ብለን በሰየምነው አዲስ ዓምዳችን ባሳለፍናቸው 50 ትውልዶች /1000 ዓመታት/ ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ብሎም ለዓለም ያበረከተችውን አስተዋፅኦ፣ ያለፈችባቸውን ውጣ ውረዶች መለስ ብለን እንዳስሳለን:: በቀጣይም የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች፣ ዕድሎችና ጸጋዎች ወደ በጎ ለመለወጥና ለመጠቀም ምን ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ለማመልከት እንሞክራለን:: አንባብያንም ከዓምዱ ዓላማ ጋር የሚሄዱ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በመላክ እንድትሳተፉ እንጋብዛለን::*



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የዓለም ሰላም ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ መስከረም 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተከብሯል:: በዕለቱ በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላም ጉባኤ ተካሂዶ ነበር:: በጉባኤው ላይ የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ኮፊ አናን፡- «*ዘመናችን በጎሳ እና በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሠረተ ጥላቻ የሰፈነበት ነው:: ስለዚህም መቻቻል ይኖርብናል::*» በማለት ተናግረዋል:: በሌላ በኩል የጎሳ እና የሃይማኖት ማንነት የሚፈጥረው ልዩነት በራሱ ሰፍኗል ለሚባለው ጥላቻ ዋነኛ መሠረት እንዳልሆነ ይታወቃል:: ይልቁንም በልዩነቱ ሰበብ ለፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሞች ሲባል ሊፈጠር የሚችለውን ውጥረት እና ግጭት ትክክለኛነት ለማላበስ፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና ለማቀጣጠል የሚጠቀሙበት ኀይሎች እንደ ሚያመዝኑ የሚገልጹ ወገኖች አሉ::


በርግጥ የጥላቻውና የግጭቱ ዋነኛ መንሥኤ፡- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ የተመጣጠነ የሀብት ድልድል አለመኖር፣ የሰብአዊ መብት ጥሰትና የመልካም አስተዳደር እጦት የሚያስከትለው የሕዝቦች አለመተማመን፣ ስደት፣ ድኽነትና ችጋር፥ ይህም በፈንታው የሚወልደው ቀቢጸ ተስፋ፣ ክፋትና ጭካኔ መሆኑ በብዙ የዓለማችን ክፍሎች በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው:: እነዚህ ችግሮች ሐቀኛ መፍትሔ የሚያገኙት ግን በጥላቻና ግጭት ሳይሆን የሰዎችን መሠረታዊ ፍላጎት፣ የዕድገትና የልማት ጥማት በሚዛናዊ ፍትሕ፣ በአስተሳሰብ ነጻነት፣ በእርስ በርስ መቻቻልና መከባበር ለማሟላት፣ አለመግባባትን በንግግርና በድርድር ለመፍታት የሚያስችል የሰላምን ባህል ለማጎልበት በአጠቃላይ ግላዊና ማኅበራዊ ደኅንነትን፣ ጸጥታንና መረጋጋትን ለመጠበቅ ጥረት በማድረግ እንደ ሆነ ይታመናል::

ዴዝሞን ቱቱን ጨምሮ ከአምስት የሰላም ኖቤል ተሸላሚዎች ጋር በአሜሪካ ኮሎራዶ ዩኒቨርስቲ በተካሄደውና በቢቢሲ ቴሌቪዥን እየተላለፈ በሚገኘው ክርክር፡ - ኀያላኑ «ለፀረ ሽብር ዘመቻው» በየጊዜው የሚያወጡት ወጪ፣ ሌሎች መንግሥታትም ለጦር መሣሪያ ግዢ የሚመድቡት በጀት ከላይ ከተጠቀሱት በጎ ዓላማዎች ለአንዱ ቢውል በሕዝቦች መካከል ጥላቻና ተስፋ መቁረጥ ተወግዶ መቀራረብና ቤተ ሰባዊነት እንደ ሚጠናከር ተመልክቷል:: እየሆነ ያለው ግን ተቃራኒው ነው:: ይህም ሆኖ ስለ ተስፋ፣ ፍቅር፣ ነጻነትና ዴሞክራሲ ጥፉነት፥ ስለ ሽብርና ጥላቻ መጥፎነት በየጊዜው የሚነገሩን እኒሁ ኀይሎች ናቸው:: የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ 3000 ያህል ሰዎች ያለቁበት የመስከረም አንድ ቀን 1994 ዓ.ም አረመኔያዊ ጥቃት የተፈጸመበት አምስተኛ ዓመት ታስቦ በዋለበት ዕለት ለኤን.ቢ.ሲ ቴሌቪዥን የሚከተለውን ዓይነት መግለጫ ነበር የሰጡት፤ «*ዓለም ሰላምን በሚደግፉ ለዘብተኞች እና የለውጥ አራማጆች፥ ሽብርተኝነትን በሚደግፉ አክራሪዎች እና ጽንፈኞች መካከል በሚደረግ የጥላቻ ርእዮተ ዓለም ትግል ላይ ትገኛለች:: ይህን የጥላቻ ርእይ በፍቅርና በተስፋ ሰጪ ርእይ መተካት ዓለምን ከሽብር የመጠበቅ ብቸኛ መንገድ ነው::*»

«የአሜሪካ መንግሥት የመካከለኛው ምሥራቅ ጣልቃ ገብነት አግባብ አይደለም» በሚል ምክንያት መስከረም አንድ ቀን 1994 ዓ.ም በአሜሪካ ላይ አስከፊ ጥቃት ከደረሰ በኋላ አሜሪካና «*የፀረ ሽብር ዘመቻው*» አጋሮቿ የሚከተሉት የብሔራዊ ደኅንነት ስትራቴጂ እና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ «*በሃይማኖት እና በጎሳ ላይ ለተመሠረተው ጥላቻ*» መጠናከር የላቀ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይነገራል:: ምዕራባውያኑ «*መካከለኛው ምሥራቅን ለአምባገነን አገዛዞች እና ለአሸባሪዎች መናኸሪያነት አሳልፈን ሳንሰጥ ነጻነትን፣ ዴሞክራሲንና ሥልጣኔን እናሰፍናለን፤ አዲሲቷን መካከለኛው ምሥራቅ እንመሠርታለን፤ ይህም በኢራቅ በሚካሄደው የፀረ ሽብር ዘመቻ ውጤታማነት ይለካል*» በማለት በተደጋጋሚ ይናገራሉ:: ይህ አካሄድ ዘላቂ ሰላምን እና ደኅንነትን ከማምጣት አኳያ የራሱ 'ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች እንዳሉት ቢገለጽም በተቃራኒው ወገን የተወሰደው ግን «የምዕራቡ ባህልና ሥልጣኔ በእስላሙ ዓለም የበላይነትን እንዲቀዳጅ የሚያደርግ የተስፋፊነት ዘመቻ» ተደርጎ ነው:: ስለዚህም እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ሰባት ቀን 2001 በአፍጋኒስታን ታሊባን ላይ ተጀምሮ ወደ ኢራቅ የተስፋፋውና አምስት ዓመታትን ያሳለፈው «*የፀረ ሽብር ጦርነት*» የታሰበለትን ብሩህ ተስፋ ከማምጣት ይልቅ ከቀድሞ የባሰ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል:: በኢራቅ ሰዎችን በብዛት በመግደል፣ ንብረትንና የልማት መዋቅሮችን በማውደም በየዕለቱ በመጠኑ እየሰፋና በጉዳቱ እየከፋ የቀጠለው ግጭት አገሪቱን ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዳያስገባት ተሰግቷል:: ከዚህም በላይ ሁኔታው በዓለም ዙሪያ የ«*አዳዲስ አክራሪዎችን*» መነሣሣት እያበረታታ መሆኑን ዘኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ የአሜሪካ የመረጃ ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል:: በደቡብ ሊባኖስ /የሒዝቦላህ ሕዝባዊ ድጋፍ መጠናከር/፣ በፍልስጥኤም /የሐማስ ሚሊሻዎችና የፋታሕ የጸጥታ ኀይሎች ግጭት/ እና በአፍጋኒስታን /የታሊባን ዐማፅያን ማየል/ ከኢራቅ የተለየ መጨረሻ ሊኖረው እንደ ማይችል ተፈርቷል:: ሌላው ቀርቶ «ሽብርተኝነትን» በቀዳሚነት እንዋጋለን በሚሉት አገሮች /አሜሪካና ምዕራብ አውሮፓ/ የሚስተዋለው ፀረ ሴማዊና ፀረ እስልምና ስሜቶች በአንድ በኩል፥ በትውልድ የሌላ አገር ሆነው በዜግነት የዚያው አገር የሆኑ ወጣቶች የአክራሪነት ዝንባሌ /*Radicalism*/ መብዛት በሌላ በኩል የቀውሱን ውስብስብነት በጉልህ የሚያሳይ ነው:: በዚህ ረገድ የእምነት ተቋማት እና ትምህርት ቤቶቻቸው አሉታዊ ሚና መጫወታቸው ተያይዞ ይወሳል:: ባላንጣ ወገኖችን ለማደራደርና በግጭት አካባቢዎች የሰላም ማስከበር ተልእኮን ለመወጣት የተንሣሽነቱ በጎነት ያይደለ የእምነትና የጎሳ ተመሳሳይነት መለኪያ የሆነበትም መሥፈርት አጋጥሟል:: በሶማልያ፣ በምዕራብ ሱዳን /ዳርፉር/ እና በደቡብ ሊባኖስ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የገጠመውን ፈተና እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል::

በቋፍ ያለውን የዓለም ሰላም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚያደፈርሰው የስድስት ዐሥርት ዓመታት የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብና ምዕራባውያኑ «*ሽብርተኝነት*» ለሚሉት ችግር ጠንቁ፡ -የእስራኤላውያንና የፍልስጥኤማውያን መጨረሻው የማይታይ፣ ክፋትና ጭካኔ የተሞላበት ግብግብ ሳይሆን እንደ ማይቀር ይገለጻል:: ይኸውም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ደኅንነት ስትራቴጂ መሠረት የወቅቱ አስጊ አገር የተባለችውን ኢራንን ጨምሮ «*ለፍል ስጥኤማውያን ነጻነት ፍትሕ ፈላጊ ነን*» የሚሉ ኀይሎች «*ጽዮናውያን [አይሁድ] መንግሥታቸውን ያቋቋሙት ፍልስጥኤማውያንን ከቤታቸው አፈናቅለው ነው*» በማለት ሲከሱ በአሜሪካ የሚመራው ምዕራቡ ዓለም ደግሞ ለእስራኤል ህልውና እና ሉዓላዊነት ተሟጋች ሆኖ የቆመ በመሆኑ ነው:: ለቀረው የዓለም ሕዝብ በሁለቱም ወገን የሚሰጠው ምርጫ፡ - «*የእኔ ወገን ካልሆንህ የጠላት ወገን ነህ*» /*you are with us or you are against us*/ የሚል ነው:: በዚህም «የጥላቻውና የፀረ ሽብር ጦርነቱ» ዒላማ ያልተወሰነና ዓለሙን በሙሉ ሊያጠቃልል የሚችል መሆኑን እንረዳለን::

ፍልስጥኤም /ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም/ ለአይሁድ፣ ለክርስትና እና ለእስልምና እምነት መገኛና መናኸሪያ የሆነችውን ያህል አገራችን ኢትዮጵያም ከዚያች መሬት ታሪክ ተካፋይ ናት:: እምነቶቹ በኢትዮጵያ እና በሌሎች አገሮች መካከል እንደ ድልድይ ሆነው በማገልገላቸው ሰዎች፣ ሐሳቦችና ባህሎች የሚዛመዱባቸው ናቸው:: የታሪክ ምሁሩ አቶ አበባው አያሌው ለዚህ እትማችን ባቀረቡልን ጽሑፍ እንደሚያብራሩት፥ በእምነቶች መካከል ባለው መከባበርና መቻቻል ኢትዮጵያችን ለዓለም ሁሉ በአብነት የምትጠቀስ አገር ናት:: የ«ሽብር» መንሥኤ ምንም ይሁን ምን በውጤቱ እንደ ሚለካ የሚሟገቱት አቶ አበባው «ሽብርን የሚያንቀለቅስ ሃይማኖት የለም» በማለት ይከራከራሉ:: እያይዘውም *በውጭ ተጽዕኖ /በመካከለኛው ምሥራቅም ይሁን በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ወቅታዊ ሁኔታዎች/ እና በውስጣዊ ችግር ተገፋፍቶ ይህ በልዩነት የመከባበር እና የመቻቻል መንፈስ እንዳይመረዝ፣ አገራችንንም ለአደጋ እንዳያጋልጥ ሁለንተናዊ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ይመክራሉ::* የእምነት ተቋማቱም ባላቸው የመንፈስ ልዕልና ግጭቶችን የመከላከልና ሲከሠቱም በማደራደርና በማሸማገል የመፍታት ታሪካዊ ሚናቸውን እንዲወጡ ያሳስባሉ:: መልካም ንባብ::




*ቅድስት አገር /ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም/*



*የጦርነት ጦሱ- በእስራኤል የአየር ድብደባ ከተገደሉት 37 የቃና መንደር /ደቡብ ሊባኖስ/ ሕፃናት አንዷ /ሐምሌ 23 ቀን 1998 ዓ.ም./*

# 'ሽብር' ሃይማኖት የለውም

አበባው አያሌው
/በአ.አ.ዩ የታሪክ መምህር/

ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት በተለይም ከመስከረም አንድ ቀን 1994 ዓ.ም ወዲህ ሽብርተኝነት /Terrorism/ የሚለው ቃል በዓለማችን የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ ግለሰቦችንና ኅብረተሰቦችን /ማኅበረሰቦችን/ የሚያስደነግጥና የሚያስበረግግ ቃል ሆኗል:: በዓለማችን የተለያዩ የዜና አውታሮችም ዘወትር የሚደመጥና የሚተኮርበት ጭብጥ ሆኗል:: በአሁኑ ሰዓት ሽብርተኝነት እጅግ በርካታ ገጽታዎችን ይዟል:: ለማመልከት ያህልም፡ -«*ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነት*» /Religious terrorism/፣ ፖለቲካዊ ሽብርተኝነት /Political terrorism/፣ ብሔረተኛ ሽብርተኝነት /Nationalist terrorism/፣ ዘረኛ ሽብርተኝነት /Racist terrorism/፣ መንግሥት መራሽ ሽብርተኝነት /State sponsored terrorism/፣ ሥነ ምኅዳራዊ ሽብርተኝነት /Eco- terrorism/ ወዘተ... ጥቂቶቹ ናቸው::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በድርጊት ደረጃ ከተመለከት ነው ደግሞ ሽብርተኝነት በአንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብና ማኅበረሰብ ከሚሰነዘሩ ጥቃቶች ጀምሮ የተደራጁ ቡድኖች እስከ ሚያካሂዱት የጅምላ ጥፋት ያለውን በርካታ የጥፋት ተልእኮ ያካትታል:: የዚህ አጭር ጽሑፍ ዋና ዓላማ ሽብርተኝነትን በጥቅሉ መተንተን ሳይሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያንና የአፍሪቃ ቀንድን ጨምሮ መላውን ዓለም እያስጨነቀ የመጣው «ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነት» /Religious terrorism/ ከምላ ጉደል ለመዳሰስ ነው:: Steven Anzovin (ed), Terrorism (New York: HW Wilson Pub.) 1996.

«ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነት» /Religious terrorism/ የትኛውንም ዓይነት ሃይማኖት ሽፋን አድርጐ ለሃይማኖቱ ህልውና፣ መስፋፋት ወይም ትክክለኛ ገጽታ መጠበቅ የተቆረቆሩ በማስመሰል ግለሰቦችና የተደራጁ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች የሚያካሂዱት እኩይ የወንጀል ተግባር ነው:: «ሃይማኖታዊ ሽብርተኝ» ልባሱ ሃይማኖት ይሁን እንጂ የአራማጆቹ ዋነኛ ዓላማ አብዛኛውን ጊዜ ፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ገጽታው ያመዝናል:: ይህም በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነትን ከፖለቲካዊ ሽብርተኝነት ነጥሎ ማየት አስቸጋሪ ይሆናል:: Bernard Schechterman and Martin Slann (eds.) Violence and Terrorism (Dashkin: MC Graw Hill) 1998. በዘመናችን «ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነት» በከፍተኛ ደረጃ ጐልቶ የሚታየው በክርስትና፣ በእስልምና እና በአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ በሆኑ የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ነው:: ባለንበት ዘመን ከፍተኛ የሽብር እንቅስቃሴ ከሚያካሂዱ ክርስቲያን ነን ባይ ቡድኖች የሚከተሉት ዓይነተኞቹ ናቸው::

1ኛ. *ኩ ክለክስ ክላን /Ku Klux Klan/:-* ይህ K.K.K በሚለው የእንግሊዝኛ ምኅጻረ ቃል የሚታወቀው «ክርስቲያን» አሸባሪ ቡድን ከ1858 ጀምሮ በሰሜን አሜሪካ ፀረ ካቶሊካዊ፣ ፀረ ጥቁርና ፀረ ሴማዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያካሂድ ቡድን ነው:: ቡድኑ ጥቁሮችን በማሠቃየት መግደል፣ ንብረታቸውን ማቃጠል ወይም በተለያየ መንገድ ማውደም፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ማቃጠል በተለይም ቅዱስ መስቀልን ማቃጠል እንደ ዋነኛ ተግባሩ ቆጥሮ ለበርካታ ሰዎች ሕይወት መጥፋትና ለአያሌ ንብረት መውደም ምክንያት ሆኗል:: በ1870ዎች መጀመሪያ የዩ. ኤስ. አሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ኡሊስስ ግራንት /Ulysses Grant/ በወሰዱት ጠንካራ ርምጃ ቡድኑ እስከ መጥፋት ደረጃ ተቃርቦ ነበር:: ነገር ግን በ1907 ዓ.ም ቡድኑ በአዲስ መልኩ ተደራጅቶ በማንሰራራት እኩይ ተልእኮውን ማስፋፋት ቀጠለ:: በ1950 ዎቹና 60ዎቹ የአሜሪካን ጥቁሮች የሚያካሂዱትን የነጻነት፣ የእኩልነትና የመብት ጥያቄ /Civil Rights Movement/ በመቃወም በጥቁር ክርስቲያኖች ላይ እጅግ በርካታ ጭካኔ የተ ሞላባቸውን ግፎች ፈጽሟል:: አንዳንድ መረጃዎች እንደ ሚያመለክቱትም በወቅቱ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የነበሩ ነጭ አሜሪካውያንም የቡድኑ ደጋፊና አልፎ ተርፎም አባልነበሩ:: ምንም እንኳ ያንያህል የጐላ እንቅስቃሴ ባያደርግም *ኩ ክለክስ ክላን* አሁንም በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ ቡድኖች አሉት:: ሃይማኖትን በተለይም የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን እንደ ሽፋን ይጠቀም እንጂ የኩ ክለክስ ክላን ዋና ዓላማና ግብ የነጭ የበላይነትን በአሜሪካ ማስፈንና የጥቁሮችን ማኅበራዊና .ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ ነው:: Tindal and David Shi America; (New York; Mc(Graw Hill) 1995.

2ኛ. «የጌታ ተዋጊ /ተከላካይ/ ጦር» /Lord's Resistance Army/:- ይህ በኡጋንዳ በ1979/80 የተቋቋመ የዐማፅያን ቡድን ነው:: ቡድኑን ያቋቋመው ዮሴፍ ኮኒ /Joseph Kony/ «በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሚገናኝ» ለተከታዮቹ ይሰብካል::

ዓላማውም:- «በዐሥርቱ ትእዛዛት እና በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የፕሮቴስታንት ክርስቲያን መንግሥት በኡጋንዳ መመሥረት» ነው:: ይህን ፕሮፖጋንዳ ዮሴፍ ኮኒ እና ተከታዮቹ በስፋት ቢነዙም ተግባራቸው ግን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝና ከእግዚአብሔር ፈቃድ እጅግ ተቃራኒ ነው:: «የሎርድስ ሬዚስታንስ አርሚ» /L.R.A/ እጅ፣ እግርና ጠ-ት መቁረጥ፣ ሕፃናትንና ሴቶችን አስገድዶ መድፈርና የተለያዩ ዓይነት የወሲብ ጥቃቶች መፈጸም፣ የሴቶችን ከንፈር መቁረጥ፣ ቤትና ንብረት ማቃጠል፣ ሕፃናትን ለውትድርና መመልመል፣ ግለሰቦችን ማሠቃየትና መግደል እና ሌሎችንም በርካታ እኩይ ተግባሮች በስፋት ያከናውናል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ሰሜን ኡጋንዳዊያን የዚህ ቡድን ሰይጣናዊ ተልእኮ ሰለባ ኾነዋል:: አብዛኛዎቹም ከላይ የተጠቀሱትን አሠቃቂ ጥቃቶች በመፍራት ከቀዬአቸው ተፈናቅለው የስደት ኑሮ ይገፋሉ:: የኤል. አር.ኤ እውነተኛ ተልእኮ በ1979 እ.አ.አ የኡጋንዳ ፕሬዝዳንት የነበሩት ቲቶ አኬሊ ከሥልጣናቸው በኃይል ከወረዱ በኋላ በሰሜን ኡጋንዳ ያሉትን የአኮሊ /Acholi/ ብሔረሰቦችን የቀድሞ የበላይነት ማስጠበቅ ወይም ከሌሎች የኡጋንዳ ብሔረሰቦች ጥቃት መከላከል ነው:: ለዐማፂ ቡድኑ መመሥረትም ዋነኛው ምክንያት ፕሬዝዳንት ቲቶ አኬሎ በብሔር አኮሊ መሆናቸውና ከሥልጣን መውረዳቸውም የአኮሊ ብሔረሰብን የበላይነትና ጥቅም ማስቀረቱ ነው እንጂ የዮሴፍ ኮኒ «በመንፈስ ተመርቶ ከእግዚአብሔር መገናኘት» አይደለም:: Ber nard and Martin, Violence and Terrorism. እንደ ዮሴፍ ኮኒ ያሉት እኩያን የመንፈስ ግንኙነታቸው ከግብር አለቃቸው ከዲያብሎስ እንጂ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም::

**«ሃይማኖታዊ ሽብርተኝነት» /Religious terrorism/ የትኛውንም ዓይነት ሃይማኖት ሽፋን አድርጐ ለሃይማኖቱ ህልውና፣ መስፋፋት ወይም ትክክለኛ ገጽታ መጠበቅ የተቀረቆሩ በማስመሰል ግለሰቦችና የተደራጁ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች የሚያካሂዱት እኩይ የወንጀል ተግባር ነው:: ሽሃይማኖታዊ ሽብርተኝነትሽ ልባሱ ሃይማኖት ይሁን እንጂ የአራማጆቹ ዋነኛ ዓላማ አብዛኛውን ጊዜ ፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ገጽታው ያመዝናል::**

3ኛ. «የእግዚአብሔር ሠራዊት» /Army of God/:- እኒህ የተለያዩ ዓላማዎች ያሏቸው «ጽንፈኛ ክርስቲያኖች» ራሳቸውን የሚጠሩበት ስም ነው:: የአንዳንዶቹ ዓላማ የክርስትናን የበላይነት ማረጋገጥ ሲሆን ራሳቸውን በመካከለኛው ዘመን ከነበሩ የመስቀል ጦረኞች /Crusaders/ ጋር ያመሳስላሉ:: ሌሎች ደግሞ እንደ ፅንስ ማስወረድ፣ ግብረ ሰዶም እና በዘመናችን እየተስፋፋ የመጣውን ልቅ የወሲብ ግንኙነት /Poronography/ በመቃወም የተለያዩ ዘመቻዎችን ያካሂዳሉ:: ሁሉም ግን ሽብርንና ጥቃትን /Violence and Terror/ እንደ ዋነኛ የዓላማቸው ማሳኪያ መንገድ ይወስዳሉ::

ለምሳሌ ያህል ፅንስ የሚያስወርዱ ዶክተሮችን ይገድላሉ፣ ንብረታቸውን ያቃጥላሉ፣ ፅንስ የሚያስወርዱ የጤና ተቋማትንና ሠራተኞቻቸውን ያወድማሉ፣ ያቃ ጥላሉ፣ ያሠቃያሉ፣ ግብረ ሰዶማውያንንና የልቅ ወሲብ ተዋናዮችን ይገድላሉ፣ የምሽት ክበቦችንና የልቅ ወሲብ መጽሔትና ፊልም መሸጫ መደብሮችን ያቃ ጥላሉ÷ ያወድማሉ:: (Ibid).

4ኛ.«የክርስቲያን መለዮ» /Chris tian Identity/ :-

ይህ ቡድን የተለያዩ በመጠነኛና ከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ «ጽንፈኛና ዘረኛ «ክርስቲያኖችን» ያካተተ ነው:: በአሁኑ ወቅት ከ50,000 በላይ ተከታዮች እንዳሉት ሲታመን አበዛኞቹ የቡድኑ አባላት በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ይገኛሉ:: የቡድኑ አባላት ራሳቸውን ከዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች የዐሥራ አንዱ /የይሁዳን ነገድ ሳይጨምር ማለት ነው/ ቀጥተኛ ተወላጅ አድርገው ይቆጥራሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከነገደ ይሁዳ መወለዱን አያምኑም:: ነገደ ይሁዳንም ከነገደ እስራኤል እንደ አንዱ አይቆጥሩም:: በመሆኑም ይሁዲዎችንና ከዐሥራ አንዱ ነገደ እስራኤል ውጭ የሆኑትን ክርስቲያኖች በሙሉ በጥላቻ ዐይን ይመለከታሉ:: የዚህ ቡድን አባላት ከፈጸሟቸው የሽብር ተልእኮዎች መካከል እ.ኤ.አ በ1996 እና በ1997 በምሽት ክበቦችና በኦሎምፒክ ፓርክ የተደረጉት የቦምብ ፍንዳታዎችና ያስከተሏቸው በርካታ የሞትና የመቁሰል አደጋዎች የሚጠቀሱ ናቸው:: (Ibid).

5ኛ. የናጋላንድ ዐማፂዎች ቡድን /Nagaland Rebels/:-

ናጋላንድ በሰሜን ምሥራቅ ሕንድ የምትገኝ አነስተኛ ግዛት ነች:: የናጋላንድ ዐማፂዎች ቡድን በ1940



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዓ.ም የተቋቋመ የጽንፈኛ «ክርስቲያኖች» ቡድን ነው:: ዋነኛ ዓላማውም የአብዛኛው ሕዝብ እምነት ሒንዱ ከሆነው ሕንድ በመገንጠል ነጻ የሆነ ክርስቲያናዊ መንግሥት ማቋቋም ነው:: ይህን ዓላማ ለማሳካት የበርካቶችን ሕይወት የቀጠፉና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ያወደሙ የቦንብ ፍንዳታዎችን አካሂዷል:: ልክ እንደ ሌሎች መሰል ቡድኖች ይህም ቡድን የፖለቲካ ዓላማውን በሃይማኖት ሽፋን እያራመደ ይገኛል:: (The New York Times, June 14,1997).

በክርስትና እምነት ስም ድብቅ ዓላማቸውን ለማስፈጸም ከሚንቀሳቀሱ በት የሽብር ቡድኖች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል አምስቱን ዘረዘርን እንጅ የተለያዩ ጽንፈኛና ጠባብ አመለካከት ያላቸው «ክርስቲያን» ነን ባይ ግለሰቦችና ቡድኖች በንጹሐን ክርስቲያኖችና ሌሎችም ወገኖች ሕይወትና ንብረት ላይ በተለያየ መልኩ ሽብርና ጥቃት ሲሰነዝሩ ቆይተዋል:: በአየር ላንድ የፕሮቴስታንት እና የካቶሊክ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች መካከል የተደረገው የእርስ በርስ መጨፋጨፍ ከሁላችንም ኅሊና የማይጠፋ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: (The Miami Herald, April 26,2001).

የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖችም በተለያዩ ምክንያቶች የእስልምና ሃይማኖትን መሣሪያ በማድረግ የሽብር ተግባር ሲፈጽሙ ነበር፤ አሁንም እየፈጸሙ ነው:: በወግ አጥባቂ እና ጽንፈኛ የእስልምና ተከታዮች የሚካሄደው ሽብር ፈጠራና ጥቃት በአሁኑ ወቅት እጅግ ጐላ ብሎ ይታያል:: ነገር ግን ልክ እንደ አብዛኛዎቹ የክርስቲያን አሸባሪ ቡድኖች የእስልምና አሸባሪ ቡድኖችም በሃይማኖት ሽፋን ዋናው ተልእኮአቸው የተቋቋሙ ለትን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓላማ በሃይማኖት መሣሪያነት ከግብ ማድረስ ነው:: የእስልምና አሸባሪ ቡድኖች በቁጥር እጅግ በርካታ ቢ ሆኑም የሚከተሉት ግን ዋነኛ ከሚባሉት ውስጥ ይጠቀሳሉ::

1ኛ. ***የአቡ ሣይፍ ቡድን፡-*** ይህ ቡድን በደቡብ ፊሊፒንስ እስላማዊ መንግሥትን ለማቋቋም ይንቀሳቀሳል:: ዓላማውን ለማሳካት በርካታ የሽብር ተግባራትን በፊሊፒንስ የተለያዩ ክፍሎች አካሂዷል:: (The New York Times August ,2003.)

2ኛ. ***አል ጋምአት አል እስላሚያ፡-*** ይህ ቡድን የግብጽን መንግሥት በኃይል አስወግዶ ወግ አጥባቂና እስላማዊ መንግሥት በግብጽ ለማቋቋም እንዲሁም በዐረብ አገሮች ምዕራባውያን ያላቸውን ተጽዕኖ ለመግታት ይታገላል:: ቡድኑ ምዕራባውያን ቱሪስቶችን ዒላማ ያደረጉ በርካታ የቦንብ ፍንዳታዎችን አካሂዷል:: አልተሳካለትም እንጂ የግብጹን መራሔ መንግሥት ለመግደል ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አድርጓል:: ከዚህ ቡድን ጋር በዓላማና በተግባር ተመሳሳይነት ያላቸው አል ጅሃድ እና የግብጽ የእስልምና ጅሃድ የሚባሉ ቡድኖች አሉ:: (Ibid).

3ኛ. ***የጄምዔላ እስላማዊ ግንባር፡-*** ይህ ቡድን ወይም ድርጅት በኢንዶኔዥያ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: የግንባሩ ዋና ዓላማ እስላማዊ የሸሪዓ ሕጐችን የኢንዶኔዥያ መንግሥት በሕጉ እንዲያካ ትታቸውና እንዲተገብራቸው ማድረግ ነው:: ይህን ዓላማ ለማሳካትም በመንግ ሥታዊ ድርጅቶችና በንጹሐን ግለሰቦች ላይ በርካታ የሽብር ጥቃቶችን ፈጽሟል:: (Ibid).

4ኛ. ***ሐማስ፡-*** ሐማስ ባሳለፍነው ዓመት በፍልስጥኤም በተካሄደ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የፋታሕ ንቅናቄን አሸንፎ መንግሥታዊ ሥልጣን የያዘ ፓርቲ ነው:: ይሁንና ምዕራባውያኑ የሚያቀነቅኑት ዴሞክራሲ ያመጣውን «*የማይፈለግ ውጤት*» በጸጋ አልተቀበሉትም:: በተለይም ደግሞ ሐማስ የእስራኤልን አገራዊና መንግሥታዊ ህልውና /ሉዐላዊነት/ ዕውቅና እንደ ማይሰጥ ይፋዊ አቅዋም ከመያዙ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ይፈጽማቸው የነበሩት የአጥፍቶ መጥፋት ርምጃዎች ከአሸባሪ ቡድኖች እንዲፈረጅ አድርጎታል:: በየዕለቱ የዜና ዕወጃዎችና ትንታኔዎች እንደ ሚገለጠው ሐማስ ማእከሉንና እንቅስቃሴውን በጋዛ ያደረገ ሽብርተኛ ቡድን ነው:: ዋና ዓላማው የእስራኤልን መንግሥት ማጥፋትና በምትኩ እስላማዊ የፍልስጥኤም መንግሥት በፍልስጥኤምና በእስራኤል መሬት ላይ መመሥረት ነው:: ሐማስ «እስራኤል ለምትወስዳቸው የኀይል እርምጃዎች አፀፋ ነው» በሚል የሚያካሂዳቸው የአጥፍቶ መጥፋት የቦንብ ፍንዳታዎች ለበርካታ ሲቪል እስራኤላውያን ሕይወት መቀጠፍ ምክንያት ሆኗል:: (Ibid)

5ኛ. ***ሒዝቦላህ፡-*** ሒዝቦላህ የእስራኤልን መንግሥት መደምሰስ ወይም መጥፋት በሚፈልጉ ጽንፈኛ የሺአት እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የተመሠረተ ሽብርተኛ ቡድን ነው:: አባላቱ ኢራንን ጨምሮ ከተለያዩ አገራት የተውጣጡና በደቡብ ሊባኖስ፣ በጋዛ፣ በዌስት ባንክ፣ በዮርዳኖስ እና በሶርያ ሰፊ ፀረ እስራኤል እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ ናቸው:: ራሱን «***የዐረብ ወታደራዊ ኃይል እና የእስልምና ተከላካይ***» ብሎ የሚጠራው ሒዝቦላህ በሚያካሂዳቸው የሽብር ተግባራትና ጥቃቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በርካታ ንጹሐን እስራኤላውያን፣ ፍልስጥኤማውያንና፣ ሊባኖሳውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ከቤት ንብረታቸውም ተፈናቅለዋል:: www.en/wikipedia. encyclopedia Wikipedia.

6ኛ. ***የታጠቀው እስላማዊ ቡድን*** /Armed Islamic Group/፡-ይህ ቡድን የአልጄሪያን መንግሥት በኃይል የመጣልና በእስላማዊ መንግሥት የመተካት ዓላማ ያነገበ ነው:: ይህን ተግባሩን ለማሳካት የበርካታ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈ የሽብር ተግባር አካሂዷል:: እጅግ አሠቃቂው ደግሞ ለዓላማው አንሰለፍም ያሉን ጹሐን ሙስሊሞችን ያለ ቅንጣት ማመንታት በሰይፍ እየቀላ መጣሉ ነበር:: (Ibid).

7ኛ. ***የዔደን እስላማዊ ጦር*** /Islamic Army of Aden/፡- ይህ ቡድን የየመንን መንግሥት ለማስወገድ፣ አሜሪካን በዐረብ አገሮች የምታደርገውን ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ ይታገላል:: የምዕራባውያንን ወታደራዊ ተቋማት፣ ጋዜጠኞችንና ቱሪስቶችን ዒላማ ያደረገ የሽብር ተግባር በተደጋጋሚ ፈጽሟል:: የመን በመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካ ፀረ ሽብር ጦርነት ዋነኛ አጋር መሆኗ ይታወቃል:: (Ibid).

8ኛ. ***አል ቃዒዳ፡-*** ይህ ድርጅት በ1980ዎቹ መጀመሪያ ሲጠነሰስና ሲቋቋም ዋና ዓላማው ምዕራባውያንን ከሳዑዲ ዐረቢያ ማስወጣት፣ የሳዑዲ ሥርወ መንግሥትን ከሥልጣን ማስወገድና ማጥፋት እንዲሁም እስራኤልንና ደጋፊዎቿን መደምሰስ ነበር:: ነገር ግን ከ1990ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ፀረ አሜሪካ ብሎም ፀረ ምዕራባዊ እንቅስቃሴ ጀመረ:: የሺዎችን ሕይወት የቀጠፉ አሠቃቂ የሽብር ጥቃቶችንም ፈጽሟል:: ከሚያከናውናቸው የሽብር ተግባራት ባሻገር የአል ቃዒዳን ቡድን ለዓለም ጸጥታና ደኅንነት ከፍተኛ ስጋት የሚያደርጉት ሁለት ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ የአል ቃዒዳ መኖርና እኩይ የሽብር ተግባሩ ለበርካታ አክራሪና ጽንፈኛ እስላማዊ ቡድኖች በየቦታው መፈልፈል ምክንያት ሆኗል:: ርግጠ ሊታወቅ ባይችልም ለተለያዩ እስላማዊ ሽብርተኛ ቡድኖች የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ እንደ ሚያደርግም የማይካድ ነው:: ቀጥሎም በተለይ በዐረብ አገሮች የሚገኙ ሙስሊም ወጣቶች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አሜሪካ በአፍጋኒስታን እና በኢራቅ ላይ ለምታ ደርገው ቅጥ ያጣ ወታደራዊ እርምጃ ያላቸውን ጥላቻና ፀረ እስራኤል አቋም በመጠቀም የእስልምና ሃይማኖት ከሚፈቅደው ውጭ ወጣት ሙስሊሞችን ወደ ሽብር ተልእኮ በመገፋፋት ውድመት እና እልቂት እያስከተለ ነው:: (Ibid).

9ኛ. ***አል ኢትሃድ አል እስላሚያ፡-*** አል ኢትሃድ አል እስላሚያ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በሰሜንና ደቡብ ሶማልያ ይንቀሳቀሱ በነበሩት ***«የሶማልያ እስላማዊ ወንድማማቾች»*** /*al - Takfir al-Wahda , al - Salafiyya Muslim brother hood*/ እና ሌሎችም አክራሪ እስላማውያን ቡድኖች ኅብረት /Somali Islamic Union/ አማካይነት እ.አ.አ በ1984 የተመሠረተ ነው:: አል ኢትሃድ አምባገነኑ የዚያድ ባሬን መንግሥት መውደቅ /1991 እ.ኤ.አ/ ተከትሎ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ /ዶሎ፣ ዋርዴር እና ደገኸቡር/ ጀምሮ በተለይም በማእከላዊና ደቡብ ሶማልያ ኃይሉን በተለያዩ መንገዶች እያጠናከረ የተንቀሳቀሰ ጽንፈኛ እስላማዊ ቡድን ነው:: አል ኢትሃድ አል እስላሚያ የ ***«ውሃቢ ነገረ መለኮት»*** /*Wahhabi theology*/ በሚባለው ዘይቤ ፖለቲካዊ ዓላማውን በሶማልያ በቆየው የእስልምና ሃይማኖት /ሙሉ በሙሉ የሱኑ ሙስሊሞች የኾኑት ሶማልያውያን የሚከተሏቸው የቃዲሪያህ፣ አሕማዲያህ እና ሳሊሂያህ የተባሉ ዘርፎች /መርሖዎች/Poletical Islam/ ሸፍኖ የሚንቀሳቀስ አሸባሪ ቡድን ነው:: /Medhane Tadesse, AL- ITTIHAD - POLITICAL ISLAM AND BLACK ECONOMY IN SOMALIA ,2002, pp.20-30; Bryden, p.3; Farole, pp.6-7 and others/.

***አል ኢትሃድ*** የግድያ ሙከራዎችንና በርካታ የቦንብ ፍንዳታዎችን በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ከተሞች ባለፉት ዓመታት መፈጸሙ ይታወሳል::

ከክርስትና እና ከእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በተጨማሪ የአይሁድ እምነት ተከታዮችም በተለያዩ የሽብር ተግባራት ተሠማርተዋል:: አይሁዳውያን የሚያካሂዱት የሽብር ተግባር በሁለት ደረጃ ሊከፈል ይችላል:: አንደኛው የእስራኤል መንግሥት እንደ አይሁዳዊ መንግሥት በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች በፍልስጥኤማውያንና በእስራኤል ጐረቤት አገሮች ሕዝቦች ላይ የሚወስደው ከመጠን ያለፈ ወታደራዊ እርምጃ ሽብር ነው:: እስራኤል በወሰደ ቻቸው ወታደራዊ እርምጃዎች በርካታ ንጹሐን ወገኖች ሞተዋል፤ ንብረት አልባና ቤት አልባ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሆነዋል:: ሁለተኛው:-አይሁዳ ውያን የሚካሂዱት ሽብር ደግሞ ሒዝቦ ላህንና ሐማስን የመሳሰሉ ቡድኖች በእስራኤላ ውያን አይሁዶች ላይ ለሚያካሂዱት የሽብር ጥቃት የተ ቆጡ አይሁዳውያን በምስጢር በመደራጀት የሚያደርጉት የግድያ፣ ቦንብ የማፈንዳትና ፍልስጥኤማውያንን የማጥቃት ተግባር ነው:: www.en/wikipedia.

እንግዲህ ከላይ እንደ ተመለከትነው «ሃይማኖታዊ» ሽብርተኝነት በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን በክርስትና እና በአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችም የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ሃይማኖትን እንደ ሽፋን በመ ጠቀም የሚከናወን ተግባር ነው::

ይሁን እንጂ ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት እስልምናን ሽፋን ያደረጉ ጽንፈኛ እና አክራሪ ቡድኖች በቁጥር በርክተዋል:: እንቅስቃሴያቸውም የዓለ ምን ማኅበረሰብ እያመሰው ይገኛል:: ከላይ እንደ ተጠቀሰው በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድና ለኢትዮጵያ ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን ሕዝብ ከፍተኛ አደጋ የመሆን አቅም ያለው እስላማዊ አሸባሪ ድርጅት አል ኢትሃድ አል እስላሚያ ነው:: ይህ የሚሆነው በሁለት ዐበይት ምክንያቶች ነው:: አንደኛ:- አል ኢትሃድ አል እስላሚያ የአብዛኛውን በጐሳ የተከፋፈለ የሶማልያ ኅብረተሰብ ወደ አንድ ነት ለማምጣትና ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ክርስትና አቋም እየያዘ መምጣቱ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ አል ኢትሃድ ከመሰል ሽብርተኛ ቡድኖች በተለይም ከአል ቃዒዳ ጋር ያለው የጠበቀ ግንኙነት ውሎ አድሮ ኢትዮጵያንም ከምዕራባውያኑ ፀረ ሽብር እንቅስቃሴ ውስጥ በግልጽ ተኀዳኝ ስለሚያደርጋት ከአል ኢትሃድ በተጨማሪ ሌሎች ግዙፍ ሽብርተኛ ቡድኖች ኢትዮጵያን ዒላማ ሊያደርጓት ስለሚችሉ ነው:: ይህ በውጭ ተጽዕኖ የሚደረገው ግፊት ደግሞ የሕዝባችንን ውስጣዊ የሥነ ልቡና አንድነት እንዳይመርዘው ከወዲሁ መጠንቀቅ ያስጠፈልጋል::

አል ኢትሃድ አል እስላሚያ ከዕንስቱ እስከ ልደቱና እስከ አሁን ድረስ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ድርጅት ነው:: ገና ሲመሠረት ጀምሮ ግንባር ቀደም አድርጐ ያስቀመጣቸው አጀንዳዎች ፀረ ኢትዮጵያ እና ፀረ ክርስትና ናቸው:: በቁጥር በርካታ የሆኑ አባላቱና በድርጅቱ ቁልፍ ቦታ ላይ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት ሰዎች ከኢትዮጵያዊ ትውልድና ዜግነት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው መሰጋቱ ደግሞ የአል አትሃድን ችግር የውጭ ብቻ ሳይሆን የውስጥም ችግር ያደርገዋል:: የአል ኢትሃድ ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ ኡጋዴንን፣ የኬንያን ምሥራቃዊ ክፍል እና የጅቡቲን ምሥራቃዊ ክፍል ከሶማልያ ጋር በማዋሐድ ታላቋን የሶማሊያን እስላማዊ ሪፐብሊክ ዕውን ማድረግ፣ በምሥራቅ አፍሪካ ጠንካራ እስላማዊ ማኅበረሰብ መገንባት እና የማይበገር ኃያል እስላማዊ ጦር ማቋቋም» የሚሉ ናቸው:: /Medhane, p.21/.

ሞቃዲሾንና ደቡብ ሶማልያን የተቆጣጠረው የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት በጦር አበጋዞች ይደርስበት የነበረውን አስተዳደራዊ በደል ለመቋቋም በሕዝብ ድጋፍ ጉልበት ያገኘና የተጠናከረ ኃይል ይሁን እንጂ በውስጡ *የርእዮተ ዓለም አንድነት* የለውም:: በኅብረቱ ውስጥ በድርድር የሚያምኑ፣የሶማልያን ብሔራዊ ዕርቅና የአካባቢውን ሰላም የሚሹ ለዘብተኞች ያሉትን ያህል እስልምናን መንግሥታዊ ሃይማኖት አድርጎ *«ታላቋን የሶማልያ እስላማዊ ሪፐብሊክ»* ዕውን የማድረግ ሕልም ያላቸው ቡድኖችም አሉ:: የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት የሚነካው ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት ውስጥ የአመራሩን፣ የርእዮተ ዓለሙን፣ የወታደራዊ ክንፉን ረድፍ በበላይነት የተቆጣጠሩት የአልኢትሃድ አክራሪ ኃይሎች የተሰለፉበት ነው::

እስልምናን እንደ ዋና ሽፋን ቢጠቀምም የአል ኢትሃድ መሠረታዊ ዓላማ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አይደለም:: ለፖለቲካዊ ዓላማው መሳካት ዋነኛ መሰናክል የምትሆነው ደግሞ ኢትዮጵያ ናት:: መላውን የሶማልያ ተናጋሪ ሕዝብ አስተባብሮና አደራጅቶ ከኢትዮጵያ ጋር መዋጋት ለአል ኢትሃድ የማይታሰብ ነገር ነው:: የሶማልሊኛ ጎሳዎችን በአንድነት አደራጅቶ ኢትዮጵያን መዋጋት ቢችል እንኳ ኢትዮጵያን ማቸነፍ አይችልም:: ከዚህ በፊትም በዚያድባሬ መንግሥት በተደጋጋሚ ተሞክሮ የሶማልያን መበታተን አመጣ እንጂ ትርፍ አላስገኘም:: ይህም በመሆኑ አል ኢትሃድ የፖለቲካ ህልሙን ለማሳካትና የኢትዮጵያን ኃይል ለመፈረካከስ ሁለት ዘዴዎችን ቀይሶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: የመጀመሪያው በርካታ የሶማልያ ጐሳዎች በኢትዮጵያ ላይ አላቸው ብሎ የሚያምነውን ጥላቻ መሠረት በማድረግ ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑ የሽብር ተግባራትን በሶማሌ ክልልና በመሀል አገር ማካሄድ ነው:: የአል ኢትሃድ መሪዎች ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ ክርስትና የሆነ አጀንዳ አብዛኛውን የሶማሌ ጐሳ ከዓላማቸው ጀርባ እንደ ሚያሰልፍላቸው ጥርጥር የላቸውም:: ሁለተኛው የአል ኢትሃድ ኢትዮጵያን የማጥቃት ዘዴ ደግሞ ኢትዮጵያን ከምዕራቡ ዓለም /ከአሜሪካ/ ጐን የተሰለፉች ፀረ ሶማልያና ፀረ እስላም ታሪካዊ ጠላት አድርጐ በመፈረጅ የጅሃድ ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ማወጅ ነው:: በእርግጥም ባለፉት ሳምንታት የጅሃድ ጦርነቱ ታውጇል:: የጅሃድ ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ማወጅ ለአል ኢትሃድ ሦስት ጠቀሜታዎችን ሊያስገኝለት ይችላል::

1ኛ. አምሳያው ከሆኑ እስላማዊ ሽብርተኛ ቡድኖች በተለይም ከአል ቃዒዳ መጠነ ሰፊ የቁሳቁስና የገንዘብ ርዳታ ያስገኝለታል:: በሶማልያ የማእከላዊ መንግሥት አለመኖሩ፣ ደቡብና ማእከላዊ ሶማልያን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠሩ ደግሞ ማንኛውንም ርዳታ ያለ ምንም መሰናክል እንዲያገኝ ይረዳዋል፤ እየረዳውም ነው::

2ኛ. የሶማሌ ኅብረተሰብ ሙሉ በሙሉ የእስልምና ተከታይ በመሆኑ የጅ ሃድ ጦርነቱን ጥሪ ያለምንም ጥርጥር ሶማ ልያውያንን ያሰል ፍልኛል፤ በሶማሊያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ሙሉ ተቀባይነትን ያስገኝልኛል፤ ሥልጣኔንም ለማደላደል ይረዳኛል፤ ብሎ ያስባል::

3ኛ. የጅሃድ ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ማወጅ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ የሙስሊም አካላትንና አባላትን በመቀስቀስ ከጐኔ ያሰልፍልኛል ብሎ ያምናል::

ከላይ የተዘረዘሩት ስልቶች እንደ ሚያሳዩት አል ኢትሃድ ሙስሊሙን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ሶማልያውያንን በእስ ልምና ከለላ በማነሣሣት እኩይ ተግባሩን ለመፈጸም ከፍተኛ መፍጨርጨር እያደረገ ነው:: የአል ኢትሃድ ወታደራዊ ክንፍ በኢትዮጵያ መንግሥት ተደጋጋሚ የሽን ፈት ጽዋ ቢጐነጭም ሶማሊያ ውስጥ በማገገም ተመልሶ ብቅ ይላል:: በተለያዩ እስላማዊ ሽብርተኛ ቡድኖች የሚደገፍ በመሆኑም ለማገገምና ለማንሠራራት ጊዜ አይፈጅበትም:: በይበልጥም በርዳታ የሚያገኘውን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመጠቀም የተለያዩ የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፎችን /የጤና፣ የትምህርት፣ የፍትሕ፣ የጸጥታ እና የአስተዳደር አገልግሎትን/ ለኅብረተሰቡ በመስጠት ቀስ በቀስ ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት አግኝቷል:: እኒህን አገልግሎቶች በእስልምና ሽፋን አስታኮ በርካታ ተከታዮችና አባላት በየቦታው አፍርቷል:: በተጨማሪም የተለያዩ ምግባረ ሠናይ እስላማዊ ድርጅቶችን በሽፋንነት በመጠቀም ዓላማውን በማራመድና በኅብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ በመግባት አል ኢትሃድ እጅግ የተካነ ነው:: በመሆኑም ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አል ኢትሃድና መሰል ሽብርተኛ ቡድኖች ለእስልምና እምነት ተቆርቋሪ በመምሰል የሚነዛውን ፕሮፖጋንዳ በጥንቃቄ ሊያስተውለውና ሊመረምረው ይገባል:: የኢትዮጵያን ሙስሊምና ክርስቲያን ኅብረተሰብ የረጅም ዘመናት አብሮና ተቻችሎ የመኖር ታሪክ ስንመለከተው እንደ አል ኢትሃድ ላሉ እኩይ ተልእኮ አራማጅ ቡድኖች መመከቻ የሚሆን ጥሩ ልምድ ነው::

ከታሪክ እንደ ምንረዳው የኢትዮጵያ /የአክሱም/ መንግሥት የመጀመሪያዎቹን ሙስሊሞች በሰላምና በፍቅር ተቀብሎ በፈቃዳቸው ወደ አገራቸው እስከ ተመለሱበት ጊዜ ድረስ ያስተናገደ መንግሥት፣ አገርና ሕዝብ ነው:: በዚህም የተነሣ ነቢዩ መሐመድ በኢትዮጵያ ላይ ምንም ዓይነት የጅሃድ ጦርነት እንዳይካሄድ አዟል:: እውነተኛውን የእስልምና እምነት ከጉዳይ የማይቆጥሩት የአል ኢትሃድ መሪዎችና ተከታዮቻቸው ግን ጅሃድ በኢትዮጵያ ላይ በማወጅ የነቢዩ መሐመድን ትእዛዝ እየተላለፉ ነው:: የእስልምና በአብዛኛው በአፍሪቃ ቀንድ መስፋፋት በሰላማዊ መንገድ የተካሄደ እንጂ በጦርነት ወይም በጅሃድ የተካሄደ አይደለም:: Trimingham : Islam in Ethiopia (Oxford: Clarendon Press) 1972.

በመሆኑም ለረጅም ዘመናት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሐዘንና ደስታን፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን አብረው በመጋራት በሰላምና በፍቅር ኖረዋል::

ምናልባት ብዙውን ጊዜ ባለ ማወቅ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መካከል ሃይማኖትን ለማስፋፋት እንደ ተደረገ ጦርነት ያህል በብዙዎች የሚቆጠረው ከ14ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ እስከ 1536 ዓ.ም በማእከላዊው የክርስቲያን መንግሥትና በኢፋት በኋላም በአዳል እስላማዊ መንግሥት ይካሄዱ የነበሩት ተደጋጋሚ ጦርነቶች ናቸው:: እነዚህ ጦርነቶች በተለይም የኢማም አሕመድ ወረራ ዋና ምክንያታቸው ኢኮኖሚያዊ እንጂ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ይዘት አልነበራቸውም:: በእርግጥ የክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት ለክርስትና፣የኢፋት /የአዳል ሡልጣኖችም ለእስልምና መስፋፋት የበኩላቸውን ድጋፍ ያደርጉ ነበር:: በሁለቱ መንግሥታት መካከል ይደረግ የነበረው ጦርነት መንሥኤ የኢፋት /አዳል ገዥ የሆኑት የወላስማ ሥርወ መንግሥት ሡልጣኖች ለክርስቲያኑ መንግሥት

/ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል/


© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እምነት እና እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች

/አዶላ ዘቦረና/

*ባለፈው እትማችን «እምነትና እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች» በሚል ርእሰ ጉዳይ፦ እምነታችን ምን ዓይነት ነው? እምነት ለምን ተሰጠን? አለማ መንና ችግሮቹ፤ የእምነት ዓይነቶች፣ በዘመነ አበው፣ በዘመነ ነቢያትና በዘመነ ሊቃውንት እምነትን ያቀዘቅዙ በነበሩ ነገሮች ላይ ትኩረት በመስጠት መማራችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ በዘመናችን እምነትን ስለሚያደክሙ ነገሮችና ስለ አስከፊ ውጤታቸው እንዲሁም እምነታችንን ማጠንከር ስለምንችልባቸው መንገዶች እንመለከታለን። መልካም ንባብ።*

*ካለፈው የቀጠለ*

1. ***ለመንፈሳዊ ሕይወት ጊዜና ቦታ አለመስጠት፦*** የብዙዎቻችንን እምነት ከበረዶ ይልቅ ለማቀዝቀዛቸው በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ነገሮች መካከል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የምንሰጠው ጊዜና ትኩረት አለመኖሩ ዋነኛው ነው። ለሥጋዊ ጤንነታችን፣ ምግባችን፣ ልብሳችንና ሰላማችን የምንጨነቀውን ያህል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ብናስብ ኖሮ ዛሬ ለምንገኝበት አሳዛኝ መንፈሳዊ ድቀት ባልበቃን ነበር። በዚህ ምክንያት ምግበ ነፍሳችንን ማግኘት ስላልቻልን በእምነታችን ደክመናል። ፈቃድ ሥጋችን አይሎብናል፤ ከብዶብናል። ለመንፈሳዊ ሕይወት የምናውለውን ጊዜም እንደ ክስረት መቍጠር ሳንጀምር አልቀረንም። ትላንት በመንፈሳዊ ሕይወት ጽሙድ ሆነን ያሳለፍናቸውን ጊዜያትና ቦታዎችን ባስታወስን ቁጥር በዚህ ድርጊታችን ብዙ ነገሮች ያመለጡን እየመሰለን ተቸግረናል። ይህ ሁሉ ድካም ከየት መጣ? ያ ከፍ ያለ እምነታችንስ የት ገባ? በእርግጥ ብዙዎቻችን በእምነት በመቀዝቀዛችን ይህ ሁሉ ተከሥቶብናል። በከፋ ድካም ውስጥ ነን። ነቢዩም፦ «እኛ ደክመናል» /ኤር.2÷4/ ያለው ለዚህ ነው። ሰው ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጊዜና ቦታ የማይሰጥ ካልኾነ ዕድገቱ ከድካም ወደ ዝለት ይኾናል።

2. ***የአገልጋዮች ምግባረ ብልሹነትና መልካም አርአያ አለመሆን፦*** በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚማርኩ፣ ለአገልግሎት የሚተጉ፣ ለመንጋው የሚራሩና ለቤተ ክርስቲያን መልካም ሐሳብ ያላቸው፥ ሰው የማያውቃቸው፥ እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸው በርካታ አገልጋዮች አሉ። እኛ በግልጽ ከምናውቃቸው በላይ እግዚአብሔር ብዙ ትጉሃን አገልጋዮች አሉት። ከዚህ በተቃራኒ ግን ለጥቅም የቆሙ፣ በዋዛና ፈዛዛ ጊዜያቸውን የሚያባክኑና ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ጋር በድብቅ የሚዶልቱ «አገልጋዮች» እንደዚህ ዘመን በዝተው አያውቁም። የተቀበልነው ማዕርገ ክህነትና በሕዝቡ ፊት የምንናገረው ቃለ እግዚአብሔር ከተግባራዊ ሕይወታችን ጋር ሲነጻጸር ድፍረታችንንና አስመሳይነታችንን አጋልጧል። በአገልጋዮች ስንፍና እግዚአብሔር እየተሰደበ ነው። «በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና» እንደ ተባለ። ሮሜ.2÷24። ስንቱን ወገን ለመንፈሳዊ ዝለት፣ ለሽሽት፣ ለኑፋቄና ለክሕደት እንደዳረግነው እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው።

አሁንም አለመጸጸታችንና ራሳችንን አስተካክለን ምእመናን ክርስቶስን ለመታደግ አለመነሣታችን ደግሞ የቀረው ሕዝብ ጥፋት የማያሳዝነን ጨካኝ እረኞች መብዛታችንን ያሳያል። እምነቱ ለቀዘቀዘ ምእመን፣ በመናፍቃንና ከሐድያን ድንኳን ውስጥ ለወደቀ ሕዝብና ለቤተ ክርስቲያን መሪር እንባ ተጠያቂዎቹ በምግባርና በእምነት ደክመን ምሳሌ መሆን ያልቻልን አገልጋዮች ነንና ወዮታ አለብን!!

የተሾምንበትን አደራ ጥለን አባግዐ ክርስቶስ ምእመናንን ጥለን በትንናልና የሾመን አምላክ «የማሰማርያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው!» ብሏል። ኤር.23÷1። ይህ ወዮታ ራሳቸውን አርመው ላላስተካከሉ ሁሉ በፍርድ ቀን ይቆያል።

3. ***መናፍቃንና አሕዛብ፦*** «የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ» ተብሏልና ራሳቸው በሞትና በክሕደት ጨለማ ውስጥ እየተመላለሱ በሕይወት፣ በእምነትና በብርሃን ሰገነት ላይ በቆሙ የእግዚአብሔር ልጆች ላይ አፋቸውን የሚያላቅቁ መናፍቃንና አሕዛብ ሞልተዋል። ገላ.1÷7።

በሰፈር ውስጥ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በጉዞ ላይ፣ በሥራ ቦታ... ወዘተ የኑፋቄና የክሕደት ቃላቸውን እየዘሩ ይዞራሉ። የእምነታቸው ከንቱነት ከእምነታቸው መሠረታዊ አስተምህሮ የተነሣ የሞት መንገድ መሆኑ ታውቋልና ሊከተሏቸው የሚሹ ጥቂቶች ናቸው። እነርሱ ግን በራሳቸው የእምነት ከንቱነት ሊያገኙት ያልቻሉትን ሕዝብ ንጹሕ እምነቱን በመተቸትና የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በማጣመም ሊያናውጡት ይተጋሉ። ብዙ ደክመው ወደ ጥፋት መንደር ያመጡትን ሰው ግን ከነሱ በባሰ የጥፋት ልጅ ያደርጉታል። «አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ።» ተብለዋልና ከፍርድ አያመልጡም። ማቴ.23÷15። ስለ እምነቱ ያላወቀ፣ ከአምላኩ ይልቅ በሰው ማንነት ላይ የተደገፈና ሆዱን የወደደ ሰው የነዚህ ሰዎች ሲሳይ ይሆናል። መናፍቃን እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው የሚያጣምሙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመከተልና የአሕዛብንም ተረት በማዳመጥ እምነታቸው የቀዘቀዘባቸው በርካታ ክርስቲያኖች አሉ። በመሆኑም መናፍቃንና አሕዛብ የክርስቲያኖችን እምነት በማቀዝቀዝ በኩል እየተጫወቱት ያለው ሚና አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። ዝለው የወደቁ መብዛታቸው ለዚህ በቂ ምስክር ነውና።

***4. ፖለቲካዊ ቀውስና አንዳንድ ፖለቲከኞች፦*** ሰዎች የእምነት ነጻነታቸውን ተጠቅመው የወደዱትን ሲከተሉ፥ ዘለፋ፣ ንቀትና መከራ ሲያጸኑባቸው ከቆዩ የሃይማኖት ተጋፊዎች መካከል ፖለቲካዊ ቀውስና አንዳንድ ፖለቲከኞች በዋናነት ይጠቀሳሉ። በተለይ እውነተኛ የሃይማኖት አባቶች ፈር የለቀቀውንና ከእግዚአብሔር ሕግ የሚጣረሰውን የአንዳንድ ፖለቲከኞች ቡረቃ አጥብቀው በመቃወማቸው ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል።

በሚያስተዳድሩት ሕዝብ መካከል መድልዎ ሲፈጽሙ፣ የአንዱን እምነት ተከታይ በሌላው ላይ ሲያነሣሡና ሲያቃቅሩ የኖሩና ያሉም ጥቂቶች አይደሉም። አንዷት ሃይማኖትንም በዘር፣ በጎሳና በመልክአ ምድር ከፋፍለው የሕዝቡን እምነት እያቀዘቀዙ ኖረዋል።

በየዘመኑ በተነሡ ፖለቲካዊ ሒደቶች ውስጥ ቢያልፉም ለሃይማኖታቸው ታማኝ የነበሩ የሃይማኖት አባቶችና ፖለቲከኞችም ጭምር የመኖራቸውን ያህል ከመጣው እኩይ አስተሳሰብና ድርጊት ጋር ሁሉ በመሰለፍ ቤተ ክርስቲያንን ያስለቀሱ፣ ወገኖቻቸውን አንገት ያስደፉና እግዚአብሔርን ያሳዘኑ ሰዎችም ብዙ ናቸው። እያንዳንዱ ቢሮ፣ ትምህርት ቤት፣ ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ መንደር፣ ከተማ፣ ገጠር በፖለቲካዊ ቀውስና በአንዳንድ ፖለቲከኞች አጉል ድርጊት የተነሣ በእምነታቸው በረዶ የሆኑ ሰዎችን በመያዙ ውበቱንና ጸጋውን አጥቷል። በዚህ የተነሣ የቀዘቀዘው እምነታችን ከአገልግሎት፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከወገኖቻችን ርቀን እንድንቆም አድርጎናል። የወደቅንበትን ቦታ ዘወር ብለን ማየት እስኪሳነን ድረስ ማሰብ አቅቶናል። አምላካችንም፦ «የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ።» እያለ ነው። ራእ.2÷4። ሕዝብንና አገርን ለማስተዳደር የራስን ፖለቲካዊ አካሄድ ማስተካከል ይገባል እንጂ የአንዱን እምነት ተከታይ በሌላው ላይ ማነሣሣት ሊጠፉ የማይችል እሳት ከማቀጣጠል ተለይቶ አይታይም። የአንዳንድ ፖለቲከኞችን የሞት ስብከት በማዳመጥ በእምነት ሰበብ ተለያይቶ መቆራቆስም የትላንት ማንነትን መርሳት ብቻ ሳይሆን ለነገም እሾኻማ ጎዳና መደል ደል ነው። በአጠቃላይ ሃይማኖትን ከዘርና ከፖለቲካ አኳያ መመዘን ጥፋት ነው፤ ሥልጣኔም አይደለም፡ በሰውቀትና



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

***ለዝማሬና ለስብከት ተጋብዘን ሳለ ጉባኤ የምንዘጋ፣ ጉባኤ የምናማርጥ፣ ሳንዘጋጅ ወደ ቅዳሴ የምንገባ፣ ማሕሌቱንና መዝሙሩን በይድረስ ይድረስ የምንቆም፣ ሰዐታቱንም በመሰልቸት የምናደርስ ሁሉ በእምነት የቀዘቀዝን ነን:: ቀደም ሲል ግን እንዲህ አልነበርንም:: መርሐ ግብር ለመምራት፣ ምእመናንን ለማስተናገድ፣ በተሰጠን ጸጋ ዕውቀትና አቅም ለማገልገል እንተጋ ነበር:: ለምን ዛሬ ይህን ማድረግ አቃተን?***

በመንፈሳዊነትም መበርታት አይኾንም:: እንደዚህ የሆነው በእምነታችን ስለ ቀዘቀዝን ነው:: ተጽጽተን ካልተመለስን የሚጠብቀን ዕጣ ፈንታ የመረረ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ላይ መነሣሣት - አይደለም ለእኛ ለነዲዮቅ ልጥያኖስ፣ ለነዮዲትና ለመሳሰሉትም አልበጀም::

*5. ጥንቆላና ጠንቋዮች፡-* ሰዎች እግዚአብሔርን በታማኝነት ሲያመልኩ በማየቱ በቅናት የነደደው ሰይጣን ጥንቆላን የሚያህል ክፉ አምልኮ ለሰዎች በማለማመድ ተቆጥረው ለማይዘልቁ ጠንቋዮችና አስጠንቋዮች መቀፍቀፍ ምክንያት ሆኗል:: የልጆቹ ንጹሕ አምልኮ በጠንቋይና በጠንቋዮች መርከሱን የማይወድ ጌታ እግዚአብሔር ግን፡- «ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ» ሲል አዘዘ:: ዘሌ. 19÷31:: ጥንቆላን እንዳይከተል ይህን የሚያህል አምላካዊ ትእዛዝ የተሰጠው የሰው ልጅ ግን ባሳለፈው ዘመን ሁሉ በጥንቆላና በጠንቋዮች ቤት ሲርመጠመጥ ኖሯል::

የሠለጠነ ሕዝብ የጠንቋዮችን ማታለል ይገነዘባል ተብሎ ይታመን ነበር:: ነገር ግን የተጠበቀው እየሆነ አይደለም:: ቀደም ሲል ከነበሩት ጠንቋዮችና አስጠንቋዮች በባሰ መልኩ ማኅበረሰባችን በጥንቆላ ረክሷል:: ከፊሉ በየጠንቋዮች ቤት ሲመላለስ ሌላው ደግሞ በየጋዜጣውና በየመጽሔቱ ላይ በሚወጡ የኮከብ ቆጠራ ጥንቆላዎች ሱስ ተይዟል:: መንገድ ለመሄድ፣ሥራ ለመጀመር፣ ትምህርት ለመቀጠል፣ ትዳር ለመያዝ፣ ...ወዘተ የጥንቆላ ጋዜጣና መጽሔት ማንበብና መከታተል የአንዳንዶቻችን የሠርክ ተግባር ሆኗል:: በዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ማመን የአምላክንም ስጦታ በተስፋ መጠበቅ ቀዝቅዟል:: ይህ ሁሉ የጥንቆላና የጠንቋዮች ውጤት ነው:: እነዚህ ጠንቋዮች ከቤተ ክርስቲያን በአፍአ ያሉ ብቻ አይደሉም:: ጣፋጭ ወተቷን ጠጥተው ያደጉና ዛሬም ከፍትፍቷ እየጎረሱ ካሉት መካከል በጥንቆላ የረከሱ «አገልጋይ ተብዬዎች ሞልተዋል:: በሰይጣናዊ አሠራር ከረከሱ ከነዚህ ጠንቋዮች እግር ሥር የማይጠፉ ትብትብ ጽሑፋቸውን የሚያነብ ሁሉ በእምነቱ የደከመ ነው::

*6. አንዳንድ ጽሑፎች፡-* ሰዎች የተለያየ እምነትና አመለካከት ስላላቸው እኛ በምናምነው እምነትና ክብር በምንሰጣቸው ነገሮች ላይ ትችትና ዘለፋ ሊሰነዝሩ ይችላሉ:: ክርስትና እንደ ዛሬው በመላው ዓለም ከመንሰራፋቱ በፊት ይህ ችግር በሰፊው የተለመደ ነበር:: ክርስቶስን እስከ መስቀል ያደረሱ ጨካኝ አይሁዶችና የባሕርይ አምላክነቱን ይጠራጠሩ የነበሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ብዙ ጽፈዋል፤ ብዙም አስጽፈዋል:: በቅዱሳን ሐዋርያት፣ በቅዱሳን አርድእትና በቅዱሳት አንስት ስም የተለያዩ ወንጌሎችንና መልእክቶችን በመጻፍና በማስጻፍ «ይህ የነ እገሌ ወንጌል፣ መልእክት ወይም ጽሑፍ ነው» እያሉ በሐሰተኛ ጽሑፎች /Pseudohagiographia/ ማታለልም የነዚህ ሰዎች ተንኮል ነበር::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የክፋት መጻሕፍት በአምላካችን፣ በእምነታችን፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳን፣ በመጽሐፍ ቅዱስና በአዋልድ መጻሕፍት ላይ ተጽፈዋል:: የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች /Apologists/ የነበሩ ቅዱሳን ሊቃውንት ግን በየወቅቱ ለተጻፉ የክሕደት፣ የኑፋቄና፣ የዘለፋ ጽሑፎች ተገቢውን ምላሽ ሰጥተዋል::

ዛሬም ይህ ድርጊት በአዲስ መልኩ ተጀምሯል:: በአምላካችን፣ በእምነታችን፣ በቅዱሳንና በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ዘለፋን የተሸከሙ ጽሑፎች በዝተዋል:: እንደዚህ ያሉትን ጽሑፎች የሚጽፉት ሰዎች አሕዛባዊ፣ መናፍቃዊና የከሐድያን አስተሳሰብ ልባቸውን ያስታበያቸው ናቸው:: በሰይጣናዊ ድፍረት የተሞሉ መሆናቸው ለዚህ ዳርጓቸዋል፤ ምክንያቱም የሚዘልፉትና የሚሰድቡት የማያውቁትን ነውና:: የያዕቆብ ወንድም ሐዋርያው ይሁዳ እንደዚህ ሲል ጽፎባቸዋል:- «እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ ጌትነትንም ይጥላሉ፤ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ... የማያውቋትን ይሳደባሉ» ይሁዳ. ቁ.8÷10:: የአንባብያንን ቀልብ መሳብ ያልቻሉ ጋዜጦችና መጽሔቶችም ትላንት ትና ተብለው የተሰለቹትንና በክርስትና ጉዞ ላይ አንዳች ነገር መፍጠር ያል ቻሉትን ጽሑፎች በዘመኑ አቀራረብ በማሣመር «የአዲስ ጽሑፍ ፋና ወጊ» ይባሉ ዘንድ በየዓምዶቻቸው ላይ ሰፊ ቦታ የሚሰጡት ለነዚህ ጽሑፎች ሆኗል:: ብዙ ኮፒዎችን ሸጦ ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ የሚደረግ ሩጫና የክርስትናን መዘለፍ ምክንያት በማድረግ ወደ መንደራቸው የሚኮበልለውን ገልበጥባጣ የቋመጠ ፀረ ክርስትና ኀይሎችም ከዚህ ጀርባ እጃቸው አለ::

የምንሰማውንም ሆነ የምናነበውን አዲስ ነገር እየተከተልን የምንነጉድ ትውልዶች መሆናችን ግን ለዚህ ሰለባነት ዳርጎናል:: «ዘዳቪንቺ ኮድ»ንና መሰል ጽሑፎችንና ዘገባዎችን አንብቦ እምነቱ የዛለበት እና ለመንፈስ ሕመም የተዳረገ አይጠፋም:: በአጠቃላይ ያመነውን እምነት የሚጻረሩ ጽሑፎች ደካማ መንፈስ ያለንን ሰዎች እምነት እያቀዘቀዙ ነው:: አለመታደላችን እንጂ መንፈሳዊ ሰው በሁ ሉም አቅጣጫ /ኃላፊያትን፣ መጻእያትን/ በሚያይና በሚያውቅ አምላኩ በመታገዝ ነገሮችን ይመረምራል እንጂ በመጡት የሐሰት ድርሰቶች መፈተን አልነበረበትም:: «ሁሉን ፈትኑ÷ መልካሙን ያዙ» መባላችንን ለምን ዘነጋነው? 2ተሰ.5÷20-21::

7. *ገንዘብ፡-* ገንዘብ ያለንን ለመሸጥ የሌለንንም ለመግዛት የሚያስችል ነገር ነው:: የዕውቀታችን ሚዛን የሞያችንም ቤዛ በመሆን ያገለግላል:: ገንዘብን የሠራነው እኛው ብንሆንም የብዙዎቻችን ገዢ ሆኖ ባሪያዎቹ አድርጎናል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በገዛ ፈቃዳችን ገንዘብን ጌታ ማድረጋችንን ስለሚያውቅ፡- «ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» ሲል በቃሉ ነግሮናል:: ማቴ.6÷24:: ሰዎች ለገንዘብ ሲሉ ያላደረጉት ነገር የለም፤ ትውልድ የታሪክ ጠባሳን ሸሮ አዲስ ምዕራፍ ሲከፍት ደስ ያሰኛል:: ይሁን እንጂ ስለ ትላንቶቹ ገንዘብ ወዳጆች ከተጻፈው መጥፎ ታሪክ በላይ እኛ ስለ ገንዘብ እየፈጸምን ያለው ጥፋት ከመዛግብቶች ሞልቶ ፈሷል:: ስለ ገንዘብ ዋሸን፣ አመነዘርን፤ ሰረቅን፤ ገደልን፤ ንዋያተ ቅድሳትን አሳልፈን ሰጠን፤ እምነታችንን ተውን:: *በሃይማኖታችን ጸንተናል የምንለውም ስለ ገንዘብ ብለን አገልግሎታችንን አቆምን:: በቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን የተነሣ ያገኘነውን ተቀባይነት በመጠቀም የየዋሆችን ኪስና ጓዳ በዘበዝን:: ለኩዌስት ኔትና የምናደርገው ሩጫም በእምነትና በአገልግሎት በራዶች አድርጎናል፤ ይህ የገንዘብ ፍትወት ምን ያልህ እንደ ተጫነን ያስጠረዳል:: በውሸትም ይሁን በእውነት ምክንያት ያገኘው ገንዘብ ኪሳችንንና የባንክ ደብተራችንን በማደለቡ ኩራታችን ከደመና በላይ ወጥቷል::* በአጭሩ የገንዘብ ፍቅር፣ ስለ ገንዘብ ያለን የተዛባ አመለካከትና ባለን ገንዘብ የመታመናችን ከንቱ ኩራት እምነታችንን አቀዝቅዞታል:: ከዚህም አልፈን ከሃይማኖታችን ፈቀቅ ያልንና የተወጋን ብዙዎች ነን:: በዚህም «ገን ዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ» ከተባለላቸው ወገኖች ተደምረናል:: 1ጢሞ.6÷10::

8. *ሆድ፡-* ዕፀ በለስን ያስቀጠፈ ብኩርናን ያሸጠ ሆድ «ደከመኝ ልረፍ»ን ባለማወቁ ተሸክመው የሚዞሩትን ሰዎች ስስታም፣ ስግብግቦችና የእርሱ ሎሌዎች ካደረጋቸው ቆየ:: በልቶ ማደር ኃጢአት ባይሆንም ለሆድ መገዛት ግን ባርነትና ታላቅ በደል ነው:: ልኳንዳ ቤቶቻችንና ሆቴሎቻችን በአርብዓ ሁዳዴ ሳይቀር የጥሉላት ምግቦችን ማቅረባቸው ሲገርም እጁን ታጥቦ የሚበላው ሰው መብዛት በእውነት ይህ ወገን ወዴት እየሄደ ነው ያሰኛል::

እኛ ክርስቲያኖቹ «ነገ መሞታችን ስለማይቀር እንብላና እንጠጣ» ከሚሉ ወገን አይደለንም:: 1ቆሮ. 15÷33:: ከምንበላው ምድራዊ ምግብ





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በላይ የእግዚአብሔር ቃልና ጸጋ የህልጠ ...ናችን መሠረት እንደ ሆነ እናምናለን። ...ድያ ለምንድን ነው ላበሉን ማዳላት፣ ...ላበሉንን መግፋት የጀመርነው? ለሆዳ ...ችን ስንልስ አጽዋማትን እስከ መሻር ...ምን በቃን? መልሱ ሆዳችንን አምላካ ... ከማድረጋችን የተነሣ ራስን በመ ...ዛትና በጾም የሚገኘውን ሰማያዊ ስጦታ ትኩር ብለን መመልከት ስለ ተሳነን ነው። በእውነት ሆዳችን በእምነት ለመቀ ...ዘቀዛችን ምክንያት ሆኗል። የመስቀሉ ...ገር ሞኝነት መስሎናል። ይህን በማድረ ...ጋችን ሥልጡን ወይም በዋቂዎች የሆን አይምሰለን፤ ሆዳችን አምላካችን ስለሆነ ...ብን ነው እንጂ። ፊልጵ.3፥19።

9. **መከራ፦** «በምድር ላይ የሰው ሕ... ወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን» ተብሏ ...ስ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ መከራ ሊመጣብን ግድ ነው። ኢዮ.7፥1። በስንፍናችን ወይም ሕይወት ጀርባዋን ሰጥታን ምግብ፡ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና፣ ትዳር፣ የሥራ ዕድገት አጥተን በመንፈ ...ስም በሥጋም የምንሠቃይ አለን። አንድ ጊዜ የተሰጠችንን አንዲት እምነት በመ ...ከተላችንም መከራ የጸናብን መኖራችን አይካድም።

አብርሃምና ሣራ በመካንነት፣ ...ንጉሥ ዳዊት ደግሞ በስደት፣ ሠለስቱ ደቂቅም በእቶን እሳት ተጥለው በመከራ ሲወድቁ ይበልጥ ከእግዚአብሔር ጋር በመጣበቅ በእምነት በረቱ እንጂ በእምነ ...ታቸው አልዛሉም።

መከራን ተሰቅቆ በእምነት መቀ ...ዘቀዝ ከዳተኝነት ነው። የገማቾችንና የተ ...ቺዎችን ትችት ፈርተን ባርኮ መብላት፣ ጸልዮ መኖር፤ በእውነትና በጽናት ማገልገ ...ልና ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ የተ...ውን የለንምን? የከበበንን መከራ በመፍራ...ት ከአሕዛብና የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕ...ርይ አምላክነት አጥብቀው ከሚቃወሙ መናፍቃን ጋር አብረን የተሰለፍን የለ...ንምን? አለን!! ነገ አልፎ ታሪክ በሚሆን የዛሬ መከራ ማመናችንን ያቀዘቀዝን ሰዎች ራሳችንን እንመርምር።

10. **ምቾት፦** «ቀይ ልብስና ቀጭን የተ...ልባ እግር የለበሰ አንድ ባለጠጋ ሰው ነበረ። ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደ...ስታ ይኖር ነበር» /ሉቃ. 16፥19-31/ የተ...ባለለት ነዌ ዘወትር በሥጋ ምቾት ተከበ ...መኖሩ በምግባር የመደኸየቱና በእምነት የመዛሉ ምክንያት ነበር። ትላንት በነበረን ትንሽ ዕድሜ፤ ዕውቀት፤ ገንዘብና ሥል...ጣን የነበረን እምነት ዛሬ ከምንኖርበት ...ድሎት ጋር ሲነጻጸር ከላራ ላይ ወድ...ቀናል። በኢኮኖሚና በኑሮ ተመችቶናል፤ በእምነት ግን ቀጭጨናል። ስናጣ አብል...ጠን ማመናችንን ስናገኝም የምንደግመው ...ሲሆን እግዚአብሔር በኛ ይደሰት ነበር። ...ግን አልሆነምና አንዳንዶቻችን በእምነት ...ቀዘቀዝን።

### በእምነት የመቀዝቀዝ አስከፊ ውጤቶች

1. **ጥርጣሬ፦** በእምነት የቀዘቀዘን ሰው ተጠራጣሪነት ያጠቃዋል፤ የአምላኩን ...ሁሉን ቻይነትና ይቅርታ ይጠራጠራል፤ ...መላእክትን ጥበቃ፤ የቅዱሳንን ምልጃ፣ ...የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚመለ ...ከተው በጥርጥር ነው። ስምዖን ጴጥሮስ፦ «አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ» ተብሎ የተገሠጸው በውስጡ ያለው እምነት ከመጉደሉና ከመቀዝቀዙ የተነሣ «እሡጥም ይሆንን?» ብሎ በመጠራጠሩ ነው። ማቴ.14፥28-33። እግዚአብሔር ሳይገልጥብን በመቅረቱ ተከለልን እንጂ በእምነት ዙሪያ ስላሉ መንፈሳዊ ነገሮች የምንጠራጠር ብዙዎች ነን። ስዎችን በመፍራት አለመናገራችን ከብርቱ ምእመናን ጎራ እንድንቆጠር አድርጎ ይሆናል። ውስጣችን ግን በጥርጥር ተሞልቷል። ይህም በእምነት ከመቀዝቀዛችን የተነሣ የመጣ መንፈሳዊ ክስረት ነው።

2. **ትችት፦** ብዙዎቻችን የምንተቸው የማናምንበትን ነገር ነው። የእምነት ጉልበቱ የደከመ ሰው ከአዲስ ክርስቲያን በባሰ መልኩ ትችት ያበዛል። ቅዳሴው ረዘመ፤ ጾሙ በዛ፤ ሰዓታትና ማሕሌት አያስፈልግም፡... ወዘተ ይላል። በዚሁ ከቀጠለ የእምነቱን ዶግማና ቀኖና ጭምር ያጣጥላል። ወይን የተባለ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ቀርጥፎ በመብላት ለከፋ ውድቀት ይዳርገናልና ከእጉል ትችት እንሽሽ። መኃ.2፥15። በእምነታቸው የበረቱ ክርስቲያኖች በተቺነታቸው ሳይሆን የሚታወቁት እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ እንደ ሚናገር ስለሚያምኑ ሁሉን ነገር በልባቸው በመጠበቃቸው ነው። ክርስቲያን ትችት ሲያበዛ ወይ ገና ወጣኒ ነው አለበለዚያም በእምነቱ ቀዝቅዟል።

3. **መናፍቅነት እና ክሕደት፦** ዛሬ መናፍቅ እና ከሐዲ ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ እንደኛው ሲያገለግሉ፣ ሲገለገሉና በኦርቶዶክሳዊት ጎዳና ሲጓዙ የነበሩ ናቸው። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ለቀዘቀዘው እምነታቸው አስቸኳይ የሆነ መንፈሳዊ እርምጃ ባለመውሰዳቸው በኑፋቄ ገደል ወድቀውና በክሕደት ጫካ ውስጥ ጠፍተው ቀሩ። አሁንም በእምነት ከመቀዝቀዛችን የተነሣ በትችትና በጥርጣሬ የተመላን ሁሉ አወዳደቃችንን እየከፋ ነውና ራሳችንን ቶሎ እንመርምር፤ «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ።» ተብለናልና። 2ቆሮ.13፥5።

4. **መተላለፍና በደል፦** ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፍ በደል መፈጸም እግዚአብሔርን እንደ ሚያሳዝን፣ ሰላምን እንደ ሚያሳጣና እንደ ሚያስቀጣ ያምን የነበረ ሰው በእምነቱ ሲቀዘቅዝ ይህን ሁሉ እንደ ሞኝነት ይቆጥረዋል። ኃጢአትንም እንደ እህል መብላት ይጀምራል። በኃጢአት ኑሮ ሠልጥነን የምንታይ ሁሉ ባለማወቅ ከምንሠራቸው ኃጢአቶች በላይ በእምነት ስንደክም የምንፈጽማቸው በደሎች ይበዛሉ።

5. **ሰላም ማጣት፦** ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው። በእምነታችን መቀዝቀዛችንን ተከትሎ የሚቆራኘን ጥርጣሬ፣ ትችት፣ ኃጢአትና ሌላም ስብራት ሰላም እንዳይኖረን ያደርገናል። የሰላምን አምላክ በመተዋችንም ድንጉጥና የምንባንን እንሆናለን። ይኸም በእምነት መቀዝቀዛችን ለክፉ ሰብእና እንደ ሚዳርገን ያስረዳል። ክፋት ባለበት ደግሞ ሰላም የለም። ምክንያቱም «ለክፉዎች ሰላም የላቸውምና።» ኢሳ.48፥22።

6. **መንፈሳውያን አባቶችን መጥላት፦** በራሱ ድክመትም ሆነ ከውጭ በሚመጡ ተጽዕኖዎች ምክንያት እምነቱ የቀዘቀዘ፥ ከባሰም ሃይማኖቱን የተወ፥ ሰው ለሃይማኖት መሪዎች ያለው ጥላቻ ጠንካራ ነው። ዲያቆናትን፣ ካህናትን፣ መነኮሳትን፣ ጳጳሳትን አጥብቆ መጥላት ይጀምራል። ቀናዒ የኾኑ ዘማርያንና ሰባክያንን ሲያይ ደሙ ይንተከተካል። ይህም በውስጡ እያሳደገው የመጣው ክፉ መንፈስ በእግዚአብሔር መንፈስ ከሚመሩ አገልጋዮች ጋር አለ መስማማቱን ያሳያል። በአጠቃላይ ሱስ ኘነት፣ አልባሌ ቦታ መዋል፣ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና መናቅና ማቃለል የመሳሰሉት በእምነቱ ከቀዘቀዘ ሰው የማይለዩ ክፉ ጠባዕያትና ልማዶች ናቸው።

7. **ከአገልግሎት መራቅ፦** በዘመነ ነገሥት የነበሩ አንዳንድ አገልጋዮች በእምነት ከመቀዝቀዛቸውና በምግባር ከመደኸየታቸው የተነሣ ከአገልግሎት በመራቅና የማይገባ ነገር በመፈጸም እግዚአብሔርን ያሳዝኑ ነበር። ይህን ያስተዋለው ንጉሥ ሕዝቅያስ አንድ ቀን ሰበሰባቸውና፦ «ልጆቼ ሆይ፥ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ አገልጋዮቹም ትሆኑ ዘንድ ታጥኑለትም ዘንድ እግዚአብሔር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ።» አላቸው። 2ዜና. 29፥11። ዛሬ በቸልታ ተሞልቶ ማገልገል እየተለመደ መጥቷል። እግዚአብሔርን ያህል ንጉሥ እያገለገሉ ቸልተኛ መሆን ከእርግማን ውጭ ምንም ትርፍ የለውም። የቱንም ያህል ሰበብ እናቅርብ ከአገልግሎት የራቅነው ከአገልግሎት የሚገኘውን ጸጋ እግዚአብሔር በእምነት ስላላየን ነው። ለዝማሬና ለስብከት ተጋብዘን ሳለ ጉባኤ የምጠንዘጋ፣ ጉባኤ የምናማርጥ፣ ሳንዘጋጅ ወደ ቅዳሴ የምንገባ፣ ማሕሌቱንና መዝሙሩን በይድረስ ይድረስ የምጠንቆም፣ ሰዐታቱንም በመሰልቸት የምናደርስ ሁሉ በእምነት የቀዘቀዝን ነን። ቀደም ሲል ግን እንዲህ አልነበርንም። መርሐ ግብር ለማምራት፣ ምእመናንን ለማስተናገድ፣ በተሰጠን ጸጋ ዕውቀትና አቅም ለማገልገል እንተጋ ነበር። ዛሬ ለምን ይህን ማድረግ አቃተን? እርስ በርስ መወሻሸት የለብንም- በእምነት ስለ ቀዘቀዝን ነው። ይህ ድካማችን የአገልግሎቱን ጣዕም አጥፍቶብናል። ራሳችንን ገሥጸን ወደ ቀደመ ሕይወታችን ካልተመለስን ወደ በለጠ ስብራት እንገባለን።

### እምነታችንን እንዴት አጠንክረን እንያዝ?

1. **በቅን ልብ፦** እምነት በትሕትናና በቅንነት በተሞላ ልብ ተቀብለው የሚኖሩበት ሰማያዊ ስጦታ ነው። ስናምን በአፋችን በመናገር ብቻ ሳይሆን በልባችን ፈጽመን በማመን መሆን አለበት፤ ሰው በልቡ አምኖ፥ በአፉ መስክሮ ይድናል ተብሏልና። ሮሜ 10፥9። በአፋችን ሳይሆን በልባችን የተቀበልነውን እምነት ደግሞ በቅን ልብ ማኖር ሌላው ተግባራችን መሆን



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

አለበት:: በቅን ልብ የተያዘ እምነት በየጊዜው ያድጋልና:: «በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ» ተብለናልና እምነታችንን በቅን ልብ ይዘን በእግዚአብሔር ፊት እንቁም:: ያዕ.1÷22::

2. *በመረዳት፡-* የምናመልከውን አምላክ ማንነት፣ የሃይማኖታችንን አስተምህሮና ኋላ የሚጠብቀንን ሽልማት ተረድተን የማንጓዝ ከሆነ በየመንገዱ ላይ ለሚደረግ ኩብለላ የተጋለጥን እንሆናለን:: ስለዚህ እምነታችንን በመንፈሳዊ ዕውቀትና በመረዳት ልንይዘው ይገባል፡ «የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል *አጥብቆ እየተረዳ* በእምነት በረታ እንጂ. በአለማመን ምክን ያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም» የተባለለት ጻድቅ እምነቱ ከመረዳት ጋር ነበር:: ዕብ.4÷ 21::

3. *በማክበር፡-* የሃይማኖታችንን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊትና አጠቃላይ ጸጋ በክብር ልንይዝ ይገባል:: እግዚአብሔር ማመናችንን ብቻ ሳይሆን እምነታችን እርሱን በማክበር ጭምር መሆኑን ያያል:: «ሃይማኖተኛ ነን» እያልን ክብር ለሚገባቸው ሁሉ ክብር የማንሰጥ ከሆነ እምነታችንን በክብር ይዘናል ማለት አንችልም:: ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የአብርሃምን እምነት ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ሲገልጥላቸው፡- «ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ ...» ብሎ ገልጾላቸዋል:: እኛም እምነታችንን በክብር እንያዝ:: እምነታችንን ብንንቅ ይፈረድብናል፤ «የፊተኛውንም እምነታቸውን ስለ ?ቁ ይፈረድባቸዋል::» እንዲል:: 1ጢሞ.5÷12::

4. *በጽናት፡-* በመጨረሻው ቀን ርትእት ሃይማኖታቸውን ከምግባር ጋር አዋድደው በጽናት የያዙ ብቻ ናቸው የሚሸለሙት:: ስለዚህ እምነታችንን አጽንተን እንያዝ:: በመጽሐፍ «የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና» ተብሎ ተጽፏልና:: ያዕ.3÷14-15::

5. *በሥራ፡-* ከመንፈሳዊ ተግባራት የማንርቅ ከሆነ መልካም ሥራችን ለደከመው እምነታችን ጉልበት ይሆናል:: ስለዚህ ባለን ጊዜ፣ ዕውቀት፣ ጉልበት፣ ገንዘብ፣ ጸጋ... ወዘተ ተጠቅመን መልካም ሥራን እንሥራ:: በጾም፣በጸሎት፣ በስግደት፣ በምጽዋት፣ በአገልግሎት፣ ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት የተያዘ እምነት ፍሬው ያማረና ጣፋጭ ነው:: ስለዚህ በሃይማኖት ያለን ሁሉ «መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት::» ገላ.6÷9::

## በእምነት ለቀዘቀዙ ምን እናድርግላቸው?

1. *እንቀበላቸው፡-* ቀደም ሲል በጠቀስናቸውና በሌሎች ምክንያቶች የተነሣ ሰዎች በእምነት ሊቀዘቅዙ ይችላሉ:: ነገር ግን በእምነት የደከሙትን ሁሉ በፍቅር ከተቀበልን በኋላ እንዲበረቱ ከማድረግ ይልቅ መቆጣት፣ ማግለል፣ መጠይፍ፣ መተቸትና ማማት የብዙዎቻችን ልማድ ሆኗል:: ይህም ከስሕተቶቻቸው ተምረውና ተጸጽተው ሊመለሱ የሚችሉ ወገኖቻችንን አሳጥቶናል:: ለወደፊት ግን እንደዚህ አይሁን:: እግዚአብሔር እኛን እንደ ተቀበለ ሁሉ እኛም በፍቅር ተቀብለናቸው የኑፋቄና የክሕደት ሰንኮፋቸውን እንንቀልላቸው፤ ከንቱና ዓለማዊ ፍላጎታቸውንም ለመዋጋት ከጎናቸው እንቁም:: «በእምነት የደከመውን ተቀበሉት» መባላችንንም አንርሳ:: ሮሜ.14÷1::

**ሕዝቡ እውነተኛ ወንጌልን እንዳይሰማ ከሚሯሯጡ አሕዛብና መናፍቃን ባልተናነሰ መልኩ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት እንቅፋት ለመፍጠር የምንጣደፍ አለን:: ይህን አሳዛኝ ተግባር አውልቀን እንጣልና ቃለ እግዚአብሔርን ከማጣቱ የተነሣ በእምነት ከመቀዝቀዝ አልፎ የእስማኤላውያንና የመናፍቃን ሲሳይ እየሆነ ያለውን**

2. *የጎደለውን እንሙላላቸው፡-* ሰዎች በእምነት ጉድለት ሲኖርባቸው ብቻ አይደለም በእምነት የሚቀዘ ቅዙት፤ የጤና፣ የሥራ፣ የመጠለያ፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የዕውቀት... ወዘተ ጉድለት ያለባቸው ሰዎችም በእምነት እየቀዘቀዙ ሃይማኖታቸውን ሲተው አይተናል:: እኛ ግን ምን እያደረግን ነው? የዕውቀት ጉድለቱን ለመሙላት በእምነት ወደ ማይመስሉት ሙዓለ ሕፃናት፣ ት/ቤትና ኮሌጅ የሚፈልሰውን ተማሪ ለመታደግ ምን ያህል ተነሥ ተናል? የምርትና የአገልገሎት መስጫ ተቋማትንስ?

ምእመናን ክርስቶስ በየጊዜው ቢጨመሩም ቀድሞም የነበረውን ሕዝብ ጉድለት በመሙላት በኩል ደክመናል:: ያለፈውን በታሪክነት ቆጥረን ዛሬ የሕዝበ ክርስቲያኑን ጉድለት ለመሙላት እንትጋ:: ሃይማኖታዊ ዕውቀቱ ጎድሎ የሚሠቃየውንም ሕዝብ እንታደገው:: ይህ ቃል በእምነት ለቀዘቀዙ ወገኖች የምናደርገውን ተግባር ይጠቁመናል:

- «ፊታችሁን ልናይ *በእምነታችሁም የጎደለውን* ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ እየጸለይን በአምላካችን ፊት ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስ ረክብ ዘንድ እንችላለን?» 1ተሰ.3÷9:: ስለዚህ በጾም፣ በጸሎት፣ በምጽዋት፣ በሐሳብና በሌሎች ነገሮች አማካይነት የጎደለውን ለጎደለባቸው እንሙላላቸው::

3. *ስብከተ ወንጌል ይጠናከር፡-* መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ለመላው ሕዝብ ሲልክ የሰጣቸው ትልቅ ትእዛዝ የወንጌልን የምሥራች ይሰብኩ ዘንድ ነው:: ማቴ.28÷16-20:: እነርሱም ሆኑ አባቶቻችን በርትተው በማስተማራቸው ዛሬ ያለነውን ጨምሮ ብዙዎችን ከሞት ወደ ሕይወት መልሰዋል::

በአሁኑ ጊዜ ያለውን የስብከት አገልግሎት በተመለከተ ግን ፈጽሞ የለም ለማለት ባንደፍርም የምንበጅተውን በጀት፣ ለማስተማር ያለንን ትጋትና ሕዝቡን ሊሰማ በሚችለው ቋንቋ መስበካችንን ስንመረምርና መሆናችንን እንረዳለን:: ሕዝቡ እውነተኛ ወንጌልን እንዳይሰማ ከሚሯሯጡ አሕዛብና መናፍቃን ባልተናነሰ መልኩ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት እንቅፋት ለመፍጠር የምንጣደፍ አለን:: ይህን አሳዛኝ ተግባር አውልቀን እንጣልና ቃለ እግዚአብሔርን ከማጣቱ የተነሣ በእምነት ከመቀዝቀዝ አልፎ የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ሲሳይ እየሆነ ያለውን ሕዝብ እንታደ ገው:: ትላንት በመዘግየታችን ዛሬ እየተቆጨን ያለን አለን? በዚህ አካሄዳችን ነገ የባሰ ነገር የማይመጣ ይመስለን ይሆን? እናስተውል:: ሰው ለማመንም ሆነ በእምነቱ ለመጠንከር ስብከተ ወንጌል ያስፈልገዋል:: «ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ፤ ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ» የተባለው ያለምክንያት አይደለም:: ስብከተ ወንጌል ያለውን ጉልበት ለመግለጽ ነው:: ሮሜ.10÷14:: ስለዚህ ለስብከተ ወንጌል የተለየ ትኩረት ሰጥተን እንበርታ፣ የእግዚአብሔር ቃል ለደከምን ሁሉ ብርታትና ጉልበት ነውና::

4. *እናጽናቸው፡-* ማጥመቃችን፣ ማስተማራችንና ቤተ ክርስቲያን መሥራታችን መልካም ቢሆንም ያጠመቅነውንና ያስተማርነውን ሕዝብ ተመልሰን የማንጎበኘው ከሆነ ለጥፋት ገብረ ነዋል ማለት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ሠርተን፡- ዕጣን፣ ዘቢብ፣ አገልጋይ ካህናት ይኖሩ ዘንድ ካልተጋን አገልግሎት በማጣቱ የተነሣ የምእመኑ መበተን አልታየንም ማለት ነው:: ስለዚህ፡- «የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤ የነከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ::» መባላችንን በማስታወስ ክርስቲያኖችን ለማጽናት እንትጋ:: ዕብ.12÷12-13::

ዛሬ ያለው ሰፊ ችግር ይኸነው:: የሚጎበኛቸው አጥተው የተፈቱ ሰንበት ት/ቤቶች፣ ጉባኤ ቤቶች ስንት ይሆኑ? የተዘጉትስ አብያተ ክርስቲያናት ማን አይቷቸው ይሆን? የሚያጸናውን ትምህርት በማጣቱ እምነቱ የቀዘቀዘበትን ምእመን የቆረጠሙ አሕዛብና መናፍቃን በየጫካ ው እንደ አንበሳ እያገሱ፣ እንደ ግስላ እየደነፉ ነውና ችግሩ አሳባቢ ሆኗል::

ስለሆነም ያስተማርነውን ተመል ሰን በማጽናት፣ ለሰንበት ት/ቤቶች፣ ለጉባኤ ቤቶችና በአጠቃላይ ለምእመኑ ተገቢውን አገልግሎት በመፈጸም በእምነት መቀዝቀዝ እንዳይመጣ እንጋደል:: እናት ቤተ ክርስቲያን፡- «በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ የደቀ መዛሙርቱን *ልብ እያጸኑ* በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና፡- ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ መግባት ያስፈልጋል» የሚሉ ታማኝ ልጆችን ዛሬ አብዝታ ትፈልጋለች:: የሐ.ሥራ.14÷21-22::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

**ባለፈው እትማችን ምስባክ ለምን ከመዝሙረ ዳዊት ተውጣጥቶ እንደ ሚሰበክ፤ በወንጌልና በምስባክ መካከል ያለውን መያያዝ ተመልክተናል። በዚህ ዝግጅታችን ደግሞ ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በተከታዩ የሥርዐት አፈጻጸም መማማራችንን እንቀጥላለን።**

/መ/ር ተስፋ እንዳለ/

ካህኑ፡- «እግዚአብሔር አምላክነ ወመድኃኒነ ወመፍቀሬ ሰብእ፤ ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ሰውን ወዳጅ እግዚአብሔር» በማለት፡- ዓለምን ፈጥሮ የሚመግብና የሚገዛ ጌታ ፈጣሪነት፣ አምላክነት፣ መድኃኒትነት የባሕርይ ገንዘቡ መሆኑን ይመሰክራል፤ «እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ» እንዳለ። ኢሳ. 45÷21።

ሰው ለማመን በዘገየ ልቡናውና በክፉ ግብሩ ለአምላኩ ጠላት በሆነበት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመላክ ፍቅሩን መግለጡን «መፈቀሬ ሰብእ፤ ሰውን ወዳጅ» እያለ ያሳስባል (ይጸልያል)፤ «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ... ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፡» እንዳለ። ሮሜ.5÷8-10።

ይህም ጸሎት ሲጸልዩ የእግዚአብሔርን የባሕርይ ቸርነቱን ማውሳትና ማዘከር እንደ ሚያስፈልግ ያስረዳል።

«ቅዱሳን የሚሆኑ ንጹሐን ሐዋርያትን ጌትነትህን የምትናገር ወንጌልን በማስተማር ያገለግሉ ዘንድ ሾምካቸው። የሹመታቸውንም ምልክት ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት ያድኑ ዘንድ ያደረግኸ» እያለ ይጸልያል። «ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወጡአቸው በርኵሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው።» እንዳል። ማቴ.10÷1። «እኛንም ወደን ፈቅደን ወንጌልን እንሰማ ስንድ የሰማነውንም እንተገብረው ዘንድ አብቃን፤» ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዘንድ ታውቆ በሰው ዘንድ ኅቡዕ /ስውር/ የነበረውን የሥጋዌውን /ሰው የመሆንን/ ምስጢር ያስተውሉ ዘንድ ለደቀ መዛሙርትህ አእምሮአቸውን እንደ ከፈትክላቸው /ሉቃ. 24÷45/ አሁንም በእኛ በነፍስ በሥጋ ፍጹም ዕውቀትን አሳድርብን፤ ጥቂት ሰምተን ብዙ ምግባር ትሩፋት እንሠራ ዘንድ፤ ጥቂትም ሠርተን ብዙ ክብር እናገኝ ዘንድ በቃልህ ለሚኖሩ ወገኖችህ ያዘጋጀሃትን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ አብቃን።» እያለ ይጸልያል።

ቃለ እግዚአብሔርን ለመማርም ሆነ ለማስተማር ጸሎት የግድ አስፈላጊ ነው። «በጸሎትም ይተጉ ነበር» እንዳል። ሐዋ.2÷42። መምህረ ሕዝብ ወአሕዛብ የኾነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡- «እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልኝ÷ ምስጢሩን ጥበቡን ያስታውቀኝ ዘንድ ርቱዕ በሆነ አንደበት በማይደክም ትጋት አገለግል ዘንድ ጸልዩልኝ።» እንዳለ። ቆላ.4÷3-4።

ካህኑ ነገረ ድኅነትን የምትናገር ወንጌልን እንደ ሚገባው ያነብና ይተረጉም /ያስተምር/ ዘንድ ሕዝቡ ማስተዋልን እንዲያገኝ ስለ ራሱ፣ ስለ አገልግሎቱና ስለ ሕዝቡ ይጸልያል።

## ማዕጠንተ ወንጌል

ካህኑ ስለ ክብረ ወንጌል አንዲት ቆቀር ዕጣን በጽንሐሕ ውስጥ ይጨምርና ቅዱስ ወንጌልን እያጠነ እንዲህ ይላል፡- «ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ፤ ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ወመድኅኒነ፤ ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ መጽንኢ ወመንጽሒ ለኵልነ፤»

• ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንዲት ሥልጣን ሁሉን የፈጠረ በአንዲት ምስጋና የሚመሰገን አብ ክቡር ምስጉን ነው ።

• ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ /ወልድ/ በኋለኛው ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚመሰገንበት በአንዲት ምስጋና ምስጉን ነው።

• የሚያጸና እና የሚያነጻ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር በአንዲት ክብርና ምስጋና ክቡር ምስጉን ነው።» ይላል። ንፍቁ ካህንም «አእኵትዎ ለአብ፣ አእኵትዎ ለወልድ፣ አእኵትዎ ለመንፈስ ቅዱስ፤ አብን ወልድን መንፈስ ቅዱስን አመስግኑ» እያለ ሕዝቡ አምላኩን የባሕርይ ገንዘቡ በሚሆን ምስጋና እንዲያመሰግኑ ያስታውሳል።

«ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርኹት ሕዝብ» እንዳለ። ኢሳ. 43÷20።

## ዜናሁ ለእግዚእነ

ዲያቆኑ፡- «ቅድመ ዓለም የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ዓለምንም አሳልፎ የሚኖር የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዜና ተአራቱን የምጠትናገር ወንጌልን ነቅታችሁ ተግታችሁ ስሙ።» ይላል። ወንጌል ጌታችን ድውይ መፈወሱን፣ ሙት ማንሣቱን፣ ለምጽ ማንጻቱን፣ ኅብስት ማበርከቱን፣ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡን፣ ሥጋውን ደሙን ምግበ ሕይወት እንዲሆን መስጠቱን ትናገራለችና ዜና ትባላለች።

ጌታችን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው የህልውና አንድነት ቅድመ ዓለም የነበረ እንደ ሆነ ሁሉ በአንዲት ሥልጣንም ዓለምን ፈጥሮአል፤ የፈጠረውንም ዓለም ያሳልፋል። ይህም የእርሱን ህልውና፣ ሥልጣንና ሥራ የምትናገር ወንጌልን ነቅቶ ተግቶ መስማት የሚገባ መሆኑን መናገር ነው።

ካህኑ በልዑል ዜማ «ወንጌል ቅዱስ» ብሎ ያዜማል።

- ወንጌሉ የዮሐንስ ሲሆን «ዘሰበከ» ይላል። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ ረቂቁ ምሥጢረ ሥጋዌ ተገልጾለት ንጹሐ ሥጋ፣ ንጹሐ ነፍስ፣ ንጹሐ ልቡና ተሰጥቶት «ቀዳሚሁ ቃል» ብሎ ከልቡ አንቅቶ ተናግሮአልና።

- የሦስቱ ወንጌላውያን ሲሆን «ዘዜነወ ማቴዎስ ፣ማርቆስ፣ ሉቃስ» ይላል። እነዚህ ሦስቱ ወንጌላት በአብዛኛው የሚያትቱት ጌታችን ያደረገውን ተአምራት ያስተማረውን ትምህርት ነውና።

ሕዝቡ ሁሉም ለየራሱ፡- «አቤቱ÷ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ÷ ሁል ጊዜ ክብር ምስጋና ይገባሃል» ይላል።

• ቅዳሴው ግዕዝ ከሆነ፡- «በወንጌል መራሕከነ፣ በወንጌል መራኽን...፤ በነቢያትም አጽናናኸን፤ ወደ አንተም ስላቀረብከን ክብር ምስጋና ይገባሃል።» ቀድሞ በነቢይ በመልአክ አድሮ ነበር፤ ዛሬ ግን እርሱ ራሱ መጥቶ አድኖናልና።

• ቅዳሴው ዕዝል ሲሆን፡- «ተፈሥሒ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ..... ሥጋ ኾኖ በሥጋው በደሙ በረዳን በእግዚአብሔር አምናችሁ ደስ ይበላችሁ፤ ለያዕቆብ ፈጣሪ ምስጋና አቅርቡ፤ በገና ያዙ፤ ከበሮውን ሳዋቂ ስጡ። በገና ከመሰንቆ ጋር ያማረ የተወደደ ነውና። አንድም ወንጌል ከሃይማኖትና ከምግባር ጋር የተወደደ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነው፡፡ «መስንቆስ ይእቲ ሃይማኖት እንተለብሰዋ ሰማዕት፤ መስንቆስ ሰማዕታት የለበስዋት / ገንዘብ ያደረጓት÷ በምግባር የገለጿት/ ሃይማኖት ናት፡፡»

## ንበተ ወንጌል

ካህኑ፡- «ነዋ ወንጌለ መንግሥት፡- ጌትነቱን የምትናገር÷ በጌትነቱ የተሠራች መንግሥተ ሰማያትን የምትሰብክ ወደ መንግሥተ ሰማያትም የምታገባ ወንጌል ይህች ናት» ብሎ ለንፍቁ ቄስ ይሰጠዋል፡፡ ንፍቁ ቄስም፡- «ጌትነቱን ቸርነቱን የምትናገር ቁሱ የሰጠኝን ወንጌልን ሰጠሁህ» ብሎ ለዲያቆኑ ይሰጠዋል፡፡ ሠራዒው ካህን የጌታ፣ ንፍቁ ቄስ የቅዱስ ጴጥሮስ፣ ዲያቆኑ የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ይኸውም ከጌታችን ቀጥሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ወንጌልን አስተምሮአል፡፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥሎ ቅዱስ እስጢፋኖስ የማስተማሩ ምሳሌ ነው ፡፡

ዲያቆኑ፡- «ንስሑ ወእመኑ» - ወንጌል የምትነገረበት ጊዜ ቀርቦአልና ነቅታችሁ ተግታችሁ ስሙ፡፡ አንድም መንግሥተ ሰማያት በልጅነት የምትሰጥበት ሰዓት ነውና ንስሐ ግቡ ይላል፡፡ «ዘመኑ ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ፡፡» እንዲል፡፡ ማር.1÷15፡፡

## «ፃው ንዑስ ክርስቲያን፤ የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ»

ከቅዱስ ውኃና መንፈስ ተወል ደው በሥላሴ ልጅነት ያልከበሩ ሰዎች ከምስጢራት መካፈል ስለ ማይገባቸው እስከ ፃው ድረስ ያለውን ሥርዐተ ቅዳሴ ሲከታተሉ ቆይተው ዲያቆኑ ፃው ሲል እንዲወጡ በድምፅም በደወልም ይታዘ ዛሉ፡፡ በጥንቱ ሥርዓት ንኡስ ክርስቲያን /ያልተጠመቁ/ የሚወጡበት ሥርዐት ነበር፡፡ ያልማድ ግን ዛሬም እንደ ቀጠለ ይታያል፡፡

በሥርዓተ ቅዳሴው በአጠቃላይ ፡-

ለተጋብዖ ይደወላል፤ የትንቢተ ነቢያት ምሳሌ ነው፡፡ ለግብር ይደወላል፤» የብሥራተ ገብርኤል ምሳሌ ነው፡፡ ለወንጌል ይደወላል፤» የጌታ ትምህርት ምሳሌ ነው፡፡ በድርገት ይደወላል፤»

የ12ቱ ሐዋርያትና የ72ቱ አርድዕት ምሳሌ ነው፡፡ ሥርዐተ ቅዳሴው ተጀምሮ እስኪፈጸም አራት ጊዜ መደወሉ የአራቱ ወንጌላውያን ትምህርት፡፡ አንድም የጌታችን ትንሣኤ አራት ጊዜ ለመነገሩ ምሳሌ ነው፡፡ ይኸውም፡-

መላእክት → ለሴቶች →ለሐዋርያት → ለሕዝቡ ለመናገራቸው ምሳሌ ነው፡፡

## የለኆሳስ ጸሎት

ካህኑ ከመቅደሱ ገብቶ፡- «አ እግዚአብሔር አምላክነ .......፤ እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ÷ ሰውን መውደድህ የማይመረመር ነው፡፡ አንድያ ልጅህን ለዓለም ቤዛ ይሆን ዘንድ መላክህን ማን ይመረምረዋል» እያለ በዝግታ ይጸልያል፡፡

በለኆሳስ /በሹክሹክታ፣ በቀስታ/ መጸለዩ አምላክ ሰው ሲሆን ሰው አምላክ ሲሆን ያወቀው የለምና፤ አንድም ለፍርድ መምጫውንም ጊዜ የሚያውቅ የለም፤ «የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ይመ ጣል» እንዳለ፡፡ ማቴ.24÷44፡፡

ካህኑም በመቀጠል፡- «እኛ ጣላቶችህ ሳለን አንድያ ልጅህን ውረድ ተወለድ» ብለህ ወደዚህ ዓለም ልከኸልናል፡፡ ለ5500 ዓመታት ያህል ከማኅበረ መላእክት ተለይቶ የነበረ አባታችን አዳም ከመላእክት ጋር ምስጋናህን እንዲሠዋ አድርገኸዋል፡፡ «አቤቱ÷ በራስህ መለኮታዊ ሥልጣን ከራስህ ጋር ያስታረቅኸን÷ ነውር ነቀፋ የሌለበትን ሥጋህን ደምህን ለመቀበል አብቃን፡፡ የምንመካው ለባሕርያችን ለነገዳችን ልታደርጋት በወደድኃት ቸርነትህ ነው እንጂ በሞያችን በጉልበታችን አይደለም» ይላል፡፡ እግዚአብሔር የወደደን የሚወደድ ነገር ኖሮን አይደለም፤ እንዲሁ መፍቀሬ ሰብእ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ «ወድጃችኋለሁ» እንዲል፡፡ ሚል.፩÷፪፡፡ ታላቁ ሐዋርያም፡- «እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን እንኳ ሙታን በሆን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፡፡» ብሎአል፡፡ ኤፌ 2÷4-6፡፡

«አቤቱ÷ ባሕርያችንን ለመዋሐድ የመረጥኃት÷ ሰው ወዳጅ የምትሆን÷ ከቸርነትህ የተነሣ እንለምንሃለን፤ እኛን ለማዳን «ወደ እኔ ኑ» እንባልበት ዘንድ ያደረግኸው ሥጋህ ደምህ በእኛ በወገኖችህ በአገልጋዮችህ ለመፈራረጃ አይሁንብን፡፡ አንድም «ሑሩ እምኔየ፤ ከእኔ ሂዱ ለመባል አይሁንብን፤ እኛን ለማዳን በነፍስ በሥጋ በቸልተኝነት የሠራነውን ኃጢአት ለማስተሰረይ የበቃ ይሁንልን እንጂ» እያለ ካህኑ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ይጸልያል፡፡

ከዚህ በኋላ ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን÷ ስለ አባቶች እንዲጸልዩ ዲያቆኑ ያዛል፡፡ እንዲሁም የሃይማኖት ጸሎት ያውጃል፡፡

ይህም በቅዳሴ ሐዋርያት፤ በቅዳሴ እግዚእ፤ በቅዳሴ ማርያምና በቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በሚቀደስበት ጊዜ «አመክንዮ...» ይባላል፡፡ በተቀሩት ዐሥሩ ቅዳሴያት «ጸሎተ ሃይማኖት» ይባላል፡፡ ከዚያም ካህኑ «ዘኮነ ንጹሐ...፤ ራሱን በንስሐ ያዘጋጀ ሥጋውን ደሙን ይቀበል፤ ንስሐ ያልገባ ግን አይቀበል» የሚለውን ዐዋጅ ያውጃል፤ ካህኑ የተናገሩት ቃል ያወጁትን ዐዋጅ ቸል ማለት እንደ ማይገባ ዲያቆኑ ያስጠነቅቃል፡፡

## እግዚአብሔር ዐቢይ

ካህኑ «እግዚአብሔር ዐቢይ ዘለዓለም፤ ይህን ዓለም በመፍጠርና በማሳለፍ ዐቢይ የሚሆን እግዚአብሔር ያለ መለወጥ ሰውን የፈጠርኸው፡፡» ይላል፡፡ ቅዱስ ዳዊት፡- «ጌታችን ታላቅ ነው፤ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ ለጥበቡም ቁጥር የለውም» እንዳለ፡፡ አንድም፡- መለወጥ ሳይኖርበት ሰውን በንጽሐ ጠባይዕ የፈጠርኸው ዓለም ሳይፈጠር የነበርህ ዓለምን አሳልፈኸ የምትኖር» ይላል፡፡ «ከጥንት ምድርን የመሠረተ፣ ሰማያትንም የእጅ ሥራው ያደረገ እርሱ የፈጠረውን ሁሉ ያሳልፋል፤ እርሱ ግን አያልፍም፤ ሁሉምን ያስረጃቸዋል እርሱ ግን ያው እርሱ ነው፡፡» መዝ.101÷55 -57፡፡

አስቀድሞ ሰይጣን ቀንቶ ያመጣውን ሞትን ፭ሺ፭ መቶ ዘመን ሲፈጸም ሕያወ ባሕርይ በሚሆን በልጅህ በጌታችን በመድኃኒታች በፈጣሪያችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን አጠፋህ፤ «የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» እንዲል፡፡ 1ዮሐ.3÷8፡፡

በሰማይ የሚኖሩ መላእክት አንተን የሚያመሰግኑባትን አንድነት ፍቅርን መላህ፤ አንድም በኢዮር በራማ በኤረር የሚኖሩ መላእክት አንተን በማመን ጸንተው የሚኖሩበትን አንዲት ሃይማኖት በዓለም ሁሉ መላህ /ለሰው ልጆች ሰጠህ/፤ ስለዚህም አምላክነትን ገንዘቡ ላደረገ ሥጋ በሰማያት ምስጋና ይገባል፡፡ በምድርም ዕርቅ በዕንስ ተጀመረ፤ በስቅለትና በትንሣኤ ተጠናቀቀ፤ ለሰው ልጅም ነጻነቱ ተሰጠው፤ «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን» እንዳለ፡፡ ኤፌ.፭÷፩፡፡ ለድኅነት መብቃት የሚቻለው ይህን የነጻነት ዐዋጅ በፍጹም ልባዊ እምነት ተቀብሎ በምግባር መመስከር ሲቻል ነው፡፡ ሮሜ.10÷10፤ ያዕ.2÷14፡፡ «አቤቱ÷ ወደህ ጸጋህን /ልጅነትን ወዳጅነትን/ አንተን መፈራትን ፍቅርህን በልቡናችን አሳድርብን፡፡» እያለ ሲጸልይ ዲያቆኑ፡- «ስለ ሰላም ጸልዩ» ብሎ ያዝዛል፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም መስፈን በአገልግሎቷ ሁሉ እንደምታሳስብ ያጠይቃል፡፡

ከዚህ በኋላ ካህኑ ቅድስት ከሆነች÷ ድኅነተ ሥጋን ድኅነተ ነፍስን ከምታሰጥ ሀብትህ /ገንዘብህ ከሚሆን «ከቅዱስ ሥጋህና ክቡር ደምህ/ እንድንሳተፍ አብቃን» ይላል፡፡

አንድም ሰማያዊ ሞትን ከምታርቅልን /ሑሩ እምኔየ/ የምትለውን ቃል ከማያሰማን የሕይወት ማዕድህ አሳትፈን ይላል፡፡ ይኸውም ሥጋውን ብንበላ ደሙን ብንጠጣ የዘለዓለም ሕይወት እንደሚኖረን ለማጠየቅ ነው፡፡ እንግዲህ በሥርዐተ ቅዳሴ ውስጥ የተተነተነው ነገረ ድኅነት ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ ላይ ያበቃል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ቅዱሳን ሐዋርያትና ሌሎች ሊቃውንት አባቶች በመጽሐፈ ቅዳሴአቸው ነገረ ድኅነትን እንዴት እንደ ገለጡት እንመለከታለን፡፡ ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ተሠግዎተ ቃል

/20ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሐዋርያዊ ቅዱስ አትናቴዎስ እንደ ጻፈው/

/ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ/

## የዚህ ጽሑፍ ዓላማ እግዚአብሔር በቃሉ ይህን ዓለም መፍጠሩን፣ የቃለ እግዚአብሔርን ሥጋ መሆንና ዓለምን ማዳኑን ማየት ነው።

ባለፈው እትማችን በዚህ ርእስ ባቀረብነው ዝግጅት ቃለ እግዚአብሔር ሰው የሆነበትን ምክንያት ተናግረናል። የሚሞተውንና የሚፈርሰውን የማይሞ ትና የማይፈርስ ለማድረግ፣ የሰው ልጅ የጠፋ በትን አርአያ እግዚአብሔርነትን፥ መልክአ እግዚአብሔርነትን ለመመለስና በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር መጀመሪያ ከምንም ከፈጠረውና የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነው ከእርሱ በቀር ለሌላ ለማንም የተገባ አይደ ለም። ስለዚህ ሕይወት ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር የሰውን መዋቲነት ሌላ ማንም ሊያስወግድ አይችልም። ጣዖታትን ሊያጠፋና ስለ አባቱ ሊያስተምር የሚችል እርሱ ብቻ መሆኑን አይተናል።

የሰውን የሞት ዕዳ ሊከፍል የሚችል እርሱ ነውና ስለዚህ ወደ እኛ መጣ።ለዚህም ኤምላክነቱን በሥራዎቹ ከገለጠና ካስረዳ በኋላ፤ ራሱን ስለ ሁሉ መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ። «ራሱን ስለ ሁሉ ቤዛ ለሞት አሳልፎ ሰጠ።» 1ጢሞ.2፥6። ይህም፦

ሀ/ ሰውን ሁሉ ከቀደመ በደሉ ነጻ ለማውጣት ነው ።

ለ/ ኃይሉንና ሥልጣኑን በሞት ላይ ያሳይ ዘንድ፤ስለ ሁሉ ትንሣኤ በኩር ሆኖ ሙስና መቃብርን /በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረትን/ አሸንፎና አጥፍቶ በመነሣት የሰውነቱን ሕያውነት ይገልጥ ዘንድ ነው።

ሰውነቱ በድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ ከድንግል የተገኘ ከኃጢአት በቀር እንደ እኛ ነውና ሞት ስለሚስ ማማው እንደ ወገኖቹ ሞተ፤ ነገር ግን ቃል የተዋሐደው ሰውነት ስለሆነ ለሥጋ የሚስማማው መፍረስና መበስበስ የሚገዛው አልሆነም። በተዋሐደው ቃል ምክንያት መፍረስና በመስበስ የማይደርስበት ሆነ እንጂ።

ስለሆነም ሁለት ድንቆች በአ ንድነት ተፈጸሙ፤ የሁሉም ሰው ሞት በክርስቶስ ሥጋ ተፈጸመ፤ ተካተተ፤ እንዲ ሁም የሥጋ ገንዘቦች የነበሩ ሞት፣ መፍ ረስና መበስበስ ቃል ሥጋን በመዋሐዱ ምክንያት በፍጹም ተወገዱ።

በርግጥም ሞትን ስለ ሁሉ የሚ ቀበል ያስፈልግ ነበርና፤በሁሉም ላይ የነበረው የሞት ዕዳ ይወገድ ዘንድ፤ ከላይ እንዳየነው ቃል በራሱ ሞት የማይስማማው ስለሆነ ሞት የሚስማማው ሥጋን ተዋሐ ደ፤ስለ ሁሉም እርሱ መሥዋዕትና ቤዛ አድ ርጎ ያቀርበው ዘንድ፤ በዚህም መከራንና ሞትን በመቀበሉ ከሥጋው ጋር በተዋሐደው መለኮት የተነሣ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለውን ሞትን፥ ዲያብሎስን ድል ነሣው። «በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፤ ይኸውም ዲያ ብሎስን ነው። በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፤ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።» ዕብ 2፥14-15።

✡ ✡ ✡

የሁላችን መድኃኒት ስለ ሁላችን ስለ ሞተልን /ሞቶልናልና/ በርሱ የምናምን እኛ እንደ ቀድሞው በኩኔ ሞት አንሞትም። መፍረስና መበስበስ በትንሣኤው ኃይል በመወገዱ ከአሁን በኋላ የምንሞተው ለሥጋችን እንደ ሚስማማው ሞት ሞቱን የበለጠውን ትንሣኤ እንድናገኝ ነው። ሞት በመድኃኒ ታችን ቸርነት ተወግዶአልና ተዘርተን እንነሣለን እንጂ ሞቱን አንቀርም።

ቅዱስ ጳውሎስ፦ «ሙታንም የማ ይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤እኛም እንለ ወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበ ሰብሰውን ሊለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲ ለብስ፣ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ» ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈ ጸማል። «ሞት ሆይ፤ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፤ ድል መንሣትህ የት አለ?» እንዳለ። 1ቆሮ. 15፥23-55። ስለ ሁሉ ሰውነቱን ለሞት አሳልፎ መስጠት አስፈላጊ ከሆነ በመስቀል ከመሞት ይልቅ ለምን በስውር አልሞተም? እንዲህ የር ግመት ሞት በተባለ በመስቀል ከመሞት ይልቅ ለምን ሰውነቱን በክብር እንዲሞት አላደረ ገውም?

እርሱ የሁሉም ሕይወትና የእግ ዚአብሔር ቃል በመሆኑ ስለ ሁሉ ሊ ሞት ቢገባውም ሰውነታችን ኃይል የሚ ያገኘው በእርሱ ነውና መሥዋዕትነቱን ፍ ጹም ያደርግ ዘንድ ሞትን በፈቃዱ ወደ ተቀበለ።

ሰው የሆነው ለዚህ ነውና ሞት ን ማስቀረት ተገቢ አልነበረም፤ ምክንያ ቱም ትንሣኤ እንዳይቀር። ስለዚህ ስለ ሁሉም ቤዛ ሆኖ ቢሞትም መፍረስንና መበስበስን አላየም፤ ሰውነቱ ቀድሞ እንደ ነበረ ተነሣ፤ ሰውነቱ የሕይወት ባለ ቤትን የተዋሐደ ነውና፤የርሱ ገንዘብ ነውና።

✡ ✡ ✡

ለምን ራሱን ከአይሁድ መከራ አልሰወረም? የእግዚአብሔር ቃል የሁሉ ሕይወትና ኃይል እንደ መሆኑ የሁሉ ቤዛነቱን ያሳይ ዘንድ ሞትን ያጠፋው ዘንድ ጠበቀው። ለሁሉም ድኅነት ሞትን ቀመሰ።

ጌታችን የመጣው ሞትን ድል በማድረግ፣ ትንሣኤን በመግለጥ፣ መፍረ ስንና መበስበስን ማስቀረቱን በግል ጽ ለማሳየትና ለማብሠር ነው። በዚህም ለእኛ ትንሣኤ መሪና አብነት ሆኖ ትንሣኤያችንን ያበሠረን ዘንድ ነውና ስለዚ ህ ሰውነቱን ከመፈረስና ከመበስበስ ጠበቀ። ማቴ.27፥42።

### ስለ ትንሣኤው አማናዊነት በአደባባይ መሞት አስፈለገው

ያለ ሕማምና ደዌ ሞትን በስውር ተቀብሎ ከዚያ በኋላ ድንገት ተገልጦ ከሞት መነሣቱን ቢናገር በሁሉም ዘንድ ተረት የሚናገር ይመስል ነበር፤ ሞቱን ያየና የሚመሰክር ካለ መኖሩም የተነሣ ስለ ትንሣኤ የሚናገረው ነገር ሁሉ የማይታመን ይሆን ነበር።

ሞት ትንሣኤን መቅደም አለ በትና /ሞት ከሌለ ትንሣኤ የለምና /ሞቱን በድብቅ ተደርጎ ቢሆን ሞቱ ሳይገለጥና በምስክሮች /ሕዝብ/ ፊት ሳይደረግ ቢቀር ኖሮ ትንሣኤውም ያለ ምስክርና ማስረጃ ስውር ሆኖ ይቀር ነበር። ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ ትንሣኤውን በዐዋጅ የሚናገር ከሆነ ሞቱን ለምን በስውር እንዲ ሆን ያደርጋል?

ርኩሳን መናፍስትን ማውጣትን፣ ውኃውን የወይን ጠጅ ማድረግን፣ ዐይንን በደረቅ ግንባር ላይ መፍጠርን...እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ይታመን ዘንድ በሕዝብ ሁሉ ፊት በገባኤ ካደረገ የሚሞት ሰው ነቱ ሕያው መሆኑን እንዲሁም እርሱ ሕይወት መሆኑ ይታወቅ ዘንድ እንዴት በሁሉም ፊት አያደርገም?

ደቀ መዛሙርቱስ መጀመሪያ ሞቱ ካላሉ ስለ ትንሣኤው እንዴት ደፍ ረው መናገርና ማስተማር ይችሉ ነበር? በሚናገሩዋቸው ሰዎች ዘንድ ስለ ክርስ ቶስ መሞት ምስክሮች እና ዐዋቂዎች ባይሆኑ ኖሮ፦ «ሞቶ፥ ተነሣ ብለው ሲያ ስተምሩ እንዴት ይታመኑ ነበር? ሞቱና ትንሣኤው በሁሉም ፊት በአደ ባባይ ተፈጽሞ እንኳ የዚያን ጊዜዎቹ ፈሪሳውያን ከካዱ ይህ ሞቱ በድብቅ ቢፈጸም ኖሮ ላለማመ ናቸው ምን ያህል በር ያገኙና ምክ ንያት ይፈጥሩ ነበር? የሞት ፍጻሜ እና ድል መነሣትስ እንደ ሞት በሁሉ ዘንድ በመሞቱና ለወ ደፊቱ ደግሞ በሥጋው ሕያው ሆኖ መነሣት ካልሆነ በቀር እንዴት ይረጋገጥ ነበር?

✡ ✡ ✡

«የትንሣኤው ነገር ይታመን ዘንድ ሞቱ በገባኤ በሁሉም ዘንድ መሆን ቢ ኖርበትም ለሞቱ የመስቀልን /የውርደት/ ሞት የሚያስቀር ሌላ የክ ብር ሞት ቢ ዘጋጅ የተሻለ ነበር» የሚል ይኖር ይሆናል።

ነገር ግን በሌሎች ያውም በጠ ላቶቹ የተዘጋጀ ሞትን በመስቀል ላይ ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ /ጠላቶቹ/ አስፈ ሪና አሳፋሪ እንዲሁም ከባድና ጽኑ ብለው ያዘጋጁለትን ሞት በፈቃዱ ተቀበለ። በዚ ህም እርሱ ሕይወት መሆኑ ይታወቅ ዘንድ እና የሞት ኃይል ይወገድ ዘንድ ነው።

ስለዚህ አስደናቂና አስገራሚ ነገር ተፈጸመ፤ ለውርደትና ለኃሣር ብለው ያዘጋጁለት ሞት፥ በሞት ላይ ድል የመጠ ቀዳጅት የድል ምክንያትና መግለጫ ሆነ።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በሞቱ እንኳ ሰውነቱ ሳይከፈል ፍጹም እንደ ሆነ ይጠበቅ ዘንድ÷ ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍሉ ምንም መግቢያ ምክንያት እንዳያገኙ::

✡ ✡ ✡

## ለምን በመስቀል ሞተ?

ከሞት ዓይነት ሁሉ ለምን በመስቀል ሞተ? የሚል ቢኖር ከመስቀል ሞት በቀር ለእኛ ድኅነት ጥሩ የሆነ ነገር አልነበረምና ጌታችን በመስቀል በመሞቱ መልካም አደረገልን::

በእኛ ላይ የነበረውን እርግማን ያስወግድ ዘንድ ከመጣ ለርግመት የተ ገባውን ሞት ካልሞተና ካልተቀበለ በቀር እንዴት ርግማናችንን ይሸከም ነበር? ይኸውም መስቀል ነው::

«በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክር ስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እር ግማን ዋጀን፤» ገላ.3፥13::

«በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግ ዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው» ተብሎ የተጻፈው ይኸ ነው:: ዘዳ.21፥23:: የጌታችን ሞት ለሁሉ ቤዛ ለመሆን እስከ ሆነ ድረስ፥ በሞቱ የጥል ግድግዳን ያፈርስ ዘንድ፥ አሕዛብን ይጠራ ዘንድ ከሆነ ባይ ሰቀል ኖሮ እንዴት ይጠራን ነበር? ሰው እጆቹ ተዘርግተው ሊሞት የሚችለው በመስቀል ብቻ ነውና:: ጌታችን ይኸንን ሊቀበልና እጆቹን ሊዘረጋ፥ሕዝብንና አሕዛብን ይጠራና ሁለቱንም ከእርሱ ጋር ያዋሕድ ዘንድ እጆቹ ተዘርግተው ሊሞት ተገባው:: ይህ ጌታችን በምን ዓይነት ሞት ይቤዠን ዘንድ እንዳለው ሲገልጽ የተናገረው ነው፤ «እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልኩ እንደ ሆን ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ::» ዮሐ.12፥32::

እንዲሁም የሰው ልጅ ጠላት ከሰማይ ወድቆ በአየሩ ላይ የሰፈነው ጠላት /ዲያብሎስ/ ስለሆነ በመናፍስቱ አማካይነት በተታለሉት ላይ ምትሃትንና ቅዠትን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ወደ ላይ ሊሄዱ ያሉትን /የሚሄዱትን /ሁሉ ለማስቀረት ይጥር ነበረና:: ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ እንዲህ እንዳለ:- «በእርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን የሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው የአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችኁባቸው::» ኤፌ.2፥2::

ጌታችን የመጣው ሰይጣንን ለማስወገድ፥ አየራትን /ዓለማትን/ ለመቀደስ፣ ወደ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ለመጥረግና ንጹሕ ለማድረግ ነውና ሐዋርያው:- «በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል» እንዲል፥ ይኸም በሞት ነው ሊፈጸም የሚችለው:: ዕብ.10፥ 20::

ይኸ በአየር ላይ ካልኾነ ማለትም በመስቀል ሞት ካልሆነ በቀር እንዴት ይፈጸም ነበር? በመስቀል ላይ የተሰቀለ ብቻ ነውና በአየር ላይ የሚሞተው:: ስለዚህ ጌታችን በመስቀል ሞት መሞቱ ፍጹም ተገቢ ነበር:: ስለሆነም በመስቀል ላይ በመውጣቱ /ከፍ ከፍ በማለቱ/ አየራትን ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ሁሉ አጠራ፤ «ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ::» እንዳለ:: ሉቃ.10፥8::

ወደ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ እንደ ከፈተው እርሱ እንደገና እንዲህ እንዳለ:- «እናንተ መኳንንቶች በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም በሮች ይከፍቱ::» መዝ. 23፥7:: ሥግው ቃል የበሮችን መከፈት የፈለገው ለራሱ አይደለምና፥ ከፍጥረትም ወገን ማንም ለፈጣሪው የማይታዘዝ የለምና፥ ነገር ግን በሰውነቱ ገንዘብ ያደረገን እኛ ነበርን ይህን የዘላለም በሮች /የሰማይ መንገድ/ መከፈት የምንፈልግ:: ስለዚህ በዚህ የሰማያትን መንገድ እንደገና ከፈተና ዝግጁ አደረገልን::

## ጌታችን ለምን በሦስተኛው ቀን ተነሣ?

በመስቀል ላይ ለእኛ ሲል መሞቱ ተገቢና መልካም መሆኑን ከሁሉም አንጻር ተመልክተናል::

ጌታችን በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ዕለቱን ወዲያውኑ አልተነሣም:: ወዲያውኑ ቢነሣ አልሞተም ወይም ፍጹመ ሞተ አልሞተም ሊባል ይችል ነበርና፥ እንዲሁም ወዲያውኑ እንደ ሞተ ቢነሣ ኖሮ የሕያውነቱ፣ የማይ ፈርስና የማይበሰብስ የመሆኑ ክብር በተሸፈነ /ግልጽ ባልሆነ/ ነበር:: ስለዚህ ሰውነቱ ፈጽሞ እንደ ሞተ ይረጋገጥ ዘንድ በሞቱና በትንሣኤው መካከል የአንድ ቀን ልዩነት አድርጎ በሦስተ ኛው ቀን ለሁሉም ሕያው መሆኑን አሳየ:: ስለዚህ በመስቀል ላይ መሞቱ ይረጋገጥ ዘንድ በሦስተኛው ቀን ተነሣ::

ሆኖም ብዙ ጊዜ በመቃብር ከቆየ በኋላ ቢነሣ ሰውነቱን በሌላ ሰውነት እንደ ለወጠው እንዳይመ ስል፥ እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች ከጊዜ ብዛት የተነሣ ያየውን ይጠራጠራልና የሆነውንም ይረሳልና እንዲህ እንዳይሆን ከሦስት ቀን በላይ በመቃብር አልቆየም:: እንዲሁም ስለ ትንሣኤው በተነገረው ትንቢትና ለሐዋርያቱ በሰጣቸው ተስፋ መሠረት በሦስተኛው ቀን ሞቶ የነበረ አምላክ የማይሞትና የማይፈርስ ሕያው መኾ ኑን አሳየ፥ የሞተውም ሞት ሊገዛው ስለሚችል /በግዴታ/ ሳይሆን በእርሱ ኃይልና ፈቃድ ሞት ይወገድ ዘንድ እንደ ሆነ ለሁሉም ግልጽ አደረገ::

✡ ✡ ✡

ሞት፥ መወገዱና በመስቀል ላይ ድል መሆኑ በሁሉም የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ዘንድ በመናቁና ሞትን ባለመፍራታቸው ይልቁንም በክርስቶስ ባለ እምነትና በመስቀል ምልክት በእግራቸው የሚረግጡት በመሆኑ ይታወቃል:: በጥንት ጊዜ ፥ጌታችን ከመምጣቱ በፊት፥ ለቅዱሳን ሳይቀር ሞት አስፈሪ ነበር:: መዝ. 54፥4፤ መዝ.88፥47::

ለሞተም ሰው ፈጽሞ እንደ ጠፋ ያህል ያለቅሱለት ነበር:: አሁን ግን ጌታችን ሞትን ድል ስላደረገው ሞት እንደ ቀድሞው አስፈሪ አይደለም፥ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በእግራቸው ይረግጡታልና፥ ክርስቶስን ከሚክዱ ቢሞቱ ይመርጣሉና ሲሞቱ አዲስ ሕይወት መኖር እንደ ሚጀምሩ እንጂ እንደ ማይጠፉ ያወቃሉና፥ በትንሣኤ የማይጠፉ መሆናቸውን ዐውቀዋልና:: የሐዋ.ሥራ.2፥24::

ለዚህም ማስረጃው ሰዎች በክርስቶስ ከማመናቸው በፊት ሞትን ይፈሩታል፤ በጽላሎቱ ያንቀጠቅጣቸ ዋል:: በክርስ ቶስ ካመኑ በኋላ ግን ሊሞቱ እስኪፈልጉ ደርሰው ንቀታቸው ይበዛል፤ በዕድሜ እንኳን ገና ያልበሰሉ ሳይቀሩ ሊሞቱ ይቸኩላሉና::

አረመኔና ጨካኝ የነበረ ሽፍታ በንጉሥ ከተሸነፈና እጅና እግሩ ከታሰረ በኋላ የሚያልፈው ሁሉ ያፌዝበታል፤ ይንጠቀዋል፤ ከዚህ በኋላ የሚፈራው አይኖርም፥ ታስሮ አልና፤ እንዲሁም ሞት በክርስቶስ በመ ስቀል ላይ ድል ከተነሣና እጅና እግሩ ከታሰረ በኋላ በክርስቶስ የሆኑ ሁሉ ሲያ ልፉና ሲያገድሙ ይረግጡታል፤ ያፌዙ በታል:: በዚህም ከጥንት ስለ እርሱ የተነገረውን:- «ሞት ሆይ÷ መውጊያህ የት አለ? ሲዖል ሆይ÷ድል መንሣትህ የት አለ?» ተብሎ የተነገረውን የተስፋ ትንቢት ፍጻሜ ያዘክሩበታል:: 1ቆሮ. 15፥55፤ ኢሳ.25፥8፤ ሆሴዕ.13÷14::

✡ ✡ ✡

ይህ እውነታ በመኖርና በመቅመስ የሚታወቅ ነው፤ የሚጠራጠሩ ሁሉ ክርስቲያኖች ይሆኑና እውነታውን ይረዳሉ:: በክርስቶስ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ይህን ሕይወት ሲያውቁትና ሲረዱት ለመሞት ይዘጋጃሉ÷ ይቸኩላሉ:: ይህ የሞትን ደካማነት በክርስቶስ የተነሣውን ድል መነሣት ለማሳየት ዓይነተኛ ምስክር አይደለምን? ሰው የተፈጥሮ ሞትንና መቃብርን ይፈራልና፥ በክርስቶስ ያመነ ግን በተፈጥሮ አስፈሪ የሆነውን ሞትን ይንቀዋል÷ ያቃልለዋል:: ብዙዎች በሰማዕትነት ሞትን ንቀው ከሞቱ ከብዙ ዘመናት በኋላ ዛሬም በየቀኑ በክርስቶስ ሞት ድል መነሣቱን የሚጠራጠር ቢኖር ብዙ አይደነቅ፥በመጠራጠርም አይኑር፥ ግልጽ የሆነው ነገር አይሰወረው:: በክርስቶስ ይመን፤ ወደ ትምህርቱ/ሕይወቱ/ ይግባ፤ የሞትን ድካም ይረዳል፤ ድል መነሣቱን ያውቃል:: ቀድሞ ተጠራጣሪዎችና ፌዘኞች የነበሩ ብዙዎች በኋላ አምነው ሰማዕታት እስኪሆኑ ደርሰው ሞትን ንቀውታልና::

✡ ✡ ✡

ሞትን ድል የነሣው ክርስቶስ÷ ሞትን የማሸነፍ ምልክት ይሆን ዘንድ በየቀኑ በደቀ መዛሙርቱ ፊት የሚያደርገው ተኣምር ድል የማድረጉን ምልክት ይገልጣል:: በተፈጥሮ ደካማና ሞትን የሚፈሩ ሰዎች ሞትንና መቃ ብርን ሳይፈሩ ወደ ሞት በደስታና በፈቃደኝነት ለሁሉም በሞት ላይ ድል ማድረግንና ሥልጣንን የሚሰጣቸውና የሚሄዱት የሞትን ኃይል ባስወገደላ ቸው በክርስቶስ ያላቸው ትምክህት መሆኑን የሚጠራጠር ጤነኛ አእምሮ ያለው ሊሆን አይችልም::

እባብ ወድቆ በእግር ሲረገጥ ቢያይ /የቀድሞ ክፋቱን የሚያውቅ/ ኃይሉን ማጣቱን ማን ይጠራጠራል? እንዲሁም ቀድሞ አስፈሪና አስጨናቂ የነበረ ሞት በክርስቲያኖች መሳለቂና መጫወቻ መሆኑን በማየት ሞት በክርስቶስ ድል መሆኑንና መሞቱን ማንም አይጠራጠር::

*ይቆየን::*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# «የስምዖን ጫማ...

/ከገጽ ፳፱ የዞረ/

4. ትርጉም

የስምዖን ጫማ ሰፊውን ፊልም ወደ አማርኛ ቋንቋ የተረጐሙትና በሌ ሎች ሥራዎች የተሳተፉት ባለሞያዎች በሙሉ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል፤ ታላቅ ትምህርት የሚሰጥ ሥራ ሠርተዋል ና:: ፊልሙ ከልጅ እስከ ዐዋቂ ትሕትናን፣ ጸሎትን፣ ለቤተ ክርስቲያን ሊኖር የሚገባ ፍቅርን እንዲሁም በእምነት ጠንክሮ መገኘትን ያስተምራል::

በትርጉሙ ከታየው ጠንካራ ጎን ብንነሣ በዋናው ፊልም መግቢያ /መጀ መሪያ/ ላይ አንድ ሰው የሚያደርገው ገለጻ ቀርቶ የፊልሙ ቅንጭብጫቢ ምስ ሎችና የጀርባ ትረካ መደረጉ ከአስልቺ ነት እንዲላቀቅ አድርጐታል::

የቋንቋ አጠቃቀሙ በአብዛኛው ግልጽና ሳቢነት ያለው በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው:: ሆኖም አንዳንድ ቦታ ላይ የቃላት ድግግሞሽ መታየቱ የትርጉሙ ደካማ ጐን ብለን ልናየው እንችላለን:: ለምሳሌ:-ቅድስት ድንግል ማርያም ለአባ አብርሃም በራእይ ተገልጻ «ወደ ገበያው በሚወስደው ትልቅ የብረት ደጃፍ በኩል ውጣ» ብላ ሁለት ጊዜ ትነግራቸዋለች:: በዋናው የፊልሙ ጽሑፍ ላይ ግን የለም::

የመጀመሪያው ፈተና ከፊታ ቸው ተደቅኖ አባ አብርሃም አባ ሳዊሮስን በጠሩበት ጊዜና ጸሎት ከጨረሱ በኋላ ስለ ጉዳዩ ተደቅኖ የሚሰማው ንግግር የአባ አብርሃም ነው:: ምስላቸው የሚታ የው ግን የአባ ሳዊሮስ ነው:: ከዚህ በተ ጨማሪ ንግግሩ ሳይጠናቀቅ የሚቆረ ጥበት ሁኔታም ይስተዋልበታል:: በመ ጨረሻው ትዕይንት ላይ አባ አብርሃም ጸልየው ጨርሰው አፋቸው መንቃነቅ ካቆመ በኋላ በአማርኛ የሚነገረው ጸሎታ ቸው ይነጠ በባል:: በእነዚህ በሁለቱ ምሳ ሌዎች የእንግሊዝኛውንና አማርኛውን ቃል ጠብቆ ያለማዋሐድ ችግር ይታያል:: ከዚህ በተ ጨማሪ የአማርኛ ትርጉም ንግግር ሲገባ የፊልሙን የማጀቢያ ድምፅ/background sound /ደምስሶ ነው:: ይህም ንግግሩ እና የፊልሙ ድምፅ ግብአት ተዋሕደውና ተናበው እንዳይሄዱ አድርጓቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ በትር ጉሙ ላይ ከላይ የተጠ ቀሱት እንከኖች በቀላሉ የሚስተካከሉ ናቸው:: በአጠቃላይ ግን በትርጉሙ ላይ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉልቶ የሚታይና በጣም የሚያስነቅፍ ስሕተት የለበትም:: ይህም የሚያሳየው በሥራው ላይ ምን ያህል እንደ ተደከመበት ነው:: እንዲህ ዓይነት ሥራዎች ይደጉ ይመንደጉ ባይ ነኝ::

የቅዱስ ስምዖን ጫማ ሰፊውን ፊልም ስንመለከተው በቀላሉና ብዙ ወጪ በማያስወጣ ሁኔታ በጣም ባልበዙ ተዋንያን የተሠራ ሆኖ ነው የምናገኘው:: ስለዚህ ከዚ ህ ፊልም የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ያሉትን ገድላትና ተአምራት ተጠቅመን ኢትዮ ጵያዊ ላህይና መዓዛ ያላቸው ብዙ ፊልሞች መሥራት እንደ ምንችል ነው:: የዚያ ሰው ይበለን:: አሜን

# ሽብር ሃይማኖት...

/ከገጽ ፲፫ የዞረ/

አንገብርም ማለታቸውና ሁለቱም መንግ ሥታት ከዘይላ ወደብ አንሥቶ ወደ ማእ ከላዊ ኢትዮጵያ የሚያመራውን ታላቅ የን ግድ መስመር ለመቆጣጠር የሚያደርጉት ሽኩቻ ነው:: Taddesse Tamrat, Church and State in Ethiopia 1270-1527. (Oxford: Clarendon Press) 1974. በተለምዶ አሕ መድ ግራኝ ተብሎ በየሚታወቀው ኢማም አሕመድ እንኳ በወረራው ወቅት /በ1531 ዓ.ም/ *«የኢትዮጵያ ክርስቲ ያኖች ጂዝያ የተሰኘውን ግብር እስከ ዝበሩ ድረስ በግድ ስለሙ አትበሏቸው፤ በክርስትና ሃይማኖታ ቸው ይኑሩ»* (Trimingham : Islam in Ethiopia ) በማለት ዐዋጅ አስነግሯል:: ከዚህ ያለፈ ታሪካችን ቅንጭብ እንደ ምን ረዳው በሃይማኖት ሽፋን በሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ቡድኖች የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ሳንታለል የቆየ አንድነታችንን ጠብቀን ማኅበራዊ ኑሮአችንን ማጠናከር እንዳለብን ነው:: የሽብር ተግባር ሁልጊዜም ቢሆን ሰለባ የሚያደርገው በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በዘር ሳይለይ ማንኛውንም ንጹሕ የሆነ ወገን ነው:: ክርስትናን እና እስልምናን ጨምሮ ማንኛውም ሃይማኖት በመሠረቱ የሚሰብከው በሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖ ርን ነው:: ሃይማኖት ከፈጣሪ ጋር የምንገ ናኝበት የዘላለምን ሕይወት የምንወር ስበት መንገድ ብቻ ሳይሆን አንድ ግለሰብ ወይም ማኅበረሰብ የዕለት ኑሮውን በተ ስተካከለ መንገድ የሚመራበት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወቱ የተ ረጋጋ ኅብረተሰብም ኾነ ግለሰብ በሥነ ልቡናም ይሁን ሆነ በአካል ደስተኛ ነው:: የራሱን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ደስተ ኛነት ይሻል:: የሃይማኖት ቤተሰቦቹንም ኾነ ሌሎችን ወገኖች ያቀርባል፤ ያከብራ ል፤ ይወዳል:: እውነተኛ የሃይማኖት ሰው የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነውን ሰውም ይሁን እንስሳ እና ዕፀዋት በከንቱ እንዲጠፉ አይፈቅድም፣ አይወድምም:: በሰው፣ በእን ስሳት፣ በዕፀዋትና በንብረት ላይ ውድ መት ለማስከተል እጃቸውን የሚያነሡ አሸ ባሪዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጣሱና እንከተለዋለን ከሚሉት እምነት ያፈነገጡ ከንቱዎች ናቸው:: ሃይማኖት ፍቅርን፣ መከባበርን፣ መረዳዳትን፣ መተዛዘንን ከሁ ሉም በላይ ደግሞ ይቅርባይነትን ይሰ ብካል፣ ያስተምራል:: እነዚህን መል ካም ዕሴቶች ወደ ጐን በመተው በፍቅር ፈንታ ጥላቻን፣ በመከባበር ፈንታ መናና ቅን፣በመረዳዳት ፈንታ መነፋፈግን፣ በመ ተዛዘን ፈንታ መጨካከንን፣ በይቅር ባይነት ፈንታ ቂምንና በቀልን የሚያራ ምዱ ግለሰቦች መውጣት በቀላሉ ለሽ ብርና የጥፋት ተልእኮዎች መሣሪያ ለመ ኾን ይዳርጋል:: ስለዚህ ማንኛውምና የየ ትኛውም እምነት ተከታይ የእምነቱን አስ ተምህሮ በመከተል ለራሱ የተስተካከለ ሕ ይወት ሊኖርና ለሌሎችም የተስተካከለ ሕ ይወት መኖር የተቻለውን ሊያደርግ ይገ ባል:: የራሱን ሃይማኖት አጥብቆ ሊከ ተልና የሌሎችንም ሃይማኖት ሊያከብር ይገባል:: ከመወያየት ይልቅ ካንተ የኔ ይሻላል ወይም ይበልጣል እያሉ ሳይፎካ ከሩና ሳይወራረዱ እርስ በእርስ ተከባብ ረው ሊኖሩ ይገባል:: ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው የሚነሡ ጽንፈኛ ቡድኖችና ግለሰቦች ለመከላከል ዋናው መንገድ ሰላ ምን፣ ፍቅርን፣ በልዩነት መቻቻ ልንና አንድነትን መስበክ፣ ማስተማርና እና በተ ለያዩ እምነት መሪዎች መካከል መከ ባበር ንና መዋደድን ማስፈን ነው::

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ እምነ ቶች ተከታዮች ዘንድ ያለውን ግንኙነት ስንመለከት እስከ አሁን ድረስ እጅግ አስደ ሳች ነው:: በተለይም በሙስሊምና ክርስ ትና እምነት ተከታዮች መካከል ያለው ማኅበራዊ ግንኙነት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ግንኙነት እስኪ መስል ድረስ እጅግ የተሳሰረ ነው:: በሐዘን ወቅት እርስ በእርስ ተረዳድቶ ማጽናናት እጅግ የተለመደ ነው:: አንድ ሰው በሞት ሲለይ «የሞተው ክርስቲያን ነው ወይም ሙስሊም ነው» በሚል ሐዘኑን ከመጋራት ራሱን የሚያገል ወይም የሚችን ቤተሰብና ቤተ ዘመድ የማያ ጽናና የለም:: በደስታ ደረጃም ብንወስድ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በልደት እና በተለያዩ ዓመት በዓላት ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን÷ ሙስሊሞችም÷ ክርስቲያኖችን የደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ይጋብዛሉ:: የክርስቲያ ንና የሙስሊም ምእምናን በመተጋገዝና በመቻቻል መኖር ኢትዮጵያችንን ከሌሎች የዓለማችን አገሮች እጅግ ልዩ ያደርጋታል:: ቀደምት አባቶቻችን ያለ ምንም እንከን በእምነት ልዩነታቸው ተከባብረው ኑረዋ ልና የእነሱን ትውፊት በመከተል እኛም ተከባብረንና ተዋደን ልንኖር ይገባል:: አሁን ባለንበት ዘመን ከአገራችን ውጭ በተለይም በሶማሊያና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚካ ሄዱ ፖለቲካዊ ክሥተቶችን ሃይማኖታዊ ገ ጽታ በመስጠት የቆየ አንድነታችንንና መከ ባበራችንን ለመመረዝ የሚጣጣሩ ወገኖችን በጋራ እና ከምንጊዜውም በበለጠ እንድነት ልንመክታቸው ይገባል:: ግለሰቦችና ቡድ ኖች የተለየ ማንነታቸውን ለማሳወቅ፣ ጭፍ ን ጥላቻቸውን /hatred/ ለመግለጥ፣ ፖለቲካ ዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማግኘትና ለማስጠበቅ ከሚጠቀሙበት በቀር የሽብር መሣሪያ የኾኑትን ጽንፈኝነትንና አክራሪነ ትን በመሠረቱ የሚደግፍና የሚያን ቀለጻ ጽስ ሃይማኖት በዓለማችን ከቶውንም የለም:: በመሆኑም *ሽብር ሃይማኖት የለ ውም::* በምንገኝበት የሣልሣይ ሺህ ዓመት ዋዜማ ላይ ሆነን ማሰብ ያለብን ለረጅም ዘመናት ጠብቀን የያዝነውን ማኅበራዊ ግን ኙነታችንን እንዴት የበለጠ ማጠንከር እን ዳለብን መሆን አለበት:: የሃይማኖታቸውን ምንነት በደንብ ልብ ሳይሉ በጭፍን ጥላቻ፣ በፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሕልመ ኝነት እምነትና ሃይማኖታቸውን ለሚያጣ ምሙ ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም ወገኖ ቻችን ፈጣሪያችን የሚያስተ ውልና ረቂቁን የሚመረምር ልቡና ይስጣቸው ዘንድ እየተ ማፀንኩ፣ አዲሱ ሚሊኒየም ለኢትዮጵ ያውያን በሙሉ የዕርቅ፣የሰላም፣ የአንድነት፣ የዕድገትና የብልጽግና እንዲሆንልን እመኛለሁ::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org

ሐመር መጽሔትን እና
ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን ያንብቡ::



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «የስምዖን ጫማ ሰፊው» ፊልም ሲቃኝ

*ፍሬ ሕይወት ግዛቸው /አ.አ./*


ፊልም ከኪነ ጥበብ ዘርፎች ጋር ሲነጻጸር የቅርብ ጊዜ ግኝት ነው። በመሆኑም ከቴአትር ጥበብ እንደ ገጸ ባሕርያት፣ ቃለ ተውኔት፣ መቼት የመሳሰሉትን አላባዎች ሲወርስ የራሱ የኾኑ እንደ መቅረጸ ምስልና ድምፅ እንዲሁም ቅንብርን የመሳሰሉ መለያዎችን ይዞ ብቅ ነው ያለው። የፊልም ጥበብን እ.ኤ.አ በ1894 የጀመረው ቶማስ ኤድሰን ነው። ነገር ግን የሚንቀሳቀሱትን ሥዕሎች ለማሳየት የሚያስችለው መሣሪያ ከፋኖስ ጋር በማዋሐድ ለተመልካች ለማሳየት የሚያስችል ምስል መወርወሪያ /ፕሮጀክ ተር/ እ.ኤ.አ በ1895 በለንደን በእንግሊዛውያኑ ሮበርት ፖልና በሁለቱ ፈረንሳ ውያን ወንድማማቾች በሊዊስና አውግስቶ ሉሜይር አማካይነት ተሠራ። እንዲህ እንዲህ እያለ ያደገው የፊልም ጥበብ ዛሬ ካለበት ደረጃ ለመድረስ በቃ።

ፊልም ከቴአትር በተለየ ኹኔታ በሚፈለገው ቦታ ላይ ለመሠራት መቻሉ፣ ብዙ ገጸ ባሕርያትን ለማሳተፍ መብቃቱ እንዲሁም እንደ ሬድዮ ከመደመጥ ባሻገር መታየት መቻሉ ዕድገቱ እንዲፋጠን ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ዘርፉ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ቢውል የሚሰጠው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለዚህም ነው በአደጉት አገሮች የሚሠሩትና መሠረታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያደረጉ ፊልሞች በየጊዜው ቁጥራቸው የጨመረው። በአገራችን ጥበቡ እንኳን ለመንፈሳዊ ፊልሞች ለዓለ ማዊ ፊልሞችም በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ አልዋለም። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትርጉም ሥራዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ተስፋ ሰጪ ጅምር ነው።

በዚህ ጽሑፍም ለመዳሰስ የሚሞከረው ከቅርብ ወራት በፊት ወደ አማርኛ ተመልሶ ገበያ ላይ የዋለውን «ቅዱስ ስምዖን ጫማ ሰፊው» የተሰኘውን ፊልም ይሆናል።

የቅዱስ ስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም መነሻ ሐሳብ የተወሰደው ከተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ነው። እስኪ በቅድሚያ ታሪኩን እንመልከት።

በግብጽ ሀገር «ስምዖን ጫማ ሰፊው» በመባል የሚጠራ ሰው ነበር። ከጫማ ስፌት ሥራው ውጭ ለደካሞች ውኃ በመቅዳት ያገለግላቸው ነበር። እርሱ በኖረበት ዘመን ከ1.5 ሚሊዮን በላይ ሕዝብን የጨረሰ ረኀብ በግብጽ ምድር ተከሥቶ ነበር። ቅዱሱ በዚህ አሠቃቂ የረኀብ ወራት ሳይቀር ያለችውን አሟጦ ለተቸገሩት እየሰጠ የበጎ አድራጎት ተግባሩን ይፈጽም ነበር። የወንጌሉን ቃል የሚፈጽመው ቃል በቃል ነበር። በመሆኑም በዝሙት ልትፈትነው የመጣችውን ሴት ከአጠገቡ የሚያሸሻት «ዐይን ብታስናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት...» /ማቴ.18፥9/ የሚለውን ቃል በደረቁ ወስዶ ዐይኑን በወስፌ አውጥቶ በመጣል ነበር።




ከረኀቡ ዘመን በኋላ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኖ የተመረጠው አባ አብርሃም ከንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ከጓደኛው ሙሳ ጋር በሃይማኖታቸው ዙሪያ እንዲከራከሩ በንጉሡ አማካይነት ጥሪ ይቀርብለታል። ጥሪውን አክብሮ አባ ሳዊሮስ የሚባል የቤተ ክርስቲያኑን ሊቅ ይዞ በመሄድ በቤተ ክርስቲያን በጠላትነት የተነሡትን ረቷቸዋል። ሆኖም ከሽንፈ ታቸው በኋላም እነ ሙሳ ቤተ ክርስቲ ያኗን ለማጥቃት ጥረታቸውን አላቆ ሙም። ይልቁኑም መጽሐፍ ቅዱስን በር ብረው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ቁጥር 20 ላይ ባለው ቃል ፈተኗቸው። «... የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደ እዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል። የሚሳናችሁ ነገር የለም...» የሚለውን ቃል መዝዘው አውጥተው ሃይማኖታቸው እውነት ከሆነ ያሳዩን ብለው ለንጉሡ ከሰሱ። ንጉሡ በቃሉ ተደሰቱ። ለጊዜያዊ ችግሩ መፍቻ ያውለው ዘንድም ተመኘ፤ ይኸውም የካይሮን ከተማ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ለማስፋት ነበር። አባ አብርሃም ደነገጠ፤ ጠላቶቹ ግን በደስታ ቦረቁ። ነገር ግን ተስፋ ሳይቆርጥ ለጾምና ለጸሎት የሚኾኑ ሦስት ቀናትን ጠይቆ ተፈቀደለት። ሕዝበ ክርስቲያኑ ለጾም በጸሎት እንዲተጋ ትእዛዝ አስተላለፈ። ስምዖን ጫማ ሰፊው ከጾምና ከጸሎቱ ባሻገር የተጣሉትን እያስታረቀ፣ ኃጢአተኞችን ንስሐ እንዲገቡ እየመከረ ይተጋ ነበር። በመጨረሻም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአባ አብርሃም በራእይ ተገልጻ የእግዚአብሔር ተኣምር በስምዖን ጫማ ሰፊው እጅ እንደ ሚፈጸም ነገረችው። እንዳለ ችውም ሆነ። በአገሪቱ ያሉ ክርስቲያ ኖችም ከተነባበረባቸው ፈተና ወጥተው በንጉሡ ዘንድ፦«እምነታችሁና ሃይማኖ ታችሁ በእርግጥ እውነተኛ ነው» እስከ መባል ደርሰው ከፍ ከፍ አሉ። ለፈተና ያጋለጧቸው እነያዕቆብ ግን የውርደት ሸማ ለበሱ።

የቅዱስ ስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም መልእክት «እምነት ካለ ሁሉን ማድረግ ይቻላል» የሚል ነው ። እስቲ አጠቃላይ ፊልሙን ከጽሑፍ ዝግጅቱ፣ ከቀረጻውና ከቅንብሩ አንጻር እንመልከተው፤ በመጨረሻም የትርጉም ሥራውን።

### 1. ከጸሑፍ ዝግጅት አንጻር

የቅዱስ ስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም ጽሑፍ ከአምስት አላባውያን የተገነባ ነው። እነርሱም መቼት፣ ባሕርይ፣ ቃለ ተውኔት፣ ሤራ፣ ጭብጥ ናቸው። ሆኖም በዚህ ጽሑፍ የምንመ ለከተው የአቀንቃኝና የተቀናቃኝ /የፀረ አቀንቃኝ/ ገጸ ባሕርያትን ሚና ይሆ ናል።

በፊልሙ ውስጥ እኩል ደረጃ /ተመጣጣኝ/ ኃይል ያላቸው አቀንቃኝና ፀረ አቀንቃኝ ገጸ ባሕርያትን እናገኛለን። አባ አብርሃምና ስምዖን ጫማ ሰፊው በአቀንቃኝ ገጸ ባሕርያት ጐራ እንዲሁም የንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ጓደኛው ሙሳ በፀረ አቀንቃኝ ጎራ በዋ ነኝነት ተሰልፈው እስከ ፊልሙ ፍጻሜ ይፋለማሉ። እነዚህን ገጸ ባሕርያት የም ንመለከታቸው ገጸ ባሕርያት ከሚሣሉባ ቸው አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡና ዊና ሥነ ምግባራዊ ጠገጎች አንጻር ብቻ ይሆናል። ሁለቱ የአሣሣል ደረ ጃዎች ኀሊናዊ፣ ጉዳዮች የምንላቸው የገጸ ባሕርያቱ ተስፋዎች፣ ስሜቶች ፣ ምኞቶች፣ የሥነ ምግባር ባለቤት በመሆንና ባለመሆን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። እነዚህም ኀሊናዊ ጉዳዮች ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ በምዕራፍ አም ስት ቁጥር 19 ላይ የመንፈስ ፍሬዎችና የሥጋ ሥራዎች በማለት ያስቀምጣቸው ናቸው።

አባ አብርሃም ከስሜታዊነት የራቀ አስተዋይ አባት ነው። ምንም ነገር ቸኩሎ ከማድረግ ይልቅ በጸሎት እግዚአብሔርን ሲጠይቅ ነው ከፊልሙ መነሻ እስከ መጨረሻ ድረስ የሚታየው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተቀመጠውን በእምነት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ተራራን ማፍለስ በተግባር እንዲያሳይ አባ አብርሃም ሲጠየቅ ይደነግጣል:: ነገር ግን ቸኩሎ «ይቻለኛል ወይም አይቻለኝም» አላለም:: ይልቁኑም በጽኑ እምነት ተነሥቶ እግዚአብሔርን በጾም በጸሎት ሊጠይቅ የሦስት ቀን ጊዜ ይጠይቃሉ በዚህም ስምዖን ጫማ ሰፊውንም ሆነ ክር ስቲያኑን አስተባብሮ የተጠየቀውን በመፈጸም ጠላቶቹን ድል ሲያደርግ እናያለን::

ከአባ አብርሃም በተቃራኒው ጐራ የተቀመጡት የንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ጓደኛው ሙሳ ስሜታዊ ናቸው፤ እምነት የላቸውም፤ ለዚህም ምስክሩ በሃይማኖት ዙሪያ ክርክር እንዲጀመር ለንጉሡ የነገሩት እነርሱ ሲሆኑ ከስሜታ ዊነት ውጭ የመከራከሪያ ነጥብ አልነበራቸውም:: በዚህም ክርክር ከጅምሩ በቀላሉ ሲረቱ እንመለከታለን:: በሁ ለተኛው ክርክርም የክርስቲያኖችን መጽሐፍ ቅዱስ በርብረን አገኘን ያሉት ፈተና በደስታ ያስከራቸዋል:: ሆኖም በክርስ ቲያኖቹ ጠንካራ እምነት ፋርሽ ሲሆን ከመዋረድና አንገታቸውን ከመድፋት የዘለለ ውጤት አላስገኘላቸውም::

አባ አብርሃምም ኾኑ ስምዖን ጫማ ሰፊው ትሑት ናቸው:: የእነሱ ክብር ከሚገለጽ ይልቅ የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጽ ነው የሚፈልጉት:: የአባ አብርሃምን ትሕትና የምንመለከተው የሊቀ ጳጳስነት ሥልጣን ሲሰጠው ከሚናገ ረው ንግግር ነው:: እንባው እየፈሰሰ፦ «ይህን ከባድ ሐላፊነት መሸከም የምችል አይመስለኝም:: እኔ አንድ ምስኪን ደካማ ሰው ነኝ::» ሲል ይደመጣል:: ስምዖን ጫማ ሰፊውም በሞካታም ተራራ የሚፈጸመው ተአምር በእርሱ አማካይነት እንደ ሚፈጸም በአባ አብርሃም ሲነገረው ለትልቅ ሥራ በመጠራቱ አልተኩራራም:: ይልቁኑም:- «እኔ አንድ ምስኪን ሰው ነኝ፤ እኔ አንድ ከንቱ የማልረባ ሰው ነኝ» ሲል ነው የሚደመጠው:: ተአምሩ ከመፈጸሙ በፊት ሁሉም ምስጢር ይሁን እያለ አባ አብርሃምን ቃል ሲያስ ገባ ነው የሚታየው:: በዚህም የሰይጣን መሣሪያ ከሆነው ውዳሴ ከንቱ በእጅጉ ሲርቅ ይስተዋላል::

የንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ጓደኛው ሙሳ ትዕቢተኞች ናቸው:: በምቀኝነት ተነሥተው በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ ፈተናን ሲያመጡ መሠረታቸው ግን አለብኝነት ነው:: ይህንንም ከሚናገሩት ንግግር ማወቅ ይቻላል::ለዚህም የሙሳን ንግግር እንጥቀስ፦ «በደካማ ጐናቸው ገብቼ በአናታቸው ላይ ቤተ ክርስቲያናቸውን እስከ አፈርስ ድረስ ¨...»እያለ ደጋግሞ ከሚናገራቸውና ሌሎች ተመሳሳይ ንግግሮቹ የምንረዳው ከትዕቢት ውጭ አንድም የትሕትና ንግግር ከአንደበታቸው እንደ ማይደመጥ ነው::

በመጨረሻም አባ አብርሃምና ስምዖን ጫማ ሰፊው ለቤተ ክርስቲያናቸው ዕድገትና ክብር ሲጥሩ በተቃራኒው የንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ጓደ ኛቸው ሙሳ በንጉሡ ዘንድ ያላቸውን ክብር እስከ መጨረሻው ለማቆየት በየ ፊናቸው ሲፈጨረጨሩ ይታያል:: በመ ጨረሻ ግን እነ አባ አብርሃም ሲሞገሱ እነ ያዕቆብ ሲዋረዱ የፊልሙ ፍጻሜ ይሆ ናል:: በዚህም የምንረዳው ቅዱስ ጳውሎስ የዘረዘራቸው የመንፈስ ፍሬዎች በሥጋ ሥራ ላይ የበላይነትን መጎናጸፋቸው ነው::

## 2. ቀረጻ

በስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም የተለያዩ የቀረጻ ቴክኒክ ጥበቦችን በመጠቀም መልእክት ተላልፏል:: ከቴክኒኮቹም መካከል አንዱና ዋነኛው የቅርብ ርእይ /close up/ ነው:: የቀረጻው ቴክኒክ የተዋንያንን የውስጥ ስሜት ማለትም ጭንቀትን፣ ድንጋጤን፣ ሐዘኔታንና ፍቅርን በቅርበት ለማሳየት ይጠቅማል:: ስምዖን ጫማ ሰፊው ተመሥጦ ሲጸልይ፣ አባ አብርሃም ፓትርያርክ ኾኖ ሲመረጥና በድንጋጤ እንባው ሲፈስ፣ ስምዖን ጫማ ሰፊው ዐይኑን በወስፌ ሲያወጣ፣ የንግድ ሚኒስትሩ ያዕቆብና ጓደኛቸው ሙሳ በሁለቱም ክርክሮች ሲረቱና ሲያፍሩ እና ሌሎችም ብዙ ድርጊቶች በቅርብ ርእይ ተቀርጸው በመቅረባቸው የገጸ ባሕርያቱን ውስጣዊ ስሜት በፊታቸው ላይ ለመመልከት አስችሎናል:: ሆኖም የሞካታም ተራራ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ በቦታው የነበሩትን ዋነኛ ገጸ ባሕርያትንና የሌሎችንም ስሜት በቅርብ ርእይ ተመልክተናል:: ይሁንና የዋና ገጸ ባሕርይው የስምዖን ጫማ ሰፊ ውን ስሜት ግን በቅርብ እንድናይ አል ተደረገም:: ይህም የፊልሙ ደካማ ጐን ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል:: ሌላው በትዕ ይንቱ መጀመሪያ ላይ በረኀብ የሞቱ ሰዎች በቅርብ ርእይ የቀረጻ ቴክኒክ ቀርበው እናገኛቸዋለን:: በመሆኑም በጣም በመቅረባቸውና በሚገባ በመታየታቸው በረኀብ የሞቱ ሰዎች ካለመምሰላቸውም ባሻገር ጠግበው ለዕረፍት የተኙ አስ መስሏቸዋል:: ስለዚህ በቅርብ ርእይ ከማቅረብ ይልቅ በመካከለኛ ርእይ /Medium shot / ወይም በሩቅ ርእይ/Long shot/ መቅረብ ነበረባቸው::

በሌላ በኩል በስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም ላይ ከቀረጻ ቴክኒኮች መካከል የእይታ መስመር /Point of view /በሚገባ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን:: ስምዖን ጫማ ሰፊው በሚሠራበት ቦታ አንዲት ሴት መጥታ በፊቱ ስትቆም በርሱ የእይታ መስመር /Point of view / ተጠቅመን ከታች እስከ ላይ እንመለከታታለን:: ተከለ ቁመናዋና ቁንጅናዋ አማላይ ነው:: ይህን አድንቀን ሳንጨርስ እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክ፣ ሥራውን ለማድነቅና ለማመስገን የሚተጋው ጻድቅ ሰው፦ «ዐይንህ ብታስትህ፣ ከአንተ አውጥተህ ጣላት...» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በአእምሮው ውስጥ ሲያን ቃጭልና በወስፌ ሲያወጣው እንመለከታለን:: በዚህም በእርሱ የእይታ መስመር ውስጥ ያየናት ሴት ወደ ሥራ ቦታው ብቅ ያለችው እርሱን በዝሙት ለመጣል እንደ ነበር ይገለጽልናል::

በስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም ላይ በሰፊው ሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው *ተምሳሌትን* ነው:: ተምሳሌት የተዋንያ ንን መውደቅና መነሣት፣ ለታሪኩ ፍንጭ እና ለፊልሙ ድባብ በመስጠት ላይ ያተኩራል:: በፊልሙ መጀመ ሪያ ላይ የሚታዩት ቅጠላቸው የረገፉት ዛፎችና የተሰነጣጠቀው መሬት ጊዜው የሰቆቃና የረኀብ መሆኑን በግልጽ ያሳያል:: በሌላ ትዕይንት ደግሞ ወንዞች ሲፈሱ፣ አበቦች ሲፈነዱና ሰዎች በደስታ ሲተቃቀፉ ሲታይ ያለምንም ንግግር የረኀቡ ዘመን ማለፉን ይነግ ረናል:: ይኹንና በፊልሙ ቴክኒኩ በትክክለኛ ቦታ ጥቅም ላይ የማይውል ልበት ቦታም አለ:: ይኸውም በረኀቡ ዘመን በየቦታው የወደቁት አስከሬኖችና ስለ ረኀቡ የሚያወሩት ሰዎች ያሉበት ስፍራ ለምለም ሣር ያለበት ሆኖ ማግኘታችን ነው:: በፊልም ቀረጻው ውስጥ የምናገኘው ቴክኒክ ንግርት /Fore shadowing/ ነው:: ቴክኒኩ ወደፊት የሚ መጣውን ነገር የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ አስቀድሞ ፍንጭ መስጠት ነው:: ለምሳሌ፦ እርሷም ሆነች ባሏ በስርቆት ላይ ተሠማርታ የምናገኛት የጋብሬላ እናት የሰረቀችውንና ያጭበረበረች ውን ስትቆጥር ከአንድም ሁለት ሦስቴ በር ተንኳኩቶ ድንግጥ ብላ ሂዳ ስትከፍት እናያለን:: ይህ ድርጊቷ በመጨረሻ ከኃጢአቷ የመላቀቂ ንግርት መሆኑ የሚገለጽልን በሞካታም ተራራ ተአ ምሩን አይታ በመደናገጥ ስለ ሠራ ችው ሥራ ሁሉ ስትጸጸት ስንመለከት ነው:: ከዚሁ ከንግርት ሳንወጣ አባ አብርሃም ስምዖን ጫማ ሰፊውን ቅድ ስት ድንግል ማርያም ወደ አመለከተ ችው ቦታ ሊፈልጉት ሲሄዱ ውኃ የሞላበት ዕቃ ይዞ ለምለም ሣር ያለበት ሥፍራ ያገኙታል:: ይኸም ሐሳባቸው እንደሚሟላ፣ ወደፊት ብሩህ ተስፋ እንዳለ የሚጠቁም ንግርት ሆኖ እናገኘዋለን::

## 3. የምስልና ድምፅ ቅንብር


የምስልና ድምፅ ቅንብር የተለያዩ የቀረጻና የማእዘናት የቀረጻ ቴክኒኮችን በተገቢው ቦታ ሳይደጋገሙ መጠቀም እንዲሁም የቆይታ ጊዜ ያቸውን መጥኖ ማቀናበር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ አላስፈላጊ ቀረጻዎችን ማስወ ገድ ነው:: በስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም ውስጥ ቅንብሩ የተዋጣለት ሆኖ ተሠር ቷል:: ይሁን እንጂ የጋብሬላ እናት /ሌባዋ ሴት/ ከባሊቢቷ ጋር ስታወራ የሚታዩት፣ የሦስት ቀን ሕፃናት አሊጋ ዎች ከታሪኩ ጋር የማይሄድ ነው:: ብዙ ልጆች አሏቸው እንዳይባል የምናው ቀው አንድ ልጅ ነው:: ስለዚህ ተቆርጦ መውጣት ነበረበት::

ተመልካች የቪድዮ ፊልምን በሚያይበት ጊዜ ከትዕይንት ትዕይንት የሚኖር የሽግግር ቴክኒክ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል:: በስምዖን ጫማ ሰፊው ፊልም ውስጥ ከትዕይንት ትዕይንት ያሉት መሸጋገሪያዎች የተዋጣላቸው ናቸው:: ለምሳሌ፦ አባ አብርሃም እምነታቸውን በተግባር እንዲያሳዩ ከንጉሡ ሲጠየቁ መስቀላቸውን ከፍ አድርገው የሦስት ቀን ጊዜ ይጠይቃሉ:: መስቀላቸው በቅርብ ርእይ /Close up/ ይመጣና ወደሚቀጥለው ትዕይንት ይሸጋገራል:: ከዚያም ለደቀ መዛሙራቸው መስቀላቸውን ከፍ እንዳደረጉ በግብፅ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሦስት ቀናት እንዲጸሙና እንዲጸልዩ ትእዛዝ እንዲያስተላልፍ ይነግሩታል:: ዳግመኛም ያው መስቀላቸውን በቅርብ ርእይ መጥቶ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ጉዳዩ ወደ ሚነግሩበት ይሸጋገራል:: በመስቀሉ መቅረብ ብቻ ከአንዱ ትዕይንት ወደሌላው መሸጋገሪያ ድልድይ ኾኖ ሲውል እንመለከታለን:: ይህንን የመሳሰሉ ብዙ የመሸጋገሪያ ቴክኒኮች በፊልሙ ውስጥ እናገኛለን::

/ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል/



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org




# የዳ ቪንቺ ኮድ» ብዙ ሐሰቶች በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ሲመዘን

/ሉሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ/

*በዘመናችን እየወጡ ካሉ ፀረ ክር ስትና ጽሑፎች መካከል "የዳ ቪንቺ ኮድ" በሚል ርእስ በዳን ብራውን የተዘጋጀው ልብ ወለድ መጽሐፍ አንዱ ነው። «የዳቪንቺ ኮድ»ን÷ተረፈ አይሁድ በሚል ጊብሰን በ2004 እ.ኤ.አ. ለተሠራው "ዘ ፓ ሽን ኦፍ ክራይስት" ፊልም ክርስትናን ለመበቀል እንደ ምላሽ ያዘጋጁት መሆኑን ብዙዎች ያምናሉ። ይኽንንም የክሕደት መጽሐፍ በተመለከተ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤ ል በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ረዳት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ሐምሌ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ለገዳማትና አድባራት አስተ ዳዳሪዎች እንዲሁም ለሀገረ ስብከቱ ሠራተኞችና ሰባክያነ ወንጌል ባስተላለፉት መልክእት የተሰማኝ መንፈሳዊ ሑራት ከፍ ያለ ነበር። እኔም ስለ መጽሐፉ ፀ ረ ክርስትና ይዘት ምላሽ እንደ ሚያስፈ ልገው በማመን ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥቂቱ ከሰበሰብኳቸው ያገኘሁትን ወደ አማርኛ መልሼ አቅርቤአለሁ።*

የዳቪንቺ ኮድ (The Da Vinci Code) ዳን ብራውን በተባለ እንግሊዛዊ ጸሐፊ የተ ጻፈ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው። ልብ ወለድ መጽሐፉም በተመሳሳይ ርእስ በፊልም ተዘጋጅቷል። ልብ ወለዱ በግድያ ወንጀል ዙሪያ በማጠንጠን ይጀምራል። ወንጀለኛውን ለማግኘት በሚደረገው ምር መራ ውስጥ ፀረ ክርስትና መልእክቱንና ክሕደቱን እናገኘዋለን። በልብ ወለዱ ውስጥ የምናገኛቸው ምስጢራውያን ቡድኖችም እርስ በርሱ የሚጋጭ ፍላጐት ያላቸው ናቸው። ደራሲው ለምስጢራ ውያኑ ቡድኖች የምሴተ ኀሙስን ጽዋ (Holy Grail) እንደ መረጃ አድርጎ ለማቅ ረብ ይሞክራል።

በዚህ ልብ ወለድ መጽሐፍ ዳን ብራውን ሐሰቱን እውነት፤ ልብ ወለዱን ትክክለኛ አስመስሎ አቅርቧል። ጸሐፊው በፈጠራቸው ገጸ ባሕርያትም ሃይማኖ ታችንን እና የቅዱስ መጽሐፍን ዐበይት ትምህርቶች ይቃወማል። ተቃውሞውም መሠረተ ሃይማኖታችንን እና የቅዱስ መጽሐፍን ዐበይት ትምህርቶች ይቃወ ማል። በቅዱሳት መጻሕፍት አማናዊነት፣ በጌታችን የባሕርይ አምላክነት /መለኮታዊ ኃይል/፣በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ በአ ጠቃላይ በምስጢረ ሥጋዌ /ተዋሕዶ/ እና በሴቶች ጾታዊ መብትና በተራክቦ ጉዳዮች ላይ ባለው የተሳሳተ አመለካከቱ ላይ ያተኮረ ሲሆን በመጽሐፉ ሁሉ ልዩ ልዩ የሥጋ ፈቃዳትን በነጻነት መፈጸምን /ልቅነት/ን ያበረታታል።

ዳን ብራውን ክርስቲያን መሆን አለመሆኑን በተጠየቀበት ክፍል የሚከተ ለውን መልስ ሰጥቷል። *"እስከ አሁን በተ ለመደው መንገድ ወይም ስሜት ከተወሰደ ክርስቲያን ላልሆን እችላለሁ። ነገር ግን ራሴን የበርካታ እምነቶች ተማሪ አድርጌ እቆጥራለሁ። ብዙ በተማርኩ ቁጥር በርካታ ጥያቄዎች ይኖሩኛል። መንፈሳዊ ጥያቄ በየጊዜው የሚያድግ የዕድሜ ልክ ጥያቄ ነው።"* ብሏል። የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 341።

የዳቪንቺ ኮድ (The Da Vinci Code) በርካታ ታሪካዊ እውነታዎች የጐደሉት ከመሆኑ በተጨማሪ ከመሠረታዊ ትምህ ርተ ሃይማኖታችን የራቀ ልብ ወለድ ሐሳቦች ስብስብ ነው። ይሁን እንጂ ጸሐፊው ሥራውን ፍጹም ልብ ወለድ አድርጐ አይመለከተውም፤ ለተጠየቀ ውም ጥያቄ በሰጠው መልስ የገለጸው፦ *"በመጽሐፉ የተጻፉት በሙሉ ፍጹም እውነት ናቸው"* በማለት ነው። በእግዚ አብሔር ረዳትነት ለነዚህ የደራሲው ተቃ ውሞዎች ከልብ ወለድ ' መጽሐፉ በመነሣት ምላሽ እንሰጣለን። ዮሐ. 8÷31-32 ፤1ኛ ጴጥ.3÷15። ልዑል እግዚአብሔር ጥረታችንን ለበረከት የድርግልን።

## የዳቪንቺ ኮድ ምንድን ነው?

«የዳቪንቺ ኮድ» በፈረንሳይና በታላቋ ብሪታንያ ያለውን ሁኔታ መሠ ረት አድርጐ የተጻፈ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው።መጽሐፉ ግራ በሚያጋቡ እንቆቅልሾች የተሞላ፣ ወደ ጥርጥርና ክሕደት የሚመራ መልእክት ያለው ነው። ይህ መጽሐፍ እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ወደ 60 ሚልዮን ያህል ቅጂ ተሸጧል። ሰዎች ድብቅ ነው ብለው ያሰቡትን ነገር የመመርመር ጥልቅ ፍላጐት ስላላቸው ብዙዎች አንብበውታል። ገድለው የተሰወሩ፣ ሤራ ወይም አድማ የሚያደርጉ ሰዎች ... ቁልፍ ናቸው ተብለው የሚቀርቡ ጉዳ ዮች የብዙዎችን ትኩረት ለምእተ ዓመ ታት ሲስቡ ኖረዋል።

እስከ አሁን በምናነበው መጽ ሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ "ክሕደት" ወይም "ሐሰት" ሆኖ ከእኛ የተሰወረ ምን አለና? በዳን ብራውን ልብ ወለድ መጽሐፍ ውስጥ የምናነበው በጥቂት እውነታ ውስጥ የታጨቀውን ግራ አስተሳሰብ ነው። ጸሐፊው የጽሑፉን አጠቃላይ ይዘት በሙሉ እንደ ልብ ወለድ አይ ወስደውም። የመጽሐፉም መልእክት ልብ ወለድ ጉዳዮችን ያዘለ ተደርጐ ቢታሰብ ብዙዎችን አይስብም ነበር።

በሰኔ 1997 ዓ.ም (June, 2005) የታተመው 'Discovery' መጽሔ ት የዳቪ ንቺ ኮድን አስመልክቶ፦ "የተ ነገረንን ሁሉ ማመን አይገባንም፤ መጽ ሐፉ በርካታ ጥያቄዎችን ቢያነሣም በበ ርካታ ሐሰቶች የተሞላ ነው..." ብሏል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ ለዓለም በግልጥ ተናገርሁ፤... በስ ውርም ምንም አልተናገርሁም። ስለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ ÷ እነዚህ እኔ የተናገርሁ ትን ያውቃሉ አለው።" ዮሐ. 18÷20-21። እኛም እርሱን ከዋለበት እየዋሉ፣ካደረበት እያደሩ፣የቃሉን ትም ህርት የሰሙትን የእጁን ተአምራት ያዩትን ቅዱሳን ሐዋርያትን ማቴዎስን፣ ማርቆስን፣ ሉቃስን፣ ጴጥሮስን፣ ዮሐን ስን... ብንሰማቸው እውነት እንዳልተ ደበቀ እንረዳለን። በቅዱስ መጽሐፍ እውነቱ ሁሉ ተገልጿል። ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍን ከነትርጓሜው እናንብበው።

ቅዱሳት መጻሕፍት "በመጨ ረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት ዘባቾች በመዘበት እንደ ሚመጡ ይህን በራሳችሁ ዕወቁ።" /2ኛ ጴጥ 3÷ 16/ "ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ:: እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ::: እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳን ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ::: ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል:: በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል::" /2ኛ ጴጥ 2÷1-3/ በማለት የሚያሳስቡን አሁንም በዚህ ዘመን ሰይጣን የሃይማኖታችን መሠረት በሆነው በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚወረወር ፍላጻውን እየሳለ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ሰይጣን ሥጋዊ ሐሤትን፣ ግራ መጋባትንና ጥርጣሬን በአማንያን ልቡና ለማሳደር «የዳቪንቺ ኮድ»ን ዓይነተኛ መሣሪያው አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል::

የዳቪንቺ ኮድ በገንዘብም ሲተመን ወደ 250 ሚሊዮን ዶላር ያህል ተሸጧል:: ፊልሙም ከሚያዝያ 11 ቀን 1998 ዓ.ም. (May 19, 2006) ጀምሮ ተሠራጭቷል:: ዳን ብራውን ልብ ወለድ ፈጠራውን ወይም ኑፋቄውን እውነት በማስመሰል ክብር ይግባውና ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና የክርስትና ሃይማኖታችን ታሪክ የራሱን ሐተታ ያቀርባል:: ልብ ወለዱ በይዘቱ የሚከተሉትን ሐሳቦች ያቀፋል::

*"ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ አይደለም:: እውነተኛ አገልግሎቱና ማንነቱ እንኳን በግልጽ ያልታወቀ ተራ ሰው ነበር::"*

*"ጌታችንና መግደላዊት ማርያም ተጋብተው ልጅ ወልደዋል:: ወደ ፈረንሳይ ሸሽተውም እስካሁን ድረስ ዘራቸው በዚያ ይገኛል:: "*

*"ጌታችን መግደላዊት ማርያም የቤተ ክርስቲያን መሪ እንድትሆን ሽቶ ነበር:: የርሱም ትምህርት ጴጥሮስን በመሰሉ ሰዎች ተሻሽሎአል:: "*

*"ቤተ ክርስቲያን እና ክርስቲያኖች ይኽን እውነት ለ2000 ዓመት ደብቀው ኖረዋል:: "*

*"ጌታችን ወደ እግዚአብሔርነት የተለወጠው ፓትርያርካዊ ሂደቱን ለመጠበቅ ነው::"*

*"ብዙ ሚሊዮኖች ስለ ክርስትና ለዘመናት የተሳሳተ መረጃ ሲሰጣቸው ኖረዋል:: በመጨረሻም እንደዚህ የተሰወሩ ምስጢራቱን ያወቁ ሰር አይዛክ ኒውተን እና ሌዎናርዶ ዳቪን ቺ 'Priory of Sion' በሚባል ቡድን እየታቀፉ አልፈዋል:: ከእነርሱም ይኽን የእውነት ፍንጭ ሌዎ ናርዶ ዳ ቪንቺ በምሴተ ኀሙስ ሥዕሉ ውስጥ ገልጧል:: "*

*"የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ማንነትና ምስጢሩን የተረዱ ከ1099 ዓ.ም. ጀምሮ 'Priory of Sion' በመባል ይታወቁ ነበር:: ሶር አይዛክ ኒውተን ሌዎናርዶ ዳ ቪንቺ የዚህ ድርጅት ቀዳሚ ተጠቃሽ አባላት ናቸው::"*

## መጽሐፉ ለምን የዳቪንቺ ኮድ ተባለ?

ዋነኛው ምክንያት ሌዎናርዶ ዳቪንቺ በዚህ ልብ ወለድ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እውነት የሚያውቅ ቀንደኛ ገላጭ ሆኖ መቀመጡ ነው:: "የተለያዩ ድብቅ መልእክቶችን (Codes) እንደ መግለጫ አድርጎ አስቀምጧል:: ከነዚህም ድብቅ መልእክቶች በምሴተ ኀሙስ ሥዕሉ ውስጥ ያካተተው አንዱ ነው" ይላል:: በሥዕሉ ከጌታችን ቀጥሎ በስተቀኝ በኩል የምትገኘው "መግደላዊት ማርያም ናት:: ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ የእርሱን ትምህርት እና በወቅቱ የተናገረውን ሁሉ በአግባቡ የተረዳች እርስዋ ናት":: ልብ ወለዱ «ይኽን ምስጢር የሚገልጽ ነው» ሲል "Code" ብሎታል::

## ጸሐፊው

በኤክስተር ኒው ሃምፕሻየር ተወልዶ ያደገ፣ ወላጆቹ ከወለዷቸው ሦስት ልጆች ታላቁ ነው::: በአሁኑ ወቅት የ 42 ዓመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ ነው::: ወላጅ እናቱ ሙዚቀኛ ነበረች:: አባቱ የሒሳብ መምህር ነበር::

በ'Amherst Glee Club' ውስጥ የዘፈን ግጥም ጸሐፊና ዘፋኝ ሆኖ ሠርቷል:: 'Synth Animals' የሚባል የሕፃናት ፊልምና በተጨማሪም "Happy Frogs"፣ "Suzuki Elephants" የሚባሉ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ውስጥም ተሳታፊ ነበር:: በ1991 በሆሊውድ የዘፈን ግጥም ጸሐፊ፣ አቀንቃኝ (ዘፋኝ)፣ እና ፒያኖ ተጫዋች ሆኖ ተቀጥሯል:: በስፓኒሽና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ጥናት ትምህርቱን ያጠናቀቀ ሲሆን የስፓኒሽ ቋንቋ መምህር ሆኖ ሠርቷል:: ቀድሞም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር ነበር:: «Digital Fortress» «Deception Point » እና «Angles and Demons » የሚባሉ መጻሕፍትንም ጽፏል:: ክርስቲያን ስለመሆኑ በተጠየቀበትም ክፍል ሲመልስ:- ሦስት ሰዎችን ስለ ክርስትና ብትጠይቃቸው

- አንደኛው:- "መጠመቅ በቂ ነው" ይልሃል::
- ሁለተኛው:- "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እውነት መቀበል በቂ ነው" ይልሃል::
- ሦስተኛው:- "በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ወይም እርሱን መቀበል በቂ ነው" ብሎ በተናጠል ያስረዳሃል::

"ሁላችንም የሕይወትን እንድምታ ወይም ትርጉም ለማወቅ እንጣጣራለን፤ራሴን የብዙ እምነቶች ተማሪ አድርጌ አስባለሁ ወይም እወስዳለሁ:: ብዙ በተማርኩ ቁጥር በርካታ ጥያቄዎች ይኖሩኛል:: ለእኔ መንፈሳዊ ጥያቄ የዕድሜ ልክ ጉዳይ ነው::: ገና ነኝ...::" ብሏል::

### መጽሐፉ ለምን ይኽን ያህል ታዋቂነትን አገኘ?

1. ራሱን የ"ሴቶች መብት" ተከራካሪ አድርጎ ስለ ሚያቀርብ፤
2. የጾታን ፈቃድ ልቅ በሆነ መንገድ መፈጸምን ስለ ሚያደፋፍር፤
3. አለ ማመንንና አለመታመንን ወይም ክሕደትን ስለሚያበረታታ፤
4. "መዳን በዕውቀት ነው" የሚል የሰብአ ፈጠራዎችን (Gnostics) ፍልስፍና ስለሚያስተዋውቅ፤
5. የ "የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ" ይህም ማለት "ኢየሱስ ታላቁ መምህር ነው:: ከብዙዎቹም አንዱ ነው::" የሚሉትን ስለሚደግፍ ነው::

## ኦርቶዶክሳውያን ይኽ መጽሐፍ ለምን ትኩረታችን ሆነ?

1. ጸሐፊው በእውነት ላይ ተመርኩዞ ይኽን ሥራ ለመሥራት ረጅም መንገድ እንደ ተጓዘ በመግለጽ ተጽዕኖ ለመፍጠር ይሞክራል:: ስለ መጽሐፉም "በዚህ መጽሐፍ የተገለጹ የጥበብ ውጤቶች፣ መረጃዎችንና ምስጢራትን ሁሉ እውነት ናቸው" ስለሚል እና በአንጻሩ እውነት የሆነውን ማስረዳት ስለሚገባን፤

2.በመጽሐፉ ገጽ 235 እንደ ተገለጸው በአጠቃላይ:- "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አባቶቻችን የነገሩን ሁሉ ስሕተት ነው" ስለሚል፤

በአጠቃላይ በመጽሐፉ ልብ ወለድ ቢሆንም ይዘቱ የክርስትና እምነታችንን መሠረታዊ ትምህርት ስለሚቃወም በዚህ መነሻነት ለክሕደት ሐሳቦቹ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል ብዬ የአምናለሁ::

### 1. ቅዱስ መጽሐፍ

1.1 የቅዱስ መጽሐፍን ቅድስና እና ተቀባይነት የማይቀበለው ዳን ብራውን ስለ ቅዱስ መጽሐፍ የራሱን ልብ ወለድ ድርሰት ጽፏል:: የቅዱስ መጽሐፍን እውነት በመተው ከእውነት የሚለዩትን ሐሰተኛ ጽሑፎች ተመርኩዟል:: *"ቅዱስ መጽሐፍን ለአንባቢው በቀላል መንገድ ለማቅረብ ከመጀ መሪያ ጀምረን መመዘን ይኖርብናል"* የሚል እሳቤ አለው::

*"ቅዱስ መጽሐፍ በፋክስ ከሰማይ አልተላከልንም፤ ከሰዎች የተገኘ ጽሑፍ ነው እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም:: በተኣምራትም ከደመና አልወረደም፤ በቀላሉ የዘመናት የታሪክ መድበል ነው::: ብዙ ጊዜ ተተርጉሟል፣ ጭማሪ ተደርጎበታል፣ ተሻሽሏል:: በታሪክም የመጽሐፉ ትክክለኛ ቅጂ ተጠብቆ አልቆየንም::"* የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 231::

ዳን ብራውን ከሚለው በተቃራኒ ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መሪነት የተጻፉ ቃላት የሚገኙበት አምላካዊ መጽሐፍ ነው::: ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር የተገለጸ፥ በመንፈሱም መሪነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው::: ለዚህም ደግሞ ብዙ ማስረጃዎች አሉ::: በመንፈሳዊ ሕይወት ለመታነጽ፣ ልብንም ወደ በጎው ለማቅናት፣ ሰውንም በጽድቅ ለመምራት ላለው ሥራ ሁሉ መገኛው አምላካችን ነው::: ከርሱ የተገኘውን የቅዱስ መጽሐፍን ትምህርት የተከታተሉት ለቅድስና በቅተው ቀዋሚ÷ ተንቀሳቃሽ ቅዱሳት መጻሕፍት ሆነዋል:: ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛጢሞ. 3÷16-17 ላይ:- "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ላሰው ምክር ደግሞ ይጠቅማል::" እንዳለ:: በአጠቃላይ ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር የተገለጸ ከስሕተትም ሁሉ በእግዚአብሔር የተጠበቀ እና በእርሱ ገላጭነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው:: ቅዱስ ጴጥሮስ:- "ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር ተልከው ... በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጻፉት... " ብሏል:: እዚህ ላይ ሐዋርያው "በእግዚ አብሔር ተልከው" ሲል የእግዚብሔርን መሪነት፣ "ቅዱሳን ሰዎች... ተናገሩ" ሲል ደግሞ የሰውን ድርሻ ይናገራል:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በተመለከተ ሰዎች በመጻፍ ብቻ ሳይሆን መጻሕፍትንም በመሰብሰብ ተሳትፎ አድርገዋል:: 2ኛ ጴጥ.1÷21፤ 2ኛጢሞ. 3÷16:: ስለዚህም ደራሲው በልብ ወለድ ድርሰቱ እንደሚለው ሐዲስ ኪዳን ታሪካዊ መጽሐፍ ሆኖ ሥልጣናቸውን ለማደላደል በፈለጉ ሰዎች ታርሞ የተዘጋጀና የተሰባሰበ አልነበረም::

እንደ አጠቃላይ መንፈሳዊ ይዘቱን መንፈሳዊ ተጽዕኖውን እንደ ጠበቀ ከ850 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሟል:: ቅዱስ መጽሐፍ ነቢያት የተነበዩት ትንቢት ሁሉ የተፈጸመበት፤ ትንቢቱም ሆነ ፍጻሜው የሚገኝበት ከእግዚአብሔር የተገኘ መጽሐፍ ነው:: "በነቢይ ከጌታ ዘንድ ... የተባለው ይፈጸም ዘንድ" በሚል መንገድ የተገለጹ ቃላትን ማንበብ በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተደጋጋሚ የምናስተውለው ነው:: ማቴ.1÷22፤ 2÷15፤ 2÷23፤ 4÷14፤ 8÷17፤ 12÷17፤ 13÷35 ፤ 21÷4፤ 27÷35:: ቅዱስ ጴጥሮስም እንደ ተናገረው:- "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም.....::" 2ኛ ጴጥ. 1÷21:: ቅዱስ መጽሐፍ በተለያየ ጊዜ፣ በተለያዩ ቅዱሳን፣ በተለያዩ ቦታዎች የተጻፈ ነው:: እነዚህ የጊዜና የቦታ ልዩነቶች ተጠብቀው ሁሉም መጻሕፍት በአንድነት አንድን ጉዳይ አስረግጠው የሚያስረዱ፣ ወደ ሕይወት መንገድ የሚመሩ መሆናቸው ያለምንም ጥርጥር ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ያረጋግጥልናል::

ቅዱስ መጽሐፍ ለ1500 ዓመታት ያህል ከ40 በሚበልጡ የተለያየ ባህል በነበራቸው የእግዚአብሔር ምርጦች ተጽፏል:: ከጸፉትም አንዳንዶቹ እንደ ንጉሥ ዳዊትና ጠቢቡ ሰሎሞን ያሉት ነገሥታት ነበሩ:: እንደ አሞጽ እረኞች፣ እንደ ዘካርያስ ካህን ፣ ከነቢያትም ኢሳይያስና ሳሙኤል፣ ሕግን ከሠሩቱ ሙሴ፣ ከመሳፍንቱ ኢያሱ፣ ከዓሣ አጥማጆች ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ ከመምህራን ቅዱስ ጳውሎስና ከሕክምና ሰዎች ሉቃስ ጽፈውታል::

በተጨማሪ ቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው በተለያዩ ቦታዎች ነው:: በሲና በረሓ፣ በይሁዳ ምድረ በዳ፣ በኤድላም ዋሻ፣ በሮም እስር ቤት፣ በፍጥሞ ደሴት፣ በጽዮን ቤተ መንግሥት፣ በባቢሎን ወንዞች ዳርቻዎችና በኢየሩሳሌምም ተጽፏል:: በተጠቀሱት ረጅም ዘመናት በተለያየ ጊዜና ቦታ በተለያየ ነባራዊ ሁኔታ ተጽፎ እስከ አሁን ድረስ በአንዱ መጽሐፍ የሚገኘው ከሌላው መጽሐፍ ጋር የሚተባበርበት፣ የነቢያቱ ትንቢት የሐዋርያቱም ስብከት አንድነቱ የተጠበቀበት የመጻሕፍት ስብስብ ከዚህ ዓለም ብናገኝ በእርግጥም ይኽ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ነው::

ቅዱስ መጽሐፍና ቤተ ክርስቲያን አይለያዩም:: ግን ቀድሞ የተገኘው የትኛው ነው? ዶሮ ወይስ እንቁላል? እንዲህ እንደ ማለት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ መጽሐፍ ትቀድማለች:: በመጀመሪያ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን የታተመ ቅዱስ መጽሐፍ አልነበራትም:: ቤተ ክርስቲያንም ቤተ ክርስቲያን ለመሆን የግድ መጽሐፍ ቅዱስ አያስፈልጋትም ነበር:: ይኽ እንዲፈጠር ባንወድም አሁን የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ቢቃጠሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ በጣም ጥቂት ነው:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር ቤተ ክርስቲያን የሮማውያንን ዘመን ያለፈችው:: ተቃራኒው ግን እውነት አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ባትኖር ቅዱስ መጽሐፍ ብቻውን ለመዳኛችን የሚሆነውን ሊያደርግልን አይችልም:: የት ልንጠመቅ? ልንቆርብ? ቤተ ክርስቲያን "የገሀነም ደጆች አይችሏትም..." የተባለችውም ለዚሁ ነው:: ማቴ. 16÷18::

1.2 *"በተለያዩ የመጽሐፍ ጥቅ ሎች የተገኙ ታሪካዊ ልዩነቶችን ስንመለከት በትክክል ዘመናዊዉ መጽሐፍ ቅዱስ ፖለቲካዊ አጀንዳ በነበራቸውና ሰው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ አምላክ በማድረግ ይኸንኑ ተጽዕኖ በመጠቀም የራሳቸውን የኃይል መሠረት ለመጣል በፈለጉ ሰዎች የተበረዘ ስብስብ መሆኑን ያረጋግጥልናል::"* የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 234 :: *ያለምንም ትክክለኛ ታሪካዊ መረጃ* ዳን ብራውን: *"ቅዱስ መጽሐፍ ፖለቲካዊ አጀንዳ ለመሆን በሚያስችል መንገድ የተጠረዘ ነው"* የሚል ክስ ያቀርባል:: ይኸም ክስ ቅዱሳት መጻሕፍት በአንድነት የተሰበሰቡበትን ቀኖናዊ ሒደት ካለመገንዘብ የመነጨ መሆኑን መረዳት አያዳግትም:: አንድን ጽሑፍ በአዲስ ኪዳን እንደ እውነተኛ መጽሐፍ ለመቁጠር ጽሑፉ ሦስት መመዘኛዎችን ማሟላት አለበት:: ፖለቲካና የሰውየው ግላዊ ሁኔታ ግን ከእነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ አልተካተቱም:: መመዘኛዎቹ የተዘጋጁት በቀደሙ አባቶቻችን አማካይነት ሲሆን ማናቸውንም የሐሰት ትምህርቶች በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ እንዳይካተቱ አድርጓል:: መመዘኛዎቹ:-

ሀ. መጽሐፉ ስለ ጌታችንና ስለ ትንሣኤው የዐይን ምስክርነት መስጠት በሚችሉ በጌታችን ደቀ መዛሙርት ወይም በሐዋርያት የተጻፈ መሆን አለበት:: የቅዱስ ጳውሎስ ጽሑፎችም ተቀባይነት ያገኙት ራሱ ጌታችን ስለ ተገለጸለትና ከወንድሞቹ ከሐዋርያት፣ ከቤተ ክርስቲያንም ርእሳን ጋር የሚስማማ ትምህርት በመልእክቱ ስለ ነበረው ነው:: የሐ. ሥራ 8÷22 ፤ ገላትያ 2÷2::

ለ. ጽሑፉ ከዕብራውያንና ከሐዋርያት መጻሕፍት ጋርም የሚስማማና ክሕደት የሌለበት ኦርቶዶክሳዊ መሆን ይገባዋል::

ሐ. መጽሐፉ በተጻፈበት ዘመን በነበረች የጥንት ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል:: ተቀባይነቱ የሚመዘነው ራሳቸውን በፈቃዳቸው በለዩ ቡድኖች አማካይነት አይደለም:: ይልቁኑ በዚያ ዘመን በነበሩ በቀናች ሃይማኖት በጸኑ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንጂ::

1.3 *"አስቀድሜ የገለጽኳቸው የናግ ሐማዲና የሙት ባሕር ጥቅሎች ግልባጮች ቀዳሚ የክርስቲያን መዝገቦች ናቸው:: በሚያስደነግጥ መልኩ ግን አሁን ካሉት ወንጌላት ጋር ምንም መመሳሰል የላቸውም::"* የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 245::

በእርግጥ *የናግ ሐማዲ ግልባጭ* በ1945 ዓ.ም. በግብጽ በናግ ሐማዲ አካባቢ ተገኝቷል:: ጥንታዊውም የዚህ መጽሐፍ ግልባጭ የተጻፈው ከ150 ዓ.ም. በኋላ ነው:: የሚበዙት የዚህ መጽሐፍ ክፍሎች የተጻፉት ከ200 - 300 ዓ.ም ነው:: በ100 ዓ.ም. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በጠቅላላ ተጽፈው ተጠናቅቀዋል:: ይኸም ቢያንስ ከጥንታዊው የናግ ሐማዲ ቅጂ 50 ዓመት አስቀድሞ ማለት ነው:: የናግ ሐማዲ ጽሑፍ የግኖስቲኮች ሐሳብ የተሰበሰበበት የክሕደት መዝገብ ነው:: ጽሑፉ ከተቀበልናቸው የሐዲስ ኪዳንም ሆነ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተለየ ነው:: የናግ ሐማዲና የሙት ባሕር ጥቅሎች ሁለቱም የተለያዩ ሰነዶች ቢሆኑም ዳን ብራውን አንድ አድርጐ አቅርቧቸዋል:: የሙት ባሕር ጥቅሎች ከጌታችን መወለድ ረጅም ዘመናት አስቀድመው የተጻፉ ናቸው:: ጥቅሎቹ ቅድመ ክርስትና የተጻፉ ስለሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ጨምሮ ማቅረቡ ወይም ማመሳሰሉ ፈጽሞ ስሕተት ነው::

1.4 *"በሐዲስ ኪዳን ከ80 በላይ ወንጌላት ነበሩ:: እስከ አሁን ግን ተቀባይነት ያገኙት የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ብቻ ናቸው::"* የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 231::

አራቱም ወንጌላት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ለክርስቲያኖች የተሠራጩና ለአምልኮታቸውም የሚጠቀሙባቸው ነበሩ:: ከዚህ ውጪ ያሉት የናግ ሐማዲ ጽሑፎች እንደ ዳን ብራውን ገለጻ ሰማንያ ሳይሆኑ አምስት ብቻ ናቸው:: አምስቱንም ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ከላይ ከተገለጹት መመዘኛ ቀኖናት ጋር ስለማይስማሙ አልተቀበለቻቸውም::

1.5 *".... በራሱ በኢየሱስ እንደ ተጻፈ የሚገመት ' Q' ዶክመንት አለ::"* የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 256::

ዳን ብራውን " Q" መዝገብ የሚለው ዘመናዊ መጽሐፍ ነው:: የተጻፈውም በራሳቸው መላ ምት ላይ በተመሠረቱ አንዳንድ ጸሐፊዎች ነው:: የጸሐፊዎቹም እምነት:- ለማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌላት የጋራ ምንጭ አላቸው:: ምንጩም " Q" ሲሆን ከጀርመንኛው " Quelle" ወይም



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የእንግሊዝኛ ትርጉሙ "Source" ቃል የተወሰደ ሆኖ ትርጉሙም ምንጭ ማለት ነው::» ይላል::

እንደ «የዳቪንቺ ኮድ» አባባል "Q" መዝገብ "ድብቅ ምናልባትም በራሱ እጅ የጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ነው"። እውነታው ግን "Q" መዝገብ ከጸሐፊው ምናባዊ አቀራረብ ውጭ ምንም አይደለም:: ይኸም በአንዳንድ ጸሐፊዎች ዘንድ "የማቴዎስና የሉቃስ ወንጌላት የጌታችንን በርካታ ትምህርቶች ተጋርተው ለምን እንደ ጻፉ እናስረዳለን " የሚል መላምት (Hypothesis) አለ:: ይኸም የዚያ መላ ምት አንዱ ክፍል ነው:: ሐሳቡም:- "ማቴዎስና ሉቃስ ወንጌላቸውን ሲጽፉ አሁን የጠፋ የጋራ ሰነድ ተጠቅመዋል:: ያ የጠፋውም ሰነድ የኢየ ሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች አጠቃሎ የሚገልጽ ነበር" ይላሉ:: ይህ መረጃ:- ስለመኖሩ ከመላ ምት ውጭ ተጨባጭ ማስረጃ የለም:: እንዳሉት ቢኖር እንኳ በቀላሉ ያ ሰነድ ሊኾን የሚችለው የጌታችን የቃሉ ትምህርት ነበር::

*1.6" ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ በገንዘብ ረድቷል:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም የተጻፉትን እውነታዎች ሰርዞ አምላክ አድርጐ አቅርቦታል:: ስለ እርሱ ያለውንም እውነት የሚናገሩ ወንጌላትንም አቃጥሏቸዋል::*

" የዳቪንቺ ኮድ፣ ገጽ 233::

ከታሪክ እንደ ምንረዳው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ቀኖናውያት መጻሕፍትን በተመለከተ ምንም ተሳትፎ አላደረገም:: ንጉሡ ክርስቲያን ለመሆን የፈለገው በሚልቪያን ድልድይ (Milvian Bridge) በተደረገ ውጊያ ካሸነፈ በኋላ ነው:: ያም ሆኖ ከመሞቱ አስቀድሞ እስከ ነበሩ ጥቂት ሳምንታት ድረስም ለመጠመቅ አልወሰነም ወይም አልፈቀደም ነበር:: በንግሥናውም ዘመን የነበሩ ሳንቲሞችንም ስንመለከት እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ የሮማውያንን የፀሐይ አምላክ ሲያመልክ እንደ ኖረ ያስረዳል:: የቀኖናውያት መጻሕፍትን አምላካዊነት፣ ምንባባዊነት፣ እሙራትነት የመለየት ሒደት የነበረው ቆስጠንጢኖስ ቄሣር ከመሆኑ በፊት ነው:: ያም በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነው:: ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ በሮም ግዛት የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ያለ ልዩነት ተቀብለው የሚጠቀሙባቸው 20 መጻሕፍት ነበሩ አቸው:: እነዚህም:- የማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ የሐዋርያት ሥራ፣ 13ቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት፣ 1ኛ ጴጥሮስና፣ 1ኛ ዮሐንስ ናቸው:: አከራካሪ የነበሩት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዕብራውያን፣ ያዕቆብ፣ 2ኛ ጴጥሮስ፣ 1ኛ እና 3ኛ ዮሐንስ፣ ይሁዳ እና የዮሐንስ ራእይ ናቸው:: የመጀመሪያው መከራከሪያ እነዚህ መጻሕፍት ከሐዋርያት የተገኙ በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ላይ ይነሣ የነበረው የሐሰት ጥያቄ ነው:: ይኸ ጉዳይ በ140 ዓ.ም መርቅያን (Marcion) በሚባለው ሰው የማቴዎስን፣ የማርቆስን፣ የዮሐንስን እና ሦስቱን የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታትን ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የመቀነስ ሙከራ አድርጎ አልተሳካለትም:: ከፍ ያለ ተቃውሞም አምጥቶበት ነበር::

ቀኖናውያት መጻሕፍትን የመለየት ሒደት እስከ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ድረስ ያልተጀመረ ቢሆን ኖሮ በ140 ዓ.ም. የነበረው የመርቅያን (Marcion) ድርጊት ለክርስቲያኖች ምንም ስሜት ባልሰጠና ባልተቃወሙትም ነበር:: የዚህ ሰው ድርጊት ብዙ የሚከፋፍል ስለ ነበር በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች በ144 ዓ.ም. ከአንድነታቸው አውግዘው ለይተውታል:: መርቅያን ከተለየ በኋላ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጠርጠሉስና አርያኖስ ስሕተቱን አስመልክተው ምላሹን ጽፈዋል::

ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ በ330 ዓ.ም አካባቢ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በ50 ያህል ጥራዝ ተባዝቶ (Copy) እንዲቀመጥ በገንዘብ ረድቷል:: ከወንጌላት የመቀነስም ሆነ ወንጌላትን የመቀባባት ሥራ ግን አልነበረውም:: ቆስጠንጢኖስ ቅዱስ መጽሐፍ በ50 ያህል ቅጂ እንዲባዛ ከማድረጉ በፊት የነበረውም ሆነ 50 ያህል ቅጂዎቹ ክርስቲያኖች ከሚጠቀሙባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ምንም የተለየ ቃል እንኳን የላቸውም::

በ367 ዓ.ም የእስክንድርያው አባት ቅዱስ አትናቴዎስ ለክርስቲያኖች "የተበከሉና የረከሱ መጻሕፍትን ከእነርሱ ዘንድ እንዲያስወግዱ" እና "በድብቅ የተሠራጩ መጻሕፍትን " እንዳይቀበሉ ጽፎላቸው ነበር:: እንደዚህ ካሉ መልእክቶቹ የተነሣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቀኖናውያት ያልሆኑ መጻሕፍትን አቃጥለው ሊሆን ይችላል:: እነዚህ የተቃጠሉት ግን ጥንታውያኑ እና እውነተኞቹ ወንጌላት አይደሉም:: የተቃጠሉት መጻሕፍት ክርስቲያኖች ከሚቀበሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ቀድሞውኑ ያልተካተቱና በኋላ በግኖስቲኮች የተጻፉ ጽሑፎች ናቸው:: "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለው "ሱዳን እጆቿን..." ብለው ለውጠው እንዳቀረቡበት ያሉትን"መጽሐፍ ቅዱስ" አለመጠቀም ክፉ ስም በእውነተኞቹ ክርስቲያኖች ሊያሰጥ እንደ ማይችል መገመት የሚያዳግት አይደለም::

በአብዛኛው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቀኖናውያት የማድረግ ሥራ የተፈጸመው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ነው:: ይኸም ቆስጠንጢኖስ ከመንገሡ ከሁለት ምእተ ዓመታት አስቀድሞ ነው:: ሐዲስ ኪዳን በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አማካይነት ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ለማድረግ ተጊጦና ተቀባብቶ የቀረበ አይደለም:: ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሮም ቄሣር ሆኖ የተሾመው ክርስቲያኖች ጌታችንን መለኮታዊ አምላክ እንደ ሆነ ካመኑ በኋላ በ306 ዓ.ም ነበር:: በዳቪንቺ ኮድ ገጽ 233 ላይ የተቀመጠው "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ የተወሰነው በቆስጠንጢኖስ ወይም በጳጳሳቱ ነው" የሚለው መግለጫ ፍጹም ልብ ወለድ ነው::

የክርስቲያኖችን መጻሕፍት ሥልጣን የሚክዱ ጸሐፍያን እንኳን ከጌታችን ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ በተከታዮቹ 20 ዓመታት ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስቲያኖች ሕይወት በሮም ግዛት ሁሉ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የጻፈውን መልእክት ይቀበላሉ:: በ40 እና 50ዎቹ ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈው መልእክቱ ጌታችንን:- "የእግዚአብሔር ልጅ፣ ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ከሁሉ በላይ የሆነ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን" በማለት ጽፏል:: ኋላም ለፊልጵስዩስና ለቆላስይስ ሰዎች ጌታችንን "እግዚአብሔር ነው፣ በእግዚአብሔርነቱ ሲኖር ሳለ ፣ የማይታየው እግዚአብሔር መልክ " ብሎ ጽፏል:: እነዚህ ጽሑፎች ተቀባይነት አግኝተው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ተደንቀዋል:: በዚያም ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖችም ተባዝተው ተሠራጭተዋል:: በ100 ዓ.ም. በግብጽ የተገኘው የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ክፍል ጌታችንን " ጌታዬና አምላኬ" ይለዋል:: ከዮሐንስ ወንጌልም በፊት የተሠራጩት ወንጌላት ጌታችን እግዚአብሔር እንደ ሆነ የሚመሰክሩ ናቸው::የክርስቲያን ጠላቶች የነበሩ ቀደምት መናፍቃን ራሳቸው ክርስቲያኖች ጌታችንን መለኮታዊ አምላክ ብለው እንደ ሚያመልኩት ያውቁ ነበር:: (ሮሜ. 9÷5፤ 1ኛ ቆሮ. 8÷6፤ 2ኛቆሮ. 4÷5፤ ገላ. 1÷1-3፤ ገላ. 1÷16፤ ገላ. 2÷20፤ 2ኛተሰ. 2÷16፤ ፊሊ. 2÷6፤ቆላ.1÷15-16፤ ዮሐ.1÷1፤ ዮሐ 20÷28፤ ማቴ 1÷23፤ ማር.1÷1፤ ሉቃ 1÷35 )::

በተረፈ ግን ወንጌላት የሚገልጹት የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ብቻ ሳይሆን በፍጹም ተዋሕዶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ነው:: 1ኛ ዮሐ. 5÷20::


አምላክ ሰው ኾኖ ሰውን የማዳኑ ምስጢር በቅዱስ መጽሐፍ ካልተገለጸ ቅዱስ መጽሐፍ መጻፉ ፊጽሞ ባላስፈለገ ነበር:: ዳን ብራውን እና ተከታዮቹ ስለ ጌታችን ሰው የመሆን ምስጢርም ሆነ ስለ ባሕርይ አምላክነቱ ለመረዳት ሐዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ ማንበብና ምስጢሩንም ከሚያስረዷቸው ሊቃውንት ጠይቀው መረዳት ይኖርባቸዋል:: ለሚደመረውና ለሚቀነሰው የቁጥር ትምህርት እንኳን ጥሩ መምህር ፍለጋ ወላጆች እንደ ሚደክሙ ተማሪዎችም ዕውቀትን ለመጨበጥ እንደ ሚጣጣሩ ይታወቃል:: ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስንም በእናቱ ዘው እያሉ በዕውር ድንበር ከሚራመዱበት ቢማሩትና ቢያጠኑት ከሥጋዊ ብቻ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ቁም ነገር ያደርሳቸዋል:: «የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?» እንዳለው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ:: የሐዋ.ሥራ 8÷30::

ይቆየን::

ወስብሐት እግዚአብሔር




© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org



*ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ነው። ማኅበራችን ይህን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ነው። አጠቃላይ የሥራ ሒደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል ይደረግበታል።*

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት ቤተ ክርስቲያን ያላት ሀብትና የሚጠበቅባት ድርሻ

*ኀይለ ኢየሱስ አዳሙ*
*/ከማኅበረ ቅዱሳን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቦርድ/*

ባለፈው እትማችን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ቤተ ክርስቲያን ያላትን ዐቅምና የሚጠበቅባትን ድርሻ በጥቂቱ ለማየት ሞክረናል። ዛሬ ደግሞ በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥና ዙሪያ የሚገኙት፦ የሰንበት ት/ቤት፣ የማኅበራት፣ የሰንበቴ እና ተመሳሳይ ስብስቦች በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ላይ ማድረግ የሚቻላቸውንና የሚገባቸውን በአጭር በአጭሩ እናስነብባችኋለን።

ቤተ ክርስቲያን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ ማኅበረሰቡን በማስተባበርና በመምራት የአንበሳውን ድርሻ በመያዟ፣ ለክፍሉም ተገቢውን የሰው ኃይል በመመደብና ከሌሎች ተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ በመቅረጿና የፕሮጀክት ሥራዎችን በመጀመሯ ብቻ የሚጠበቀውን ውጤት አስመዝግባለች ለማለት አይቻልም፣ ገና ጀመረችው እንጂ። ይህ ጅማሮ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙት አካላት በሙሉ ዐቅምና በባለቤትነት ስሜት መንቀሳቀሳቸው ሥራው የታሰበለትን ዓላማ በጊዜው እንደሚያሳካ አይጠረጠርም። ስለዚህም የሰንበት ት/ቤት፣ የጽዋ ማኅበራት፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ የሰንበቴ ስብስቦች እንዲሁም የገዞ ማኅበራት የየበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ በኋላ በምልዐተ ሕዝብ የታቀፈ የማኅበረሰብ ንቅናቄ ለቫይረሱ ሥርጭት መገታትና የኤድስ ሕሙማንም ተገቢው ክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ዕድሉ አስቸጋሪ እንደማይኾን እሙን ነው።

ይህ አካሄድ ቤተ ክርስቲያናችን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራትና ለዓለምም ተጠቃሽ «ሞዴል» አድርጎ የሚያሳያት ይሆናል። የዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስንና ሌሎች ተዛማጅ ችግሮችን ረጅም በማይባል ጊዜ ውስጥ ለመፍታት ያስችላል። በተያያዘም ለቫይረሱ ሥርጭት መንሥኤም ውጤትም የሆነውን ድህነትን ለመዋጋት ዋነኛ መንገድ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱትን የመንፈሳዊ አገልግሎት አካላት ሚና ለመመልከት በቅድሚያ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በጋራ መወያየትና በመቀናጀት መንቀሳቀስ ይገባል። ከመንፈሳዊ አገልግሎት አካላቱ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

## 1ኛ *የሰንበት ትምህርት ቤት*

ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ወጣቱ ለቫይረሱ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ከሆኑት መካከል ዋናውን ቦታ ይይዛል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከ6.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ወጣቶች በሰንበት ት/ቤት በመታቀፍ የሃይማኖት፣ የሥነ ምግባር እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን በማንሣት እርስ በእርስ በመማማር ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል። ይህን ያህል ቁጥር ያለው ወጣት የአመለካከት፣ የጠባይና የምግባር ለውጥ አምጥቶ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት ትልቅ ቁልፍ ነው። ይሁንና በተናበበ እና ወጥነት ባለው መልኩ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ባማከለ መልኩ ለወጣቶች የተዘጋጀ የመማሪያም ይሁን ሌላ አጋዥና ማጣቀሻ መጻሕፍት አልተዘጋጁም። ይህ ደግሞ አልፎ አልፎም ቢሆን የተጀመረውን በልምድ ልውውጥ የመማማር የአቻ ላቻ ዘዴ ወቅታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ያደርገዋል።

የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በቅድሚያ ራሳቸውን በተጨባጭ ዕቅበውና ጠብቀው አለፍ ሲልም በየቀዬአቸው ለሚገኙ ከሰንበት ት/ቤት ውጭ ላሉት ወጣቶች አርኣያ መሆን ይችላሉ። ይህን እውነታም አልፎ አልፎ በአንዳንድ አጥቢያዎች ላይ ማስተዋል ይቻላል። የቫይረሱን ሥርጭት ባለበት ለማቆም ዋነኞቹ የመከላከያ መንገዶች ከሚባሉት ውስጥ÷ ቤተ ክርስቲያን ድሮም ቢሆን ስታስተምራቸው የኖረቻቸው ከጋብቻ በፊት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መታቀብና ከሥርዐተ ጋብቻም በኋላ በመተማመን እና እግዚአብሔርን በመፍራት መኖር ናቸው። የእኒህንም ተግባራዊነት በተመለከተ ክትትል ማድረግ፣ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ትልቅ የሥራ ፍሬን ያስገኛል። ይህም ማለት ሁሉም አካል ያለውን አቅምና ችሎታ በመጠቀም ለሚመጣው ጥያቄ ሁሉ በቂ ምላሽ በጊዜው መስጠት ይገባዋል። ከምላሹ በኋላ የሚገኘውን ውጤትም በተገቢው መንገድ አጠናቅሮ ለሌሎች መማማሪያ ይሆን ዘንድ ማስተላለፍ፣ የሌሎችንም ልምድ መቅሰም ያስፈልጋል።

የሰንበት ት/ቤት የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን አካላት ጋር መተሳሰር አለበት። ለምሳሌ፦ ከጽዋ ማኅበራት፣ ከሰበካ ጉባኤያት፣ ከሰንበቴና ከመሳሰሉት ጋር በመቀናጀት የመምራቱንና የማስተ ባበሩን ድርሻ መወጣት ይገባል። እንዲህ ከሆነ በቅርብ ጊዜ ለውጥ እንደሚመጣ በድፍረት ለመናገር ያስችላል። ከግንዛቤ ማነስ፣ችግሩ አይመለከተኝም በማለት፣ በቸልተኝነትና ለጉዳዩ ትኩረት ባለ መስጠት ወይም ደግሞ በእግዚአብሔርም ዘንድ ኾነ በኅሊናችን የምንጠየቅበትን ሥራ በተቀናጀ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ባንችል ደግሞ ሁሉም የተወቃሽነትና የጸጸት ስሜት ሰለባ መኾኑ አይቀሬ ይሆናል።

## *2ኛ. ማኅበረ ቅዱሳን*

ማኅበረ ቅዱሳን ከመንፈሳዊ አገልግሎቱ ጐን ለጐን ማኅበራዊ አገልግሎት እንደ ሚፈጽም በማኅበሩ ደንብ አንቀጽ 4.11 ላይ ተመልክቷል። በዚህም መሠረት የማኅበሩ አምስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪ ቦርድ አቋቁሞ ከተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከዋናው ማእከል ባለፈ መልኩም በማእከላት፣ በወረዳ ማእከላት እና በየግቢ ጉባኤያትም ኰሚቴ በማዋቀር የአሠራር ስልቱን ዘርግቷል። ይህ ግን ብቻውን በቂ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ማኅበረ ቅዱሳን ካለው ዐቅም ጋር የሚገናዘብ፣ የሚዳሰስ፣ የሚታይ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። በተለይም ደግሞ ከየከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በመላ ሀገሪቱ የሚሠራጩ በመሆኑ መላ ኅብረተሰቡን ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግንዛቤ በመፍጠር በአንድ ጊዜና በሁሉም ዘንድ ምላሽ ለመስጠት በተቻለ ነበር። በእርግጥ አንድ ሥራን ለማስፈጸም የገንዘብ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም። በየማእከላቱና፣ በየወረዳ ማእከላት ያሉ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን በተግባር የተደገፈ ለውጥ ቢያመጡ ይህ በራሱ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ግና ይህ የሚናፈቀው በተግባር ሊታይ የሚችል ለውጥ በአባላቱ ላይ እየታየ ነው ወይ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ ከባድ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት ብዙ ብዙ ነገሮች ይጠበቃሉ። በተለይም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭትና የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ቀውስ ለመቀ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ልበስ መሪ ተዋናይ ሆነው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል:: በትምህርቱ፣ በልማቱ በሌላ ውም የማኅበረሰባዊ ጉዳዮች ትልቅ ሚና መጫ ወት ብቻውን በቂ አይሆንም:: በቅ ድሚያ ራስ ተለውጠ ለሌላውም አርአያ መሆንን ከማኅበሩ አባላት በተግባር ለማየት የሚናፍቁ አያሌዎች ናቸው:: ስለዚህ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ከስም ያለፈ ሥራ መሥራት፣ ድርሻን መወጣት ያስፈልጋል:: ለዚህ አስጨናቂ ጊዜ ያል ሆነ ዕውቀትና ችሎታ ለመቼ ሊያገለግል ነው? የማኅበረ ቅዱሳን አባላት በየአካባቢው ከላይ እስከ ታች ድረስ ባሉት የቤተ ክርስቲያን እና የመንግሥት መዋቅሮች በመግባት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታ ቸውን ሊወጡ ይገባቸዋል:: ሞያዊ እገዛው ለፀረ ኤድስ ዘመቻው አካሄድ በሚጠበቀው መንገድ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻም ሳይ ሆን ዐቅምንም ያጕለብታል፣ በዘላቂነት ሥራው እንዲቀጥል ይደረጋል::

የማኅበሩ የዋናው የማእከላት እና የወረዳ ማእከላት አመራር አካላትም ተገቢ ውን ትኩረት በመስጠት በዕቅድ ማካተት ብቻ ሳይሆን ለተግባራዊነቱም በቁራጥነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል:: አባላቱን በደ ብዳቤ፣ በስልክና በመሳሰሉት የመገናኛ ዘዴዎች ከማዘዝ ባለፈ መልኩ በአካልም በመገኘት መቀስቀስና ማነቃቃት ይገባል:: ለዚህ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን ግብዐት ሁሉ በማቀናጀት መሟላቱን መከታተል ጥሩ ውጤት ያስገኛል:: የፕ ሮጀክቱን ውጤት በመገምገም ካለፈው ስሕተት በመማር ለወደፊቱ በተጠናከረ መልኩ ፕሮጀክቱን ማስፋፋት፣ ኅብረተ ሰቡን ማገልገል ይገባል:: ይህ ነው ከተ ወቃሽነት ነጻ የሚያደርገው:: ያለበለዚያ በወረቀት ላይ ብቻ የማረ ዕቅድ ሆኖ እንዳይቀር መጠንቀቅ ይበጃል::

የማእከላትና የወረዳ ማእከላት በተለይ አሁን ከክልል እና ከወረዳ የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤ ቶች እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ክፍ ሎች ወይም ዴስኮች ጋር በመተባበር ትልልቅ ሥራዎች ሊሠራበት የሚችል የጋራ ዕቅድና ትግበራ ማካሄድ እንደ ሚቻል ግልጽ ነው:: ያም ባይሆን እንኳን በየግላችን ያለንን ዕውቀት፣ጊዜ፣ገንዘብ፣ ጉልበትና ወዘተ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ በሚያደርሰው ጉዳት ብዙዎችን በማ ጽናናት፣ በመደገፍና በመርዳት ለፀረ ኤድስ ዘመቻው ዕገዛ ማድረግ ይቻላል:: ይህ ደግሞ ዛሬ ቫይረሱ ያመጣው ሳይሆን አባቶቻችን ያወረሱን በጐ ሥራ ነው:: ገንዘብ ሳይወጣም ሥራ መሥራት ይቻላል::

የማኅበረ ቅዱሳን የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቦርድ ፕሮጀ ክቶችን በመቅረጽ፣ የገንዘብና የሞያ ድጋፍ በማፈላለግና ሌሎችንም ግዴታዎቹን በመ ወጣት ላይ ብቻ መቆም የለበትም:: ባለው ዐቅም ሁሉ ሠርቶ የማሠራቱን ሂደት ሊያስተባብርና ሊመራ ይገ ባዋል:: የማኅበሩ አባላት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ያላቸውን ሁለንተናዊ ግንዛቤ በማጥናትና ለሚመለከታ ቸው በማቅረብ ያሉትን ክፍተቶች የመሙ ላት ሐላፊነት አለበት:: በዚህ እንቅስቃሴም ሁሉንም አመራር በማሳመን የቅስቀሳና የማ ሳመኑን ሥራ መሥራት የግድ ነው:: በማወ ቅም ይሁን ባለማወቅ ስለዚህ ርእስ ጉዳይ እንቅልፍ የደበታቸው ካሉ የማንቃቱ ሥራ በቅድሚያ የቦርዱ መኾኑን መገንዘብ ያሻል:: በየክፍሎች ያሉትን ባለ ሞያዎች እንደ የፍላጐታቸውና እንደ የሞያቸው ለዚህ ፕሮ ግራም ማስተባበርና ማሰለፍ ዓላማን ያሳ ካል፣ ግብን ያስ መታል::

እንግዲህ ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ ክር ስቲያን የሳይንስና ቴክኖሎጂው ተጠቃሚ የምትሆንበትን፣ በጥናት በተደገፈ የመረጃ አያያዝና ሥርዓት ያለውን ሀብ ትና ዕውቀት በሚገባ የምትጠቀም በትን ሁሉ ለማመቻቸት ባለው ዐቅም መትጋት ይኖርበታል::

3. *የጽዋ ማኅበራትና ሰንበቴዎች*

የጽዋ ማኅበራትና ሰንበቴዎች ከሚ ፈጽሙት መንፈሳዊ አገልግሎትና ክርስ ቲያናዊ ትውፊት በተጨማሪ ማኅ በራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችንም ጉዳዮች በማን ሣት የሚወያዩበት፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚዘይዱበት መድረክ ነው:: ይህ የመወ ያያ መድረክ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የመከ ላከል ሥራ ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ እስከ የጠባይ ለውጥ ድረስ ትልቅ ሥራ ሊሠራ የሚችልበት ቦታ ነው:: በእነዚህ ሰፊውን ሕ ዝብ በቅርበት ማግኘት ይቻላል:: ማኅበራ ዊ፣ ኢኮ ኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶችን ያገ ናዘበ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ቁርጠኛነት የታከለበት የተቀናጀ የመከላከል፣ ክብካቤና ድጋፍ ሥራዎች በማካሄድ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሊያደርስ የሚችለውን ዘርፈ ብዙ ቀውስ በማኅበ ረሰብ ንቅናቄ ማስቀረት ይቻላል:: ስለሆ ነም የፀረ- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘመ ቻን /የሕዝብ ንቅናቄን/ በአግባቡ ለመ ምራት የሚያስችል አደረጃጀትን በጽዋ ማኅበራትና ሰንበቴዎች ውስጥ መፍጠር፣ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ፣ የወረር ሽኙን የመስፋፋት መንሥኤ ዎችንና የመ ከላከያ መፍትሔዎችን ያመ ላከቱ ተከ ታታይ ውይይቶች በእነዚህ መድረኮች ማዘ ጋጀት ይቻላል:: በተጨ ማሪም ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን ሰዎችንና ወላጆ ቻቸውን ያጡ ሕፃናትን አስፈላጊውን ድጋ ፍና ክብካቤ እንዲያገኙ ከሌሎች መሰል ስብስቦች ለምሳሌ ከዕድሮች ጋር በማ ቀናጀት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ሌሎ ችንም ሥራዎች መሥራት ይገባል::

ከላይ የተገለጹትን ጉዳዮች ለማ ሟላት የጽዋ ማኅበራቱ እና ሰንበቴዎቹ ጉዳዩን እንደ አንድ አሳሳቢ ጉዳይ አድ ርገው ሊወስዱት ይገባል:: በሚገናኙበት ጊ ዜ ሁሉ በግልጽ ስለ ጉዳዩ በመወያየትና ለችግሩም መፍትሔ በማመንጨት የማን ንም እጅ ሳይጠብቁ ራሳቸውን፣ ቤተሰ ቦቻቸውንና ሌሎችንም መጠበቅ ይችላሉ:: ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያውያን አዲስ ነገር አይደለም፤ ድሮም ቢሆን ለአንድ ቤት ችግር በውይይትና በጋራ በመተሳሰብ መላ መዘየዱን ይችሉበታልና::

በእነዚህ ቦታዎች ላይ ይህን ለማ ድረግ ግን አቅጣጫ የማሳየቱን ሥራ የሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ ሊያ ስቡ በትና አፋጣኝም ውሳኔ ሊያስተላልፉ ይገ ባል:: በሌላ በኩል የዕድሮች፣ የጉዞ ማኅ በራት እና የመሳሰሉቱ ሚናቸው በዚ ሁ ዐይን ሊታይ ይችላል::

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ያላ ትን ሀብት በመጠቀም የኤች.አይ.ቪ /ኤድስን ሥርጭት ለመግታት እንደ ምት ችል እሙን ነው:: ነገር ግን በጽሑፍ ላይ ያለ ሁሉ ተግባራዊ ይሆናል ማለት አይደ ለምና ለተቀረጸው ዕቅድ መሳካት የሁ ሉም ድርሻ ሊታከልበት ይገባል:: ሁሉም በተሰጠው ጸጋ በመጠቀም የፀረ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረት በአሸናፊነት እንደንወጣ መታገል አለብን::

ያለፉ ሥራዎቻችንን ዘወር ብለን በማየት ክፍተቶችን በመሙላት በጊዜው የሚጠበቀውን ፍሬ ለማየት መሮጥ ይገ ባል:: ያለበለዚያ ሁላችንም ከመወቀስ አን ድንም:: የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥራ የሚደ ግፍ ሁሉ ደግሞ በገንዘብና በቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ አለሁ ሊል ይገባል:: ይህ ከሆነ በረጅም ጊዜ የሚጠበቀው ውጤት በአ ጭር ጊዜ ሊመጣ እንደ ሚችል አያጠያ ይቅም::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት



የተለያዩ የመዝሙር እና
የስብከት ካሴቶችን፣
መንፈሳዊ መጻሕፍትንና
ንዋያተ ቅድሳትን
በተመጣጣኝ ዋጋ ያገኛሉ::

አድራሻ:-
ወላይታ ሶዶ ከተማ ሼል ሰፈር
ከባልቱ ሆቴል ፊት ለፊት
ስልክ 046-5- 51 37 61
091-1- 01 62 01



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን

## ንግድ እና ቅድስና

*በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትማችን በትዳር ሕይወት ውስጥ ቅድስናን እንዴት ለመግለጥ እንደ ሚቻል ተመልክተናል:: የትኛውም የሕይወት ጎዳና በፈተናዎች የታጠረ ነው:: ከዚህ በመነሣት የቅድስና ሕይወትን በትዳር ውስጥ ለመኖር ስንሻ የሚገጥሙንን ልዩ ልዩ ፈተናዎችና የመፍትሔ ሐሳቦች በትዳር ውስጥ ካሉ ምእመናን ተሞክሮና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅዎች ለመመልከት ሞክረናል:: ቅድስና በትዳር ውስጥም መገለጥና መዳበር የሚችልና የሚገባው መንፈሳዊ ሕይወት መሆኑን ተመልክተናል:: ለመሆኑ ነጋድያን የቅድስና ሕይወትን መኖር ይችላሉ? በንግዱ ዓለም ያለው የቅድስና ሕይወት መሰናክልና መፍትሔውስ ምንድን ነው? በዚህ እትማችን እኒህን ነጥቦች አንሥተን በመወያየት ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን:: መልካም ንባብ::*

### በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት ውስጥ

/መ/ር ደረጀ ጅማ/

አዳም አባታችን «ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ» /ዘፍጥ.3÷19/ ተብሎ ወደ መሬት ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ልጆቹ በተለያየ የሥራ መስክ ላይ በመሠማራት ምድራዊ እንጀራቸውን ሲበሉ ኖረዋል፤ እየኖሩም ነው:: ከነዚህ የሥራ መስኮች መካከል ንግድ ዋነኛው የሥራ ዓይነት ነው::

ንግድና ክርስትና የረጅም ዘመን ቁርኝት አላቸው፤ ክርስትና በዓለም ይስፋፋ ዘንድ በንግዱ ዓለም ተሠማርተው የነበሩ ክርስቲያን ነጋዴዎች ያበረከቱት አስተዋፅኦ ታላቅ ነውና:: በአገራችንም ከሚገኙ ክርስቲያኖች ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ምእመናን በዚህ ሥራ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ::

ይሁን እንጂ በንግድ ሥራ ተሠማርቶ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ የቅድስና ሕይወት መኖር ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ኀሊናዊ ጥያቄ ለአንዳንድ ነጋዴዎች ዘንድ አሉታዊ ምላሽ ሲያስከትል ለሌሎች ደግሞ አዎንታዊ ኾኖ ተገኝቷል:: ከሁለቱም ጎራ ያልቆሙ ነጋድያንም ሊኖሩ ይችላሉ::

አቶ መስፍን መንግሥቱ ይባላሉ:: መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰው በግል ሥራቸው የሚተዳደሩ የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው:: በንግድ ውስጥ የተሠማሩ ክርስቲያኖች የቅድስና ሕይወትን መኖር ስለ መቻል አለመቻላቸው ተጠይቀው ሲመልሱ:- «ቅድስና ለማንም ሰው ተራራ ነው:: ምክንያቱም ቅድስና:- መለየት፣ መክበር፣ መመስገን ነውና በቀላሉ አይደረስበትም:: ወደ ንግዱም ስንመጣ ቅድስናን በንግድ ዓለም ይዞ ለመጓዝ በእጅጉ ይከብዳል:: የተራራ ያህል ያዳግታል:: በትጋትና በረድኤተ እግዚአብሔር ግን ይቻላል::» ብለዋል:: ነዋሪነታቸው በክብረ መንግሥት ከተማ የሆነውና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩት መሪጌታ መሐሪ መለስም:- «በንግዱ ዓለም ውስጥ የቅድስና ሕይወትን የሚፈታተኑ ብዙ እንቅፋቶች ቢኖሩም እየነገዱ ቅዱስ ኑሮ መኖር ይቻላል» ሲሉ የአቶ መስፍንን ሐሳብ ይጋራሉ:: «ማንኛውም ሥራ ቅድስናን አይከለክልም» በማለት የሚጀምረው ደግሞ በደሴ ከተማ በንግድ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ያገኘነው ወጣት አበባው ደስታ ነው:: አያይዞም:-«ራሳችን ምክንያት ካልፈጠርንና ካልደከምን የትኛውም በጎና ጠቃሚ ሥራ የቅድስና ሥራን ላለመሥራት እንቅፋት አይሆንም::» ብሏል:: አንዳንዶች ግን አይደለም ለመሥራት በምድር ላይ ለመኖርም እየተፈተኑ ነው:: ክርስትና ግን የማይቻሉ መስለው የሚታዩ ነገሮችን ሁሉ፥ ሁሉን በሚችለው አምላክ ኀይልና በግል ጥረት እንደ ሚቻሉ ማሳያ መድረክ ነው:: በተለይ ነጋድያን ሆነው የቅድስና ኑሮ ኖረው ያለፉና እየኖሩ ያሉ ክርስቲያን ነጋዴዎች ታሪክና አማናዊ ሕይወት የሚታወቅ ስለሆነ አይቻልም የሚሉ ሁሉ ራሳቸውን መፈተሽ አለ ባቸው::

«በንግድ ዓለም ውስጥ የቅድስና ሕይወትን ለመኖር ይቻላል::» ሲባል ግን መሰናክሎች የሉበትም ማለት አይደለም:: የትኛውም ነጋዴ የቅድስና ኑሮን እንዳይኖር የሚፈታተኑት ፈተናዎች አሉ:: እነዚህ ፈተናዎች ከራሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ሊመነጩ ይችላሉ:: በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራውና የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆነው አቶ ሶምሶን:- ውሸት ነጋዴ ዎች ቅድስና እንዳይኖራቸው እያደረገ ያለ ክፉ ልምድ መሆኑን ሲገልጥ የሚከተለውን ብሏል:- «እርግጥ በንግድ ውስጥ ውሸት የተለመደ ነገር ሆኗል:: አብዛኛውን ሰው እንዲዋሽ የሚያደርገው የገበያ ውድድር ነው:: ጥሩና ጥራት ያለው ነገር ይዘህ ገበያ ላይ ስትቀርብ ሌላው አንተ ከያዝከው ዕቃ በደረጃ ዝቅ ያለ ነገር ይዞ በመምጣት ከገበያ ውጭ ሊያደርግህ ይሞክራል:: አንዳንዱ ደግሞ የእርሱ ዕቃ የተሻለ ተደርጎ እንዲታይለትና ገዢ እንዲያገኝለት ሲል ወደ ውሸት ይገባል:: አንዳንድ ጊዜ ዕቃዎች ላይደርሱልህ ይችላሉ:: ነገ ይመጣል ብለህ ትቀጥራለህ፥ላይመጣ ይችላል:: ከነገ ወዲያ ትቀጥራለህ፥ ላይደርስልህ ይችላል:: አንተ ይመጣል እያልክ በተስፋ ነው የምትቀጥረው:: ዕቃው ባልመጣ ቁጥር የገባኸው ቃል ወደ ውሸትነት እየተቀየረ ይመጣል::» በተጻራሪ ዳግማዊ ወጣት ዓለማየሁ «በንግዱ ዓለም የምትዋሸው ሠርተህ ለመግባት ስለ ምታስብ ነው::» ይላል:: አያይዞም:- «አንተ ያለህ ዕቃ አንተ ብቻ የምትይዘው ቢሆን ያለ ስጋት ትሠራለህ:: ሌላ ገበያ ላይ ግን የሳንቲም ለውጦች ይኖራሉ:: አንደኛ ደረጃም ሆን አልሆን እኔ ጋር ያለው አንደኛው ነው ብለህ ትዋሻለህ:: ይህ በንግዱ ዓለም ተለምዷል:: የቻ ይና የሆነውን የቱርክ ነው፤ የዱባይ ነው፤ የታይላንድ ነው፤ ትላለህ:: የዚህ ዓይነት ውሸቶች አሉ::» አቶ አበባው ደስታ ደግሞ በበኩሉ:- «ንግድ ላይ ካል ሸህ አትሠራም የሚባል ነገር አለ:: አንተ ጥሩ ነገር ልሥራ ብለህ ስትነሣ ከጎንህ ያለው ሰው በሌላ መንገድ ሊገባብህና ገበያህን ሊወስድብህ ይችላል:: የግድ እንደ እርሱ ዋሽተህ መሥራት ሊኖርብህ ነው:: ይህን መሰሉን ሥራ ስትሠራ ደግሞ ቅድስናህን እንዳትጠብቅ ያደርግሃል:: አንተ ፈጣሪህን እየፈራህ ስትሠራ ከአንተ በተጻራሪ ከጎንህ የሚሠሩ ጎረቤቶች ስለ




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሚኖሩ የግድ እንደ እነርሱ ሆነህ ለመሥራት ትገደዳለህ» በማለት ተገቢ ያልኾኑ ድርጊቶች በቅድ ስና ጉዞ ላይ የሚፈጥሩትን አስገዳጅ ሁኔታ አብራርተዋል:: መሪጌታ መሐሪ መለስ ደግሞ: - «በውድ ያልተገዛ ውን ዕቃ በውድ ገዝቻለሁ፤ የተበላ ሸውን አልተበላሽም፤ የአንዱን አገር ምርት የሌላ አገር ነው÷ እያሉ መዋሸት በንግዱ ዓለም የተንሰራፋ ነገር ነው::» ብለዋል::

እየተስተዋለ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሣት ውሸት በንግዱ ዓለም ውስጥ መንሰራፋቱንና የበርካታ ነጋዴዎችን የቅድስና ሕይወት ማጥቆሩን መገንዘብ አያዳግትም:: እኒህ አስተያየት ሰጪዎች ጥቂት ለማይባሉ ነጋዴዎች መዋሸት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ጨምረው ገልጸዋል:: ተቀዳሚው ግን ፍራቻ ነው:: የሚፈሩ ነጋድያን ካልዋሹ ሸጠው የማይገቡ ይመስላቸዋል:: ለውኃ፣ ለመብራት፣ ለቤት ኪራይ፣ ለግብር የሚከፍሉት የሚያጡ እየመሰላቸው ይሰጋሉ:: ባለመዋሸታቸው የሚበሉት፣ ለት/ቤት የሚከፍሉት የሚያጡና ከስረው የሚወድቁ እየመሰላቸው በመስጋት ይዋሻሉ:: መጋቤ ዓለማት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን:- «እናንተ እምነት የጎደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ» ይላል:: ማቴ.8÷26:: ሰው የሚፈራው እምነት ሲጎድለው ነውና::

እኔ ብቻ ሸጬ ልግባ የሚለው የራስ ወዳድነትና ስግብግብ መንፈስም በንግድ ዓለም ውስጥ ላለው ውሸት በምክንያትነት ይጠቀሳል:: ዐይኑ÷ ልቡ የሚሳሳ ሰው ለውሸት የተጋለጠ ነው:: ሌላውን ነጋዴ ,በልጦ ለመገኘት የሚደረገው ፉክክር መልኩን አጥቶ በቁጥር ለበዙ ነጋዴዎች መዋሸት ግፊት ይሆናል:: በበርካታው የንግድ ማኅበረሰብ ዘንድ ውሸት የንግዱ ሕጋዊ አካል ተደርጎ መቆጠሩ ደግሞ በንግዱ መስክ ለተንሰራፋው መጠነ ሰፊ ውሸት የዕድሜ ማራዘሚያ ሆኗል:: በዚህ የተነሣ እንግዲህ በአንዳንዶች ዘንድ በንግዱ ዓለም ያለው ውሸት እንደ ኃጢአት መቆጠሩ ከቀረ የሰነባበተ ይመስላል:: ቅድስና ደግሞ ሕገ እግዚአብሔርን በመፈጸም የሚገኝ ጸጋ ነው::

«በሐሰት አትመስክር» የሚለውን ሕግ በየቀኑ በመተላለፍ እንዴት ወደ ቅድስና መድረስ ይቻላል? ዘጸ. 20÷16:: ወገኖቻቸውን በመዋሸት ለሚያታልሉ ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ይላል:- «ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ፣ ታታልሉማላችሁ ያውም ወንድሞቻችሁን::» 1ቆሮ.6÷7-8:: ሸማቹ ሕዝብም ስለሚገዛቸው ነገሮች ያለው ቅድመ ግንዛቤ በቂ ስለማይኾን ወይም አማራጭ ስለ ማይኖረው ባለማወቅ ያለ በቂ መረጃ ይገበያያል::

«እውነቱን እየነገርክ ስትሸጥ ደግሞ ሰውየው ላይረዳህ ይችላል:: ያ ሰው የራሱን ዋጋ ነው ያቀረበው:: አንተ ደግሞ መሸጥ ይገባዋል ብለህ የወሰንከው ዋጋ ይኖራል:: የዕቃውን ምንነትና ዋጋውን ባልተረዳልህ ጊዜ ልትምል ትችላለህ:: እንደ ሚመስለኝ መሐላ በራሱ ከቅድስና ጎዳና እንድትወጣ ያደርግሃል፤ ወይም ልኑር ብለህ የተነሣህለትን የቅድስና ሕይወት ያሰናክልኻል» በማለት በንግዱ ዓለም ያለውን የቅድስና እንቅፋት የጠቆመው ደግሞ ወጣት ዓለማየሁ ውቤ ነው::

አቶ ሶምሶን ግላዊ ተሞክሯቸውን ሲገልጡ:- «ሰው በንግድና በክርስትና ሕይወት መካከል ያለውን መሠረታዊ እውነት አለማወቁ ራሱ በንግዱ ዓለም ለተሠማሩ ነጋዴዎች ከቅድስና ሕይወት ማፈንገጥ ምክንያት ይሆናል:: አንድ ገጠመኜን ልንገርህ፤ በአጋጣሚ አንድ ሰው ዕቃ በዱቤ ይወስዳል:: ይመጣል እያልኩ ብጠብቅ የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: ከዕለታት አንድ ቀን መንገድ ላይ ተገናኘን:: በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባለኝ አንዳንድ አገልግሎት ስሳተፍ ያውቀኛል:: እና ብሬን ከፈለኝ አልኩት:: ምን አለ መሰለህ÷ «ክርስቲያን አይደለህ፤ እንዴት እንደዚህ ትላለህ?» አንዳንድ ሸማች አንተ ነጋዴ ብትሆን እንኳን ያንተ የሆነውን እየጠበና የሰው የሆነውን እያከበርክ መሄድ እንዳ ለብህ ይዘነጋል:: ገንዘቤን ስጠኝ አይ አል ሰጥም በሚል አለመግባባትና ለክርስትና ሕይወት በማይመች ቦታ ብዙ ነጋዴዎች ወድቀዋል:: *በስድብ፣ በጥልና በበቀል የተከበበ ሕይወት ለቅድስና ቦታ የለውም::»*

አንዳንድ ነጋዴዎች ልብ የሚሚገርክ ተግባር አላቸው:: የዕቃቸውን ምንነት ለማስረዳትና ዋጋውን ለመንገር ሲሉ አፋቸውን ለመሐላ አያላቅቁም:: የትኛውም ገዢ ይመለስ ዕቃቸውም ሳይሸጥ ይዋል ይደር እንጂ አይምሉም:: እንዲህ ዓይነት ነጋዴዎች ምስጉኖች ናቸው፤ ባለመማል ከሚገኘው ቅድስና ተካፋይ ሆነዋልና:: ለሁሉም የሰው ልጆች አንድ መብት ተሰጥቷቸዋል፤ እውነቱን እውነት÷ ሐሰቱንም ሐሰት እንዲሉ:: ነጋዴዎችም ሆኑ በሌላ ሥራ የተሠማራነው ወገኖች በሐሰት እንጂ እውነት ለሆነ ነገር መማል ተገቢ ይመስለናል:: በመሐላችን ውስጥ ስመ እግዚአብሔርን፣ ስመ ወላዲተ አምላክን፣ ስመ መላእክትንና ስመ ቅዱሳንን ጠርተን በመማል አድማጮችን የእምነት ሰዎች ናቸው ብለው ፈቃዳችንን እንዲፈጽሙልን እንፈልጋለን:: «እኔ እውነት ነኝ» ያለው መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ግን:- «ለቀደ ሙት:- በውሸት አትማል፤ ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ:- *ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግዚአብሔር የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና:: ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን:: ከነዚህም የወጣ ከክፉ ነው::» ብሏል:: ማቴ.5÷33-37::*

**ንግድና ክርስትና የረጅም ዘመን ቁርኝት አላቸው፤ ክርስትና በዓለም ይስፋፋ ዘንድ በንግዱ ዓለም ተሠማርተው የነበሩ ክርስቲያን ነጋዴዎች ያበረከቱት አስተዋፅኦ ታላቅ ነውና::**

ስለዚህ መሐላ በክፉት ላይ የበቀለ ልማድ ነው:: ክፉ ነው የተባለውን መሐላ አዝሎ በቅድስና መጓዝ ይከብዳል:: በዚህ ምክንያት ከቅድስና ኑሮ ያፈነገጡ ነጋዴዎች አሉ::

ክርስትና የእግዚአብሔር ሕግ፣ የራስና የሌሎች መብትና ግዴታ፣ የአገርም ሕገ መንግሥት የማይከበርበትና የማይጠበቅበት ሕይወት አይደለም:: የአንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ መሳተፍም የበለጠ ዋጋ ለማግኘትና የተጣለበትን መንፈሳዊ ግዴጅ ለመወጣት እንጂ ያበደረውን መልሶ ላይቀበል፣ የገዛውን ላይሸጥ፣ ከኃጢአት ውጭ በኾኑ በጎ ሥራዎች ላይም ተሳትፎውን ሊያቆም አይደለም:: ስለዚህ በክርስትና ውስጥ ያሉ ነጋዴዎችም ሆኑ ሌላው ሕዝብ አንድ እውነት መረዳት አለባቸው-ድጋፍና ርዳታ በአግባቡ ጠይቆ መቀበል፣ የተበደሩ ትንም መመለስ ተገቢ መሆኑን::

ተበዳሪው የወሰደውን ለመመለስ /ለመክፈል/ ጊዜ ይሰጠኝ ካለ ግን ጊዜውን ማራዘም መልካም ይሆናል:: በዚህ ጊዜ አበዳሪዎች ስንቶች ለእነሱ ጊዜ እንዳራዘሙላቸው ያስቡ:: እግዚአብሔርም መዳናቸውን ወደ ያረዘመላቸውን ዕድሜ ዘመናቸውን ያስታውሱ:: ተበዳሪውም ጊዜ ስለ ተራዘመለት ቸል ተኛ መሆን የለበትም:: «ጊዜው የተራዘመ ብድር መጨረሻ ላይ ይረሳል» የሚለው የተበዳሪዎች ይትበሃል በክርስትና ዐይን ሲታይ ስሕተት ነው፤ ጥፋት ነው:: ተበዳሪው ለመክፈል አቅም እንዳጣ ባዩ ጊዜ የሚምሩ አበዳሪዎች እግዚአብሔርን ያስደስታሉ:: «የሚከፍሉት ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው» /ሉቃ.7÷42/ የሚል ምሳሌ ጌታ በወንጌል ተናግሯል:: ምሳሌዎቹን ደግሞ ሌሎች ይከተሏቸውና ይጠነቀቁባቸው ዘንድ መጻፋቸውን ማስተዋል ተገቢ ነው:: ፍጹም መክፈል ያልቻሉትን ሰዎች የሚምሩ አበዳሪ ነጋዴዎች: - «የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ይማራሉና» ተብሎ ተጽፎላቸዋል:: ምሕረትን ከእግዚአብሔር የሚቀበሉቱና የሚያገኙቱ ደግሞ ለቅድስና ሕይወት የቀረቡ ናቸው::

«በንግዱ ዓለም ያሉ አንዳንድ ነጋዴዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ንዋይ እግዚአብሔር ላልፈቀደው ቅምጥልነት ሲያውሉት ይስተዋላሉ::» በማለት አስተያየታቸውን የጀመሩት ደግሞ አቶ መስፍን መንግሥቱ ናቸው:: ገጠመኛቸውን በዚህ መልኩ ነበር የገለጡት: - «ትዳር ልመሠርት ስዘጋጅ ጋብቻዬ መንፈሳዊ መሆኑን ያወቁ ነጋዴ ጓደኞቼ በመገረም ወደ እኔ መጡ:: "ሰርግህን ለቅሶ ልታስመስለው ነው እንዴ? ሒልተንን በሚያኽል ሆቴል ደግስህ እንዴት ባንድ አይኖርም" አሉኝ:: እስኪ ለቅሶ እንደ ሚሆን ታያላችሁ፤ እግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ተጠርቶ ሐሜትና ጉድለት የለም። ኑና እዩ፤ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን እኛም ተደስተን እንውላለን አልኳቸው። እግዚአብሔር ክብሩን በሰርጌ ሊገልጥ ፈቅዶ ብዙ ሁኔታዎችን አመቻቸ። በሒልተን ሆቴል ለመጀመሪያ ጊዜ ያን ያህል ቁጥር ያላቸው መዘምራን ተገኝተው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ዋሉ። ነጩም ጥቁሩም በሥርዐቱና በአገልግሎቱ ተደነቁ። መንፈሳዊነት በማይታይበት ቅምጥል ሰርግ ተታለው የነበሩ ነጋዴ ጓደኞቼ ሁሉ፡- "በእውነት አሰናክለንህ ነበር፤ በሕይወታችን አይተነው የማናውቀውን ሰርግ አየን፤ አንዲት ደቂቃ የቆየን ሳይመስለን ያንን ሁሉ ሰዓት በምስጋናና በመገረም አሳለፍነው» ብለውኛል። እና መጠኑን ያለፈና አጓጉል ድርጊቶች የተቀላቀሉበት የቅምጥልነት ሕይወት ነጋዴዎች ለተቀደሰ አነዋወር እንዳይተጉ እየከለከላቸው ነው።»

በቅድስና ሕይወት ለመሸለም የፈለገ ሰው ሁሉ በመጠን መኖርን መልመድ አለበት። ክርስቲያን በመጠኑ የሚኖረው ስላጣና አጎድላለሁ ብሎ ስለሚሳሳ ሳይሆን ሊውጠው እያገሣ የሚዞረው ዲያብሎስ እንዳይቆረጥመውና ከቅድስና ሕይወቱ እንዳይለየው ነው። 1ጴጥ.5÷8-9። ነጋዴውም ሆነ ሌላው የእግዚአብሔርን ውዱንና ፈቃዱን ትቶ በሥጋ ኑሮው ቢቀማጠል የግል ምርጫው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ያለ አይምሰለው፤ በኀሊናው ሞቷል። «ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት» ተብሎ እንደ ተጻፈ። 1ጢሞ. 5÷6። ለጽድቅ ሞቶ ለኃጢአትና ለቅምጥልነት ሕያው የሆነ ሕይወት ለቅድስና ደግሞ በድን ነው። ይህ ገንዘብ አለን የሚሉ ነጋዴዎች ብቻ ችግር አይደለም፤ የሌሎችም እንጂ። ስለዚህ ሌሎች ችግረኛ ወገኖችንም በማሰብና በመርዳት እንዲሁም በኃጢአት ከተሞላ የቅምጥልነት ሕይወት በመራቅ ቅድስናን ገንዘብ ማድረግ ያሻል።

አቶ አሸናፊ ፈጣ ይባላል። የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲሆን በጎጃም በረንዳ አካባቢ ቅቤና ማር ከሚነግዱ ነጋዴዎች መካከል አንዱ ነው። «በቅቤና በማር ንግድ ውስጥ ያሉ ነጋዴዎች የቅድስና ሕይወት እንዳይኖሩ ችግር ሆኖባቸዋል» ሲል የሚከተለውን ጠቅሷል። «የቅቤና የማር ንግድ በጣም አስቸጋሪ ሥራ ነው። ገበያ ላይ ከምታገኛቸው ቅቤና ማር መካከል የተቀየጡና ትክክለኛ ቅቤና ማር ያልሆኑ አሉ። ቅቤውን በውኃና በተለያየ ነገር ይቀይጡታል። ማሩ ደግሞ ከሰፋፍና ከስኳር እየተቀየጠ ይዘጋጃል። ለዚህ ድርጊት ብዙ ምክንያቶች ይደረደራሉ። እውነተኛ ነጋዴዎች ንጹሕ ማርና ቅቤ አቅርበው ያንኑ በውድ ዋጋ ይሸጣሉ። በዋጋው ሊገዛ የሚችል ማኅበረሰብ ቁጥር ደግሞ ጥቂት ነው። ለጥቂት ግለሰቦች ከምትሸጠው ጥቂት ኪሎ ማርና ቅቤ ውስጥ ደግሞ በቂ ትርፍ አግኝቶ ለመኖር ይከብዳል። ሌላው ትላንት ከአንተ ጋር አብሮህ ይሠራ የነበረ ሰው ይህን ሥራ ሠርቶ ከአንተ የተሻለ ኑሮ ሲኖር ታያለህ። የሚያይህ ሰው ደግሞ በሐሰት ከመክበር ይልቅ በእውነት መደኽየትን የመረጥክ አይመስለውም። «ይህ ሰነፍ ነው፤ አይሠራም» ይልሃል እንጂ «በእውነት ስለ ሠራህ ነው» አትባልም። ሌላው በዚህ መልኩ ካልሠራኹ ብዙ ገንዘብ ማግኘት አልችልም የሚል ሐሳብ ይመጣብሃል። ቅቤና ማር ደባልቀው የከበሩ ባልንጀሮችህን ስታይ የባሰ ልትገፋፋ ትችላለህ።

የራሴን ታሪክ በምሳሌነት ልጥቀስ። የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ ወደዚህ ሥራ የገባ ሰው ከማርና ከቅቤ ጋር ሌሎች ነገሮችን በመቀየጥ ነግዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሱ የሆነ መኪና፣ ቤትና ብዙ ነገሮች ያዘ። በዚህ ጊዜ እኔስ የምፈዘው ለምንድነው አልኩ። ቅቤና ማር በመደባለቅ ልሠራ ዕቅድ ያዝኩኝ። ኀሊናዬ ግን በተቃውሞ ሞገተኝ። በዚህ ጊዜ ወደ አንድ አባት ሄድኩና አማከርኳቸው። «ልጄ እዚህች መሬት ላይ ስንት ዓመት ትኖራለህ?» አሉኝ። አላውቅም አልኳቸው። «ይሁንልህ እንበልና ሁለት መቶ ዓመት ኑር። ከዚያ በኋላ የት ትገባለህ? በዚህ ሥራህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ታገኛለህን? የሰው ልጅን አካላዊ ጤንነት እያጎደልክና ሕይወት እያጠፋህ ኖረህ ገነትን የምትወርስ አይምሰልህ።» አሉኝ። እኔም ተጸጸትኩ፤ ያለኝን ይባርክልኝ ብዬ በቀደመው እውነተኛ ሥራዬ ጸናሁ። የጌታን የመከራ መስቀል በማየትና ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆን ልኑር ካላልክ የቅድስናን ሕይወት በንግድ ዓለም መምራት ይከብዳል። «ያለኝን ይባርክልኝ» እያለ ትርፉን ለማብዛት ለማይሠራ ነጋዴ ለቅድስና ሕይወት መትጋት በርግጥም ይከብዳል።»

እግዚአብሔር ያልፈቀደው ሥራ ሁሉ በሠሪውም ሆነ በሚሠራበት ሰው ላይ የሚያስከትለው ሥነ ልቡናዊ፣ መንፈሳዊና አካላዊ ጉዳት አለ። ለምሳሌ ይላል አቶ አሸናፊ ፈጣ፡- «ለምሳሌ ቅቤ ውስጥ ሞራ ይገባል፤ ሙዝ ይገባል። ሌላም ከዚህ የባሱ ብዙ ነገሮች ይገቡበታል፤ ማር ውስጥ የቀለጠ ስኳርና ሰም ይታጀላል። በአጠቃላይ በኛ ሥራ ውስጥ በጣም የሚያስጸይፍ ብዙ ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች ተጠቃሚውን ሕዝብ ለበሽታና ለሞት እየዳረጉት ነው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የመጀመሪያው ተጎጂዎች በዚህ ሥራ ላይ የተሠማሩ ናቸው። «አንድ ወንድም ትዝ ይለኛል። ቅቤና ማር ደባልቆ በመሸጥ ይተዳደር ነበር። አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፡- «ብር እፈልግ ነበር÷ አገኘሁኝ፤ ቤት እፈልግ ነበር÷ ቤት ገዛሁ፤ መኪና እፈልግ ነበር÷ አራት አምስት መኪና ገዛሁ፤ የትዳር ጓደኛ እፈልግ ነበር÷ በመንፈሳዊ ጋብቻ ትዳሬን መሠረትኩ፤ ለፊተኛው ክፉ ሥራዬም ንስሐ ገባሁ። ይህን ሥራ ትቼ ሌላ ሥራ ጀመርኩኝ። ነገር ግን ትልቅ ነገር አጣሁ።» ምን? አልኩት፡- «ጤናዬን አጣሁኝ» አለኝ። ይህ ሰው ለገንዘብ ሲል የብዙዎችን ጤና ሲጎዳ ቆይቷልና የሠራውን እፎይ ብሎ በሚበላበት ጊዜ በሽተኛ ሆነ። የክፉ ሥራው ደመወዝ በሥጋው እየተከፈለው ይሆንን ስል አስባለሁ።... «በዚሁ መንገድ የከበረ ሌላ ወንድም ዐውቃለሁ። ብዙ ሀብት አለው። ትዳር ከያዘ ስድስት ዓመት ቢሆነውም ልጅ የለውም። በዚህ ሥራ ይህን ሁሉ ሀብት አካብተሃል። ለመሆኑ የኀሊና እርካታ አለህ? ብዬ ጠየቅኹት። መልሱ አስደንጋጭ ነበር። "ብሞት ይሻለኛል» አለኝ» ሲሉ በዚሁ ሥራ የተሠማሩትን ሰዎች ኀሊናዊና ሥጋዊ ስቀቀን የነገሩን በጎጃም በረንዳ አካባቢ በቅቤና በማር ላይ የተሠማሩ አንድ ነጋዴ ናቸው።

«አንድ ሰው ባምታታ ቁጥር ሰላሙን ያጣል» ይላሉ አቶ መስፍን መንግሥቱ። «አምታተነው የምንሸጥለት ሰው አንዳንድ ጊዜ ምንም ላይሆን ይችላል። የቻይናውን ጨርቅ የአሜሪካ ወይም የጣልያን ጨርቅ ብለን ስንሸጥለት በጨርቅ ላይ ያለው ዕውቀት አናሳ ስለሆነ ወይም ስላመነን ሊገዛን ይችላል። ለእርሱ ልብሱ ልብስ ነው። እውነተኛ ዕቃ ገዛሁ ብሎ ሊረካ ሁሉ ይችላል። ሻጩ ግን ያልሆነውን ሆነ ብሎ በመሸጡ ሁልጊዜ በጸጸትና በኀሊናው ዳኝነት ሲከሰስ ይኖራል።

እግዚአብሔር ሰዎች ለፈጸሙት መተላለፍ ንስሐን ያዘጋጀ ቢሆንም ለማይመለሱና በክፉ ሥራቸው ለጸኑ ግን ሁሌ የሚያጠፋ ቅጣት ባያዝም በመጠኑ ሳይቀጣ አይተውም። የሰዎችን ጤና ለሚጎዱና ላባቸውንም በማይገባ መልኩ ለሚበዛ ብዙ ነጋድያንም እንዲሁ፡- «አንተን ግን ፈጽሜ አላጠፋህም፤ በመጠን እቀጣሃለሁ፤ ያለ ቅጣትም ከቶ አልተውኽም» ይላል። ኤር.30÷11። ይህ ቅጣት ከመታዘዙ በፊት በኀሊናቸው ክስ የሚረቱና የሚጸጸቱ ነጋድያን ሰላምን ያተርፋሉ። አለበለዚያ «ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል» ተብሏልና እየሸሹ ይኖራሉ።

«ከሁሉም የሚገርመኝ» ይላሉ አቶ አሸናፊ፡- «ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱና ከንስሐ አባቶቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በዚህ ሥራ ተሠማርተው መገኘታቸው ነው። እነዚህ ባለማወቅ ሳይሆን በድፍረት የሚሠሩ ይመስለኛል። የንስሐ አባቶች ይህን አይወቁ ወይም እያወቁ ዝም ይበሏቸው አላውቅም። እነዚህ ሰዎች በሥጋቸው ቢገዝፉም መንፈሳቸው የመነመነ ነው።»

እንደ መሪጌታ መለሰ አገላለጽ በንግዱ ዓለም ያለውን መልካም የፉክክር መንፈስ በተበላሸ መንገድ የሚጠቀሙበት አሉ። ለማትረፍና ለማደግ የሚሮጡ ነጋዴዎች የመኖራቸውን ያህል ሌላውን ከንግዱ ዓለም አክስሮ ለማስወጣት የሚሮጡ አሉ። ገንዘብ በመያዝህ የተነሣ ገንዘብህን የሚፈልጉ ሰዎች ይቀርቡሃል። በልባቸው ያለውን ሐሳብ ለመፈጸም ሲሉ ከእግዚአብሔር በሚለይ የኃጢአት ሥራ ያባብሉሃል ወይም ያለማምዱሃል። እነዚህ ነገሮች ነጋዴዎችን ከቅድስና ሕይወት ያርቃሉ።

ሌላው አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው፡- «ክርስቲያኑ ነጋዴ ሊኖር ከሚፈልገው የቅድስና ሕይወት ማራቅ ብቻ ሳይሆን የቅድስናው መሠረት ከሆነው እምነቱ የሚያርቀው ችግር የበለጠ አሳሳቢ ነው» ይላሉ። የአሕዛብ ርብርብ የሰነበተና የታወቀ ቢሆንም መናፍቃኑ በይበልጥ አሳዛኝ የሆነ ሩጫ ጀምረዋል። ችግሩ እንዲህ ነው፡- አንዱ የተሠማራበት ሥራ የሚሳካና ውጤታማ መስሎ ከታየው ሌሎች ሁለት ሦስት ጓደኞቹን ጠርቶ በዚያ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ለምሳሌ 15 ሰዎች ባሉበት ሥራ ውስጥ አምስቱ ፕሮቴስታንት ቢሆኑ ሌሎች አምስት የራሳቸውን ሰዎች ወደ ሥራው ያስገባሉ:: እንዲሁም የእነሱ እምነት ተከታዮች የሆኑትን አድራሻ ለእምነት አባሎቻቸው በመበተን ከሌላ ነጋዴ እንዳይገዙ እያደረጉ ነው::» ይላሉ::

እነዚህ ወገኖች ለአድራጎታቸው የትኛውንም ምክንያት ሊያቀርቡ ይችላሉ:: በቤተ ክርስቲያን ልጆች ላይ የሚያደርሰውን ችግር ማየቱ ግን ግድ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ ሰው ለሥጋዊ ትርፍና ጥቅም ሲል ወደነሱ ዘንበል እንዲል ፈልገዋል:: ምድራዊ ከበሬታና ኃላፊ ባለጠግነትን ከሃይማኖት ይልቅ የሚያስቀድሙ ስግብግቦች የዚህ ሰለባ ናቸው:: «ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሠጥምና በሚያስንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ፤ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና:: አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ::» ተብሎላ ቸዋል:: 1ጢሞ.6÷9-10:: እንደዚህ ያሉትን ጥቅም ፈላጊዎች ለማጥመድ ነው ይህን መረብ የዘረጉት:: በምድራዊ ሀብት መክበር ችግረኛውን ሕዝብ በእምነት እኔን ከመሰልክ ልቀጥርህ /ላሠራህ/ እችላለሁ ለማለት እንደ ሚያስችላቸው ስለሚያውቁ ይህን አስገዳጅ ሁኔታ ይፈጥራሉ:: ከሁሉም በላይ ነውረኛ የሆነው ሐሳባቸው በዚህ መልኩ ክርስቲያኑን ነጋዴ ከገበያ ውጭ ማድረግ አልያም በእነርሱ የኢኮኖሚ ጥላ ሥር እንዲወድቅ ማድረግ ነው:: ያኔ:- «እኛ እኮ በዚህ ምድር እንኳን የተመቸን ትክክለኛ አምልኮት ስላለን ነው» ይላሉ፤ ዛሬስ ቢኾን በአንዳንድ ቦታ የሚሉት ምን ሆነና::

እነዚህንና ሌሎች ዓላማዎቻቸውን ለማስፈጸም ብለው በንግድ ዓለም ውስጥ የዘረጉት አስነዋሪ ድርጊት አንዳንድ ክርስቲያኖችን ከቅድስና ሕይወታቸው ብቻ ሳይሆን ከእምነታቸውም እንዳይነቅላቸው ያሰጋል:: ይህ እንግዲህ በንግዱ ዓለም ባሉ ሰዎች ላይ የተነጣጠረ ፈተና ነው::

ለንግዳቸው መቃናት መፍትሔ ይሰጧቸው ይመስል በመንደራቸውና ከከተማ ውጭ በሚኖሩ ጠንቋዮች ቤት ደፋ ቀና የሚሉ ነጋዴዎችም የቅድስና ሕይወታቸውን ያረከሱ ናቸው:: የቱንም ያህል ገንዘብ ለእግዚአብሔር ቤትና ለአገልጋዮች ቢያፈሱ ራሱን አምላክ ያደረገውን ጠንቋይ አምልከዋልና የቅድስናን ሕይወት ሊኖሩ አይችሉም::

*ቃለ እግዚአብሔር ብዙዎችን ምን እናድርግ ያሰኝ አይደለምን? ነገር ግን መሰማት÷መደመጥ አለበት:: ሰዎች ቃሉን ከሰሙ በኋላ ነው ጥፋታቸውን አምነው ንስሐ በመግባት የቅድስናን ሕይወት ሊጀምሩ የሚችሉት::*

በንግዱ ዓለም የተሠማሩት ነጋድያን የጠቀሷቸውም ሆኑ ያልጠቀሷቸው ምክንያቶች በንግዱ ዓለም ያለው ማኅበረሰብ ለቅድስና ሕይወት እንዳይተጋ እንቅፋት እየሆኑበት ነው:: ምን ቢያደርግ ከነዚህ ችግሮች ተላቆ ለቅድስና ሕይ ወት ሊበቃ ይችላል::

«በንግዱ ዓለም መዋሸትም ሆነ አለመዋሸት የባለቤቱ ምርጫ ነው:: ነጋዴው ከበረታ አለመዋሸት ይችላል:: ባልተገዛበት ዋጋ ተገዝቷል ማለትን መተው ይችላል:: የተበላሸውንም ዕቃ ሊያዋጣ በሚችል ዋጋ መሸጥ ወይም ተበላሽቷል ብሎ ማሳወቅ ይቻላል:: ሰውን ባለማታለል፣ ዐሥራት በኵራት በማውጣት ቅድስናን በንግዱ ዓለም መተግበር ይቻላል:: እየሠሩ ነዳያንን መርዳት በተለይ ራስን እየረዱ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ታላቅ ደስታን ይፈጥራል» ያሉት መሪጌታ መሐሪ መለስ ናቸው::

ወጣት አበባው ደስታ መፍትሔው ይኸ ነው ይላል:- «ሁል ጊዜ ፈጣሪህን ከፈራህ ከኀሊና ሕግ የተነሣ ኃጢአት ልሥራ ብትል እንኳን እንዳትሠራ ትገደዳለህ :: ስለዚህ ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል መመከርና መገሥጽ አለብን:: ፈሪሃ እግዚአብሔር በንግዱ ዓለም ያለነውን ሰዎች ከምንሠራው ኃጢአት ይጠብቀናል:: ቃሉን መስማት ብቻ ሳይሆን በቃሉ መኖር ስንጀምር ነጋዴዎች በንግዱ ዓለም ቅድስናን እንኖረዋለን::» «በአግባቡ እየሠራህ በአግባቡ ማትረፍ አለብህ» የሚለው ደግሞ ወጣት ዓለማየሁ ውቤ ነው:: «ክርስቲያን ስለሆንክ ብቻ ማግኘት ከሚገባህ በታች ማግኘት የለብህም:: ከስረህ መሸጥም አይጠበቅብህም:: ከአቅም በላይ ማትረፍ አግባብ አይደለም:: ለውሸት የሚዳርገውም ስግብግብነት ነውና ይህን መንፈስ እየተቃወሙ ቅዱስ የሆነውን ኑሮ መኖር ይቻላል::»

እንደ አቶ ሶምሶን አገላለጽ ስሜታዊ አለመሆንና በክርስትና ሃይማኖት መጠንከር ነጋዴዎችን ከድካም አላቆ ለቅድስና ያዘጋጃል:: «አንዳንድ ጊዜ ንግድ ውስጥ ሳታስበው ስሜታዊ የምትሆንባቸው ጊዜያት ይኖራሉ:: በምትወ ስደውም እርምጃ ወዳልተፈለገ ነገር ትገባለህ:: አብዝቶ ወደ ቤተ ክርስቲን መቅረብ የተረጋጋ መንፈስ እንዲኖረን ያደርጋል:: የተረጋጋ መንፈስ ሲኖረን ደግሞ ለውሳኔያችን ሁለቴ ማሰብ እንጀምራለን:: ሁለቴ ማሰብ ስትጀምር ስሜታዊነትህ ስለ ሚቀንስ ትዕግሥት ይኖርሃል:: የትዕግሥት ፍሬ ደግሞ መልካም ነው:: እንዲሁም ነጋዴዎች በክርስትና ሕይወታቸው የበለጠ ጠንካሮች ቢሆኑ ከዚህ ችግር ተላቀው የቅድስናን ሕይወት መምራት ይጀምራሉ:: ንስሐን የመሰለ ስጦታ ስላለ በዚህ ድርጊት የወደቅን ሁሉ ዛሬ ተነሥተን መንጻትና የተቀደሰ አነዋወር መጀመር እንችላለን::»

ነጋዴዎች ዋሽቶም ሆነ እውነቱን ተናግሮ መሸጥ የእነርሱ ውሳኔ መሆኑን እስካወቁ ድረስ ውሳኔያቸውን በእውነት ላይ ማጽናት አለባቸው፤ ነጻ ገበያ ቢባልም በሐሰት መራወጥ አግባብ አይደለም:: ቃለ እግዚአብሔርን በተገኘው አጋጣሚ ለማንበብና ለመስማት መቸኮልም ከስሕተት መንገድ ተመልሶ በተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ያበቃል:: አቶ አሸናፊ እንደሚሉት:- «በንግድ ላይ የተሠማራን ሰዎች ከሥራችን ጠባይ የተነሣ ቃለ እግዚአብሔርን በአግባቡ ስለማናገኝ በየሥራ ቦታችን ሊሠራጭ የሚችል በራሪ ወረቀትን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች የተዘጋጁ ትምህርቶች ቢሰጡ መልካም ነው:: በንግዱ ዓለም ያለውን ችግር በቃለ እግዚአብሔር እየፈቱ ቢያቀርቡልን ይመረጣል:: የበረቱት በካሴትና ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ይማራሉ:: ለነዚህም ሆነ ለሌሎች በጽሑፍ መልክ ባሉበት ቦታ ትምህርቱ ቢዳረስ የሚያስደስት ለውጥ ማየት ይቻላል::» ይላል:: «እምነት ከመስማት ነው:: መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» ተብሏልና:: ሮሜ.10÷17::

የአዲስ አበባ ነዋሪና ኢንቬስተሩ አቶ መስፍን መንግሥቱ በንግዱ ዓለም ለተሠማሩ ሁሉ የሚከተለውን ብለዋል: - «ነጋዴ እውነት ቢናገር÷ የሰው ሐቅ ባይጨምር የተባረከለትን ይዞ ቢገኝ ከሚያተርፉት በላይ አትራፊ እንደ ሚሆን አምናለሁ:: ውስጣችን ቅድስናን ቢጠማም <ከሰው አንሻለሁ> የሚለው ፍርሃታችን አንቆ ይዞናልና ከዚህ መላቀቅ አለብን:: ዓለምን አተርፋለሁ ብሎ በመደባለቅ፣ በመለዋወጥና፣ በመዋሸት የሚገኝ ንዋይ መጨረሻው ነፍስንና ሥጋን ይጎዳል:: ሰው ዓለሙን ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢጎዳ ምን ይጠቅመዋል:: በንግድ ሥራ ላይ ስን ሠማራ ከመጠን በላይ እንድናተርፍ፣ አጭበርብረን እንድንከብር፣ የተለያዩ ኃጢ አቶችን እንደ ንፈጽምና የሚያስነቅፍ የቅ ንጦት ሕይወት እንድንመራ አይደለም:: በንግዱ ዓለም የምንኖረው ኑሮ ለእግዚአብሔር ክብር መሆን አለበት:: እግዚአብሔር የሚመሰገነውና የሚከበረው በኛ የቅድስና ሕይወት ነውና:: ስርቆት፣ ውሸት፣ ማታለል የሰይጣን ናቸው:: ሰይጣ ንን የምናስደስት ከሆነ የእግዚአብሔር አይደለንም:: ቅድስና መጠራት÷መለየት÷ መመረጥ ነው:: በክርስትና የእግዚአብሔር ሆነን ከተመረጥን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኳዝ አለብን:: የሰው ልጅ ኅሊናውን ለሰይ ጣን፣ ለሰበብና ለፍርሃት ካላስረከበ በስተቀር የሌሎችን ለመንጠቅ መስገብገብ ወደ አይደርስም::

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ፍጥረትን ተመልከት
# ቀመረ እግዚአብሔር ቀመረ ውበት

/ምስጢረ ናግራን/

/ካለፈው የቀጠለ/

«ባለፈው እትማችን በጀመር ነው አዲሱ የሥነ ኪነ» ዓምዳችን የሥነ ሕንጻ ባለሞያው» «ምሥጢረ ናግራን» የፍጥረተ እግዚአብሔርን የውበት ቀመር ገላልጠው ሊያሳዩን ሞያዊ ወጋቸውን ጀምረዋል:: እንደ ጸሐፊው እምነት የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ቅርጽና ሞገድ አለው፤ ቅርጹንና ሞገዱን በማቀናበር በጥልቀት ወደ ውስጥ በግዝፈት ወደ ላይ መመርመር ራሳችንንና አካባቢያችንን ለማወቅ ይረዳናል:: የዘመኑ ሥልጣኔ መነሻና ትኩረት፥ የሳይንስና ቴክኖሎጂው ምጥቀት- አዘቀቱ፣ ነቁ፣ምንጩ፣ መምጫው መገለጫው ቅሉ ይኸው ነው:: በዚህ እትማችን «ምሥጢረ ናግራን» ሞያዊ ወጋቸውን በመቀጠል ቀደም ሲል የሰጡትን ሐተታ ተጨባጭ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ምሳሌዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ይጠቁሙናል:: መልካም ንባብ::

## በውስጡ ያለውን እናስተውል

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋ ሥጫ እመቤታችንን በተለያዩ ዕፀዋትና የከበሩ ድንጋዮች ሲመስላት የምናስተውለውም የከነበሩ ነገር አለ:: አንደኛው:- የእመቤታችንን ክብርና ቅድስና ከእምነታችን አንጻር እንረዳበታለን:: ሁለተኛው:- አባ ጊዮርጊስ ስለ ዕፀዋትና ድንጋዮች ወይም ስለ መሰለበት ነገር ያለውን ጥልቅ ዕውቀት እናስተውልበታለን:: ሦስተኛ:- የተመሰለባቸው ነገሮች ለምን አገልግሎት እንደ ሚውሉ ዐውቀን የተካበተባቸውን ዕውቀት እግዚአብሔር በሰጠን ችሎታ ተረድተን እንድንጠቀምባቸው ያስችለናል::

እመቤታችንን:- «ስሂንና ሜኢ ሰሌሆት በውስጧ የተጨመረባት ሙዳይ ሆይ...» ይላታል:: /አርጋኖን ዘቀዳሚ 5÷2/:: ለመሆኑ እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው? ለምን ይጠቅማሉ? ባሕርያቸውና ቅርጻቸውስ ምንድን ነው? የእንኮይ እንጨት ከጥላ ጋር ያለው ግንኙነት፤«የዘይት እንጨት» ከአቋቋም፣ ከደም ግባት፣ ከማማር ጋር ያለው ግንኙነት፤ የበለስ እንጨት ስለ መከለያነቱና ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ የለቀመውን በለስ ከመሶብ ባኖረው ጊዜ ለ66 ዓመት ያስተኛው፥ ሲነቃም ትኩስና እንደ ተቆረጠ ሆኖ ያገኘው ምሥጢሩ ምንድን ነው? «የሎሚ እንጨት» ከበጐ መዓዛ ና መልካም ፍሬ ከመሆኑ አንጻርና ሳይተከል ከመለምለሙ አንጻር ፤እሳት ያላቃጠላቸው የእንጆሪ፣ የጅብራና፣ የደደሆ - እንጨቶች የማይቃጠል ባሕርይ በውስጣቸው ይኖር ይሆን? /አርጋኖን ዘሰኑይ 5÷1-18/:: ለምንና እንዴት ብለን ጠይቀን እናውቃለን?

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የተለያዩ የከበሩ ድንጋዮችን ስም በመጥቀስ የድንጋዮቹን ምንነት ተረድቶ እንዳወደሳት አርጋኖን በተባለው ድርሰቱ ገልጾልናል:: /ዘሰኑይ 8÷ ክፍል 4 ቁጥር 1/::

«ንጽሕና ያላቸው መረግድ፣ ጳዴር፣ ኤሞዳ የሚባሉ ድንጋዮች፣ደስ የሚያሰኙ ጳዝዮን፣ ሰንፔር፣ ሶምና፣ ክርስቲሎቤ ድንጋዮች፤አደፍ ጉድፍ የሌለባቸው አሜቴስጢኖስ፣ ኢያስጲድ፣ ሰርዲኖ ድንጋዮች፤ ÷ እንደ ዕንቍ ባሕርይ ድንጋይ ጥፋት ክፋት የሌለባቸው ድንጋዮች ፣ ያክንት / በወርቅ የተጌጠ/ ፤ክርኩሰት የሚያነጻና የዝገት ማደሻ ድንጋይ በሆነ በእልመቅሊጦስ ድንጋይ ...´´»

ሊቁ እመቤታችንን ረድኤት የሚሰጥና መቅሠፍት የሚያርቅ «የአቤኔዘር ድንጋይ» ብሎ ሲመስላት የድንጋዮቹን ምንነት ከነጥቅማቸው ሳያውቅ እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ነው:: እስኪ እመቤታችንን መስሎ ካወደሰበት ድንጋዮች ውስጥ የደወል ድንጋይን እንመልከት:: /አርጋኖን ዘሰኑይ 11፥12/::

የደወል ድንጋይ:- ድምፁ የሚወደድ፣ ምጥ የተያዘች ሴትን ከምጥ ጭንቀትና ሕመም አውጥቶ የሚመሥጥ፣ ምጥን የሚያስረሳ ድንጋይ እንደ ሆነ አባ ጊዮርጊስ መርምሮ አሳውቆናል:: ይህ ድንጋይ ዛሬም በተድባበ ማርያም ይገኛል፤ እንዴትና ለምን ብለን ግን ስላልጠየቅን አባ ጊዮርጊስ ያመላከተንን የዚህን ድንጋይ ጥቅም ጨምቀን በማውጣት በምጥ የሚሠቃዩ እኅቶቻችንና እናቶቻችንን ልንረዳበት አልቻልንም::

ሌላው የተጠቀሰው የአድማስ ድንጋይ የሚባለው ነው:: ይህ ድንጋይ ብረት የማቅለጥ ችሎታ ያለው ጥኑ ድንጋይ እንደ ሆነ ወይም ከፍተኛ ሙቀትን መቋቋም የሚችል ድንጋይ መሆኑን ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመረዳቱ እሳተ መለኮትን የተሸከመች እመቤታችንንም በዚህ የአድማስ ድንጋይ መስሏታል:: ይህን ድንጋይ ብንለየው ከፍተኛ ጥቅም አይሰጠን ይሆንን?

እንግዲህ የዛሬዎቹ የቤተ ክርስቲያናችን የዕፀዋት ሳይንስ፣ የሥነ ምድር ሳይንስ... ወዘተ ባለሞያዎቻችን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቁምታዎች መሠረት በማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት ገባ ብላችሁ ብታዩ ለራሳችሁም ለወገናችሁም የምትጠቀሙባቸውን የምርምር መነሻ ሓሳቦች እንደ ምታገኙ ጥርጥር የለውም:: በዚህ ጽሑፍ አቀጣጣይነት የእኒህን ዕፀዋትና ድንጋዮች ምንነት ተነሣስታችሁ በሰላ ብዕራችሁ ጽፋችሁ ወደፊት በሰፊው በብዙ እንደምታሳውቁን ተስፋ አደርጋለሁ::

አባ ጊዮርጊስ በዚህ ብቻ ሳይወሰን የፈጠራ ምንነትንም እንደ ሚከተለው አትቶልናል:: አርጋኖን ዘሰኑይ ዘጠኝ / ሰባት/ ቁጥር አራት ላይ :- «ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት እንዲያበሩለት፣ በመውጣታቸው በመግባታቸው የዘመኑ ቁጥር እንዲታወቅ ተፈጠሩ::» ይላል:: ዘፍ.1፥14-15:: የጠፈር ሳይንስን እዚህ ላይ ያስታውሱ::

ቁጥር 20 ላይ ደግሞ:- «እግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ አደረገ፤ አዳምን ከአራት ባሕርያት አከናውኖ በሠራው ጊዜ ከአራቱ ባሕርያት አንዱ ከሁለቱ፣ ሦስተኛው ከአራተኛው እርስ በእርሳቸው እንዳይጣሉ ባሕርያትን አስማማ» ይለናል:: ይህ ፈጠራ የሚለውን ያሳየናል:: የአራቱ ባሕርያትን መስተጋብር አስማምተን ብንይዝ የማንሠራው እንደሌለ ያስረዳናል:: ፈጠራ ማለት ይህ ነው:: ለምሳሌ:- መኪናን ብንመለከት ብረቱ እንደ አፈር፣ ማቀዝቀዣው ውኃና /ነዳጁ/ እንደ ውኃ፣ የጐማው መሽከርከሪያና ነፋስ እና የነዳጁ ትነት እንደ አየር፣ በሞተር ውስጥ የሚቃጠለው እንደ እሳት አንዱ ከአንዱ ተስማምተው አባ ጊዮርጊስ እንዳለው እምቢ ሳይባባሉ /ተጣዮች ሳይሆኑ/ በመኖራቸው ሰው በምድር ላይ የምንሽከረከርበትን መኪና ፈጠረ::

ቁጥር 21:- «እርጥብን ከደረቅ ፥ሙቀት ያለውን ከቆሪር /ቀዝቃዛ/፥ የሚታየውን ከማይታየው ፥የሚዳሰሰውን ከማይዳሰሰው አንድ አድርጐ አስማማ::» ይለናል:: እስኪ በመኪና ውስጥ የገለጽናቸውን እነዚህን ባሕርያት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንመርምር፡፡ በተመሳሳይም በሌሎች ሥርዐተ ተፈጥሮ ውስጥ ያለውን እናስተውል፡፡

ቁጥር 22፡- «ከሚዳሰስ ሦስት ከማይዳሰስ ሁለት፣ ከደረቅ ሦስት ከእርጥብ አንድ፣ ከቆሪር ሦስት ከሙቀት አንድ አድርጎ...» ቁጥር 23 ላይ፡- «ሠሪው ቤቱን ሠርቶ የሚኖርበትን ምክንያት ዐወቀ፡፡ የቤቱም ማእዝን በአራቱ ባሕርያት /እሳት፣ ነፋስ፣ ውኃ፣ መሬት/ ላይ መሠረተ፡፡» ይለናል ፡፡ ስለዚህ ለባዊት ነፍስ ያለን በመሆናችን እንደ ዚህ የፍጥረታትን መገኛ ባሕርያትን መርምረን አዳዲስ የፈጠራ ሥራ ብን ሠራ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወታችን በተቀየረ ነበር ፡፡

በቀጣይም ቁጥር 24 ላይ፡- «ለመናገር ለመንቀሳቀስ...»ይለናል አባ ጊዮ ርጊስ «... የእርሱ ትንፋሽ የሕይወትም መንፈስ ያስፈልገዋልና እፍ ብሎ የሕይወት መንፈስን በንፍሐት አሳደ ረበት፤ ተንቀሳቃሽ ተናጋሪ አደረገው፡፡» በማለት የተሠራው ነገር ሊንቀሳቀስ እንዲችል የኀይልን አስፈላጊነት ያወሳ ናል፡፡ በዚህም እንደ እግዚአብሔር እፍ ብለን በንፍሐት ሕይወትን /ጸጋን/ ማሳደር ባንችልም ግዐዛኑን እግዚ አብሔር በሰጠን ዕውቀት አገጣጥመን ኃይል ሰጥተን ማሠራት የምንችልበት ዕውቀት እግዚአብሔር እንደ ሰጠን በማወቅ አእምሮአችንን ልናነቃቃው ይገባል፡፡

## ልኬተ ምድር ፥ ልኬተ ቅርጽ /Geometry/

የቀመር (ሒሳብ) ዕድገት ከጥንተ ቅሪት ስብርባሪዎች /Archeological fragments/፣ ከሥነ ሕንፃ ቅሪት / Architectural Remains/ በዕውቀት ከተደገፉ ግምቶች /Educated guesses/ እንደ ተነሣ ይገመታል፡፡ ዘርፉ ከብዙ ሺ.ሕ ዓመታት በፊት ከግብርና አጀማመርና ዕድገት ጋር የሰው ልጅ ቁጥሮችንና ቦታን ከመጠ ቀም አንጻር በስፋት በገበሬው ዘንድ ከጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዘመን ብዛት እየዳበረ ለቤት እንስሳት መቁጠርያ፣ ለእህል መከፋፈያ ቁጥርን ከመጠቀም ጀምሮ ወደ አርቲሜትክ እና ከዚያም ወደ አልጀብራ አድጓል፡፡ የቦታ ቀመር ደግሞ የእርሻ ቦታ፣ የግጦሽ መሬት አከፋፈልና አጠቃቀም ጋር ተያይዞ እንዳደገና አሁን ጂኦሜትሪ እንደ ተባለ፣ በአጠቃላይ በጥንት ጊዜ አርቲሜትክና ጂኦሜትሪ ይታወቁ እንደ ነበር መጻሕፍት ይነግሩናል፡፡ (Willia Dunhan, Journey through the Genius ).

ሒሳብ በቁጥሮችና በሌሎች ሊለኩ የሚችሉ መጠኖች ያለውን ግንኙነት መግለጫ መንገድ ነው፤ ለሳይንስም ቋንቋው ነው፡፡ ሁለት ዓይነት የሒሳብ ትምህርቶች አሉ "ንጹሕ" (Pure mathematics) ና "ተግ ባራዊ" .(Applied Mathematics/፡፡ ሁሉም ለጥያቄዎች (ችግሮች) መፍ ትሔ ሰጪ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ንጹሕ ሒሳብ በምልክቶች ወካይነት ረቂቅ ግንኙነቶችን ሲያጠና ተግባራዊ ሒሳብ ደግሞ የገሃዱን ዓለም ጥያቄ ዎች ፈተናዎች /ችግሮች/ መፍቻ ነው፡፡ ለሳይንስና ለምሕንድስና ሥራዎች መሠረታዊ መሣርያ ነው፡፡

ከተግባራዊ ሒሳብ አንዱ ጂኦሜትሪ ነው፡፡ ጂኦሜትሪ ደግሞ ቃሉ የግሪክ ሆኖ ከሁለት ሥርወ ቃላት የተ ገኘ ነው፡፡ እነርሱም፡- 'geo' ማለ ትም መሬት (Earth) ከሚለውና 'metrein' ማለትም መለካት (to measure) ከሚለው ቃላት የተገኘ ሲሆን ባንድ ላይ ልኬተ ምድር /ቅርጽ / ጂኦሜትሪ/ የምንለውን ቃል ይሰጠናል፡፡ ይህም ስለ ምድር ወይም ቅርጽ አለካክ የሚያጠና የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ ልኬተ ምድር/ቅርጽ/ /ጂኦሜትሪ/ የተለያዩ ዘርፎች አሉት፡፡ እነርሱም፡- ጠፍጣፋ ልኬት ቅርጽ *(Plane Geometry)፣ ጠጣር /ግዙፍ/* ልኬት ቅርጽ *(Solid Geometry)* ይባላሉ፡፡ ***ሁለቱ ባንድ ላይ ኢኩሊዲያዊ ልኬት ቅርጽ (Euclidean Geometry)*** ይባላሉ፡፡

ተንታኝ ልኬት ቅርጽ / Analytical Geometry/፣ ገላጭ ልኬት ቅርጽ (Projective Geometry) የሚባሉት ለምሕንድስና ዘርፍ ንድፍ ሥራ መሠረት የሆኑ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተ ጨማሪ አክሊዳዊ ያልሆኑ ልኬት ቅርጽ (Non Eucoledecn Geometry ) የሚባሉት እንደ ሃይፐርቦሊክ ና ኢሊፕቲክ /Hyperbolic and elliptic/ ልኬት ቅርጽ ናቸው፡፡ እነዚህ ለሥነ ከዋክብት ጥናት የዘርፉ ሊቃውንት የሚገለገሉባቸው ሲሆን ለአልበርት ኤንስታይንም አንጻራዊ ሕግ /Theory of Relativity/ መነሻዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ ዳግመኛ ከጥቅም ላይ የዋለው «n-Dimensioal Geometry" ወይም አራት ገጽና ከአ ራት ገጽታ በላይ ያለው ልኬት ቅርጽ የሚባለው ደግሞ ስለ ተደጋጋሚ ትንንሽ ቅርጾች የሚያጠናውና ክፍል ፋይ /ጥቃቅን/ ልኬት ቅርጽ / Fractional Geometry/ የሚባለው ነው፡፡ ይህም ለኮምፒዩተር ግራፊክስና ለሕዋ ጥናት የሚያገለግለው የልኬት ቅርጽ ዘርፍና /Differential geometry ና topology/ የቅርጾችን ጠባይ ከመተጣጠፋቸው አንጻር የሚያጠና ነው፡፡ በማንኛችንም ውስጥ የሚገኘውና ለብዙ የሳይንስ ግኝቶች መነሻ የሆነው ግን በአሁኑ ሰዓት በማንሰራራት ላይ ያለውና በየገዳማቱ ተደብቆ የሚገኘው *<ቅዱስ ልኬት ቅርጽ>* /Sacred Geometry/ ነው፡፡

ሁሉም የልኬት ቅርጽ ዓይነቶች ከቅርጽና ከልኬት ወይም አለካክ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ጽሑፍ በሰፊው የምንመለከተው ግን <ቅዱስ ልኬተ ቅርጽ> /Sacred Geometry/ ስለሚባለው የልኬተ ቅርጽ ምንነት ነው፡፡

ቅዱስ ጂኦሜትሪ፥ ቅዱስ የመልክአ ምድር ጥናት /Sacred Geography/ ተብሎም ይታወቃል፡፡ ቅዱስ ልኬተ ቅርጽ ቅዱስ፥ የተባለበት ምክንያት ማንኛቸውም እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት በሙሉ በውስጡ በተመሳሳይ ስሌት ወይም ልኬት ሆኖ በመገኘቱና በዓልም ላይ ያሉ ከ83,000 በላይ የተቀደሱ ቦታዎች ተብለው በሰው ልጅ የሚታወቁ ሁሉ አንዳቸው ካንዳቸው የሚገናኙበት በዚሁ በተቀደሰ ልኬተ ቅርጽ መነሻነት በሚሠራው፣ መጀመርያና መጨረሻ በሌለው ጥምዝ (Spiral) ላይ መደዳውን በመገኘታቸው ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችንም እንደ ሚታመነው የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም በነጠበበት ቦታ እንጂ እንደው በዘፈቀደ በማንኛውም ቦታ ቤተ ክርስቲያን አይታነጽም፡፡

በዓለም ላይ ያሉ ሁሉም የተቀደሱ ቦታዎች በግብጽ ሀገር ከሚገኘው ከአንድ ነጥብ ቦታ ጋር ይገናኛሉ፡፡ እርሱም የፀሐይ መስቀል /Solar Cross/ ይባላል ፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ቅዱሳን ቦታዎች በአጋጣሚ የተመሠረቱ ወፍ ዘራሽ ሳይሆኑ በስውር ና በረቀቀ ጥበብ ከዚህ መስቀል ጋር ተገናዝበው ተነጻጽረው የቀንድ አወጣ ቅርፊት / Spiral/ በሚመስል መስመር ተስተካክለውና ተገናዝበው የተቀመጡ መሆናቸውን በዘርፉ የጠለቀ ምርምር ያካሄዱ ልሂቃን ያስረዳሉ፡፡

./Durnvalo,p. 110-117/.

ቅዱስ ልኬት ቅርጽ ለበርካታ የሳይንስ ግኝቶች መገኛ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ***ዜሮ ነጥብ ሥነ ኪን /Zero-Point technology/፡፡***

ይቀጥላል፡፡

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ

# «ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በምርጫ እንዲጠና ዕድል ይሰጠው።»

/ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ
የሴማዊ ሥነ ቃላተ ልሳን ምሁር/

*በ14ኛው ቁጥር ሦስት 1998 ዓ.ም እትማችን ከጣልያናዊው የሴማዊ ሥነ ቃላተ ልሳን ምሁር ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ የመጀመሪያ ክፍል ማቅረባችን ይታወሳል። በቆይታችንም በመግቢያ ደረጃ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት በአጠቃላይና በአውሮፓ የኢትዮጵያን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥናት አጀማመርና ዕድገት በተለይ ተመልክተናል። ፕሮፌሰር ማራሲኒም የኢትዮጵያን ጥናት ሥነ ቃላተ ልሳን የጀመሩት ገና የ17 ዓመት ወጣት እያሉ መኾኑን፣ በመስኩ በርካታ ተመራማሪዎችን አስተምረው ማውጣታቸውን፣ በአውሮፓ የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ይዘታ ምን እንደ ሚመስል፣ የብራና ጽሑፎቻችንን አያያዝና በእርሱም ተጠቃሚ ለመኾን ምን ማድረግ እንደ ሚገባን አጫው ተውናል። በዚህ ዝግጅታችን ዲ.ን ደሴ ቀለብ፣ዲ.ን ቸርነት አበበ እና ዲ.ን ደረጀ ጅማ ከፕሮፌሰሩ ጋር ያደረጉትን አጭር ቆይታ የመጨረሻ ክፍል ይዘን ቀርበናል። ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ በጣሊያን ፍሎሬንስ ዩኒቨርስቲ የግእዝ ሥነ ጽሑፍን በሴማዊ /ሥነ ቃላት ልሳን/ /Semitic Philology /ና በደቡብ ዐረቢያ ቋንቋዎች ጠገግ በስፋት በማጥናት የታወቁ ምሁር መኾናቸውን በድጋሚ እያስታወስን ስላ ደረጉልን ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን።*

## «ያለ ግእዝ ቋንቋ ከ19ኛው ምእት በፊት ያለውን ታሪካችሁን ልትረዱት አትችሉም።»

የግእዝ ጠቀሜታ ሃይማኖታዊ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ቀደምት ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ታሪክ ሲጠና የግእዝ ቋንቋ ድርሻ የላቀ ነው። ምክንያቱም በግእዝ የተጻፉት ሃይማኖታዊ መዛግብት ብቻ ሳይሆኑ የነገሥታቱ ዜና መዋዕል፣ ሥርዐተ መንግሥታቸውና ሌሎችም ታሪኮች ጭምር ናቸው። እስከ 19ኛው ምእት ድረስ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጽሑፍ በግእዝ ተጽፏል። እርግጥ በጣም ጥቂት ጽሑፎች በጥንታዊው አማርኛ ተጽፈው ተገኝተዋል። እንዲሁም በጥንታዊው ሐረሪኛ የተጻፉ ጽሑፎች በ15ኛው ምእት ተገኝተዋል። ይሁን እንጂ ጥቂት ናቸው። *ከ80% እስከ 90% የሚሆኑት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጽሑፎች የተጻፉት በግእዝ ነው።* ይህ በራሱ ግእዝ የነበረውን ጠቀሜታ በይፋ ይናገራል። ያለ ግእዝ ቋንቋ ከ19ነኛው ምእት በፊት ያለውን ታሪካችሁን ልትረዱት አትችሉም። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህልና ኹለንተና ለማወቅ ያለ ግእዝ ቋንቋ ዕውቀት አይቻልም።

ሁለተኛው የግእዝ ቋንቋ ወሳኝ ጠቀሜታ ለሴማዊ ሥነ ቋንቋ /የቋንቋ ጥናት/ ነው። ምክንያቱም ሦስተኛው ጥንታዊ ሰነድ ነውና፤ የመጀመሪያው ዶኪመንት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሦስተኛው ምእት የተጻፈው ነው። ልክ ንጉሥ ጋደራት እንደ ጻፋቸው ትንንሽ ጽሑፎች ያሉቱ ማለት ነው። ነገር ግን ከቋንቋው ዘይቤ /typology/ አንጻር ካየነው ግእዝ ሴማዊ የሆነ ጥንታዊ ቋንቋ ነው። እንዲሁም ዛሬ ላለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ግእዝ ያበረከተው አስተዋፅኦም ሆነ ያለው ጠቀሜታ ታላቅ ነው።

## «አንድ ቋንቋ ሕያው ነው ለመባል በተለመዱ ዕለታዊ ንግግሮች ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት»

አንድን ቋንቋ «ሞቷል» የምንለው ካለበት ሁኔታ በመነሣት ነው። «ሕዝቡ የግእዝን ቋንቋ በየዕለት ሥራውና ግንኙነቱ ውስጥ ለንግግር እየተጠቀመው አይደለም» የምንል ከሆነ እንደ ላቲን ሁሉ ግእዝም ሞቷል። ኢትዮጵያ ውስጥ ከካህናት በስተቀር በግእዝ የሚጠቀም ማኅበረሰብ ያለ አይመስለኝም። ካህናቱም ቢሆኑ ቋንቋውን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንጂ ከዚህ ወጣ ላለ ነገር አይጠቀሙበትም። ስለ እግር ኳስ፣ ስለ ዩ.ኤስ.አሜሪካ ችግሮችና ስለ መሳሰሉት በግእዝ ያወራሉ ብዬ አላስብም። ይህ ዐይነተኛ ችግር ነው። ከዚህ አኳያ ከተመለከትነው ግእዝ ሞቷል። ምክንያቱም ዕለት በዕለት በሚደረጉ ንግግሮች ውስጥ ተሳትፎ የለውምና። ይኸውም ልክ እንደ ላቲን ቋንቋ ማለት ነው።

በትክክል ግእዝ መቼ እንደ ሞተ አናውቅ ይሆናል። በዛም አነሰም በ10ኛው ምእት ገደማ /በዘመነ አክሱም ፍጻሜ/ ላይ ሊኾን ይችላል። መደነቅ አያስፈልግም፤ የላቲን ቋንቋም የሞተው የሮም ግዛተ መንግሥት ሲወድቅ ነውና። እርግጥ ላቲን በስድስተኛው ምእት ገደማ በመሞቱ ከግእዝ ይቀድም ይሆናል።

በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሴማዊ የሆኑ ሌሎች ቋንቋዎች አሉ። ይሁን እንጂ ከአውሮፓውያን ቋንቋ በተለየ ሁኔታ የግእዝ ድምፅ እንዳላቸው እየተቆጠረ አይደለም። የጣልያንኛ፣ የስፓኒሽ፣ የፖርቹጊዝና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ከላቲን እንደ ተወሰዱና የላቲን ድምፅ እንዳላቸው ይታመናል።

ትግርኛ፣ ትግረ፣ አማርኛና ሌሎች መሰል ቋንቋዎች ደግሞ የግእዝ ድምፅ እንዳላቸው ይታመናል። ነገር ግን አሁን ባለው የኀላ ዝንባሌ መሠረት እነዚህ ቋንቋዎች የሌላ ቋንቋ ድምፅ እንዳላቸውና የግእዝ እኅት ቋንቋዎች እንደ ሆኑ መታመን ተጀምሯል። ከግእዝ ጋር በቀጥታ ይመሳሰላሉ። ነገር ግን ከግእዝ በቀጥታ አልተወሰዱም። የሆነው ሆኖ የግእዝ ቋንቋ ቢቆይ ከ10ኛው ምእት ቢቀርብ ደግሞ ከዘጠነኛው ምእት ጀምሮ በሕዝቡ ዘንድ መነገር የቆመ ቋንቋ ነበር። በግእዝ ቋንቋ ያለመናገር ችግር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የተጀመረው።

በሌላ በኩል *«አንድ ቋንቋ ዕለት በዕለት በሚኖረው የሕዝቡ ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ በኅብረተሰቡ ባይነገርም በተወሰነ ደረጃ አገልግሎት ላይ ካለ ሞተ ልንለው*



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ላንችልም» ብለን ካተትን ግእዝ እስከ አሁን ያልሞተና በሕይወት ያለ ቋንቋ ነው ማለት እንችላለን። ይህን ግን በእውነትና በታማኝነት ለማለት የማያስችለን ምክንያት አለ። አንድ ቋንቋ «ሕያው ነው» ለመባል በተለመዱ ዕለታዊ ንግግሮች ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። በግእዝ ዙሪያ ያለው ችግር ከላቲኑ ጋር ተመሳሳይ ነው። በጣልያንም ሆነ በፈረንሳይ የላቲን ቋንቋ መነጋገሪያ እንዲሆን በየጊዜው የሚሠሩ ሥራዎች የሉም። ይህ በመደረጉ ግን ላቲንን ሕያው አያሰኘውም። ከአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ውጪ አገልግሎት ስለ ማይሰጥ ሞቷል ማለት ይቻላል። ግእዝም እንዲሁ ነው።

## የግእዝ ቋንቋን ሕዝባዊ ለማድረግ

ጥንታዊ ለሆነው የአገሪቱ ታሪክ ያላችሁን ፍቅርና ፍላጎት ሕዝባዊ ማድረግ፣ ማለትም ሕዝቡ ለአገሩ ታሪክ ፍቅርና ፍላጎት እንዲኖረው መሥራት አለባችሁ። በአጠቃላይ ባልልም አብዛኛው የአገራችሁ ሰው ለዘመናዊ ታሪክ ብቻ ነው ፍቅርና ፍላጎት ያለው። ይህ ዝንባሌ ደግሞ ግእዝ ቦታ እንዳይኖረው ያደርጋል። በጣልያን የላቲን ቋንቋ አሰልቺ ተደርጎ የሚቆጠረውን ያህል ግእዝም ያ ዕጣ ሊደርሰው ይችላል። አሁን ወደ ጣልያን ልጆች ወይም ወጣቶች ሄዳችሁ ስለ ላቲን ብትጠይቋቸው፦ «እኛ የዚህ ዘመን ትውልዶች ነን። ፍላጎታችን አሁን ባለው ዕድገትና ሥልጣኔ ላይ ነው ይሏችኋል።» እርግጥ የዘመኑ የሆነ ነገር በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ትላንት የነበረውንም ጠቃሚነት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

ለሁሉም አገሮች የቀድሞ ታሪካቸው በጣም ጠቃሚ ነው። ጣልያንም ሆነች ፈረንሳይ፣ እንግሊዝም ሆነች አሜሪካ እንዲሁም ኢትዮጵያ የቀድሞ ታሪካቸው ጠቃሚያቸው ነው። ኢትዮጵያ በተለይ በአፍሪካ ከሰሐራ ደቡብ ከሚገኙ አገሮች ጋር ስትነጻጸር ያለፈ ታሪኳን በደንብ መዝግባ የቆየች አገር ነች። ምክንያቱም ሩዋንዳና ኮንጎን የመሳሰሉት አገሮች የቀድሞ ታሪክ ነበራቸው። ነገር ግን በጽሑፍ ተመዝግቦ የተቀመጠ ምንም ነገር የላቸውም። በዚህ የተነሣ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ስለነበረው የሩዋንዳና የኮንጎ ታሪክ ለመናገር ያዳግታል። ስለዚህ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከሰሐራ ደቡብ ካሉ አገሮች ውስጥ የቀድሞ ታሪኳን በአግባቡ መዝግባ የጠበቀች ነች። በአፍሪካ ደቡብ ሰሐራ ያልኩት ሰሜን ሰሐራ ያሉ የአፍሪካ ክፍሎች ዐረቦች ስለሆኑ ነው።

ላለፈው የአገሪቱ ታሪክ ፍቅራችሁንና ፍላጎታችሁን ጥልቅ ካደረጋችሁና በዚሁ ከቀጠላችሁ ለግእዝ ሊደረግ የሚገባውን ተገቢ ትኩረት መስጠት ትችላላችሁ። ቋንቋው ትኩረት እንዲያገኝ ብላችሁ ስፋት የሌለው ሥራ ማለትም በጥቂት ሰዎች፣ በካህናቱ... ወዘተ ብቻ የምትሠሩት ሥራ መልካም ቢሆንም ብዙ የሚያስተማምን አይደለም።

## «ብቸኛውና መሠራት ያለበት ነገር ግእዝ ለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ያበረከተውን አስተዋፅዖ ዛሬ ላለው ትውልድ ማስተማዋወቅ ነው።»

በተወሰነ ደረጃና ለተወሰነ ዓላማ ግእዝን በደንብ መናገር የሚችሉ ሰዎች ልታወጡ ትችላላችሁ። ለምሳሌ፦ ለሥነ መለኮት ጥያቄዎች /ጉዳዮች/ መፍቻ መዝገበ ቃላት አላችሁ። ይሁን እንጂ ለምሳሌ፦ ስለ ስፖርት፣ ስለ ፖለቲካ በግእዝ እንደ ልብ ለመናገር ያዳግታችኋል።

ምክንያቱም ለነዚህ የሚሆኑ ቃላት የሏችሁም። ለምሳሌ፦ የአንድን አውሮፕላን በቦምብ መጋየት በግእዝ እንዴት ብላችሁ ትገልጣላችሁ? የምትገልጡበት ቃል አላችሁ? የሚቻል አይመስለኝም። በአንድ ወቅት ላቲናውያን በደቡብ አሜሪካ ያደረጉት ኮንፍረንስ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። እኔ ላቲናዊ ስላልሆንኩ በስብሰባው ላይ አልተገኘሁም ነበር። ይሁን እንጂ ከፍሎረንስ ሄዶ በስብሰባው ላይ የተገኘ ጓደኛዬ የሚከተለውን አጫውቶኛል። እርሱ ደግሞ በላቲን ቋንቋ በጣም የሚኮራ ሰው ነበር። ታድያ በስብሰባው ላይ ጠፈርተኞች በጨረቃ ላይ ስላደረጉት ምርምር በላቲንኛ ይናገር ነበር። እንደ ሚታወቀው ጨረቃ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ <በሕዋ መርከብ > ያረፈው ኒል አርምትስሮንግ ነው። የዚህን ሰው ስም ወደ ላቲንኛ ለመተርጎም ተፈለገ። በመሆኑም ጉባኤው በእንግሊዝኛ አርም ስትሮንግ የሚባለውን ስም ወደ ላቲንኛ <ፎርቴብራኩዌም> ሲል ተረጎመው። በላቲንኛ <ፎርቴ> ማለት ጠንካራ ማለት ሲሆን <ብራኩዌም> ደግሞ ክንድ ማለት ነው። ጉባኤው <ፎርቴብራኩዌም> የሚለው ግኝት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ስላገኘው በዚህ መልኩ ሰይሞታል። ይህ ግን ለኔ ገርሞኛል።

እናንተም ፡ መሞከር ትችላላችሁ። ለግእዝ ትክክለኛውንና አማናዊውን ዋጋ የሚሰጠው የኔ አእምሮ አይደለም። ግእዝ እንደ ቋንቋ እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ቀደምት ታሪክ ውስጥ ጉልህና ሰፊ ድርሻ አለው። ሌላ መንገድ አትፈልጉ። እስከ አሁን ለታሪክ ባለው ወሳኝ ጠቀሜታው ላይ የበለጠ ሙከራ ብታደርጉ ለአሁኑ እና ለቀጣዩ መሠረት መጣል ትችላላችሁ። ብቸኛውና መሠራት ያለበት ነገር ግእዝ ለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ያበረከተውን አስተዋፅኦ ዛሬ ላለው ትውልድ ማስተዋወቅ ነው።

ለምሳሌ፦ በስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ በድኅረ ምረቃ ፕሮግራም የተጀመረው የሥነ ቃላተ ልሳን /Philology/ ትምህርት ክፍል ይህን ለመሥራት እንደ አንድ መንገድ ሆኖ ያገለግላል። ምክንያቱም እስከ አለፉት ጥቂት ዓመታት ድረስ ለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ በዩኒቨርሲቲው የተሰጠ ይፋዊ ፍላጎትና እንቅስቃሴ አይታይም ነበር። እናንተም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የራሳችሁን መንገድ በመጠቀም በግእዝ ዙሪያ መሥራት ይገባችኋል። ይሁን እንጂ ከዚህ የሥነ ቃላተ ልሳን ትምህርት ክፍል፣ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጋር ቅንጅት መፍጠር አለባችሁ። ለምሳሌ፦ ከማስተምራቸው ተማሪዎች ብዙዎቹ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የመጡ ናቸው። ግእዝን ቀደም ብለው ስለ ሚያውቁ ለትምህርት ክፍሉም ሆነ ለራሳቸው ጥሩ ነው። ይህ ደግሞ ለሚደረገው ልዩ ልዩ ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። በቅንጅቱ ለአገሪቱ የቀደመ ታሪክ ዋጋ መስጠት ይኖርበታል እላለሁ። የሥነ ቃላተ ልሳን /Philology/ ተማሪዎች ሥልጠናቸውን ሲያጠናቅቁ ጠቃሚ ፋይዳ ባለው ጥንታዊና ታሪካዊ በኾኑችው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበለጠ ዕውቀትና ልምድ ይኖራቸዋል። ይህ ከዕንሰ ሐሳባዊ ጥናቶች መካከል አንዱ ስለሆነ የፊሎሎጂ ተማሪዎችም ሆኑ ትምህርቱ የብዙዎችን አእምሮ ይከፍታል። በዚህ ምክንያት ሰዎች የቀደመውን ለመረዳት ሰፊ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።

## «ግእዝ ተፈላጊነት የሚኖረው ለቀድሞው የአገሪቱ ታሪክ ፍቅር ያለው ሰው ማፍራት ስትችሉ ነው።»

ግእዝን በመማርና በማስተማር ሂደት ላይ የአፈጻጸም ችግሮች አሉ። ሥር ከሰደደው የግእዝ ችግር ይልቅ የቋንቋ ፋክክር ላይ ነው ሙከራችሁ። እዚህ ላይ ግን ብዙ አትድከሙ። ይህ ማስገደድ ይሆናል። ከዚህ ይልቅ ቀደም ሲል የነበረው፣ የአገሪቱ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ የተቀመጠበት ቋንቋ /ግእዝ/ ተፈላጊነት የሚኖረው ለቀድሞው የአገሪቱ ታሪክ ፍቅር ያለው ሰው ማፍራት ስትችሉ ነው። ለየትኛውም አገር ያለፈው ታሪኩ ጠቃሚ እንደ ሆነ ከተገነዘባችሁ ይህን አድርጉ። ደግሞም ጠቃሚ ነው። ጠቃሚነቱን ደግሞ ደርሳችሁበታል። ለምሳሌ፦ በአ.አ.ዩ የተቋቋመው የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር ይህን ማድረግ ይችላል።

*ይህን ምክሬን እዚህ ባለመሆኔ ለሌሎች ማካፈል አልችል ይሆናል። ነገር ግን ቀደምት የሆነውን ነገር አስረግጣችሁ ልትይዙት ይገባል። የቀድሞውን ታሪክ ስል በአጠቃላይ የአገሪቱን ታሪክ ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያንን፣ የሕዝቡን፣ የጦርነቱን፣ የኢኮኖሚውንና በአጠቃላይ ያለፈውን ታሪክ ይይዛል። ይህ በአውሮፓ በጣም ቀላል ነው። ባለፈው ነገር /ታሪክ/ መማረክ ማለት አሁን ባለው ነገር መማረክ ማለት ነው፤ ምክንያቱም ያለፈው በዛሬው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አለና። ስለዚህ ስለ ቀድሞው ሳታውቅ ዛሬ ያለውን ነገር በትክክለኛው መንገድ መመርመር አትችልም። የቀድሞ ታሪክ ጠቃሚ ነው የሚባለው ለዚህ ነው። አሁን ያለውን በትክክል ለመረዳትም ይጠቅማል።*

ወደ ገጽ ፵ ዞሯል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን «አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» የተሰኘ ዓምድ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል። በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም በተቋቋመው «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» የሚዘጋጅ ነው። ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው።

*ባለፈው የ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ግንቦት/ሰኔ/ሐምሌ 1998 ዓ.ም. እትማችን የግሶችን ሂደት በካልአይ አንቀጽ /በሁለተኛ ዐቢይ አንቀጽ/ በዝርዝር መማማራችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ ዘንድ አንቀጽ ወይም ትእዛዝ አንቀጽ መሠረት በማድረግ ትምህርታችንን እንቀጥላለ። ከዚህ በፊት ግን ባለፈው እትም ላቀረብናቸው መልመጃዎች ምላሹን እናስቀድማለን።*

*/መ/ር ደሴ ቀለብ/*

*በሐመር መጽሔት 14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስተኛ ግንቦት /ሰኔ/ ሐምሌ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም አቡጊዳ የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ዓምድ የወጣው ምልማድ/መልመጃ መልሶች*

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ሀ | 7. | ለ |
| 2. | ሠ | 8. | ሀ |
| 3. | ሀ | 9. | ለ |
| 4. | ለ | 10. | ለ |
| 5. | ሀ | 11. | ሀ |
| 6. | ለ | 12. | ለ |

## *ዘንድ አንቀጽ ወይም ትእዛዝ አንቀጽ*

### *የአርእስቱ ዘንድ አንቀጽ*

| ኃላፊ | ዘንድ/ትእዛዝ |
|---|---|
| 1. ቀተለ | ይቅትል- ይግደል/ይገድል ዘንድ |
| 2. ቀደሰ | ይቀድስ - ያመስግን/ያመሰግን ዘንድ |
| 3. ባረከ | ይባርክ- ይባርክ/ይባርክ ዘንድ/ /ይላላ/ |
| 4. ዴገነ | ይዴግን - ይከተል /ይከተል ዘንድ/ |
| 5. ኖለወ | ይኖሉ - ይጠብቅ/ይጠብቅ ዘንድ/ |
| 6. ደንገፀ | ይደንግፅ - ይፍራ/ ይፈራ ዘንድ/ |
| 7. ብህለ | ይብሃል - ይበል /ይል ዘንድ/ |
| 8. ማህረከ | ይማህርክ - ይማርክ /ይማርክ ዘንድ/ |
| 9. ገብረ | ይግበር- ይሥራ /ይሠራ ዘንድ/ |
| 10. ሤመ | ይሢም - ይሹም /ይሾም ዘንድ/ |
| 11. ቆመ | ይቁም - ይቁም /ይቆም ዘንድ |

### በዐሥሩ መራሕያን

| | ዘንድ | | | ትእዛዝ |
|---|---|---|---|---|
| አነ | እቅትል | እገድል ዘንድ | እቅትል | ልግደል |
| አንተ | ትቅትል | ትገድል ዘንድ | ቅትል | ግደል |
| አንቲ | ትቅትሊ | ትገድይ ዘንድ | ቅትሉ | ግደይ |
| አንትሙ | ትቅትሉ | ትገድሉ ዘንድ | ቅትሊ | ግደሉ |
| አንትን | ትቅትላ | » » | ቅትላ | ግደሉ |
| ንሕነ | ንቅትል | እንገድል ዘንድ | ንቅትል | እንግደል |
| ውእቱ | ይቅትል | ይገድሉ ዘንድ | ይቅትል | ይግደል |
| ይእቲ | ትቅትል | ትገድል ዘንድ | ትቅትል | ትግደል |
| ውእቶሙ | ይቅትሉ | ይገድሉ ዘንድ | ይቅትሉ | ይግደሉ |
| ውእቶን | ይቅትላ | ይገድሉ ዘንድ | ይቅትላ | ይግደሉ |

*ማስታወሻ፦ ከአንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን ውጭ፣ ዘንድም ትእዛዝም አንድ ነው።*

- ዘንድ አንቀጽ እንደ /ደ/ የሚለውን ቃል እና ሊ/ል/ የተባለ ሆሄያዊ ቃላት ይይዛል። እንድገድል /እቅትል/፣ ልገድል /እቅትል/፣ ሊገድል /ይቅትል/...።

ከመ /እንደ/ በአንቀጾች ላይ ሲያርፍ እንደ አንቀጾቹ ሁኔታ እና ጊዜ ይፈታል።

ከመ ነነድግ፡ ይቅር እንድንል /ለወደፊት/ - ከመ ንቀትል /ካልአይ አንቀጽ/

# ንግድና እና ቅድስና ..

[illegible]

ይህን ያህል ደክሜ እንዴት ይቺን አገኛለሁ አንበል። ይህ ሰይጣንና አልጠግብ ባይነት የሚቀርጽብን ሐሳብ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በወር አንድ ሺሕ ብር ያተርፋል፤ ሌላው ደግሞ ዐሥር ብር ሊያገኝ ይችላል። ባለ ዐሥር ብሩ ለኔ የተደረገው ብዙ ነው ካለ በዚያ እርካታ አለው። ሰውኮ ባቄላ በልቶ ቁርበት ላይ ተኝቶ ተመስገን እያለ በጤና ይኖራል። እንቅልፉ እንኳን የሰላም ነው። ከዝሆን ጥርስ በተሠራ አልጋ ላይ ቢተኛ፣ ጥሬ ቢቆረጥም እግዚአብሔር የሌለበት ሕይወት ሰላም የለውም። ሰላም በማጭበርበርና በበደል መንገድ በተሰበሰበ ገንዘብ አይገኝም። አንድ ሰው ብዙ ባምታታ ቁጥር ይበልጥ የኅሊና ሰላሙን ያጣል።

*ዛሬ ክርስቲያን ነጋዴዎች ከብልሹ ተግባራት መለየት አለብን፤ «የሚያምን ከማያምን ምን «ኅብረት አለው» /2ቆሮ. 6+14/ ተብሏልና። እንዲያውም «ወይ ሞቃት አይደለህ ወይ በራድ አይደለህምና ከአፌ አውጥቼ ልተፋህ ነው» /ራእይ.3+15/ የተባለው ለእኛ ይመስለኛል። ክርስቲያን ነኝ የሚለውም ነጋዴ ከዋሸ ከአሕዛቡ ነጋዴ በምን ይለያል? ቅድስና መለየት ነው። የእግዚአብሔር ከሆን በእውነትና በመልካም ሥራችን መለየት አለብን። የዕለት ከዕለት ሕይወታችን የመናገርን ያህል መስበክ መቻል አለበት። ጊዜው ከፊት ይልቅ ባጠረበት በዚህ ዘመን ቆም ብለን ማሰብ ይገባናል። ትላንት ዐሥር ብር ማግኘት እንፈልግ የነበረውን መቶ ላይ አድርሶናል። መቶ እንመኝ የነበረውን ሺሕ ሺውንም+ እልፍ...ታድያ ከምንም እዚህ ካደረሰን ዛሬ ካለንበት ወደ ሌላ ማድረስ እንደ ሚችል ለምን አናምንም? መቼም ቢሆን እግዚአብሔር ከጥያቄያችን በላይ ሰጠን እንጂ ከንፍገት የተነሣ የከለከለን ነገር የለም። ሰዎችን በማየት ስንከተል መድረሻችንን ሳናውቅ እንቀር ይሆናል። ከእኛ በዓለም ትርፍ የበለጡንን ልንደርስባቸው ስንሮጥ እነርሱም ሲሸሹን «የመዳን ቀን ዛሬ ነው» መባሉን ረስተናል፤ በቀኒቱም ሳንጠቀም የተቀደሰ ሕይወትም ሳንኖር ጊዜያችንን ጨረስን። ድንገት መጠራታችን አይቀርም። በእግዚአብሔር መንግሥት ቦታ ከምናጣና በምድርም ሰላም የለሽ ሕይወት ከምንመራ እግዚአብሔር ኑሩት ያለንን የቅድስና ሕይወት ለመኖር እንሽቀዳደም። ያን ጊዜ ሰላማችን ይበዛል። ፍጻሜያችንም በእግዚአብሔር ዕቅፍ መኖር ይሆናል።*

በዘመናችን ወጣቶች /ያላገቡ/፣ ባለ ትዳሮችና ነጋዴዎች ከዕውቀታቸውና ከሕይወት ተሞክሮአቸው በመነሣት ስለ ቅድስና የሰጡንን ልዩ ልዩ አስተያየት ማቅረብ በዚህ ዝግጅት ፈጽመናል። በቀጣዩ እትም የቅድስና ሕይወት በሌሎች የሕይወት መስኮች ውስጥ ባሉ ሰዎች ዘንድ እንዴት እንደ ሚታይና እንደ ሚኖር ልናስነብባችሁ እንሞክራለን።

**ይቆየን።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ይቅር እንደምንል /ልማዳዊ፣ ዘወትር/
-ከመ ንኅድግ- ይቅር እንል ዘንድ - ከመ ንቅትል /ዘንድ አንቀጽ/

**ቀደሰ - አመሰገነ**

| | ዘንድ | (In order to ) | ትእዛዝ | (In order to )Praise | |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | እቀድስ | አመሰግን ዘንድ | እቀድስ | ላምስግን | |
| አንተ | ትቀድስ | ታመሰግን ዘንድ | ቀድስ | አመስግን | » |
| አንቲ | ትቀድሲ | ታመሰግኚ ዘንድ | ቀድሲ | አመስግኚ | » |
| አንትሙ | ትቀድሱ | ታመሰግኑ ዘንድ | ቀድሱ | አመስግኑ | » |
| አንትን | ትቀድሳ | ታመሰግኑ ዘንድ | ቀድሳ | አመስግኑ | » |
| ንሕነ | ንቀድስ | እናመግን ዘንድ | ንቀድስ | እናመስግን | » |
| ውእቱ | ይቀድስ | ያመሰግን ዘንድ | ይቀድስ | ያመስግን | » |
| ይእቲ | ትቀድስ | ታመግን ዘንድ | ትቀድስ | ታመስግን | » |
| ውእቶሙ | ይቀድሱ | ያመሰግኑ ዘንድ | ይቀድሱ | ያመስግኑ | » |
| ውእቶን | ይቀድሳ | ያመሰግኑ ዘንድ | ይቀድሳ | ያመስግኑ | » |

ማስታወሻ፡- ከአንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን ውጭ÷ ዘንድም ትእዛዙም አንድ ነው።

**ገብረ - ሠራ**

| | ዘንድ | (In order to ) | ትእዛዝ | | (In order to )Do |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | እግበር | እሠራ ዘንድ | እግበር | ልሥራ | |
| አንተ | ትግበር | ትሠራ ዘንድ | ግበር | ሥራ | » |
| አንቲ | ትግበሪ | ትሠሪ ዘንድ | ግበሪ | ሥሪ | » |
| አንትሙ | ትግበሩ | ትሠሩ ዘንድ | ግበሩ | ሥሩ | » |
| አንትን | ትግበራ | ትሠሩ ዘንድ | ግበራ | ሥሩ | » |
| ንሕነ | ንግበር | እንሠራ ዘንድ | ንግበር | እንሥራ | » |
| ውእቱ | ይግበር | ይሠራ ዘንድ | ይግበር | ይሥራ | » |
| ይእቲ | ትግበር | ትሠራ ዘንድ | ትግበር | ትሥራ | » |
| ውእቶሙ | ይግበሩ | ይሠሩ ዘንድ | ይግበሩ | ይሥሩ | » |
| ውእቶን | ይግበራ | ይሠሩ ዘንድ | ይግበራ | ይሥሩ | » |

**ሤመ - ሾመ**

| | ዘንድ | | ትዕዛዝ | | (In order to )appoint |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | እሢም | እሾም ዘንድ | እሢም | ልሹም | |
| አንተ | ትሢም | ትሾም ዘንድ | ሢም | ሹም | » |
| አንቲ | ትሢሚ | ትሾሚ ዘንድ | ሢሚ | ሹሚ | » |
| አንትሙ | ትሢሙ | ትሾሙ ዘንድ | ሢሙ | ሹሙ | » |
| አንትን | ትሢማ | ትሾሙ ዘንድ | ሢማ | ሹሙ | » |
| ንሕነ | ሢም | እንሾም ዘንድ | ንሢም | እንሹም | » |
| ውእቱ | ይሢም | ይሾም ዘንድ | ይሢም | ይሹም | » |
| ይእቲ | ትሢም | ትሾም ዘንድ | ትሢም | ትሹም | » |
| ውእቶሙ | ይሙ | ይሾሙ ዘንድ | ይሢሙ | ይሹሙ | » |
| ውእቶን | ይማ | ይሾሙ ዘንድ | ይሢማ | ይሹሙ | ». |

**ቆመ=ቆመ**

| | ዘንድ | | ትእዛዝ | | (In order to )Stand |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | እቁም | እቆም ዘንድ | እቁም | ልቁም | |
| አንተ | ትቁም | ትቆም ዘንድ | ቁም | ቁም | » |
| አንቲ | ትቁሚ | ትቆሚ ዘንድ | ቁሚ | ቁሚ | » |
| አንትሙ | ትቁሙ | ትቆሙ ዘንድ | ቁሙ | ቁሙ | » |
| አንትን | ትቁማ | » | ቁማ | ቁሙ | » |
| ንሕነ | ንቁም | እንቆም ዘንድ | ንቁም | እንቁም | » |
| ውእቱ | ይቁም | ይቆም ዘንድ | ይቁም | ይቁሞ | » |
| ይእቲ | ትቁም | ትቆም ዘንድ | ትቁም | ትቁም | » |
| ውእቶሙ | ይቁሙ | ይቆሙ ዘንድ | ይቁሙ | ይቁሙ | » |
| ውእቶን | ይቁማ | ይቆሙ ዘንድ | ይቁማ | ይቁሙ | » |

ማስታወሻ፡- በዘንድ እና ትእዛዝ የፊት ቅጥያዎቹ /Prefix/ እንደ ካልአይ ሲሆን በግሱ ላይ ግን የመለዋወጥ ጠባይ ይታያል። ቀተለ- ብዙውን ጊዜ የሳድስነት ጠባይ አለው። ቀደሰ የግእዝነት ጠባይ አለው።

ይቆየን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## «ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በምርጫ እንዲጠና ዕድል ይሰጠው»

ከገጽ ፴፫ የዞረ

በዕንስ ሐሳብ ደረጃ ግእዝን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መስጠት ቢቻል መልካም ነበር። በተግባር ግን ይከብዳል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ለዚህ ማስረጃ የሚሆን የጣልያንን ተሞክሮ ልነግራችሁ እችላለሁና።

ሕፃን ሳለሁ የላቲን ቋንቋ በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጥ ነበር። ይሁን እንጂ ሁሉም ትምህርት ቤቶች እኩል ለሆኑ ዓመታት ቋንቋውን አይሰጡም። አንዳንዶቹ ለሦስት ሌሎቹም ለአምስት ዓመታት ይሰጡ ነበር። በአጠቃ ላይ እንደ የትምህርት ቤቶቹ ዐይነት ይለያይ ነበር። በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ ማለት ይቻላል ምንም ዓይነት የላቲን ቋንቋ አይሰጥም፤ ተማሪዎችም ትተውታል። ምክንያቱም ያን መሰሉን እስጣጥ የቀድሞዎቹም ሆነ የዛሬዎቹ ተማሪዎች እንደ ሥቃይ ቆጥረውታል።

እናንተም በዚህ መሰል ሁኔታ ውስጥ ሁኑ አትሁኑ የማውቀው ነገር የለም። ልትሞክሩት ትችላላችሁ። ለምሳሌ፡- የግእዝን ቋንቋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲጠና እንደ ምርጫ አድ ርጋችሁ ማቅረብ ትችላላችሁ። አንድ የሁ ለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪን እንዲህ ብላችሁ ልትጠይቁት ትችላላችሁ፡- *«በሳምንት ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ግእዝን ለማጥናት ጊዜ ይኖርሃልን? ግእዝ ያለፈውን የሀገ ርህን ታሪክ ለማወቅ ያስችልሃል። ከዚህ በኋላ የወደፊቱን አማራጭ አንተ ትወ ስዳለህ።»*

ስለዚህ ተማሪዎች ግእዝን በምርጫ እንጂ በግዴታ እንዲያጠኑ አለማድረግ ያስፈልጋል። እንዲህ ካደረጋችሁ ተቃራኒ የሆነ ውጤት ታገኛላችሁ። በየትኛውም ትምህርት ቤት በምርጫ የሚጠኑ ትም ህርቶች አሉ። ግእዝስ ለምን ይህ ዕድል አይሰጠውም? ምናልባት በኢትዮጵያ ያለውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተለምዷዊ አሠራር አላውቅም። የሆነው ሆኖ ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማራጭ ሊጠና የሚችል ትምህርት መሆን ይችላል። ማስታወስ ያለባችሁ ነገር÷ ግእዝን በግዴታ በሰዎች ላይ መጫን እንደ ሌለባችሁ ነው። ከዚህ ይልቅ ጥንታዊውንና ያለፈውን ታሪክ ለማወቅ የሚያስችል ጠቃሚ ቋንቋ መሆኑን በስፋት ማሳወቅ ይኖርባችኋል።

ስለዚህ ታሪካዊ ጠቀሜታውን ሳታስገነዘቡና ፍላጎት ሳታሳድሩ ተማሪዎች ግእዝን እንዲያጠኑ አታስገድዷቸው። ይህን መሰሉ ድርጊት ካለ ግእዝ እንደ ላቲን አስልቺ ነው የሚሆነው።

ቀደምት የሆነውን የአገራችሁን ታሪክ ጠቀሜታ ማሳወቅ አለባችሁ። ያን ለማወቅ ሲል ነው ትውልዱ ግእዝን ሊያውቅ የሚችለው። ከዚህ በኋላ ብዙ ሳይሆን ጥቂት ተማሪዎችን ታገኛላችሁ። እነርሱም እንደዚህ በማለት ሊጠይቋችሁ ይችላሉ። *«ቀደምት የሆነውን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማወቅ የግእዝ ድርሻ ምንድን ነው? ለመሆኑ በጥልቀት የተመሠረተና በአግባቡ የተመዘገበ ጽሑፍ እናገኝ ይሆን?»* ያን ጊዜ ተማሪዎች ለግእዝ ያላቸው ፍላጎት አመርቂ በሆነ መልኩ ያድጋል። እናንተም የዘመን አክሱምን ጽሑፎች፣ ሐውልቶች በፊልም፣ በፎቶግራፍ ልታሳዩአቸው ይገባል ወይም ጥንታዊውን የደቡብ ዐረቢያ ጽሑፍ ማሳየት አለባችሁ። ያላቸውን መመሳሰል ሌሎች ነገሮችም ማሳየትና ማስረዳት ይጠበቅባችኋል። እርግጠኛ ነኝ ያን ጊዜ በቀድሞው የአገሪቱ ታሪክ ይማረካሉ። ያንንም ለማወቅና ለመረዳት ግእዝን ይማራሉ። ♦



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መናገር በሚገባቸው ወቅት ዝም የሚሉ ሁሉ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ይገድላሉ።»

«ከዚህ ያደረሰኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድን ነው?» አለ ንጉሡ። ለዚህ ያበቃኝ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። የዛሬ ዓመት በዚህች ምድር ነዋሪዎች የነበሩ ዛሬ ግን በሞት ተጠርተው የሄዱ ብዙዎች ናቸው። እኔና እርስዎ ደግሞ ስለ ቀደመው ኃጢአታችን ንስሐ ገብተን ፈቃደ እግዚአብሔርን ወደ መፈጸም እንድንመለስ ዕድሜ ሰጠን። ተመስገን እንበለው። እንደ ምን ሰነበታችሁልኝ።

ዛሬም መንገደኛ ነኝ፤ ግን ወደ ራሴ መንዝ የተሳነኝ። እንዲያው እርስዎ ግን ወደ ራስዎት ተጉዘው ወይም ከራስዎት ጋር ሆነው ተጉዘው ያውቃሉ? ከተጓዙ ታድለዋል...።

ያኔ በመጋቢት በሚያዝያ ቃል ገብቼላችሁ ነበር። እናንተዬ፥ ዝም ብላችሁ ቃል አትግቡ። ቃል ከገባችሁም ቃላችሁን ጠብቁ። አዎ፥ ስለ መዝሙሩ ነበር ቃሌ። የዚህች ሀገር ድኽነት መች ይሆን የሚያበቃው? የእርስዎ መደኸየት የመዝሙሩን ቃናና ለዛ አበላሸ ብዬ ብነግራችሁ ደግሞ ወይ ታሙኛላችሁ ወይ ትከራከሩኛላችሁ። እኔ ምን ቸገረኝ። ሥራ ላጣው ክፍት የሥራ ቦታ ሆኖ የተገኘው መዝሙር ማውጣትና ትጻር መመሥረት ነው ብላችሁስ፤ ለዚያውም «Qualification» የማይጠይቅ ክፍት የሥራ ቦታ።

የሥራ ፈጠራ ባለቤት መሆን ጥሩ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ እስካሁን ያላቀረበችልንን «መዝሙር» ፈጥሮ ማቅረብ ድንቅ ፈጠራ ነው፤ እንነጋገር፤ እንማማር። ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ክብር እንሥራ። መዝሙር ለፈጣሪ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። እግዚአብሔርም የምስጋና መሥዋዕት ይሠዋለት ዘንድ ፈቃዱ ነው። መዝ.49፥14። እንዲህ ማለቴ እኔ ላስተምርዎት አይደለም። እንነጋገር ብዬ ነው እንጂ። መሥዋዕትን ደግሞ እግዚአብሔር የሚቀበለው የአቅራቢውን ልቡናና የመሥዋዕቱን መልካምነት ተመልክቶ ነው። ስለዚህ የመዝሙር ካሴቱ ገበያ ተኮር ሳይሆን እግዚአብሔር ይመሰገንበታልን? ወዶ ይቀበለዋልን? ወገንስ ይማርበታልን? ምን ይማርበታል? የቤተ ክርስቲያኒቷስ መዓዛ ይገለጥበታልን? የሚሉ ነገሮች ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

ባለፈው መዝሙር ላወጣ ነው ብያችሁ አልነበር። የሆነ ግጥም ገጣጥምኩና አንዱ መዝሙር ቤት ሄድኩና እንዲያወጡልኝ ተነጋገርሁ። ለምሳሌ፦ በካሴት የቀረጹኋትን መዝሙርም አሰማኋቸው። ሰውየው ካዳመጡ በኋላ፦ «ጥሩ ነው፥ ግን ሰው የንስሐ መዝሙር ስለማይፈልግ አናስተናግድህም» አሉኝ። እውነት ይሆን? እኔ ግን ከነአካቴው ተወኹት። እዚያው ቆሜ አንድ «የመዝሙር Clip» አየሁ።

ምንባብ አለው። ብርሃን ያንስዋል። አንባቢው ማንነቱ በውል አይታወቅም። እንዳይታወቅ ሰግቶ ይሆን? ሙሉውን የካሴቱን ይዘት ቆሜ ሰማሁት፥ አየሁት። 'VCD' ነው። አንዱ ዘማሪ በዳገት ቁልቁለቱ በየወንዛወንዙ የሆነ ነገር ፍለጋ ሲንከራተት ይታያል። እኔን!!መልእክቱ ምን ይሆን? እንጃ። የሰውን ኑሮ ውጣ ውረድ ያሳያል እንዳልል ቀሚስ ለብሶ መስቀል በደረቱ ላይ አንጠልጥሎ ነው። ግን ቀሚሱን መስቀሉን ማን ባርኮ አለበሰው? እዚህ ላይ የሰማሁት ነገር አለ። ዲያቆናት በየዓውደ መንበሩ የሚያደርጉትን መስቀል ያደርጉ ዘንድ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድላቸውም። ግን ዛሬ የትኛው ጳጳስ፣ ቆሞስ፥ መነኩሴ፣ ቄስ፣ ዲያቆን ወይም ምእመን መሆኑን ለመለየት እስኪያዳግት ድረስ የታችኛው የላይኛውን ልብስ እየለበሱ መስቀል እያደረጉ ምእመኑ ግራ ገብቶታል።

ሌላኛው የ'VCD'ው Clip ደግሞ ስለ ተንደላቀቀው ኑሮው ያሳያል። ቢሮው፣ ኮምፒውተሩ፣ መኪናው፣ የመኖሪያ ቤቱ ....። "ተመስገን አደረግኸልኝ።" የመዝሙሩ መልእክት። ጥሩ ነው፥ በመዝሙሩ ውስጣዊ ፍላጎቱን አሳይቷል። ግን ለሰሚው ለተመልካቹ በተለይ ለእኔ ቢጤው ለድኻው ምን ይሆን መልእክቱ? በርግጥ ድኻው እንኳንስ 'VCD' ማጫወቻ 0.10 ግራም ዳቦ መግኘ አጥቷል። ደግሞስ «አሳባቸው ምድራዊ» እንደ ተባለው አይሆን ይሆን?

ሌላም አለ። ከእጆቹ እሳት /ብርሃን/ የሚያወጣ። ይኼ እኮ የዲያብሎስ ሥራ ነው። የቅዱሳን ብርሃን የልቡና ብርሃን ነው። የአስተሳሰብ፣ የምኞት፣ የምግባር ብርሃን ነው። ያዘነውን የሚያረጋጋውም የመልካም ምክራቸው ብርሃንነት ነው። ክርስቶስ እንኳን ብርሃን ሲሆን ከእጁ የብርሃን ጨረር አልነዛም። ሌላም አለ። አንዴ ሲመነኩስ አንዴ ሲቀስስ፥ ሴቷም እንዴ በቆብ ስትታይ ደግሞም ስታወልቅ፥ አንደኛው ዘማሪ አንዴ ሲከናነብ ... ሁሉም ይታያል፤ የባቢሎን ዓይነት ነገር ነው የተደበላለቀበት።

ስለዚህ 'VCD' አንዱ ተጠይቆ ምን አለ መሰላችሁ። «ትክክል ነን አይደለንም ለማለት ያስቸግራል። ብቻ ጊዜው ገና ነው» አለና መልስ ሰጠ። /ቬሮኒካ ጋዜጣ ቁ.1/። የምን ጊዜ? የቤተ ክርስቲያኒቱን የመዝሙር ስልት ወደ የት የመወሰድ ዕቅድ ነው ያለው? አንድ ጊዜ ከአንድ የፕሮቴስታንት ድርጅት «ገነት ቤተ ክርስቲያን» ለተባለው የፕሮቴስታንት እምነት ተቋም የተጻፈና የወደፊት ዕቅዳቸውን የሚገልጥ ደብዳቤ እጄ ገብቷል። ምን ይላል? 1/ በቀላል አማርኛ የተተረ ጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ገዳማት መውሰድና ለመነኮሳቱ ማደል 2/ የኦርቶዶክስ የሚመስሉ «መዝሙራትን» በብዛት ማዘጋጀት፤ ይላል። ልብ ያለው ያስተውል። ታድያ «ምድራቱን በምስ ጋናቸው የከደኑ፣ የሸፈኑ ዘማርያን» ተብለው በአንድ ግለሰብ ሙገሳ የቀረበላቸው የነዚህ ጉዞ ወዴት ይሆን? እነርሱም «ጊዜው አልደረሰም» ብለውናል፤ እኛም ዕድሜ ይስጠንና ጊዜው ሲደርስ እናየዋለን።

ፕሮቴስታንቶችና የተሐድሶ መናፍቃን በመዝሙር በኩል ሕመም ሲጀምራቸው ሕዝቡ የሚወደውን ነገር አስመስለን ሕዝቡን እንይዝበታለን በሚል ሰበብ ነበር። ዛሬስ የት ደረሱ? እኛስ ነገ መዝሙሩና ዘፈኑ አንድ ሆኖብን ለመለየት ግራ አንጋባ ይሆን?

ይህ ገብቷቸው ጥሩ መልእክትና ቃና ያላቸውን መዝሙራት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ያቀረቡ ልጆቿ በእውነቱ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ምእመናንም የቤተ ክርስቲያኒቱ የኾነውንና ያልኾነውን እንለይ።

ይብቃኝ። እግዚአብሔር እንደ ቅዱስ ዳዊት በዝማሬያቸው አጋንንት ከሚያደርሱት የመንፈስ ሥቃይ የሚያላቅቁ፣ እንደ ቅዱስ ያሬድ ነገረ ሃይማኖታቸውን ከምስጋና ጋር አስተባብረው የሚያስተምሩ ለሳምንትና በወረት የሚደመጡ ሳይሆኑ ኃይለ መንፈስ ቅዱስ ያላቸውና ሰውን ሁሉ ከሥጋዊና ከምድራዊው አስተሳሰብ አላቅቀው ሰማያዊውን ነገር የሚያሳስቡ መዝሙራትን እስኪያድለን፣ ሁሉን በሥርዐትና በአግባቡ የሚያደርጉ ዘማርያንን እስኪያስነሣልን ድረስ ዝም ልበል።


ቀን ከሌሊት ቅዱሱንና ታላቁን ያሬዳዊ ዝማሬ ምድራዊ ደመወዝ ሳያገኙ እንደ ዓምድ ተተክለው ያመሰገኑ፥ አሁንም የሚያመሰግኑ አበው ***«ጊዜው ገና ነው»*** ስለ ተባለው 'VCD' ምን ይሉ ይሆን? እንነጋገርበት። ***«መናገር በሚገባቸው ወቅት ዝም የሚሉ ሁሉ ራሳቸውን ገድለው ሌላውንም ይገድላሉ።»*** መንገደኛው።

## ጉዳዩ ከ«ድምፅ ብክለት» ጋር እንዴት ይያያዛል?


በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ዐይናማው መንገደኛ- ***«አዲሱ የመዝሙር ዝንፈ»*** በሚል ርእስ ላቀረቡት ሒስ በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትም ላይ አብነት ገብሩ፦ ***«መልካሙን አገልግሎት የሚቃወም የቤተ ክርስቲያናችን ወገን አይደለም»*** በማለት ከአዋሳ የሰጡትን ትችት ተመልክቸዋለሁ። አቶ አብነት ገብሩ ያዙኑት እውነቱ በግልጽ ስለ ተነገራቸው ነው። እኔ እንደ ተገነዘብኹት የመንገደኛውና የሌሎች አስተያየት ሰጪዎች ዋና ሐሳብ «የካሴት መዝሙር ለምን ተዘመረ? አገልግሎቱስ ለምን ተስፋፋ?» ሳይሆን ለምን በአግባቡና በሥርዐቱ አልኾነም፤ ለዝና፣ ለክብር ወይም ገንዘብ ለማግኘት በግጥምም ኾነ በዜማ ይዘቱና በመልእክቱ አጠያያቂ የኾነ «መዝሙር» በየጎዳናውና በቅርቡ ደግሞ በየመሥሪያ ቤቶች ደጃፍ ላይ በሞንታርቦ ማስታ ወቂያ ማስጮኽ አስፈላጊም ተገቢም አይ ደለም፤ ማስቀደም ያለብን የቤተ ክርስቲያንን ክብር ነው፤ የሚል ነው። ሌላው ስሕተት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ኹሉ ተጠቅልሎ ለዘማርያኑ መሰጠቱ ነው። ዘማርያኑ ከመነሣታቸው በፊት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በወርቃማ ሁኔታ የተስፋፋበት ዘመን ነበር፤ በእነርሱም ጊዜ አለ፤ ከእነርሱም በኋላ ይኖራል። ቤተ ክርስቲያን በምእመናን የምታሸበርቀው የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች፣ እግዚአብሔር ደግሞ ሁሉንም በጸጋውና በረድኤቱ በሚጠራበት፥ በሚሰበስብበት ጥበቡ ነው። ከእኒህም አንዱ የመዝሙር አገልግሎት ነው፤ ብቸኛው ግን አይደለም። በርግጥም ደግሞ ይህ መዝመር በቅዱስ ያሬድ በኩል የተሰጠን፣ የራሱ የዜማ መደብ፣ ምልክት፣ መሣሪያና ላህይ /ጣዕም/ ያለው ሰማያዊና ኦርቶዶክሳዊ ጸጋ ነው። የዘማርያኑ አገልግሎት የተባለውን ያህል ቢኾን እንኳ ትክክለኛነቱና ተቀባይነቱ የሚመዘነው በዚህ ዐይን ብቻ ነው። ማስታወቂያዎች እንዲህ ሳያደነቁሩን በፊት ምእመናን ጥሩ ናቸው የሚሏቸውን መዝሙሮች መለየት፣ መግዛትና ማዳመጥ ችለዋል እኮ። ከዚህ አኳያ አቶ አብነት እንዳሉት [illegible] መንገደኛ ዓይነት ሒስ አደባባይ ስለ ወጣው ችግራችን በግልጽ እንድንወያይ የሚያነሣሣን እንጂ የሚያስተቸን አይኾንም። የሚያስተቸንስሚ፥ የሚያሳቅቀንስ፦ «መዝሙር በሞንታርቦ እያስጮኹ፥ ካልገዛችኹን» ማለት ነው። አቶ አብነት ይህን በቀላሉ ለመረዳት የሚሹ ከኾነ በአንድ የወር በዓል ቀን ከአዋሳ ወደ አዲስ አበባ ብቅ ብለው የሞንታርቦዉን ጩኸትና የምእመኑን ስሜት /ምላሽ/ ማጤን ይችላሉ። እስኪ አቶ አብነት ሌላ ጥያቄ ልጠይቅዎት? ቀድሞ ነገር ዘማርያኑ መኪና ተከራይተው፣ አስተዋዋቂ ቀጥረው አዋሳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ድረስ እንዲያ የሚደክሙት ለምን ይመስልዎታል? መዝሙር ቤት የከፈቱ ሰዎችስ እንዴትና ምን ሠርተው ይብሉ? ውይይታችን ከንቱ መመላለስ እንዳይኾን እስኪ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለ ከታቸውም አስተያየት ይስጡበትና መነቃ ቀቶ ቀርቶ ወደ አንድ የመፍትሔ ሐሳብ እንድረስ። ጉዳዩ ከሕግ አኳያስ እንዴት ይታያል? ከ«ድምፅ ብክለት» ጋር እንዴት ይያያዛል? በእኒህ ነጥቦች ላይ ምእመናን ግን ዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በመጨረሻም የዝግጅት ክፍሉ ይህን የውይይት መድረክ በማዘጋጀቱ ሊመ ሰገን ይገባል እላለሁ። የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን አማላጅነት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።

ኤርሚያስ ዓምደ ብርሃን - አየር ጤና
ዳግም ተመስገን - ልደታ
ዲ/ን አበበ መንግሥቴ -አላማጣ
ይመስላል አለባቸው - ወልድያ


© ማኅበረ ቅዱሳን 




መጽሐፈ ሶስና
DVD
በዲ.ን ዳንኤል ክብረት
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
በገበያ ላይ

የጠፋው ጌጥ
በ ቅ ር ብ ቀ ን
DVD
በዲ.ን ብርሃኑ አድማስ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

የቤተ ክርስቲያን
መረጃዎች
አዘጋጅ
ዲ.ን ዳንኤል ክብረት
አሳታሚና አከፋፋይ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፲፱፻፺፱ ዓ.ም

አዲስ መጽሐፍ
✞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን
• ቅዱሳን
• ሊቃውንት
• ገዳማት
• አድባራት
ታሪክ እና ሌሎችንም
መረጃዎች የያዘ ዐውደ ጥበብ
በ ቅ ር ብ ቀ ን
ዋጋ ብር 3.50
ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

© ማኅበረ ቅዱሳን
ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣ እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።